
# የቡና ቤት ስዕሎች
# እና
# ሌሎችም ወጎች



አንድ ቀን እንደ ሀብታም
የዚግ ዓለም ጨዋታ_____
ሽሽት______
እና____

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

ከመስፍን ሀብተ ማርያም

# የቡና ቤት ስዕሎች

## እና ሌሎችም ወጎች

(1976 – 1999)

ከመስፍን ሀብተ ማርያም

NIGUSS DIGITAL LIBRARY

# አስተያየቶች።

- በጽሑፎችህ የራስህን ገጠመ ያለ ይሉኝታ በድፍረት ማንሣትህ አደንቃለሁ። ወግ ጸሐፊው ራሱን ሊደብቅ አይችልምና።

ዶ/ር ሣራ ታደሰ

- ሰው ያየውን በሰው ዓይን ገብተህ አዕምሮው እንዲቀበለው በጥልቀት እንዲያስተውለው ማድረግ ትችላለ።

ዶ/ር ጌትነት ንጉሤ

- ውበትና የገንዘብ ጉዳይ በጽሑፎችህ አይጠፉም። ስለ አይጥ የጻፍከውን ወግ በጣም አደንቃለሁ።

በድሩ ሙክታር

- በወግ ጽሑፎችህ ራሴንና ሌሎችንም ያለ ምንም ቅሬታ አይበታለሁ። የቡና ቤት ስዕሎችን ዓይነት ድንቅ ወግ የምትጽፍ አይመስለኝም።

ረከብኪ ጸጋዬ

- የአገላለጽ ችሎታህ ሁሌም ይጥመኛል። ነገር ግን የምትወደውን ታጋንንናለህ፣ የምትጠላውን ታንኳስሳለህ። ያም ቢሆን እውነቱን ይዘህ በጥሩ ቋንቋ ስለምታሳየው ታሣምነኛለህ።

መሐመድ ኢድሪስ

- በአፃፃፍህ ሥነ - ጽሑፋዊ ውበት ስለምትጠቀም በጉጉት ተነብቦ ጎልቶ እንዲታይ ታደርገዋለህ።

ደረጀ ከበደ።

- ለፈጠራ አፃፃፍ በተለይ ለወግ ባለህ ፍቅር ራስህን ረስተህ የኖርክ ይመስለኛል።

መዓዛ ጳውሎስ

- ለኮሜዲ የሚሆኑህን ቀልዶች ሁሉ በወግ ጨርሰህቸዋል። መቼ ነው ቲአትር የምትጽፈው?

ዓለም ፀሐይ መንግሥቱ

- ያንተ ብዕር እንደምወድ አትጠራጠር። ነገር ግን ስለ ጫትና መጠጥ ዕድሜ ልክህን አትጽፍም።

ተቋም ወርቁ

- እኔ እንደማውቀው በሥነ ጽሑፍ ሌላ ተሠጥዎ ሊኖርህ ይችላል። ጥሩ ወግ ጸሐፊ መሆንህን ግን መቼም የትም እመሰክራለሁ።

ኃይሉ ኢሳያስ

# ማውጫ

ማለፊያ ምዕራፍ ... 5
የቡና ቤት ሥዕሎች ... 8
ቆርጦ ቀጥሎች ... 13
የፈተና ሰሞን ... 17
ዕድል ወይስ አጋጣሚ ... 19
ፎቶ ግራፍ ... 23
በሽተኞችና ጠያቂዎች ... 28
ሙዚቃ ... 31
ጸጉር ቤት ... 34
ሲኒማና ቲያትር ተመልካቾች ... 36
እረኞች ... 39
ነጋዴዎች ... 42
ዕድሜ ... 47
የዚህ ዓለም ጨዋታ ... 50
ጩኸት ... 53
በዓልና አዲስ አበባ ... 56
ስብሐት ገ/እግዚአብሔር.....እኔ እንደማውቀው ... 59
ጡረታ ወይስ ማሕበራዊ ዋስትና? ... 64
ሦስቱ ክፉ ቃላት ... 68
ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ ... 72
ራስን መቀበል (Self Acceptance) ... 75
ሽሽት ... 79
ገንዘብ ... 83
የውበት ጉዳይ ... 87
አንድ ቀን እንደ ለማኝ ... 92
አንድ ቀን እንደ ሰዓሊ ... 98
አንድ ቀን እንደ ቢሮ አለቃ ... 102
አንድ ቀን እንደ ሀብታም ... 106

ጥላሁን ገሠሠ እኔ እንደማውቀው ........ 108
ስለደራሲው በጥቂቱ........ 114
የደራሲው ሥራዎች ........ 114

# ማለፊያ ምዕራፍ

## (በደበበ ሠይፉ)

ደራሲውና አሳታሚው ድርጅት፤ መግቢያ ብጤ ለመጻፍ ፈቃደኛ መሆኔን ሲያረጋግጡ የግላቸውን አደራ ይጥሉብኝላ። «እባክህ ለ Essay የአማርኛ አቻ - ቃል ፈልግለት» ይለኛል ደራሲው። አሳታሚው በበኩሉ ስለ Essay አንዳንድ ሐሳቦች አስፍርልኝ ሲል ይጠይቀኛል። ከመነሻው፣ የእኔ እንኳን ሐሳቡ፣ እዚህ ባሉት ስብስቦች ላይ ተወስኜ ጥቂት ነጥቦችን ለመሰንዘር ነበር። ይሁን እንጂ፣ የደራሲውንና የአሳታሚውን ፍላጐት ማድመጡም ተገቢ ነውና፣ እነሱው በጠቆሙኝ አቅጣጫ አመራለሁ አደራቸው ቢቀለኝ ብዬ።

ሚሼል ደ. ሞንታኝ ለሙከራ ያህል በፈረንሳይኛ ይተልመዋል። ፍራንሲስ ቤከን ወደ እንግሊዝኛ ያዛምተዋል። እየቆየም ለአንድ ዐቢይ የሥነ ጽሑፍ ዘርፍ መጠሪያ ለመሆን ይበቃል - ይህ Essay የተሰኘው ቃል። Essay በሥነ ጽሁፍ ዓይነተኛ ቤተሰብነቱ ከታወቀ አንድ አራት ምዕት ያልፉታል። ቃሉ ከመነሻው ዛሬ Informal ወይም Familiar Essay የምንለውን ብቻ ነበር የሚወክል። እያደር ግን ይሰፋ፤ ይደረጅና ቁንጽል ዜና ሕይወታትን፣ በልዩ ልዩ አርዕስት የሚቀርቡ የጋዜጦች መጽሔቶች ሬዴዮኖች ወዘተ. እያካተተ በመምጣት ለማንኛውም <u>አጭር ስድ ንባባዊ ኢልቦለዳዊ</u> ሥነ ጽሑፋዊ ክንዋኔ ይውላል።

በሀገራችን ከላይ እንደ ጠቀስኳቸው ያሉ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች አሉን። ሆኖም በጥቅሉ እስከ ዛሬም ስም አላወጣንላቸውም፤ በደምሳሰው እንለያቸው እንጂ፤ በቤተሰብ ጠገጋቸው ገናም መጠሪያ አልሰጠናቸውም። የሥነ ጽሑፍ ታሪክ፣ ሂስ፣ ዲስፕሊን በድምሩም ባህል እያደገ ሲሄድ ደግሞ፤ በነቂስና በድምር ስማቸው ልናውቃቸው ግድ ይሆንብናል።

እኔውም የፈረንጅኛውን ቃል የሚተካ የአማርኛ አቻ ስፈላልግ ብሰነብትም፣ በሚገባኝ ምክንያት ግን፣ ቀላል ሆኖ አላገኘሁትም። መቼውንም የአንድ ቃል - ቅርፅ ሳይሆን ቃል - ቅርፁ ያካተተው የሐሳብ ይዘት መለየቱንና መለመዱ ነውና ዐቢይ ቁም ነገሩ፤ ለምን የፈረጅኛውን ወስደን በኢትዮጵያዊ አንደበታችን ላይ አናለመልመውም? ማለት ዳድቶኝ ነበር። ይሁንና ቃሉ በቀደምት የተለመደ ከሆነ - በሌላ የተለየ አገልግሎቱ እንኳን ቢሆን - ከአዲስ ይዘት ጋር ለማዛመድ የበለጠ ቀና ይሆናልና በአማርኛ አንዳንድ ሙከራዎችን አደረግሁ። ከነዚህ ሙከራዎች አንዱ በቃላት አፈጣጠር አንድ ዘዴ (acronym) በመጠቀምነበር። ይኸውም Essayን የሚገልጹ <u>አጭር ስድ ንባባዊ ኢልቦለዳዊ</u> የተሰኙትን ወሳኝ ቃላት በመውሰድና የየቃላቱን የየመነሻ ሆሄሃት በመልቀም፣ የተእልቀሙትን በመገጣጠም <u>አስኢን</u> ማስገኘ፣ ከዚያም <u>አስኢ</u> ለማለት የአማርኛ ሥነ ድምፅ ባህል አይፈቅድምና (ለዚህም ምክንያት አለው) <u>አስኢን</u> ወደ <u>ኢሲ</u> በመለወጥ ለEassy ተኪ ቃል ማግኘት ነበር። ይሁን እንጂ እንደ Eassy ላለ ቃል በዚህ በተባለው ዘዴ አቻ የመፈለጉ ነገር ቅሬታ አሳደረብኝና ተውኩት።

ፍለጋዬን በሌላ በመቀጠል ከEassy ወደ Informal Eassy ሄድኩ። መስፍን በዚህ መጽሐፍ የሰበሰባቸው Informal Eassy የሚባሉትን ነው። ለInformal Eassy «ወግ» ተገቢ አቻ ቃል ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ይህ ቃል እያደር ደጅቶ (እንደ ፈረንጅኛው ሁሉ) የትኛውንም አጭር ስድ ንባባዊና ኢልቦለዳዊ ሥነ ጽሑፋዊ ሥራ ሊይዝ ይችል ይሆናል። ባፋራሹ ቃላት የየራሳቸው ውስብስብ ታሪክ አላቸውና እንዲህ ባይሆን ወይም በዚህ አዲስ እሳቤው እንኳን ባይጸና የሚያስገርም ጉዳይ አይሆንም፣ የሚያሳዝንም። ለማንኛውም «ወግ» የተሰኘው ቃል ለInformal Eassy ጉልህ ባሕርያት እንደሚስማማ በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

Informal Eassy ባጠቃላይ ስናየው አተኩሮቱን እሚያኖረው እንደ አጭር ልብ ወለድ ሁሉ - አንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ ነው። ሆኖም አትኩሮቱን በሚያውልበት መንገድ ከአጭር ልብ ወለድ ይለያል። የአጭር ልብ ወልድ ትኩረት ግራ ቀኝ እማያስብል በቀጥታ መስመር የሚሄድና ድድር ሲሆን፣ የInformal Eassy ግን ዙሪያ ጥምጥምነትና ልልነት አለው። ይህም Informal Eassy መነሻውን ጉዳይ ደጋግሞ አሰልሶ ይቃኘው፣ ይህንንም እንደ ዓላማ ይውሰደው እንጂ - ወደ ሌሎች ጉዳዮች እንደ ልቡ ሩቅ ሆነ ቅርብ መዝመት መመላለስ ይችላል ማለት ነው። በInformal Eassy ውስጥ ዙሮ ዙሮ ንግብእኬ ጎበ ጥንት ነገር ያለው ነው - የተለመደ። ልክ እንደ ወግ ሁሉ፣ አንድ ነገር ሌላን ሲያስከትል (ጨዋታን ጨዋታ ሲያመጣው እንዲሉ) ከዋናው ጉዳይ ጋር እጅጉንና በቅርበት ያልተዛመዱ ጉዳዮች ቢሆኑም እንኳን - አይገድባቸውም። ራሱን ኢዲት እንዲያደረግ ጥብቅ ተፅዕኖ የለበትም። ወዴትም አቅጣጫ በምንም መንገድ ይንጐድ። ዋናው ቁም ነገር መነሻውን ዓላማ አውቆ (በምን ነበር ይህን ያነሣው - እንዲህል ወግ ደርዳሪ) ወደ ዋናው ጉዳዩ ለመመለስ የሚያደርገው ሙከራ መኖሩ ብቻ ነው።

በInformal Eassy ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የምናየው ሌላው ዐቢይ ባሕርይ፣ ዋናውን ጉዳይና ከሱም እየተቀረነጨፉ የሚወጡትን ዝርዝር ጉዳዮች በልዩ ልዩ ዘዴዎች ለማብራራት ሲል በማወዳደርና በማነጻጸር፣ በአስረጅዎች፣ በትርክቶች (anecdotes) በተዋስኦቶች (dialogues) ወዘተ ሊጠቀም መቻሉ ነው። ይህንን ባሕርይ ከሌሎቹች የEassy ዘሮች ጋር እንደሚጋራው ብናውቅም በInformal Eassy ውስጥ ይህ ባሕርይ እሚኖረው ከነውበታዊ ዕሴት (aesthetic value) ግን አየል ብሎ እናየዋለን። እዚህ መልእክቱ መሸጋገር ብቻ ሳይሆን ሳዕመለዛ ባለው መገድም እንዲተላለፍ ስለሚያስፈልግ። ለወግ ደርዳሪዎችስ፣ «ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ» አይደል ነባር የውግ አዝማቻቸው?

ሳይጠቀስ ሊታለፍ እማይገባው ሌላው ተጨማሪ ነጥብ፣ Informal Eassy በደራሲውና በተደራሲው መሐል አንዳች ውስጣዊ ትውውቅን፣ ጥብ ግብብነትን የመፍጠር ባሕርይው ነው። የነዚህ - ማለት የደራሲውና የተደራሲው - ግብብነት፣ ከአስተማሪነትና ከተማሪነት እሚመነጭ ዓይነት አይደለም - የአለቃና የምንዝር ብጤም። ይልቅስ የወዳጅነት ዓይነት ነው፣ የእኩዮሽ ተደማማጭነት። ደራሲው ይህን ታውቃላችሁ ሳይሆን ይን አስተውላችኋል የማለት ያህል ስንዝሮቹን ሲደረድር፣ ተደራሲው እውነትህንኮ ነው እያለ በአዎንታ ራሱን እየነቀነቀ እደሚመልስ ብጤ። እንደዚህም በመሆኑ Informal Eassy እጅጉን ትምህርታዊ ሳይሆን ትዕዛዛዊ ይበልጡን ውይይታዊና አዝናኛዊ ባሕሪይ ነው ያለው - እንደ ወግ ሁሉ። ቋንቋውም ብዙውን ጊዜ መደባዊ (ጽሑፋዊ) ሳይሆን፣ ኢመደባዊ (ንግግራዊ) መሆኑ በዚህ ምክንያት ነው - እንደ ገናም እንደ ወግ ሁሉ።

በልብ ወልደ፣ በድራማና በሥነ ግጥም ሥራዎች ሆነ (ሊሪካል ሥነ - ግጥምን ትተን) በሌሎች የኢልብወድ ሥራዎች ውስጥ (ዜና ሕይወታችን ትተን) የደራሲውን «የእኔነት አሻራ» ሊያድበሰብሱ እሚችሉ አያሌ ዘዴዎችንና ምክንያቶች አሉ። በInformal Eassy ውስጥ ግን የደራሲው ማንነት ሊደበቅ አይችልም። ደራሲው በአንዳች ጉዳይ ላይ ያለው ሐሳብ ይበልጡንም ስሜትና አስተያየት ጐልቶ ይወጣል። ጥላቻዎቹና ውዴታዎቹ ምፀቱ ሆነ «የእስቲ ይሁን» ትዝብቱ፣ ሽርደዳው ሆነ አድናቆቱ ሊሰወር ከሚችል በላይ ነው። «እኔኑ እንዳይመስል» የማያስብል ዓይነት መከራ ደራሲውም ቢሆን አያደርግም። ይህም የሚታወቅ ብዙውን ጊዜ «እኔ»፣ «እኛ» እሚሉት ቃላ በድርሰቱ ውስጥ በመፈነጣጠቁ ብቻ አይደለም። ይልቅስ በሱ በጉዳዩና በተደራስያን መሐል ባለወ ቀጥተኛና ቅርብ የገጠመኝ ውርርስ መሠረት ይህን ውርርስ በሚያስተላልፍባቸው ብቻ አይደለም። ይልቅስ በሱ መሠረትና ይህን ውርርስ በሚያስተላልፍባቸው ዓይነት ዘዴዎች ምክንያት እንጂ። ያም ሆነ ይህ የInformal Eassy ደራሲ አንዳችን ጉዳይ በሱነቱ ቀለም ሳይፍካካ (ወይም ሳያጠይም)

በሱነቱ ሚዛንም ሳይመጥን .... እንዲሁ በቁሙ ወይም በደምሳሳው - አንዳችን ጉዳይ ሊያነሣ አይችልም። ስለዚህም ባጭሩና በደምሳሳው ስናጤነው፣ የዚህ ዓይነቱ ሥራ ያንዳች ጉዳይ መበለቻ የመሆኑን ያህል የደራሲው ስብዕና መከሰቻም ነው። በወግም ውስጥ ቢሆን ይኸው አይደል? የወጉ ምንነት ብቻ ሳይሆን፣ የደርዳሪውም ማንነት ባንድ ቃብሮ ነው እሚለይ። ሞት እሚያበሥር፣ ሹመት እሚያረዳ ዓይነት ወግ ደርዳሪ እውነተኛ እሱነቱን፣ ውስጣዊ ገበናውን አላጋለጠም ትላላችሁ?

የInformal Eassy ምንነት በሚመለከት የምናነሣው ጉልህና የመጨረሻ ነጥብ ድምፀትን በሚመለከት ይሆናል። መቼውንም የአንዳች ሥራ ድምፀት መደበኛ መልክ የሚታወቀው ደራሲው በአንዳች ጉዳይ ላይ ካለው አተያየትና ከዚሁ አተያይ ጋር እሚሰናኝ የቋንቋ አጠቃቀም ዘዴና ችሎታ ሲኖረው ነው። ቀደም ብዬ በደምሳሳው እንዳነሣሁት Informal Eassy ውይይታዊ ንግግራዊ እንደ መሆኑ፣ የፅማዊነት፣ የቁጣ፣ ወዘተ ድምፀት ብዙ ጊዜ አናገኝበትም። ይልቅስ በInformal Eassy ውስጥ የሚገኙ ገናን ድምፀቶች፣ የትዕዝብት፣ የትርብት፣ ግፋም ቢል የምፀትና የሽርደዳ ዓይነት ናቸው። ተደራስያንን (በተለይም ጉዳዩ እጅግ እርቦ የሚነካቸውን) ቢጐንጥ የማያቆስል፣ ዓይነት ነው - ቢወጋ የማያደማ። ይህም በመሆኑ ከደራሲው ጋር ተደራስያን «ጉዳቸውን» እንኳን ሲወያዩ አይሰቀጥጣቸውም። ይልቅስ በራስ እንደማሾፍ ያህል ያዝናናቸዋል። ይህ ከዝርዝር ነገሮች በላይ - በድምር ድምፀቱ ውስጥ እሚገኝ የማዝናናት - የማዋዛት ባሕርይ Informal Eassyን እጅጉን ወደ ወግ እንደሚያቀርበው ልንገነዘብ እምንችል ይመስለኛል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፣ መስፍን መልካም እሚሰኙ ወጎችን አቅርቦልናል። እሚወያይባቸውን ጉዳዮች በሚገባ ከማወቁ ጋር፣ በጉዳዩም መነሾ ወደ ወጎቹ የተሳቡትን ሰዎች ድርጊትና አባባል በብሩህ አእምሮ እንዳስተዋለው፣ እንደተረዳውም፣ ሊያስገነዝበን የቻለ ይመስለኛል። በድክመታቸው ሳያመር፣ እኛን ተደራስያኑንም ሳያስመርር፣ በትግርምት - ትንሽ ጠንከር ሲልም ለትዕዝብት - ያህል ብቻ ስቀን እንድንሸኛቸው ያደርገናል። ይህ በራሱ ቀላል ችሎታ ባይሆንም፣ ወደ ፊት ዛሬ ከሰጠን ወጎች የተሻሉም ሊያቀርብልን እንደሚበቃ ከፍተኛ እምነት አለኝ።

ከዚህ በፊት አንዳንድ ወጎች በጋዜጦች ላይ ወጥተው ማንበቤን አስታውሳለሁ። ባንድ ጥራዝ ተካተው የወጡበት ጊዜ ግን፣ እስከ ዛሬም አላጋጠመኝም። እንዲህ ብቻ ሳይሆን፣ ይህ ጥራዝ የመስፍን የመጀመሪያ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን፣ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍም የመጀመሪያ የወግ መጽሐፍ መሆኑ ነው። ሁለቱም ማለፊያ ምዕራፍ እንበላቸው።

# የቡና ቤት ሥዕሎች

ሠዓሊ አይደለሁም። ትንሽም ልሞክር ብል ዱሮ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተለማመክዱትን ባለ አራት እግር ጠረጴዛ ነው እምሥለው። ሆኖም አንድ ሥዕል ማየት ብቻ ሳይሆን ማስተዋል፥ ውበቱን መልእክቱን ማየት ብቻ ሳይሆን ማስተዋል፥ በአጠቃላይ አቅሜ በሚፈቅድልኝ መሠረት መተቸት - ደስ ይለኛል። ሙያው ባይኖረኝም አንዳች እርካታ አገኝበታለሁ። ከዚህ በመነሣት ስለ ቡና ቤት ሥዕሎች የመሰሉኝን ነገሮች ለመናገር እሞክራለሁ።

«የቡና ቤት ሥዕሎች» የሚል ስያሜ የሰጠኋቸው በብዛት በቡና ቤቶች አካባቢ ስለሚገኙ ነው እንጂ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ የሉም ለማለት አይደለም። በሌላ አቅጣቻ ደግሞ ጥሩ ጥሩ ሥዕሎች በቡና ቤቶች ፈጽሞ አይገኙም ለማለት አይደለም።

ሥዕል በጣም እወዳለሁ፣ ሠዓሊዎችንም አደንቃለሁ። «ለሥዕል ከፍ ያለ ስሜት እያለኝ ለምን ሠዓሊ አልሆንኩም» ብዬ የጠየኩት አንድ ወዳጄ፥ «በልጅነትህ ጥሩ የሥዕል አስተማሪዎች ስላላጋጠሙህ ይሆናል» ብሎኝ ነበር። በሞላም ባይሆን ነገሩ የሚያስኬድ ይመስለኛል ፡

እርግጥ፣ የሥዕል አስተማሪዎቻችን ራሳቸው ሥዕል የማይችሉ ነበሩ። አፋቸው ላይ የመጣላቸውን ነገር ሳሉ ማለት ነበር የሚቀናቸው። ለምሳሌ፣ መኪና፣ ሰው፣ እንሥራ፣ አበባ። በተለይ ሰባተኛ ክፍል ሆኜ በመኮት ያዩትን ነገር ለምሳሌ ባቡር ሲያልፍ ካዩ ባቡር ሳሉ አህያም ካለፈች አህያ ሳሉ የሚሉ አስተማሪ እንደ ነበሩ ትዝ ይለኛል። በዚያን የልጅነት ዕድሜ ለመጀመሪያ ጊዜ ችሎታ አላቸው ብለን ያመንባቸው መምህር ያጋጠሙን አራተኛ ክፍል ብቻ ነው። እሳቸውም እስከ ዛሬ ያልረሳኋትን ያችን «ጠረጴዛ» ዓመት ሙሉ ብላክ ቦርድ ላይ ሲሥሉልን ከርመው አዲሣባ ተቀየሩ። የሆነ ሆኖ የሠዓሊነቱን ሙያ ባልታደልም አድናቂነቱን አላጣሁምና አይቆጨኝም።

ግን ስታስቡት፣ በአንዲት እርሳስ ጭረት ብዙ መናገር፣ በአዲት እርሳስ ጭረት ርቀን፣ ቅርበትን፣ ጥላና፣ ብርሃንን፣ ከፍታና ዝቅታን ማሳየት፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ እንደ ኃዘን፣ ደስታ፣ ጸጸት፣ ናፍቆት፣ ያሉትን ፈቂቅ ነገሮች ወረቀት ላይ መፍጠር ምንኛ ደስ ይላል!

በዕድሜ ጐዳና ሲያዘግም ኖሮ ወደ ሞት አፋፍ ብቅ የሚል ጺጋ የሞላበት ሽምግልና እንደ እምቡጥ አበባ የሚፈነዳ በተስፋና ምኞት አዝመራ ያሸተ ወጣትነ፣ በረሃብ የተፈታተነ አካል፣ ሥቃይ ካጎደጎደው ዓይንና ከተጨማደደ ፊት ጋር ተባብሮ የሚያሳየው ብሶት፣ የፍቅር ምትሐት፣ የኃዘን ምሬት፣ በአጠቃላይ ተፈጥሮ በሸራ ልያ የምትሽሞነሞንበት ትልቅ ጥበብ ቢኖር ሥዕል ነው።

ታዲያ ይህቺው ተፈጥሮ ተሰጥኦና ችሎታ ባላቸው ሠዓልያን የምትጌጠውንና በእውነታ የምታሽበርቀውን ያህል ሙያውን በወጉ በማያውቁ ሰዎችም ትዋረዳለች። ይኸን ለማረጋገጥ የቡና ቤት ሥዕሎችን መመልከቱ ይበቃል። የቡና ቤት ሥዕሎች ስል የሥዕል ጥበብ የሌላቸውን ተራ - በጣም ተራ - የሆኑትን ማለቴ ነው። ለምሳሌ፣ «ምን ልታዘዝ» የምትል እጉራ ክርኗ ሥር ሊሆን ትንሽ የቀረው የመጠጥ ቤት ኮማሪት፣ ወይም፣ «ታዲያስ ምን ይምጥ» ከሚል ጽሑፍ ሥር አንዴ አዳምጡኝ እንደሚል አስተማሪ እጁን የዘረጋ የምግብ ቤት ቦይ ግድግዳ ላይ ተሥለው አይታችሁ አታውቁም? ቀንዱ ተጠምዝዞ ጭራው ጋ የደረሰ ዋልያ፣ ጽጌረዳ ሊቀጥፍ የተዘጋጀ እንደ ሰው ጥርሱ ችምችም ያለ አንበሳ፣ ማይክሮፎን የሚመስል ቡና ማፍያ መኪና፣ ዝርዝር ብዙ ነው።

ዕድሉ ካጋጠማችሁ የመነኩሴ ቆብ ያጠልቀ ወጥ ቤት፣ «እንኳን ደህና መጡ» ሲላችሁ ቁመቷ ከጠረጴዛው ያነሰ ትልቁን ቢራ ከነትሪው ታሳያችኋለች። እንዲህ ዓይነቶቹን ከሚሥሉት መካከል አንዳንዶቹ ሠዓሊ ካልሆንኩ ሞቼ እገኛለሁ ብለው በኪነ ጥበብ አምላክ ላይ ዓይናቸውን አፍጠው፣ ከንፈራቸውን ነክሰው ብሩሽ የሚጨብጡ ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የመተዳደሪያ ሥራ ለመፍጠር ቀለም ከቀለም ጋር እያደባለቁ በሚያገኙት ውጤት ቀስ በቀስ ችሎታውን ያዳበሩ የሚመስላቸው ናቸው። አብዛኞቹ ግን ተፈጥሮ ከጽዋዋ በጥቂቱ አስጐንጭታ መልሳ የነጠቀቻቸው ነገር ግን በዚያች በቀመሷት መጠን፣ «እኛም አለን» የሚሉ፣ የጥበቡን ፍቅር ከድፍረት ጋር አጣምረው የያዙ ናቸው።

በዚህ መልክ የተሠሩትን እኔ ያየኋቸውን አንዳንዶቹን ሥዕሎች ቀጥሎ አቀርባለሁ።

አንድ ቡና ቤት ውስጥ ግድግዳው ላይ የተሣለ ነው። ሰውዬው በአንበሳው ላይ ይነጣጥራል። በሰውዬና በአንበሳው መካከል ጅረት አለ። አዳኙን እግሩ ቀጥ እንዳለ ስታዩት ሣሩ ላይ ተኝቷል ብላችሁ ታስባላችሁ። እንገር ግን መሆን አለበት ብላችሁ ስለምትገምቱ ነው እንጂ ሥዕሉ ላይ የሚታየው በሣሩ ላይ ሲሳፈፍ ነው። እሺ ብሎ አይዞርላችሁም እንጂ ግድግዳውን ዞር ብታደርጉት ደግሞ ቆሞ እሚተኩስ ይመስላችኋል። አንበሳው በተዝናና ሁኔታ ሰውዬን ትኩር ብሎ ያየዋል። አስተያየቱን ለመግለጽ ያስቸግራል። ብቻ፤ «እውነት አሁን ልትተኩስ ነው እስቲ ወንድ!» የሚል ይመስላል።

የሥዕሉ ምጣኔ ነገር አይወራም። የፊት እግሮቹ እኩል አይደሉም። አንዱ ወፍራም አንዱ ቀጭን ነው። የጅራቱን ማጠር ስታዩ፣ ሥዕሉ ሲሣል ግድግዳው ጠባብ ነበር እንዴ ማለታችሁ አይቀርም። የወገቡም ቅጥነት፣ «ሸንጧ ስምንት ቁጥር» የሚለውን ዘፈን ያስታውሳችኋል። የቅርበቱ - ርቀቱ ሚዛን እንዳልተጠበቀ በግልጽ ይታያል። ለምሳሌ ጠመንጃው ከሰውዬው በልጦ ጅረቱን አቋርጦ አንበሳው አፍንጫ ሊደርስ ትንሽ ቀርቶታል። ከወዲያ ማዶ ያለው ጋራ ደግሞ አንበሳው ጀርባ ላይ ያረፈ ይመስላል። ከሁሉም ይልቅ የሚናገረው አውሬው ጥቂት እንኳ እንደ መዝለል ወይም እንደ መሸሽ ሳይል በኩራት ዝም ብሎ አዳኙን ማስተዋሉ ነው።

ይኸን ሥዕል ሳይ የአንዳድ አርበኞች ሥዕል ትዝ አለኝ። ወረቀቱ ስለማይበቃ ነው እንዳይሉን እንጂ የአርበኛው ጠመንጃ የጣልያኑን ዓይን እየወጋ፣ «ደጃች እገሌ ላይ ሲያነጣጥሩ» የሚል ከሥሩ እየተለጠፈበት፣ እንደ እንቁጣጣሽ አበባ እየዞረ ሲሸጥ፣ የእነ አቡየ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የቅዱሳን የሰማዕታ፣ ያ ያ ሁሉ ታየኝ። ታዲያ አሁን እዚህ ለምናነሣቸው መሠረቱ እነሱ ይመስሉኛል። ጥንት ከምዕተ ዓመታት በፊት የተሣሉትን ግን ለጥናት ሊጠቅሙ ስለሚችሉ ለታሪክና ቅርስ ተመራማሪዎች ቢተው ጥሩ ነው።

ሌላው ያያሁት የፋሲል ግንብ ነው። ይኸ ሥዕል በብዛት በየቦታው ይታያል። አሣሣሉ አንድ ይምሰል እንጂ አጠቃላይ መልኩ የተለያየ ነው። አጥር ያለው አጥር የሌለው ዛፍ ያለው ዛፍ የሌለው በጽጌረዳና በሀረግ ያጌጠ፣ በለምለም ሣር ያሸበረቀ። የአንዳንዱ ጥላ አጣጣል ፍጹም ቅጥ ያጣ ከመሆኑ የተነሣ ፀሐይዋ ሁለት የሆነች ሊመስላችሁ ይችላል አንዳንዱ ከበረንዳው በታች ዘንባባ፣ በሕር ዛፍ፣ ጥድ፣ በያይነቱ በሰልፍ ይተክልበታል። ምን ያህል እውነት እንደሆነ አላውቅም እንጂ ፓፓያ የተሣለበትም አለ ሲባል ሰምቻለሁ።

የግንቡ የአካባቢ ሁኔታ ብቻ ሳይሆን ቀለሙም ብዙ ዓይነት ነው። ቢጫ፣ ሰማያዊም ሮዝ። የአራት መቶ ዓመት ሕንፃ በፒያሳ ቀለም መታደሱ እንኳን አይከፋም። እኔን በጣም ያስገረመኝ ግን፣ ከግንቡ ፊት ለፊት፣ ከቤተ መንግሥቱ ፊት ለፊት አንዲት ሹርባ የተሠራች የሀገር ልብስ የለበሰች ውብ ወይዘሮ ጃንጥላዋን ከፍ አርጋ ይዛ ገበያ አዳራሽ እምትሄድ ይመስል በቄንጥ ስትራመድ የሚያሳየው ሥዕል ነው። እስቲ ሴትየዋ እዚያ ምን ታደርጋለች? ላልጠፋ ግድግዳ ለብቻዋ መሣልስ ይቻል የለም!

በተለይ የፋሲል ግንብን፣ የአክሱም ሐውልትን፣ ጢስ ዐባይን፣ ላሊበላን የሚሥሉ ሰዎች፣ ባዶ ቦታ ለምን ባዶውን ይቅር እያሉ ነው መሰለኝ ደስ ያላቸውን ነገር ይጨማምራሉ - ባዶ ማስፈለግ አለማስፈለጉን ሳያስተውሉ። ለምሳሌ ወፎች ከሩቅ እየበረሩ ሲመጡ - እንዲያውም ሰማይ ካለ ወፎች በግድ ይኖራሉ። ወንዝ ወይም ኩሬ ከተነሣ ዳክዬዎች ሲዋኙ መታየት አለባቸው። ዛፍ ወይም ጦጣ ከሌለችበት ዛፍ ሊሆን አይችልም። ሣሩም ሁልጊዜ አረንጓዴ ነው። ምናልባት ለዚህ የሚገፋፋቸው የኢትዮጵያ ልምላሜ ይሆን? በአጠቃላይ የቡና ቤት ሠዓሊዎች ትልቅ ድክመት ዝምድና ወይም ግንኙነት የሌላቸውን ነገሮች ጐን ለጐን ማስቀመጣቸው ነው። ማን ያውቃል፣ ከፍ ብሎ የተጠቀስውችዋ ሴትዮ ሲገርመን፣ ላሊበላ ቤተክርስቲያንላይ ጂንስ ቢትልስ ለብሶ ኳስ የሚያነጥር ልጅ አንድ ቀን እናይ ይሆናል።

በአንድ የባህል ምግብ ቤት ውስጥ ያየሁት ሌላ ሥዕል አለ። በምን አወቅህ እንዳትሉኝ እንጂ የተሣሉት ባልና ሚስት ሳይሆኑ አይቀሩም። ጐን ለጐን ቁጭ ብለዋል። ቁሱም ተቀምጠዋል። ምግብ ቀርቧል በመሶብ ወርቅ። አንድ ውሻ ተጋድሟል። ዓይኖቹን ጨፍኗልም እንቅልፍ የወሰደው ይመስላል። ምግብ እየሸተተው የሚተኛ ውሻ እናንተ ታውቃላችሁ ከምጣኔ ስሕተት የተነሳ ውሻው ያለው ካልጠፋ ቦታ እመሶብ ወርቁ ሥር ነው። ጭራው እንደ ደህና ነገር ባልዮው እግር ላይ አርፏል። ሴትዮዋ እጃቿን ዘርግታለች - ወደ ሰዎቹ «ብሉ ብሉ እስቲ፣ እንደነገሩም ቢሆን» ትላለች ለማለት ነው። ነገር ግን እጅ አዘረጋጓ መድረክ ላይ ሆና ንግግር የምታደርግ አስመስሏታል። ባልዬው እጁን ይጣጠባል - የሱ እንኳን ደህና ነው። የምታስታጥበው ልጅ ግን በቅጣት ላይ ያለች ነው የሚመስላችሁ። ምክንያቱም ጎበስ በማለት ፈንታ እንደ መንበርከክ ብላለች። የቁሱ ከሁሉም የተለየ ነው። ለመብላት የተዘጋጁ አይመስሉም። ብቻ ዝም ብለው መስቀልና ጭራችውን ለምግብ ቤቱ ደምበኞች ያሳያሉ። የምግብ ቤቱን ባለቤት፥ «ማነው ይኸው ሥዕል የሣለልዎት» ብየ ጠየቅኋቸው።

«አንድ የተባረከ ልጅ ነው፣ እንዲሁ እናንተ ሲመገብ መጥቶ» አሉኝ።

«ለመሆኑ ምን ያህል አስከፈልዎት?»

«ዛሬ አታገኘው፣ ምን ያረግልሃል። ክፍለ ሃገር ከሄደ ዘበንም የለው።»

«እንዲያው ለማወቅ ብዬ ነበር» አልኳቸው

«የለም ብዬሃለሁ እንግዲ። ሰውዬው የለ አዲሳባ።»

«ግን ሥዕሉ ጥሩ ነው እስዎስ ሲያስቡት።»

«ያው ታየዋለህ ምን ትጠይቀኛለህ።»

«ስለ ሥዕሉ ያለዎትን አስተያየት።»

«አንድ አስተያየት የለም! የበሉትን ከፍሎ ውልቅ።»

አብዛኛዎቹ የቡና ቤት ሥዕል ባለቤቶች ባሏቸው ሥዕሎች ይኮሩባቸዋል። ነገሩ፤ «እኔጋ ያለው በየትም አይገኝም» ዓይነት ነገር አያጣውም። እንዲያውም አሁን አሁን ሳስበው ዋጋውን ሳይነግሩን፣ «ክፍለ ሀገር ሄዷል» ያሉኝ በዚህ ምክንያት ሳይሆን አይቀርም።

የሌሎቹን ከተሞች እንጃ እንጂ አዲስ አበባ በርከት ባሉ ቡና ቤቶች የሚገኝ አንድ የታውቀ ሥዕል አለ። ፍሬሙ ትልቅ ነው። በዓይነተኛ ምሳሌነቱ ብቻ ሳይሆን ለዚህ ጽሁፍ መነሻ ስለሆነኝ በጣም እወደዋለሁ። እንዲያውም ስለ ብዙዎቹ ሥዕሎች ሲያወሩ ከመዋል ስለዚህኛው መናገሩ ይበቃል። ምክንያቱም ዝብርቅርቅ

ነገሮች በደንብ ተዘበራርቀው የሚታዩበት፣ ቅጥ ያጡ ሁኔታዎች በጣም ቅጥ አጥተው የሚጎለብት፣ በባላገር አሉ የሚባሉትን ነገሮች ሁሉ ጥቅጥቅ አየያዘ በኢትዮጵያ፣ እንዲያውም በዓለም ተወዳዳሪ የማይገኝለት የቡና ቤት ሥዕሎች ሁሉ ቁንጮ ነው። ያውላችሁ። በዓይነ ሕሊናችሁ ተመልከቱት። ሁለት ጐጆዎች አሉ። አንድ ከፊት፤ አንድ ከኋላ። ትንሹ ጐጆ በራፍ ላይ የልኳንዳ ቤቶች ዓይነት ልዩ ሻኛ ያለው፣ ዓይኑን አጉረጥርጦ አካባቢውን የሚገላምጥ ነጭ ሰንጋ ቆሟል። ትንሹ ጐጆ ጋ ደሞ አንድ ሴትዮ ጥራጥሬ መሳይ ለፈርሱ በገበታ ይዛለታለች። ፈረሱ ግን አይበላም። አንገቱን እንደገተረ ትክ ብሎ ያያል። ግዝፈቱ አይጣል። ጭራው መሬት ይነካል። ቀይ ልጓም ተደርጎለታል። ባልዮው ሊያመጣው ሄዷል መሰለኝ ወይም ጠፍቶ ይሆናል - ኮርቻው ግን የለም።

የሴትዮዋንና የፈረሱን ሁኔታ ሆን ብላችሁ ስታዩ አንድ ጨዋታ የያዙ ወይም የሚነጋገሩ ይመስላችኋል። በስተቀኝ በኩል ከእንጨት የተሠራ የሚመስል ሌላ ፈረስ እንደ መሣቅ ብሎ ቆሟል። በነሱ ዙሪያ ባላገር ያፈራው ነገር ሁሉ አለ። በግ፣ ውሻ፣ ዶሮ፣ ላም፣ በሬ፣ ጥጃ፣ ፍየል፣ ድመት - ሁሉም አሉ፣ ከአሳማና ከአይጥ በስተቀር። አንዳንዶቹ ተኝተዋል። አንዳንዶቹ ቆመዋል። ዋሽህ አትበሉኝ እንጂ ወገቡን እስኪነካው ድረስ ጭራው ወደ ላይ ቀልብሶ የተኛ ውሻም አለ። ሰውዬው ከእንስሶቹ አጠገብ እቤት ሊገባ ትንሽ የቀረው በሬ ጠምዶ ያርሳል። ሞፈሩ ግን የምታውቁት ዓይነት እንዳይመስላችሁ። ከአንደኛው በሬ ጭራ ጋር የተያያዘ ነው። ከጐጆው በስተቀኝ ቀፎ የተሰቀለበት ቅጠሉ የጎዘነ ኮፍያ የመሰለ ዛፍ አለ። በጣም ጠጋ ብሎ ላየ ሰው ንቦችም ሳይኖሩበት አይቀሩም። መቼ ይሄ ብቻ! ማሩን «ሊሸውዱ» እንደሆነ እንጃ እንጂ ሲጃራ ፓኬት ላይ ከሚታየው የተለየ ደማቅ ቀለም ያላቸው ቆንጆ ቆንጆ ጉሬዛዎች ቀፎውን ከበው ተቀምጠዋል። እንደገና ከዛፉ ቀጥሎ ሌላ ገበሬ ያርሳል። እረኛም አለ። ከወዲያ ማዶ ደሞ አንድ ቀጭን መንገድ መጨረሻ ሌሎች፣ «ዛፍ የበቀለባቸው» ጐጆዎች ይታያሉ። ምን ልበላችሁ ! ወንዝ፣ ተራራ፣ ገደል፣ ሣር፣ ቡቃያ፣ ቆቅ፣ ጅግራ፣ መዘርዘሩ ያደክማል።

የቡና ቤት ሥዕሎች ዋናው መታወቂያ የቀለማቸው ደማቅነትና ውጥንቅጥነት ነው። ለምሳሌ የአንድ አትክልት አበባ የተፈጥሮ መልክ ቢጫ ቢሆን ሰማያዊና ሮዝ ይጨመርበታል። ቤት ደሞ ሲሣል በሩ ቀይ፣ መስኮቱ ሰማያዊ፣ ቆርቆሮው ወይን ጠጅ መሆን አለበት። ለምን ብላችሁ የቡና ቤቱን ሠዓሊ ለመጠየቅ እንዳትሞክሩ። «ይበልጥ ቢያምር ምናለበት» እንደሚላችሁ ማወቅ አለባችሁ። እጡብ ነው ድንቅ ነው! ብቻ በዚህ ዓይነት አረንጓዴ ላም ከማእይት ይሠውረን።

በመካከለኛ ዕድሜ ያሉ አንድ የዚህ ዓይነቱ ሥዕል ባለቤት ያሉኝን ልንገራችሁ።

«እንዲህ ያለ ፈረስ አይተው ያውቃሉ?» አልኳቸው

«ምነው ሊበጥስ ምን ቀረው።»

«ይበጥሳ፣ ምን አለበት።»

«ደሞ እህሉን ትቶ ሴትዮዋን ያያል።»

«ይያታ፣ ፈረስ ዓይን የለውም አሉህ!»

«መኖርስ አለው ግን አመለካከቱ እንደ ሰው መሆኑ ተገቢ ነው?»

«ይሁና እሱም እንደ ሰው ዓይን አለው።»

«በጠቅላላው ልክ ነው ነው የሚሉት?»

«እንዴታ ሥዕል እኮ ነው! የእውነት መሰለህ!»

ይህ አባባል ሥዕልን ከእውነታ ነጥሎ ለማየት ጥሩ ምሳሌ ሊሆን ይቻልላ። ሠዓልያኑም ቢሆኑ እውነታውን ቀንጭበው ነው የሚያቀርቡት። ለምሳሌ ከዚህ ሥዕል አንዱን ብቻ እንጥቀስ ብንል ጭራውን ወደ ላይ ቀልብሶ እሚተኛ ውሻ በዓለም ላይ አለ? ምናልባት የሠለጠነ ውሻ እንዲህ ሊያደርግ ይችላል የሚሉ ይኖሩ ይሆናል። ለዚህ ለዚህማ የለመድነውን አበላል ትተን እጃችንን በማጅራታችን በኩል አዙረን ለመጉረስም እንችላለን ማለት ነው።

በተለይ ባህላዊ ሁኔታዎችን አንድ ላይ በአንድ ጊዜ በጠባብ ቦታ ለማሳየት ሲባል ዝብርቅርቅ ነገሮችን ማመቅ የቡና ቤት ሠዓልያን ዓይነተኛ ልማድ ነው። ይኸን በሚያደርጉበትም ጊዜ፤ ሳይታወቃቸው ከእውነታው ይርቃሉ። ለምሳሌ፣ ሴትዮዋ እንስራ ተሸክማ ትሄዳለች። ታዲያ ሠዓሊው ለውኃ መቅጃ ያልተለመደውን የጥምቀቱን ባለ ጥልፍ ቀሚስና ነጠላ በግድ ያለብሳታል። እዚያው ውስጥ ደግሞ እንስራውን ለመስበር ትንሽ እስኪቀራቸው ድረስ ወደ ሴትዮዋ ጭራቸውን የሰነዘሩ፣ ጢማም ቂስ ከነመስቀላቸው ቁጭ! አንዷ ላም ስታልብ ሌላዋ አጠገቧ ጥጥ መፍተል፣ ደሞ ሌላዋ ሲኒዋን ደርድራ ቡና ማፍላት፣ አንዷ ጌሾ መውቀት፣.....አንዷ ጃንጥላ ዘርግታ ቤተ ክርስቲያን መሄድ፣ ሁሉም እዛው!

ለምሆኑ ስለ ሥዕል ምን ያህሉ የኅብረተስባችን ክፍል ነው ትክክለኛ ግንዛቤ ያለው? አንድ በዕድሜ ገፋ ያሉ ጠይቄ የሰጡኝን መልስ ላጫውታችሁ።

«ስለ ሥዕል ምን ያውቃሉ» አልኳቸው።

«ሥዕል?» አሉኝ።

«አዎን፣ ሥዕል።»

«ሥዕል - ይህ እያዞሩ የሚሸጡት ነው?»

«አዎ።»

«እኮ፣ ይኸ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ የሚካኤል.........ዓይነት?»

«አዎ፣ የንሱ ዓይነት.......የነሱ ዓይነት!»

«እህ፣ ግድግዳ ላይ የሚሰቀለው ነው የምትለኝ?» ቢቸግረኝ በረጅሙ ተነፈስኩና ዝም አልኩ።

«አሀ! ሥዕል ነዋ! ሌላ ስም አለው?» አሉኝ።

ስለ ሥዕል የሰማሁት አንድ ታሪክ አለ። እውነት ይሁን የፈጠራ አላውቅም። አንድ ወጣት በአንድ ክፍለ ሀገር የሚገኝ ቡና ቤት ገብቶ ሲጠጣ፣ አንድ የተሰቀለ ሥዕል ያይና ባለቤትዮዋን «ሠዓሊውን ያውቁታል?» ሲል ይጠይቃቸዋል።

«አላውቀውም በመንገድ ሲያልፍ ጠርቸው ነው የገዛሁት» ይሉታል።

ወጣቱ ቀጠል አድርጎ «ለምን ይሆን ስሙን ያልጻፈበት?»

ይላቸዋል።

«ምን ያደርጋል የሱ ስም! ሥዕሉ እንደሆን የኔ» አሉት ይባላል።

# ቆርጦ ቀጥሎች

ያልተደርገውን እንደ ተደረገ ያልተባለውን እንደ ተባለ አድርጎ መናገር የሚወድ፣ በቅንዝንዝ ዓይኑ እያማተረ የሚያገኘውን ወይም በጆሮው የነፈሰውን የነገር ግሳንግስ ሁሉ አጋኖ ማቅረብ ልማድ የሆነበት አንድ የለየለት ወሬኛ ሰው ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን በድንገት ታሞ ይተኛና ሰዎች እየመጡ ሲጠይቁት እርስ በርስ የሚያወሩትን ሁሉ ልማደኛው ጆሮውን አንቅቶ በል ሲለውም ድገሙልኝ እያለ እየወተወተ አንድ ባንድ ሲያዳምጥ ይቆይና፣ ከሕመሙ ፋታ ያገኘ ይመስል እንደምንም እያቃሰተ ላልሰሙት ሲያዳርስ ይሰነብታል።

አንድ ቀን አብሮ አደግ ጓደኛውን ሊጠይቀው መጦ በወሬ ወሬ የሰማውን ይነግርዋል። «የሰሞኑን አስደናቂ አደጋ አልሰማህም? የለሁም አትለኝም አዲስአባ! ለካ ደህነኞቹም ከኛ ትሻሉም! ሰውዬው ጓደኛውን አጠገቡ አስቀምጦ ታክሲ እየነዳ ይሄዳል። ከዛ ድን ሰው መግጨት። የፊቱ መስተዋት እንክሽክሽ። ቆይ መች በዚህ አበቃ ብለህ እንው ተግጭው በመስተዋት ዘሎ መባት። ሁለቱ መሃል ቁጭ! በደንብ እንደነሱ ፊቱን መልሶ። ከዛ ወሰዱታ ወደ ሆስፒታል!» አለ፣ በሰለለች ድምፁ ብርድ ልብሱ ውስጥ እንደተሸጎጠ።

ጓደኛው በነገሩ ተገርሞ «እግዜር ይማርህ» ብሎ ይሄድና በማግሥቱ ተመልሶ ይመጣል። «ምነው አለ ወትሮህ ምን ሰማህ ዛሬ» አለው በሽተኛው፣ አከታትሎ መምጣቱን አላምን ብሎ። «ትላንት አንተን ጠይቄ እንደ መጣሁ» አለው ጓደኛው፣ «በአውቶብስ ስሄድ ያየሁትን ልንገርህ ብዬ ነው። መሸቶ ስለ ነበረ አውቶብሱ ውስጥ ጥቂት ሰዎች ነበርን። አውቶብሱ በኃይል ይሮጥ ነበር። በኋላ ድንገት ፍሬን ሲያዝ አንድ ወፍራም ተሳፋሪ የጨበጠውን ብረት ለቆ አንደረደረና መስኮቱን ሰባብሮ እፊት ሲሄድ የነበረ ታክሲ አናት ላይ ሁለት እግሩን ዘርግቶ ተቀመጠ።» «አይደረግም!» አለ፣ ወሬኛው እብሽተኛ፣ «እንዴት ሊሆን ይችላል? የአውቶብሱ መስተዋት በቀላሉ ተሰበረ ቢሉኝ አላምንም!» ይኼኔ ሰውዬው ከት ብሎ ሣቀና፣ «እንዴት ሊሆን አይችልም? ትናንት ያወራህልኝ ሰውዬ የታክሲ መስተዋት ሰባብሮ ከገባ ይኸኛው ደሞ ትልቁን የአውቶብስ መስተዋት በርቅሶ መውጣት እንዴት ያቅተዋል?» አለው ይባላል።

በእርግጥ የደረሰም ይሁን ለቀልድ የተነገረ እኔ ሳስበው ሰውዬው ያልተደረገውን ፈጥሮ በተመሳሳይ ሁኔታ ያወራው ወዶን አይመስለኝም። እንዲያው ለምናልባቱ በሽታ ያላስታገሠውን ልማደኛ ውሸታም ለመቋቋም ይረዳ እንደሆነ ብሎ ሳይሆን አይቀርም።

በሥነ ልቦና ምሁራን ለሚደረግ ትንተና ወይም ጥናትና ምርምር ካልሆነ በስተቀር፣ ለዚህ ጽሑፍ የውሸትን ምንነት ጠልቅ ባለ ሁኔታ መመልከቱ አስፈላጊ አይደለም። ቢሆንም ግን፣ ዐበይ ገጽታዎችን ለማሳየት ያህል፣ ቀንደኛ ውሸታሞችን በምናብ ትይታ በየዓይነታቸው መድቦ ማቅረቡ መጠነኛ ግንዛቤ ሊያስገኝ የሚችል ይመስለኛል።

ብርቱካን ሲያዩ ብርቱካን እንቁላል ሲያዩ እንቁላ እንወዳለን በማለት ያለ ምክንያት ከሚናዘዙት፣ ወይም ንግግር ለማጣፈጥ ብቻ ጨማምረው ከሚያወሩት ጀምሮ፣ በተንኮልና ቅናት፣ በምቀኝነት ተነሣስተው ስም እስከሚያጠፉትና ትዳርና ንብረት እስከምሚያፈርሱት ድረስ ያሉትን ውሸታሞች ስናይ፣ አንድ የምንገነዘበው ነገር አለ። ይኸውም ውሸት ሲባል ዕድሜ የማይወስነው መሆኑ ነው። ለምሳሌ አዛውንቱ አዛውነትነታቸውን ትተው፣ በወጣትነታቸው ያልሠሩትን ሠርቻለሁ ብለው ሊያወሩ ይችላላ። ወጣቱ ደግሞ በሐሳቡ ዕድሜውን ከፍ አድርጎ እያየ፣ ያልሆነው ሆንኩ ሲል ይችላል። መቸም በዚህ መካከል የውሸቱ ደረጃና መጠን እንደ

ሁኔታው ከፍ ዝቅ ማለቱ የታወቀ ነው። አንድ ጊዜ አንድ የአምስት ዓመት ሕፃን መሬት የተውለትን መሶብ እንደምንም ከፍቶ፥ የቀረችውን እንጀራ የቻለውን ያህል በልቶ፥ እናቱ ከደጅ ገብታ፣ «እንጀራውን ምን ወሰደው» ገና ከማለቷ፣ «እኔ አልበላሁም» እያለ ራሱን በትናንሽ እጆቹ ይዞ የማልቀሱ ሁኔታ፣ የዋህ መልኩ ነውና እዚህ ውስጥ አይገባም።

የውሸት ፈተና ብሎ ነገር የለም እንጂ ቢኖር ምንጊዜም አንደኛ የሚወጡ ልማደኛ ውሸታሞች ናቸው። ልማደኛ ውሸታሞች ካልዋሹ መኖር የማይችሉ፣ ከብዙ ዓመት ልምድ የተነሳ የእውነት ትርጉም የማይገባቸው ሊዋሹ ያሰቡትን ነገር ለራሳቸው እስከመዋሸት የሚደርሱ፣ ወይም «ከውሸት ያለፉ» ናቸው። ከሌሎች ሁሉ በጣም ስለሚለዩ «የለየላቸው ውሸታሞች» ቢባሉም ያስኬዳል።

«የለየላቸው ውሸታሞች» ዋንው ምልክታቸው መረን የለቀቀ ጉራቸው ነው። ከዚህም የተነሳ ከነሱ ያነሰው ሰው ቢቻል ማንነታቸውን ሳይጠይቅ የሚያወራላቸውን ሰው ሲፈልጉ ይኖራሉ። አንድ ቀን የተዋወቁቱን «ጓደኛዬ ነው» ከማለት አልፈው ተርፈው፣ ባለሥልጣን ሲያዩ ባለሥልጣን፣ ሀብታም ሲያዩ ሀብታም ሆነው ይቀርባሉ። ከጥሩው ነገር አንሥቶ «ታላቅ» እስከሚባለው ድረስ ያለውን ሁሉ «አለሁበት» ከማለት አይመለሱም። ተቃውሞ ወይም ሂስ ቢያጋጥማቸው ፈገግታና የእጅ እንቅስቃሴ ባቀነባበረው መልቲ ባሕሪያቸው የቋቋሙታል። ከሁሉም በላይ ማመሰል ይወዳሉ። ለምሳሌ በጣም የሚያደንቁትና የሚያከብሩት ሰው አጠገብ ሲያልፉ፣ ውልብ ብለው አብረው የተነሡትን ፎቶ ቢኖር ፎቶውን ይዘው እንደገና ፎቶ ከመነሣት ወደ ኋላ አይሉም።

ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ በተረትና ምሳሌ መጠቀም አዋቂነት የሚመስላቸው፣ አሽሙርና ተረብ የሚወዱ፣ ጮሌ ነን ባዮች ናቸው። ውሸታቸውን በሚያቀነባብሩበት ጊዜ ወደ ዋናው ነጥብ ከመምጣታቸው በፊት የዙሪያ ጥምጥም ተረት መፈለግ ለነሱ እንደ ግዴት ነው።ድ ብቅ አርገው ካልተናገሩ እሚሳካላቸው አይመስላቸውም። የሰው እንገር ለመረዳትም ራሳቸው በሚፈጥሩት ቅኔ አወሳስበው ካልተረጐሙ አይሆንላቸውም።

አንዳዶቹ ደግሞ ይዋሻሉ ተብለው የማይጠረጠሩ ጠጋ ካሏቸው ግን ቶሎ እሚነቃባቸው ልማደኞች ናቸው። በኑሮ የደረጁ፣ ወይም በሕይወት ልምድ በሰል ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ። የሌለውን ጥናትና ጽሑፍ ትንሽ ቀለም ብጤ ቀባብሮ «የኔ ነው» እሚለው ምሁር፣ የሙዚቃው ቅንበ ሲያምርለት ዘፈኑ ሲደነቅለት......«ዜማውንም ግጥሙንም የደረስኩት እኔ ነኝ» ባዩ ድምፃዊ ከልብወለዱ ቀነጫጭቦ እሚጽፈው ደራሲ፣ ኮራጁ ተማሪ፣ አጭበርባሪው ሰባኪ፣ ዝግ ባለ አነጋገራቸው፣ በቃላት ከመራረጣቸው ሳይንቀዠቀዙ በድብቅ እንደ ተኮፈሱ እሚገኙት በእዚህ ክልል ነው።

ልማደኛ ውሸታሞች ከሁሉም ይልቅ በቀላሉ እሚጋለጡት አላስችል እያላቸው በትምህርትና በዕውቀት ሲሸፍጡ ነው። ለምሳሌ ጓደኛሞች አንድ ላይ ተቀምጠው ካነበቧቸው ልብ ወለድ መጻሕፍት መካከል የትኛውን እንደሚወዱ ሲጠያየቁ እጁን አውጥቶ «ሎንግማንስ» ያለውን የሃያ ዓመት ሰው ምን ትሉታላችሁ? የዲግሪውን ትምህርት ሳይማር ካባውን ተውሶ ለብሶ ፎቶ የተነሣ አንድ ግለሰብ ከአማርኛ ማንበብና መጻፍ ያላለፈ ዘመዱ «ምንድን ነው የተማርከው?» ብለው ለጠየቁት «ፋኩልቲ» ሲል መልሷል ይባላል። አዛውንቱ አልገባ ብሏቸው፤ «ምን እሚሉት ነው እሱ» ቢሉት፣ «የተመረቅኩበት ነዋ» ብሎ አልፎአቸዋል። «ያውና ፎቶው ላይ፣ አያዩትም?» ቢል ኖሮ አያስገርምም ነበር።

የማስታወስ አድናቆት ለማግኘት ለመመስገን፣ ወይም ለመወደድ ሲሉ ሌላውን የሚከቡ ውሸታሞች ደሞ አሉ። «ትዝ ይልሃል? ያኔ ሰባት ቁጥሩን፣ አራትን በአብዶ ጥለህ፣ ሦስት ቁጥሩን ቀድመህ፣ ሁለት ሲመጣብህ

አጥፍ በልህ፣ ያገባሽው ጎል? ይለዋል የዱሮ ትምህርት ቤት ጓደኛውን።» «ውሸት» እንዳይል ደሞ ማሳፈር ይሆንበታል። ይገርማል እኮ፣ ለካ ማዳመጥም ችግር አለበት! በጣም የሚገርመው፣ «ትዝ አይለኝም» ወይም «ረስቸዋለሁ» ቢልም እንዲህ ያለው የፈረደበት ጓደኛ ሳይነዘንዝ በቀላሉ አይለቅህም። «ያውም እንኳን እገሌ የተባለው ተጫዋች እግሩን የተሰበረው ያንለት ነው። ሚኒስትሪ ስንፈተን። ልክ በ45 ዓ.ም ያለፈው ሳይንሳችሁ።

ይኸንንም «አላስታውስም» ብትሉ ወዮላችሁ! እነሱ ለራሳቸው የትኛው ጉቶ የትኛው እግራችሁን እንደ መታና ማን በፋሻ እንዳሰረላችሁ ሁሉ ጥርት አርገው ያውቃሉ። ይህን የመካብ ዘዴ ስለ ራሳችሁ ለማውራት ይጠቀሙበታል። «የኔም እኮ በትምህርት ጎበዝ ነበርክ። ረሳኸው? አቤት ያን ጊዜ! አንተ አንደኛ እኔ ሁለተኛ አልነበረም እምንሆነው? ሰከንደሪ እስክንገባ ድረስ። አንድ ጊዜ ብቻ እኔ በላሁሽ! ኖ - ኖ - ኖ - አምስተኛ ክፍል አንደኛ ወጥቻለሁ እንጂ! አስተውስክ! ከነምልክቱ እኔና አንተ ሽልማት ስንቀበል ሚስተር ፒትርያኖስ፣ ዘ ዳይሬክተር በቀኝ እጁ ሰርተፍኬት የሰጠን ዕለት። ያንተ ፋዘርም ነበሩ! ነፍሳቸውን ይማረውና!» አጃኢብ ማለት ነው ዝም ብላችሁ።

የራሳችው ውሸት እንዳይታወቅ መጀመሪያ ሌላውን ውሸታም ያሚያደርጉም አሉ። መቼም በእኔ ግምት «እነ እገሌን ታውቃለህ» የሚለው ጥያቄ በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ጤነኛ ዓላማ የለውም። ምክንያቱም ምን ያህል ትውውቅና ግምት እንዳለ ለማጥናትና እንደሚፈልጉት ሆኖ ከተገኘ የሌላውን ግለሰብ «ውሸታምነት» እንደ መግቢያ አድርጎ የራስንም ሳይነቃ በዘዴ ማስተላለፊያ ይሆናል።

የሰው ትዳር ነካህ ባትሉኝ፣ ይህ ሁኔታ በአንዳንድ ፉክክር ባላቸው ባልና ሚስት ላይ ይታያል። ለምሳሌ፣ አንዱ አባ ወራ ምሳ ይጋብዛሁና፣ በጨዋታ ስለ እገሌ ወሬ ይነሣል። «በዚህ ወጥቶ በዚህ ወርዶ እንዲህ ብሎ፣ እንዲህ አድርጎ......» ነገሩም አብሮ ይፈተፈትና፤ «እኔ ደሞ ውሸት የት እወድልህና» በሚል ቅባት የእራስ፣ ከግብዣው ጋር ተቀናብሮ «እሷም ነበረች ያልሞተች» እየተባለ፣ ሚስትም፣ «አዎን ምን ይጠየቃል» እያለች፣ ሠራተኛዋ በቅንዝንዝ ዓይኗ በእረፍት አሳሳቅ እያጀበች፣ ውሻዋ ብቻ ምስኪን ውሻ ሳይናገር ዓይኑንም ዝም ብሎ አፍጦ ሲጠብቅም የሚታማው ሰው የሙሽራ ልብሱን አውልቆ ከነውሸቱ ብቅ! ከዛ በኋላ ጨዋታው ያልቅና ራስ ሙገሳው ይመጣና፣ «እኔ እኮ እንዲህ ነበርኩ፣ እንደዚህ ልሆን ነው! ደሞ ለወደፊት» ቅብርጥሴ። ነገሩ ከውሸት አልፎ ኩራትም አይጠፋበትም። መቼም በዚህ ጊዜ ጆሮአችሁ መዝጋት ስለማይቻላችሁ የሚኖራችሁ ምርጫ ቢቻል ብቹ በልቶ ስለ ቁንጣን ማሰብ ብቻ ይሆናል።

ለማስመን እንዲያመች ሲባል ቦታና ጊዜን ምልክት እያደረጉ፣ የምራቅ ቱፍታን መቆጣጠር እስኪያቅት ድረስ መለፍለፍ ሌላው የውሸት ዘዴ ነው። የዚህ ደንበኞች የሆኑ ግለሰቦች ባነጋገር ፈጣን ናቸው። የንግግራቸውን ጣልቃ፤ «እኮ፣ ታዲያስ፣ እንዴታ» ማለት ያበዛሉ። ለማስተማመን ሲሉ የማያደርጉትን ነበር የለም። ለምሳሌ በራሳቸው ትረካ በሚገረሙበት ጊዘ ዕቃ እንደሚያወርዱ ሁሉ ሁለት እጃቸውን ድንገት ወደ ላይ ከዘረጉ ከተቀመጡበት ብድግ ሲሉ ምንም አይቀራቸውም። ቦታውን ለማመልከት በአሥሩም ጣታቸው ቢጠቁመንዳይገርማችሁ። ምክንያቱም ይባስ ብለው በቅብጥብጥ አወራራቸው ድንገት ጠረጴዛውን በኃይል መትተው ሊያስደነግጧችሁ ይችላሉ። «ይኸ ትልቁ ሕንፃ ስሙን አምጣልኝ። ምነው ይኸ ዛሬ ላውንደሪ የሆነው» ይላሉ። ነገር ሲጀምሩ ወስፌ ዓይናቸውን ከአንዱ አድማጭ ወደ ሌላው እያንቀዣቀዡ፤ «ታዲያ ያኔ ፎቁ አልተሠራም። ስንሰልና ግራዋ ጥቅጥቅ ያሉበት ነበር።» ደሞ ያመጡታል ሐቁ እንዳይገኝና እንዳይጋለጡ። ባጋጣሚ የማውቃቸው ካለ ለመናገር ገና ጉሮሮውን እንደማጣራት ሲል፣ የተሳሳቱ ወይም የረሱ በማስመሰል ነገሩ እንደሚስማማ አድርገው ለመለዋወጥ አይሳናቸውም።

ከነዚህ በደረጃ ከፍ የሚሉት የሚወራውን ወሬ መነሻ አርገው እዛው መፍጠር የሚችሉ፣ በምናብ አጠቃቀማቸው በጣም የተራቀቁ፣ ባጋጣሚ ከድርሰት ያመለጡ ውሸታሞች ናቸው። ለምሳሌ የአደን ጨዋታ ተነሥቶ አንበሳ እንዴት እንደ ገደለ አንዱ መናገር ሲጀምር፣ ከቻሉ ስለ አውራሪስ ካልሆነላቸውም ስለ ሚዳቋ ለማውራት ይዘጋጃሉ። የአድማጮቻቸውን ሥነ ልቦናዊ እርካታ ማወቅ ሌላው ተሰጥኦዋቸው ስለሆነ፣ የሚጥመውን የአቀራረብ ሂደት እዛው ፈልገው ለፈጠራቸው ያውሉታል። ታዲያ በዚህ ጊዜ ነገሩን በተመስጦ ስለሚያቀነባብሩ ብቻ ሳይሆን ድንገት ሊመጣባቸው ለሚችል ጥያቄ በቅድሚያ መግቢያ መውጫን ስለ ሚያፈላልጉ፣ ዓይናቸውን ብቦዘዝ አርገው ይመለከታሉ እንጂ የሚወራውን አይሰሙም። እንደሚሰማ ሆነው ለመታየት ሲሞክሩ ግን፣ ለምሳሌ ከመሬት ተነሥተው ሲስቁ፣ ልብ ብሎ ላያቸው በእንቅልፍ ልባቸው የሚቃዡ ይመስላሉ።

በማናቸውም ቦታና ጊዜ ነገር ሳያዳምጥ ያዳመጠ ለመምሰል የሚሞክር ሰው በይሉኝታ ጣል በሚያደርጋቸው ትርጉም የለሽ ቃላትና በተደበተ አኳኋን ለምሳሌ፣ ገርበብ በሚል ፈዛዛ ዓይኑ፣ በማዛጋቱ ሁሉ ያናድዳል። ከዚህም በላይ የተናጋሪውን ጊዜና ጉልበት በማበከኑ፣ ቁም ነገሩን ቸለል በማለቱ ያበሳጫል። ነገር ግን አንዳንዱ እንዲህ የሚያደርገው ወዶን አይደለም። የድምፁን ከፍታ ሳይቀንስ፣ ያነጋገር ዜማውን ሳይለውጥ፣ በዛ የመሐላ ቃላቱን ቅደም ተከልተ ሳያዛንፍ አንዱን ነገር ደጋግሜ ካላወራሁ የሚል ሲያጋጥመው፣ ወይም እንቶፈንቶውን እያነበነበ፣ ከዛም ብሶ፣ «ካላየኸኝ አላወራም» በሚል ዓይነት ፈላጭ ቆራጭነት አገጭ ይዞ እሚጎትት ወሬኛ ሲጥልበት ሳይወድ በግድ አስመሳይ አዳማጭ የሚሆን አለ።

ሰው መቼም እውነትም ይሁን ውሸት ወሬ አልሰማም ብሎ ከሰው አይጣላም። ባይሆን ከውሸታም ሰው በዘዴ ለመለየት ይሞክራል። ነገር ግን ይኸም የማይቻልበት ጊዜ አለ። ሩቅ ሳትሄዱ፣ ዝናብ ሲጠለል በውሸታም ወሬኛ የተጠመደ ሰው ጠፈጠፉን እያየ የውኃውን አንክብሎች እየቆጠረ ባለበት ቦታ ይቆማል እንጂ፣ እስኪያባራለት ድረስ የት ይሄዳል? መኪና በመንዳት ላይ ያለውስ ስልክ እንጨቱንና አስፋልቱን በዓይኑ እየፈለገ ለይምሰል ፈገግታውን ከማሳየት በስተቀር ምን አማራጭ አለው?

ነገሩ ምን ያህል እንደሚያሰለችና እንደሚያስመርር የደረሰባችሁ ታውቁታላችሁ። ለዚህ ምናልባት፣ ውሸት የተሞላው ወሬ ፊቱ ተደቅኖ መንገድ አልለቅ ሲለው በትላልቅ ዓይኖቹ ትክ ብሎ እያየ ከሦስት ከአራት ሰዓት በላይ በትዕግሥት የመቀመጥ ችሎታ ያለው ምሕረት ወርቁ የተባለው የትምህርት ቤት ጓደኛዬ የሚጠቀምበት ዘዴ ችግራችሁን ሊያቃልልላችሁ ይችል ይሆናል። እንደሱ አባላ «ውሸታሙን ወሬኛ በዓይናችሁ እዩት። ፈገግ ሲል ፈገግ በሉ። ራሱን ሲነቀንቅ እናንተም ነቅንቁ። ሲገረም ተገረሙ። ነገር ግን የሚለውን አታዳምጡ። ዝም ብላችሁ የራሳችሁን ጥሩ ሐሳብ (ኑሮ ነክ ወይም እውቀት ነክ የሆነ ሐሳባችሁን) አስቡ። እንዲሁም ስታደርጉ ጊዜያችሁን ተጠቅማችሁበት ማለት ነው። በደንብ ከተለማመዳችሁት ይቻላል!!»

ፍርጥም ያለ ምክሩ ይኸው ነው።

# የፈተና ሰሞን

የልጅነት ዘመን ሲታዘብ በትዝታ መልክ የሚመጡ ብዙ ነገሮች አሉ። ገጠር እረኝነቱ፣ እርሻው ማኅበሩ፣ ከተማ፣ ላደገው እስፖርቱ ሙዚቃው ሲኒማው፣ በትምርህት ቤት ዓለም የሚገኘው ሁሉ ሊታወስ ይችላል። በተለይ የትምህርት ቤት አካባቢ ያለ ትዝታ ከሁሉም የጎላ ይሆናል። ወደ ኋላ መለስ ብለው ካዩት ዛፍ ጥላ ሥር በክብ ተቀምጦ መዝምሩ መዘመሩ፣ ጅምናስቲክ መሥራቱ፣ ሥዕል ብጤ መሞነጫጨሩ፣ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ጋር መንገዳገዱ፣ ጫካ ሂዶ ማጥናቱ፣ መንበርከኩ፣ መገረፉ በዚያ የዕድሜ ክልል ጉልህ የሆነ የሕይወት ድርሻ ይኖረዋል። ታዲያ ለሁሉም መቋጫው ፈተና ነው - ከክፍል ወደ ክፍል ማለፍ - በዕውቀት ደረጃ ለመወዳደር መለኪያ የሚሆነው።

እስቲ ከአንድ ዘመም ያለች ጎርፍ እሚያስፈራራት ጎጆ ውስጥ እንግባ። ወራቱ ሰኔ ነው። ጊዜው መሸትሸት ብሏል። የእንቁራሪቶቹ ቁርቁርታ፣ የነፍሳቱ ሲርሲርታ፣ የውሾቹ ጩኸት ይሰማል። ጋዟ ልታልቅ የደረሰች ኩራዝ ጭልጭል ትላለች። አንድ ልጅ ጋቢ መሣይ የተደረተ ጨርቅ ደርቦ ያጠናል - ነገ ፈተና ነው! የኩራዙ ጭስ አፍንጫውን መግባቱ አይሰማውም፣ ብቻ ያጠናል - ያጠናል። ከዛ፣ ውድቅት ላይ ይተኛል። ግን እንቅልፍ አይወስደውም - «ነግቶልኝ ብቻ።» ያጠናውን ሁሉ ካለብት ጎልጉሎ ሲያወጣው አንደኛ ሲሆን፣ ሲሸለም፣ ከዛ ክፍል ሲያልፍ ሲቀጥል ሲገሰግስ በሐሳቡ ይታየዋል።

ሌላው ደግሞ በቪላ ቤቱ ውስጥ በሥዕል በተጌጠ መኝታ ቤቱ ውስጥ በአረግራጊ አልጋው ላይ ከነፒጃማው በጀርባው ጋደም ብሏል። ደብተሮቹና መጽሐፎቹ ውድ በሆነ ቦርሳ ውስጥ በዚፕ እንደ ተዘጉ ኮመዲኖው ላይ ተቀምጥው የማንበቢያውን መብራት ይሞቃሉ። እሱ ግን እንደ ኮረዳ ጡት በሾሉት አምፖሎች ላይ ዓይኑን ተክሏል። እና፤ ዝም ብሎ ያስባል፣ ያሳባል። ምክንያቱም ነገ ፈተና ነው! ለመሆኑ ምን ሊመልስ ነው? መቼም ስም ብቻ ተጽፎ አይወጣ......ደብተርም ተይዞ አይገባም........እስከነአካቴው ባይፈተንስ........አይ፣ ይኸ እንኳን አይሆንም? ምን ሰበብ ሊሰጥ? ለወላጆቹ ምን ሊነገር! ከጓደኛስ ለምን ይታነስ......ደሞ ማን ያውቃል......እሚያስኮርጅ ከተገኘ.......ወይም በአቦ ሰጡኝ ከተሳካ? መሞከር አለበት......

በፈተና ሰሞን ባጠናና ባላጠና ተማሪ መካከል ያለውን ልዩነት ይህ ብቻ አይደለም። ላጠና ተማሪ ቀኑ ብሩህ ሆኖ ይታየዋል። ሰማዩ ያረገዘው ደመና ሙዚቃው ነው። በጥሩ ስሜት ያስፈነድቀዋል። የጠዋት ውርጭና ጤዛ አይቀዘቅዘውም። ጎርፍና ድጡን እያለፈ በቁራጭ ጋዜጣ ብጤ ጠቅለል አድርጎ በንጽሕና እየያዘ ትምህርት ቤት መድረሱ ነው።

ያላጠና ተማሪ ግን ትምህርት ቤቱ የሚደርሰው ጨፍጋጋ ፊቱን ይዞ ዕድሉንና ራሱን አስተማሪዎቹንም እየተራገመ ነው። ሁሉ ነገር ያስጠላዋል። «ብርድ ብርድ የሚል ዘገ ቀን። ነፋሱም አስቀያሚ። ደሞ አህዮቹ ሲጋፉ። ያውና ተገትሯል። ደባሪ ትምህርት ቤት!» ያየውም ሰው ሁሉ ያናድደዋል። ቀናተኛ ባል ከሚስቱ ጋር ተጨቃጭቆ ሲወጣ ፍቅረኞችን እጅ ለእጅ ተያይዘው ሲሄዱ ሲያይ እንደሚያገረሽበት ሁሉ እሱም በደንብ አጥንተው ለፈተና የተዘጋጁ የክፍል ጓደኞቹን ባየ ቁጥር ደካማነቱ እንደ መብረቅ ብልጭ ይልበትና ጊዜያዊ ጥላቻ ያድርበታል። አካሄዳቸው ያስጠላዋል። አነጋገራቸው አሣሳቃቸው ሁሉ ያደንቁረዋል። ረጅሙን ለምን ረዘመ፣ አጭሩን ለምን አጠረ፣ አይበል እንጂ አኳኋናቸው ሁሉ ያበሽቀዋል። አንዳንዱ ተፈታኝ በመውደቅ ተስፋ የቆረጠና የሚመጣውን ለመቀበል የተዘጋጀ ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ተማሪ እንኳን ለጥያቄ ሊበረግግ ዓይኑን ቢደለቁለትም ፍንክች አይልም። የመውደቅ ፍራቻ ያለበት ግን

የአለማጥናተፍረትም ሰለሚጨማመርበት ፈተናው እስካለቀ ድረስ የተረጋጋ መንፈስ አይኖረውም። ገና ወደ ፈተናው አዳራሽ ሲገባ እግሮቹ እንደ መተሳሰር ይሉበታል። መቀመጫው ይጠፋበታል። የጥያቄው ወረቀት ሲታደል በላብ መጠመቅ ይጀምራል። የእጅ መንቀጥቀጥም ሆነ የቴርሞ ሜትር ንረት በመጠኑ አይጠፋበትም። ራስ ምታት የሚያማቸው ወይም አዙሯቸው ነፋስ ወደ አለበት ተወስደው ተሽሏቸው የሚመለሱ ተፈታኞች አሉ። ጥያቄ ወረቀቱን በርጋታ በመቀበል ፈንታ ለተማሩት ትምህርት እንግዳ ሆኖ፣ አባቱ ሊገርፈው አለንጋ ሲያነሣ እንደሚርበተበት የስምንት ዓመት ልጅ ዓይን እያጮለጮሉ፣ ሐውልት ሆኖ መቀመጥ፣ እንደ ገመምተኛ ገርጥቶ መታየት ሁሉ ይኖራል።

አንዳንድ ተፈታኝ ደግሞ ያጠና በመምሰል ራሱን አታሎ ሌሎቹንም ያታልላል። «ታዲያስ፣ እንዴት ነው?» ሲባል፣» ሃምሳ አናቷ ላይ ካገኘሁ ሌላ ምን እፈልጋለሁ» ይላል፣ ወዝ ያላት ፈገግታውን እዛው በዛው ይፈጥርና። በልቡ ግን ሃያም እንደማያገኝ ያውቃል። ታዲያ ፈተናው ቀለበት የማጥቆር ዓይነት ሆኖ በአቦ ሰጥ ሃምሳ ወይም ከዚያ በላይ ካገኘ፣ በወዛም ፈገግታ ላይ ጉራውን ለማርከፍከፍ አይመለስም። በአፍራሻው ደግሞ፣ «ምንም አላጠናሁም ዘንድሮ ወዳቂ ነኝ» ሲል ቆይቶ ዘተና አምስቱን ማርከ የሚጨረግድ፣ ራሱን ዝቅ ዝቅ ማድረግ የሚወድ በአቋሙ ኮስስ፣ በአለባበሱ በመልኩ አነስ ያለ፣ ባዩት ቁጥር ዳገት ጨርሶ ብቅ ያለ የሚመስል ድምፀ ሰላላ ተማሪ ይኖራል።

በፈተና ሰሞን፣ በተለያዩ መፈተኛ ክፍሎች ወይም አዳራሾች ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ይታያሉ። አንዱ ጋ የከበደው ሌላው ጋ ቀላል ይሆናል። ሌላው የሠራውን መቅዳት፣ መገልበጥ ወይም ሌላው የለፋበትን ቁጭ ብሎ መብላት። ኩረጃ ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ድረስ የሚዘልቅ ደፋር የሆነ የፈተና ጠላት ነው። እርሳስ ለመቅረጽ ልዩ ልዩ ቀለም ያለው አስክርፒቶ ለማጠራቀም ጉጉትና ጥረት ባለበት በአንደኛ ክፍል ይጀምርና ትላላቅ መጻሕፍትና የኮምፓስ መሣሪያ ይዞ መታየት የዕውቀት ምልክት ነው በሚባልበት ሁለተኛ ደረጃ መግቢያ ላይ አድጎ ከዚያም በላይ ይቀጥላል።

መቼም ለሁሉም መሠረቱ አንደኛ ክፍል ነው። የዚህ ክፍል ሕፃናት ተማሪዎች እርሳስ እስኪርፒቶ እየጣሉ መግዛት ልዩ ምልክታቸው የሆነ፣ ቁልፉ በተበጣጠሰ ኪሳቸው ውስጥ ከዳቦ ፍርፋሪና ቆሎ ጋር ምላጭና ላጺስ የሚይዙ ናቸው። አንዳንዶቹ ራሳቸውን ሊያህል ትንሽ የሚቀረው ቦርሳ ጀርባቸው ላይ የሚያነግቱ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ነፋስ ከእጃቸው እንዳይነጥቃቸው የሚጠነቀቁለት የተሻሸ ደብተር ያላቸው ናቸው። ከመካከላቸው የከለር ዓይነት የሚወዱ፣ ኮፒ እርሳስ የማይለያቸው፣ መሬት የወደቀ እንጨት መሳይ ፈልገውም ቢሆን ከቁመታቸው ጋር የማይመጣጠን የራሳቸውን ማስመሪያ የሚይዙ ይገኙባቸዋል። ከየቤቱ ሲጠሩሩ ይዘገዩ እንደሆነ ነው እንጂ ከትምህርት ቤት ያውም ከፈተና አይቀሩም። ሲጫወቱና ሲታገሉ ማንገቻው ቢበጠስ እንኳን ሱሪያቸውን እንዳይወልቅ ባንድ እጃቸው ከፍ እያረጉ እክፍላቸው ከች ይላሉ። በሚፈተኑበት ጊዜ ግን አስተማሪ እሚያበግኑ እነሱ ናቸው። ኩረጃቸው አይጣል ነው ለዛውም ፈታኙ እያያቸው። ተው ሲባሉ ይደነግጡና ይተዋሉ። ወዲያው ግን የሌላውን ማየት ይጀምራሉ። እነዚህ ሕፃናት መኮረጅ ብቻ ሳይሆን በፈተና ሰዓት ላጺስና መቅረጫ ይናጠቃሉ። ደሞ አንድ ቦታ አርፈው ሰለማይቀመጡ ካንድ መቀመጫ ወደ ሌላው እንዳስፈለጋቸው ይዘዋወራሉ። ወይም ዝም ብለው እግራቸውን ያለማቋረጥ ያወዛውዛሉ።

በዕድሜ ከፍ ባሉት ዘንድ ኩረጃ የተለያየ መልኮች አሉት። ዘዴዎቹ ወረቀት ከመለዋወጥ አንሥቶ ምልክት ማስተላለፍ መቀበል ድረስ የተራራቁ ናቸው። ሆኖም፣ «የሰይጣን ጆሮ አይስማው» ብንል እንኳን የተማሪ የኩረጃ ጆሮ ገና የወደፊቱን ቴክኒክ ካህኑ የሚያውቅ ስለሆነ መዘርዘሩ አስፈላጊ አይሆንም። እኔ ለራሴ ላስበው ግን ሲኮርጅ እንደሚያዝ ተፈታኝ ይበጥል የሚያስገርም አጋጣሚ እሚኖር አይመስለኝም። ልክ

ስታዩት ጨልጯላ ዓይኑ መግቢያ ቀዳዳ ያጣና ሽቅብ ቁልቁል ማለት ይጀምራል። ይባስ ብሎ ሊያባባችሁ ሲፈልግ ከቻለ እንባ ያቀራል። አለዚያ እጆቹን እያሻሸ ጸጉሩን እያከከ ጣራውን በንዴት ማየት ይጀምራል ፡

ዓይን ቀቅሎ የበላው ደረቅ ኮራጅማ እንደትነቁበት ስትዩት ዝም ብሎ ያያችኋል፣ ሲቅነዘነዝ የነበረውን ዓይኑን በአንድ ቦታ ላይ ተክሎ ይቆያል - ዞር እስክትሉለት ድረስ። ሌላም ደሞ፣ «የምኮርጅ መስሎህ ነው እንጂ መልሱን አውቀዋለሁ» የሚል ዓይነት መልዕክት ለማስተላለፍ ከመሬት ተነሥቶ ወደ እናንተ እያየ ሣቅ ሣቅ፣ ወዲያው ግንባሩን ኮስተር፣ ከፍነሩን ነክስ፣ ደሞ እንደገና ቁንጥንጥ ፈገግ ይልና አንዳች ነገር ያስታውስ በማስመሰል ወረቀቱ ላይ እብስክሪፕቶው ጫር ጫር ያደርጋል።

አንዳንዱ ኮራጅ ንቅንቅ ሳይል ቁጭ ብሎ ያስተውላችኋል። ብዙም ሲጸጽፍ አታዩትም። ዝም ብሎ ያስባል። ድንጋጤ እሚባለው ዝር አይልበትም፡ እሱን ተጠንቀቁ፣ የብዙ ዓመት ልምድ ያለው ነው። «ቁጭ ብያለሁ - ታዲያ ምን ይጠበስ!» በሚል ዓይነት መዝናናት ብቻ የሚመለስ የዋዛ ተማሪ እንዳይመስላችሁ። እንኳን እፊቱ ቆማችሁለት ይቅርና ከኋላውም ብትሆኑ የተደበቀ የኋላ ዓይን ያለው ይመስል ዞር ሳይል ያላችሁበትን አካባቢ ፊታችሁን ወዴት እንደመለሳችሁ እንቅስቃሴያችሁን ሳይቀር አንድ ባንድ ያውቃል። እና፣ አንድ ጥሩ አጋጣሚ ሲያገኝ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ የሚፈልገውን ገጽ መልሱን ገልብጦ ተዝናንቶ ሲያይችሁ እንደቆየው ተዝናንቶባችሁ ከአዳራሹ ይወጣል።

የኩረጃ ዓይነቱ ተዘርዝሮ አያልቅም። ቴክኒክም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ነው የሚሄደው። ላብ ዝም ብሎ በመሐረብ መጥረግ፣ የተሰላቸው በመምሰል በረጅሙ መተንፈስ፣ ማዛግት፣ እየተንጠራሩ በጣት መናገር.......ደሞ አትደንግጡ እንጂ ፈታኝን በስውር ጥቅሻ መማፀን.......የቴክኒኮቹ ቀላል የሚባሉት ናቸው።

ታዲያ ይኸን ሁሉ ስታስቡት፣ ለኩረጃ እሚውለው ጭንቅላት ለትምህርት ቢውል ምን ነበረበት አትሉም!?

# ዕድል ወይስ አጋጣሚ

በአንዳንድ ሰዎች ላይ ተደጋግመው የሚደርሱ አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ። ሰውየው የተለያዩ ጃኬትችና ቲትሮን መሳይ ጨርቆች ሲለብስ ይከርማል። ከዚያ አንድ ቀን እርሙን ሰማያዊ ቤት ይለብስና በእግሩ እንዳይሄድ ከአባሯ የዳነ መስሎት አውቶብስ ውስጥ ይገባል። መቼም መጨናነቁ ያለ ነገር ነውና ብዙ ሳይቆይ በግራውም በቀኙም ጋቢ የለበሱ ሰዎች ያጋጥሙታል።

ሴትዮዋ በሀገር ልብሷ አጊጣ በታክሲ ትጓዛለች። ጥቂት ሄድ እንዳለች ግራሶ የጠጣ ቱታ የለበሰ ጋራዥ ሠራተኛ መለዋወጫ ዕቃውን በግዙፍ እጁ እንደጨበጠ ይገባና አጠገቧ ይቀመጣል። መከላከያ ወይም መፍትሄ የሌለው ችግር ነው - አጠገቤ አትቀመጥ ወይም ውረድ አይባል ነገር።

ታዲያ እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ ምን ትሉታላችሁ? ዕድል ወይስ አጋጣሚ ፡

ከዚህ ጋር የሚነሣው ሌላ ጥያቄ ደግሞ ይህ ዓይነቱ ነገር የሚደርሰው በተለያዩ ግለሰቦች ላይ ነው። ለምሳሌ ማጋነንና ልዩ ትኩረት መስጠት በሚወዱ፣ ወይም አስቀድመው በሚፈሩና በሚሠጉ ሠዎች ላይ የሚለው ነው። ዝናብ ጃንጥላ ገዝቶ ከገበያ አዳራሽ የሚመጣ ሰው መሞከሪያ ወይም ማሚሻ ሊሆን ቢችልም፣ ከላውደሪ የወጣ ልብስ ለለበሰ ግን ምን ያህል እንደሚያበሳጭ መገመት አያስቸግርም። ጨርቅ

ያሰጣች የቤት እመቤኢት እምትመኘው የፀሐይ ሙቅት ሲሆን፣ በእግር ጉዞ ለሚያደርግ ሰው ምንኛ አስፈሪ ሆኖ እንደሚታየው ግልጽ ነው። እንደሚመስለኝ፣ ይኸን መሳይ ነገር አንዳንድ ሰዎች የአጋጣሚ ጉዳይ ነው ብለው ያልፉታል ፡ አንዳንዶቹ ግን፤ «ዕድሌ ነው፣ ወ፣ ወትሮም አዲስ ልብስ ስለብስ አሮጌውን አይጥ ይበላብኛል - ጠላ ስጠምቅ ብርዱና ውርጩ እጓዳዬ ድረስ ይገባል - ለጥሩ ግብዣ ስጠራ ተቅማጥ ይይዘኛ - የቤተ ዘመድ ወይም የጓደኛዬ ሠርግ ዕለት ድምፄን ይዘጋኛል....» የሚለውን አባባል ልማድ አድርገው ይጠቀሙበታል።

የእነዚህ ሰዎች እምነት እኮ ምን ያህል ልክ ነው የሚለውን ጥያቄ ለመመልከት አልሞክርም። እኔ ሳስበው እንዲህ ያሉት ግለሰቦች ትእግሥት ከማጣታቸውና ከመበሳጨታቸው የተነሣ ተደጋግመው የደረሱባቸውን ሁኔታዎች በመገረም መልክ ሲያጤኑባቸው ይቆዩና ቀስ በቀስ ሳይታወቃቸው እያመኑባቸው በመሄድ ልማዳዊ አነጋገር ያደርጓቸዋል። ለምሳሌ፣ በሆቴል ቤቶች ምግብ ሲያዝ በተደጋጋሚ ቀናት ለሌሎች ባላተኞች ጥሩ ጥሩ ቅልጥም ሲመጣ ለሱ ግን የተጠጋ መሳይ ፍርምባ የሚደርሰው ሰው ምግብ አቅራቢዎች ያደሙበት ይመስል፣ «እኔ ድሮም የሆቴል ነገር አይሆነኝም.......» ማለት ይጀምራል። «ለገንዘብ ሲሆን ዕጣ አይወጣልኝም - በማልፈልገው ጊዜ ግን ይወጣብኛል። አምሮኝ ልገዛ የጓጓሁት ዕቃ ከገበያ ይጠፋል - ደስ ያለኝ ቀን ለካፊ አላጣም» የእነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ አባባሎች መነሻ መድረሻ የአጋጣሚ ጉዳይ መሆኑ አያጠያይቅም።

በሌላ በኩል ተደጋግሞ ባይደርስም ከፉኛ የሚያበሳጭ ሁኔታ ካጋጠመም ንዴቱን የሚያጋነነ አባባል በወቅቱ ሊፈጠር ይችላል። ትልቅ ዕቃ አግዝኝ ተብሎ ሲሸከም ክብደቱ ያስመረረው ሰው፣ «ዱሮም ዕቃ ልግዝ ስል ከባዱ ወገን ነው የሚደርሰኝ!» ብሎ ሊነጫነጭ ይችላል። ሆኖም ይህ አባባል፤ «ደሞ ይቺ ላንተ ምንህ ናት!» ብለው ሲሉት ቁም ሳጥኑን ካልተሸከምኩ ብሎ ሽንጡን የሚበጥሰውን ወይም፣ «በምግብ ማን ሊስተካለው - አንበሳ እማይደል እንዴ?!» ከተባለ ትንፋሽ እስኪያጥረው ድረስ ጎስጉሶ ስሚንቶ ላይ በቁጣን የከሚንከባለለውን ግብዝ ሰው አይጨምርም።

በዕድል ወይም በአጋጣሚ ሁኔታዎች አካባቢ በቂ ምክንያት እየታጣለት ራስን የራስ ምቀኛ አድርጎ በመቁጠር የሚዘወተር ልማዳዊ አባባል ደግሞ አለ። የዚህ ልማዳዊ አባባል ደንበኛ የሆነ አድን ወዳጄ፣ «ጥሩ የበግ ቅልጥም ቀርቦልኝ ለመብላት እጓጓና ገና በጥርሴ ስነካው ተፈናጥሮ ይወድቅብኛል» ሲል አጫውቶኛል። ይኸንን ምን ትሉታላችሁ? ዕድል ወይም አጋጣሚ? ደሞስ ምናልባት አጥንቱን የሚይዝለት ሰው ያስፈልገው ይሆን?

አዋቂ ለመምሰል ሲባል ምግብን አለ አግባቡ ከመብላት ግን ቅልትም ቢፈናጠር ይሻላል። አንድ ጊዜ ወይዘሮ አንድ ግብዣ ላይ ጨር ይመስላቸውና የስኳር ማስቀመጫውን ብድግ አድርገው ምግቡ ላይ መነስነስ ሲጀምሩ፣ አድራጎታቸውን የተመከተ ፊት ለፊታቸው የተቀመጠ ወጥት «ኸረ እሱ ስኳር ነው፣ እሜትዬ! ጨው ይውልዎት?» ቢላቸው፣ «ስኳርና ጨው የማልለይ ሆኜ ታየሁት እንዴ?» ብለው የማሾፍ ሣቅ ሣቁበትና ስኳሩን ደህና አድርገው መነስነስ ቀጠሉ፣ የቀረበም ምግብ አይመለስምና እንክት አድርገው በሉት። በእርግጥ የተደረገ ነው መሆኑን ማረጋገጥ ያስቸግራል። ሆኖም የሕዝብ ቴሌፎንን አጠቃቀም ሳያውቅ ዝም ብለው ሃያ ሳንቲም ጨምረው «ሃሎ! ሃሎ! ስልኩን ምን ነካው» የሚሉ ሰዎች አጋጥመዋቸው ልታስረዷቸው ስትሞክሩ፣ «ባላገር መሰልኩህ? ልታስተምረኝ ከጀልክ?» በማለት ከፍ ዝቅ አድርገው ካገላመጡዋቸው በኋል እንደ ገና «ሃሎ!» እያሉ ስልኩን ሲያሠቃዩ ካያችሁ፣ የሴትዮዋ በስኳር መብላት የሚያስገርማችሁ አይመስለኝም።

በብዙ ሰዎች ላይ የደርሳል ብዬ እምገምተው ሌላው ደግሞ ኪስ ባዶ ሲሆን የሚግተለተው የንጭንጭ ጋጋታ ነው፣ «እጇ አመድ አፋሽ ነው - ጋብዘኝ እንጂ ልጋብዝህ የሚለኝ አላገኝም - በይ ተበይ አያዝልም። ምኑ ቅጡ! ተረፍረፍ ባለ ጊዜ ሲመነዘሩ መዋል እንዳለ ሁሉ ሲታጣም የዕለቱን «ዕድል» እያጋነኑ ያዩትን ሁሉ መራገም አለ። «የዛሬው ለማንኝ አበዛዝ! ጥፉ ካጠገቤ! ታድያስ? ሱቅ በደረቴ - ዛሬስ ሱቁን ራሱን ነው ያነገገው! ሎተሪ - ነገ እሚወጣ! እናሳምራ! ሊስትሮው - ደሞ በዚህ በብርድ ራሱን ይላጫል! ቆሎ - የገብስ፣ የሽንብራ፣ የስንዴ - ለምን ራስዋ በልታ አትጨርሰውም?! - ዛሬ የተቀጠፈ ትኩስ ብርቱካን - ቁጭ አረገላችሁ፣ አውላላ ሜዳ ላይ፣ ራሱ የሰራውን ሚዛን! ባለኦቾሎኒው ብቻ - ደርበብ እንዳለው - ወንበሩ ላይ - የሱ እንኳን ይሻላል። ምን ዓይነት ቀን ነው? በዚህ ረገድ የሚዘወተሩ አባባሎች ሞልተዋል። «ዛሬ ምንም ነገር አልተሳካልኝም - ደብዳቤ መጻፍ አይዋጣልኝም - ሮብ ቀን አይቀናኝም - ህዳር ወር አይሆነኝም......» ጥቂቶቹ ናቸው። ዕድል ወይስ አጋጣሚ?

እንደሚታወቀው ሁሉ ዐውደ ዓመት በኃይማኖት ረገድ ብቻ ሳይሆን በአመጋገብም የተለየ ደማቅ ይዞታ አለው። ጠላው ይጠመቃል - ዶሮው በጉ ይታረዳል። በተለይ በፋሲካ በዓል፣ ለዚያ ቀን ብቻ የተፈጠሩ ይመስል የጾም መፍቻ ይሆናሉ።

ታዲያ በአንዱ በዓለ ፋሲካ ባልዮው ሲጾም ከርሞ በመፈሰኪያው ዕለት የኮቱን እጅጌ ሰብሰብ አድርጎ በአባወራነቱ ቀረርቶ እንደሞሞከረው አዝማሪ ኮራ ብሎ ቢላውን ይስልና ዶሮውን ካረደ በኋላ ወደ ሚሄድበት ይሄዳል። ሚስትዮዋ የአደገችበትን ብዙ ቀን ያስመሰከረች መሆኗ ባይዘንጋትም፣ ቀኑ ከሌሎች ቀኖች የተለየ መሆኑ እየታሰባት መወራጨቱን ገና እንዳቆመ ዶሮውን የፈላ ውሃ ትገለብጥበትና የበዓሉ እለት የክት ልብሷን ለብሳ አምባሯን አጥልቃ ለመታየት ከጓጓችው ሠራተኛዋ ጋር ሆና የወጡን ስራ በቅልጥፍና ትያያዘዋለች።

«ሽንኩርቱን አቀብይኝ።»

«ይኸው።»

«ሎሚውስ የት ደረሰ?።»

«ይኸው።»

«ቀሰሙን እንዲሁ ሰባብራችሁ ጨርሳችሁታል እስቲ አገልግሉ ውስጥ ፈልጊ።»

«ውይ እትዬ! ድመቷ ብገባችልዎት!»

«ክፍ! ኧረ ውጪ! አይንሽ ይውጣ።»

« በይ እኮ ውጪ! ዋ ዛሬ ቀን ልብ አድርጊ!»

«የቅቤውን ዕቃ! ቶሎ በይ።»

«ኪሎውን በሙሉ ሊያረጉበት?»

«ደሞ ማን ገማች አደረገሽ ባሌን፣ እሱ ለራሱ ቅቤ ሲያንስ አይወድ።

«እትዬ! የዘንድሮ በርበሬ.....ቅመሙ ሽክ ህኖ ተዋጥጧል።»

«አብራ እሱማ! ሐኪሙ በርበሬ ተው አለው እንጂ.......መስሎት እኮ ነው......የኔ ባል አልጫ ሊበላ ማለት። »

ባል መሸት ሲል ይመጣና የታመቀ የሳጥን ቃና ያለውን ሻሽ የመሰለ ጋቢውን ተከናንቦ፣ አከፋዮች እንደሚያደርጉት ሁሉ በጥሞና ተቀምጦ ቤቱን ቃኘት ቃኘት ያደርጋል።

«ምን ጭስ እያጨሳችሁ ነው? ከሰል ነው እንዴ?»

«ታዲያ በምን እንስራ? ወይ ኮረንቲውን ግዛልና።»

«ኸረ ይኸን ከሰል ራዲዮ ከልክሏል።»

«የዛሬው ከሰል ጭስ የለውም። እልቅዬ ጋደም በል ደክሞሃል።»

«ወቸ ጉድ! ጎፈሬ የምናበጥር መሰለህ? ሥራው መቼ ፋታ ሰጠንና።»

«የውጭውስ በር ተዘግቷል?»

«አላንተ ማን ከፈተው! የወጣ የለ፣ የገባ የለ። መቸ እንዲህ ደላንና።»

«ኸረ በጉን አስገቡት። እሚበላውም ስጡት። ተሰበታ ጭኜ ያመጣሁትን በግ በራብ አትግደሉብኝ።»

«እሺ።»

«የምቀባው ቅቤ ገዝታችሁ የለም.....ለዚህ ለራስ ምታቴ?

«አዎን።»

«ተልባስ?»

«ሁሉም ዝግጁ ነው - አሁን ጋደም በልና - ዶሮአችን ብስል ስትል - ብድግ እናስነሣሃለን።»

«ኸረ ዛሬ ጤናም የለኝ.........ይበላልኛል ብለሽ ነው።»

«ምን ይደረግ.....ይኸን በፀሐይ መዞር ተው ብልህ አሻፈረኝ አልክ፣ ደሞ ሹራብ ይገዛል፣ ይገዛል - አይለብስ። አድን ቀን ብቻ ይኸ ብርድ - ኸረ ከሱስ ይሰውርህ።»

«ይኸ የደረቅ ሆድ ብዬ ነው እንጅ፣ እሱስ......»

«ግድየለህም፣ አይቡ ያባላሃል።»

«እውነትሽን ነው። በአንቺ እጅ የተቀመመድ ኦሮ ካልበላሁማ።»

«እንግዲህ ይኸን ማሽሟጠትህን ተወኝ።

«አይ የአንቺ ነገር ባሽሟጥጥሽ መቼ አገባሽ ነበር።»

«እሱስ እውነትክን ነው። ትተነው እንጂ ለሙያውማ ቁሱ ነበርን።»

ከዚያ በኋላ ጋደም ይልና ወጡም ይሰራና የነጩ ጤፍ እንጀራ ይቀርብና፣ «አሁን ከእንቅልፌ ባትቀሰቅሱኝ ምን ነበረበት!» እያለ በመግደርደር ሁለቱም እጃቸውን ታጥበው፣ ሚስትዮዋ፣ «በይ ድስቱን አምጪው» ስትል ሠራተኛዋ ይዛ ስትመጣ፣ አንድ አምስቴ እንደተራመደች መሶቡ ጋ ልትደርስ ሁለት እርምጃ ሲቀራት......ልጆች የወረወሩት የሙዝ ልጣጭ ያንሸራትትና.....ድስቱ ከእጅዋ መውደቅ!!

«ሰበረችው!!» ሚስት ራሷን ይዛ መጮህ። ለወትሮው ዶሮ ወጥ የያዘ ድስት ይቅርና ስኒ ሰብራ የማታውቀው ሠራተኛ ባለችበት እንደ ሐውልት ድርቅ - ዓይኗን ስብርባሪው ላይ መሬት እንተጣለለው

የቅቤና ሽንኩርት መረቅ ላይ ተከላ ፍጥጥ። «ሰበረችው!! ሰበረችው!» አሁንም ሚስት ከጣሪያ በላይ መጮህ! «ይሰበርሽ፣ ስብር ያርግሽ፣ የዛሬው ፋሲካ እንዳለ! ያንሣሽ! እውነት የለማ! አበስኩ ገበርኩ፣ አበስኩ ገበርኩ!» ባል ከንዴት የተነሣ እንደ መሣቅ፣ እንደ መሣቅ፣ «ሃ! ሃ! ሃ!» ወዲያው የታጠበውን እጁን ጠረግ። ከዚያ በረጅሙ መተንፈስ፣ «ዱሮም ዓውደ ዓመት አይሆነኝም!»

ምን ትሉታላችሁ? ዕድል ወይስ አጋጣሚ?

# ፎቶ ግራፍ

ትዝታ የሚቀሰቀስበት መንገዱ ብዙ ነው። የመልክ አምሳያነት፣ የአነጋገር ለዛና ጨዋታ፣ የመቃብር ወዳጅ ዘመድ ያስታውሳል የአዋቂነት ልቦና የሚጭረው እሳት የጉርምስና ድፍረትን፣ የብቸኝነት ፍርሃትን፣ የአንድዋን ቀን ደስታ፣ የአንድዋን ቀን መከራ፣ ሌላም ሌላም አስገራሚ የሆነ የሕይወት ድራማ ይዞ ብቅ ይላል።

በቀን ተቀን ውሎ የሚታዩ ሁኔታዎችና እንደ ዘበት በጆሮ ሽው የሚሉ ንግግሮች በዓይነ ሕሊና ግላዊ የሆነ ብሩህ መልካቸውን ሲይዙ አንዳንድ የሕይወት ነፀብርቆችን ብልጭ አድርገው ማለፋቸው አይቀርም። ለምሳሌ የወዳደቀ ቆርቆሮ በገመድ ቀጣጥሎ እሚጫወት ሕፃን ሲያጋጥመው ልጅነቱ ድቅን እማይልበት እሚኖር አይመስለኝም። በተለይ ያደጉበት ሥፍራ የሠላሳ አርባ ዓመቱን የትዝታ ደለል ይዞ ሲቀርብ ከክብ ተቀምጦ ተረት ይወራሩበት የነበረ አንጋፋ ግራር ከቦታው ጠፍቶ እሸት የሌለበት ማሳ መንደር ሆኖ፤ የተንቦራጨቁበት ጅረት ደርቆ፣ ይኸን ይኸን መሳዩ ነገር በገረጣ የዕድሜ ጓሮ አብቦ ሲታይ ሣቅና እንባ ሲቀላቀል፣ ምን ዓይነት ስሜት እንደሚፈጥር መገመት አያቅትም :

መቸም የተረሳው ይረሳል እንጂ ትዝታ ገደብ የለውም። ስለዚህም የኑሮና የሥራ ገጠመኝ ከዓመት ዓመት እየዳበረ በሄደ ቁጥር ዛሬው ለትናንቱ መነሻ እየሆነ፣ «ዕድሜዬን ለምን ቁም ነገር አውየዋለሁ? ምን ያህሉንስ አባክኘዋለሁ?» ብሎ ራስን ለመጠየቅና አብረው የዋሉትን ጓደኛ፣ ያሳለፉትን ጊዜ ክፉ በጎውን ወደ ኋላ ተመልሶ ለማየት ማስገደዱ አይቀርም።

በተለያየ ጊዜና ሁኔታ ትዝታን ከሚያስከትሉ ነገሮች መካከል ዋነኞቹ ደብዳቤ፣ ሙዚቃ፣ ሲኒማ፣ ፎቶግራፍና የመሳሰሉት ናቸው። ማንም ሰው ዱሮ የተጻፈለትን ደብዳቤ ሲያነብ እንዲያውም ባጋጣሚ ሌላ ዕቃ ሲፈልግ አንዱዋ ገጽ ተደባልቃ በድንገት የመጀመሪያው እምስመር እጅ ጽሕፈት ላይ ዓይኑ ሲያርፍ አንዳች ነገር ሊቀሰቀስበት ይችላል። አፍቅሮ የከዳት ሰው በወቅቱ የጻፈላትን የማግባቢያ ደብዳቤ የምታነብ ሴት፣ በሞት የተለየችው ሚስቱ የላከችለትን የጉብኝት ካርድ ትክ ብሎ እሚያይ ሰው ምን እንደሚያሰማቸው መገመት አያዳግትም። ሌላው ቀርቶ የእርጥባን ወርቀት እንኩና ብዙ ዓመት ወደ ኋላ ይመልሳል። ሙዚቃም እንዲሁ ነው። በሙዚቃ መሀል የተሰማ የምስራች ወሬ የትም ይሁን መቼም ያ ሙዚቃ በተሰማ ቁጥር በጆሮ ሲያስተጋባ ይኖራል። ለምሳሌ፣ በፍቅር ዋዜማ ደጋግመው ያዳመጡትን ዘፈን የተፈቃሪዎቹን መልክና አኳኋን ብቻ ሳይሆን ያን ዕለት የለበሱትን የልብስ ዓይነት፣ ያወሩትን፣ የሄዱበት፣ ቀኑን፣ ሰዓቱን፣ ሁሉ ያስተውላሉ። ሲኒማ ፈጣን ሂደት ይኑረው እንጂ ከነዚህ ተለይቶ የሚታይ አይደለም።

እነዚህ ነገሮች በኀዘኑም በደስታውም የተደረገውን እንደ መስታወት ማሳየታቸው ሳስብ ነገር ነገርን ያነሣዋል እንዲሉ የትዝታችን መጠን በተዛምዶሽ አስተሳሰብ እየዳበአ ለመሄድ የመቻሉ ጉዳይ ተአምር ነገር

ሆኖ ይሰማኛል። ይሁን እንጂ የፎቶ ግራፍን ያህል አያስደንቀኝም። ምክንያቱም ፎቶ ግራፍ በገሃድ ዓይን የሚታይና የዕድሜ ጭጋግ የማይጋርደው በመሆኑ የሚያመጣው ትውስት በምናባዊ ደረጃው ከሌሎቹ ሁሉ የጎላ መልክ የሚኖረው ይመስለኛል። እስቲ የሥርጋችሁን ፎቶ ግራፍ ከልጆቻችሁ ጋር ሆናችሁ በጥሞና ተመልከቱት። ምን ታዩበታላችሁ? ወጣትነት? ፍቅር? ተስፋ? በሌላ በኩል ደግሞ ሽበት? ድካም? እርጅና?

መቸም መረን ባጣ ሁኔታ ደግሣችሁ ልትወጡ ከማትችሉት ዕዳ ውስጥ ተዘፍቃችሁ ከሆነ ደህናውን ገጽታ በቅጡ ላታዩት ትችላላችሁ። ኧረ እንዲያው ሌላ ሌላውን። የትኩስነት ስሜት የነበራችሁ መሆኑ። ዛሬ የከበቧችሁ ፍሬያችሁ ያኔ ያልተጨበጡ የምኞት ጉም እንደ ነበሩ። አሁኗ ጉጁዋችሁ ሥር በእፎይታ የመጠለላችሁ ነገር። የፍቅራችሁ መዳበር.......አይታሰባችሁም? ደሞ ያለፈው ማንነታችሁ እንደ ነበረ በጥሬነቱ ብቻ ሳይሆን ከዛሬ ጋር ተጠላልፎ በስሎ ወይም ከስሞ ከነድምር ቅናሹ ብሩህ ሆኖ ዓይናችሁ ላይ ድቅን አይልም? ምናባችሁ መጠቅ እያለስ ሲሄድ የሥርጉ ጭፈራና እልልታ፣ አናስገባም የሚል ግርግር ደርሶ የማትገቡ ይመስል አያት ከሆናችሁ በኋላም ሲያባባችሁ የሚኖረው ዜማና ግጥም እንደ ገደል ማሚቶ እየተደጋገመ አይሰማችሁም? መቸም ከዚሁ ጋር አፍላ ጉርምስና፣ ግዴለሽነቱ፣ ልበ ሙሉነቱ በተለይም የተፈጥሮን ጸጋ እንደማንም መታገሉ፣ ለምሳሌ፣ የጸጉር አለመመለጥ፣ የትከሻ አለመጉበጥ፣ የሥጋ አለማለቅ፣ ይኸን መሳዩ አብሮ መታየቱ አይቀርም። ታዲያ በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ ፎቶ ግራፍ ሲባል፣ በይሉኝታ ቢስ በረከትነቱ በሙሽራ ዘመን  ልብ የማሞቁን ያህል በፀፀትና በወጣትነት ናፍቆት ዓይን ቦዘዝ ቢያስደርግና እርጅናን ቢያስታውስ ትዝታ በሁሉም ቤት አለና ከቶም አያስገርምም።

በሌላ በኩል ደግሞ በዓይነ ሥጋ የመተያየት ነገር ካከተመ ወይም ዕድሉን ለማግኘት ካልተቻለ አስታዋሽ ሊሆኑልን ከሚችሉ ነገሮች ሁሉ ትልቁን ድርሻ እሚይዘው ፎቶ ግራፍ ነው። ለምሳሌ በሞት የተለያችሁን ሰው ፎቶ በረጋ መንፈስ ልብ ብላችሁ ተመልከቱት። ምን ነገር ታዩበታላችሁ? መቼም እንደተመልካቹ ነው። አንዳንዱ ከሰውየው ጠባይ ደጋግ ደጋጉን ያያል። አንዱም ክፉ ክፉውን። ሌላው ደግሞ ሁሉንም ሊያይ ይችላል። የደረጃው መጠንም በምናልባት ስፋትና ጥልቀት አኳያ የሚሄድ ይሆናል። እኔ እሚደንቀኝ ፎቶው ሳይኖር እንዲሁም በምናብ አማካይነት ከሚቀሰቀሰው ትዝታ ይልቅ ይኸኛው የበለጠ ሕይወት ያለው የበለጠ ብሩህ መሆኑ ነው። ሥዕሉ ሲታይ ሰውየው እዛው ያለ ዓይነት ሆኖ ይሰማል። ነበርኩ አሁን ግን የለሁም የሚል ይመስልና በኀዘን ጭጋግ እየሸፈነ አንዳች የሕይወት ምርምር ውስጥ ይጥላል። በተለይማ ፍጹም ፀጥታ ሠፍኖ፣ አሮጌ የግድግዳ ሰዓት ፎቶው አጠገብ ህኖ፣ ቀጭ ቀጭ እሚለውን ድምፅ እየሰማችሁ ፣ ሳትንቀሳቀሱ በሙሉ ስሜት፣ ትክ ብላችሁ ካያችሁት፣ የትዕይንቱ ድባብ የልብ አመታት ዓይነት ስሜት እያመጣ፣ የራሱን ረቂቅ ሙዚቃ በለሆሳስ እያፈለቀ፣ ልብ የሚነካና አንጀት የሚያላውስ ሁኔታ ይቀርጽላችሁና የትዝታችሁ መጠን በጣም ሊባባስ ይችላል። ይህ የሚሆነው ከፎቶ ግራፉ ጋር ሲሆን፣ የዓይነ ሕሊና አመለካከታችን ወይም የምናብ ኃይላችን በጣም ስለሚጐላ ይመስለኛል። እኔ እንድኒህ ዓይነቱን ፎቶ ግራፍ በማይበት ጊዜ የሰውየውን የሕይወት ጉዞ ሳወጣ ሳወርድ ዓይኖቹ እንደማያዩ ባውቅም፣ ወደ እኔ የሚያተኩሩ ዓይነት ሆኖ ይሰማኛል። ፈገግታም ካለው ለኔ የተሰነዘረ፣ እንዲያውም ዓይኖቹ ወደኔ የሚቃኙ አፉም እኔን ሊያውራ የተሰናዳ ይመስለኛል።

አንዳንዴ ይኸ የፎቶ ግራፍ ነገር ሳስብ በሞት የተለያት ባሏ በሠራላት ሳሎን ውስጥ እሱው በገዛውና ብዙ ጊዜ ይቀመጥበት በነበረው ፎቴ ላይ ከወዳጅዋ ጋር ተቃቅፋ ቁጭ እንዳለች በደስታ ከጣራ በላይ የምትስቅ ሴት ድንጋት ቀና ስትል ዓይኗ እባሏ ፎቶ ግራፍ ላይ ቢያርፍ በዚያች ቅጽበት ምን ይሰማት ይሆን? እላለሁ። ነገሩ ለምን ሌላ ወደደች አይደለም። በሕይወት አለመኖሩን ብታውቅም በአንዲት የሰኮንድ ቅንጣትም ቢሆን ትክ ብሎ የሚያያት፣ የሚታዘባት፣ ይመስላታል? ወይስ በዚያው የሰኮንድ ጅጨረር ውስት ትዳር ንብረታቸው

ፍቅራቸው የጫጉላ ቤት ሳይቀር በዓይነ ሕሊናዋ ብልጭ ድርግም ይልባታል ለማለት ነው። ምን ዓይነት እንደሚሆን ለማወቅ ያስቸግር እንጂ በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ አንዳች ትዝታ እንደ መብረቅ ታይቶ መጥፋቱ ግልጽ ነው።

ስለ ፎቶ ግራፍ ሌላው የሚያስደንቀኝ ነገር ደምነ የአነሣሱ ጉዳይ ነው። ኧረ ለመሆኑ ስንት ዓይነት አነሣስ አለ? መቸም ሁሉንም መዘርዘር አይቻልም። ግን እስቲ ለናሙና ያህል ጥቂቶቹን እንውሰድ። እጅ ለእጅ ተጨባብጠው ማንሻውን ትክ ብለው ከሚያዩት አንስቶ አምላኪች ጣቷን አገጯ ላይ አድርጋ እንደመፈላሰፍ እያለች ጣራውን አትኩራ እስከምትመለከተው ወይዘሮ ድረስ ያሉትን ብንመለከት እጅጌ ነገር እናያለን። አንዳንዱ ሰዓቱ እንዲታይ የኮትና የሸሚዙን እጅጌ ሰብሰብ አድርጎ ጉልበቱ ላይ እጆቹን እንዳሳረፈ እግሩን አንፈራጦ በዘጠና ዲግሪ አቀማመጥ ኮስተር ብሎ ይነሣል። አንዳንዱ በተጠንቀቅ ቆሞ ዓይኖቹን ፈጠጥ ያደርግና የተቆታ መስሎ ይነሣል። እንዲህ ዐይነቱ ሰው ልክ አንድ ነገር ሊወረወርበት የተቃጣ ይመስል የድንጋጤ መልክ ወይም መገርጣት ሊታይበት ይቻልላ።

የሥራቸውን ዓይነት ለማሳየት የሚፈልጉም አሉ። ቄሱ መንፈሳውነታቸው ስቧቸው መስቀልና ጭራቸውን ያሳያሉ። ሼኪው ኮፍያቸውን ያስተካክላሉ። ጋራዥ ሠራተኛው ቱታውን ለብሶ ብሎን መፍቻውን ከፍ አርጎ ይይዛል። በል ካለውም ጆሮ ግንዱ ላይ ያስደግፈዋል። ሌላው ቀርቶ የፍቅር ወላፈን ገረፍ ያደረጋት ወጣት በቁመቷ ልክ የሆነ አትክልት ፈልጋ አበባውን ትይዝና እንደመተከዝ ታለለች። በዚያ ሰዓት ፍቅር እንደ ሥራ መሆኑ ነው ለሷ።

ፎቶ ግራፍ የሚወዱትን ሰው ማሳወቂያ ወይም መዋደድን ማረጋገጫ የሚሆንበት ጊዜ አለ። በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ ባርኔጣ መለዋወጥ፣ በራስ መነካካት፣ ትከሻ መያያዝ ሁሉ ይኖራል። ጊዜና ቦታን ወይም ያለፉ ሁኔታዎችን ማሳያም ይሆናል። ይኸ በቡድን በሚነሡ ሰዎች ላይ ጐልቶ የሚታይ ነው። አንዳንዱ በጓደኛው ሠርግ ላይ የጠጁን ጠርሙስ ከፍ አድርጎ እያሳየ ወይም ብርጭቆውን ወዳ አፉ አስጠግቶ እንደመጠጣት እያለ ይነሣል። እንዲህ ዓይነቱ ፍቶ፣ «የእገሌ ሠርግ ጊዜ» እየተባለ ሲወራለት ይኖራል። አንዳንዱ ደግሞ ቤተሰቡን ይሰበስብና ያሳደገው ውሻ ይመስል ለአክፋይ የመጣለትን ሙክት አጠገቡ አርጎ ይነሣል። የሚገርመው ግን፣ «እገሌ ያመጣልኝ ዕለት» ለሚል ማስታወሻ ታርዶ ከሚባላ እንስሳ ጋር ፎቶ መነሳት ማስፈለጉ ነው።

ፎቶ ግራፍ ጓደኝነት ብቻ ሳይሆን ጥልቅ ስሜትን የልብ ፍቅርን የዘላለም ትዝታን ማሳያም ነው። እስቲ አድን ደሳሳ ቤትና ግቡና ወደ ግድግዳው ተመልከቱ። «የሆዴን ውስጥ እሳት ጥርሴ እየመሰለው፣ እንደ ልቡ አዳሪ እመስላለሁ ለሰው» የሚሉ ዓይነት የጨርቅ ጥቅሶችና ልትወድ በቃጣት ምስማር ላይ ጠመም ብለው የተንጠለጠሉ ጭስ የጠጡ ፎቶ ግራፎች አታጡም። እንዲያውም በውድ ዓይን የሚታዩት ከነመስታወታቸው የሚቀመጡት እሳጥን ውስጥ ነው። ይሁን እንጂ ለእንዲህ ዓይነቱ እንክብካቤ ያልታደሉ ሊኖሩ እንደሚችሉ መዘንጋት የለባቸውም።

የማይወዱትን ወይም የተቀየሙትን ሰው ለይተው ቆርጠው የሚጥሉ አንዳንድ ሰዎች አሉ። እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች ወዳጅ ጓደኛ ብቻ ሳይሆን ዘመድም ቢሆን፣ በኋላ የተጣሉትና የተቆራረጡት ከሆነ፣ «ደሞ የሱ ዘር ነኝ ሲል አጠገቤ ቆሟል፣ በል ዓይኔ እንዳያየው ቅደድልኝ» ማለት ይቀናቸዋል። ቁርሾውና ንዴቱ ከቁጥጥር ውጭ ከሆነማ ያልታደለው ፎቶ ገና ከመጣሉ በፊት ዓይኑ አፍንጫውን ሳይቀር እየተደነቆለ ቁም ስቅሉን ያያል።

እስቲ ስለ ጉርድ ፎቶ አነሣሥ ደግሞ አንዳንድ ነገሮችን እናንሣ። ጸጉሯን ከመጠን በላይ ቆልላ፣ ሽቶና ፓውደሯን ተቀብታ፣ ዓይኖችዋን በጣም ተኩላ፣ ገለጥ ባለ ደረቷ ላይ ያለ የለሴ ጌጧን ደርድራ፣ ዓይኗን ስልምልም፣ ከንፈሯን ጠመም አድርጋ የውሸት ፈገግታ እዛው ለመፍጠር የምትሞክር ዘመናይ ሴት ፎቶ ሲታዩ እንደ መሳቅ ብላችሁ አታውቁም? ታዲያ እኮ እምትሰቁት ከብዙ ነገር ጋር ስለምታያይዙት ነው። ስለ ውበት ጣጣ፣ ስለ ወጣትነት ማሰብ ትጀምራላችሁ። በተለይም እንዲህ ዓይነቷን ሴት ከእሷነቷ ድንበር ልታመልጥ ስትሞክር ታዩዋታላችሁ። ስለ ራሷ ምን እንደምታስብ ሌላው እንዴት ቢያያት ደስ እንደሚላት ለመገመት ትሞክራላችሁ።

የወንዱም እንደዚሁ ነው። ሰው ጠርቶት ዘወር ያለ ይመስል ገደድ ብሎ ሾል ያለ ጠጉሩ እንዲታይለት አንገቱን ደፋ አድርጎ የሚነሣ ዘመናይ አለ። ሥራ የለህም እንደ ተባለ ሁሉ ብዕር ይዞ ወረቀቱን ሳያይ ትልቅ ሣቅ እየሣቀ ዓይኑን ፎቶ ማንሻው ላይ የሚተክልም አለ።

የሣቅ ነገር ከተነሳ ብዙ ዓይነት አሣሣቅ አለ። ያንዳንዱ በመገደድ የመጣ ይመስላል። ማለትም ከሌላው የፊቱ ክፍሎች ጋር አብሮ ሳይሄድ ይቀራል። ያንዳንዱ ደግሞ ጥርሶቹ በጣም ከመታየቻቸው የተነሣ የመገልፈጥ ዓይነት ይሆናል። ከሁሉም ያሚያስገርመው ግን ከሁሉ አሁን ልሣቅ እያለ ሲያመነታ ካሜራው ቀጭ ያለእብት ሰው ፎቶ ግራፍ ነው። መቸም በዕድሜ ጠና ያሉ ወይም ክብራቸው እንዲታወቅላቸው የሚፈልጉ ካልሆኑ በስተቀር ብዙ ሰዎች ደሞዛቸው የተቆረጠ ዐልት እንኳን ቢሆን፣ ሥቆ መነሣት ደስ ይላቸዋል። አንዳንዱ ሰው እንዲህ የሚያደርገው «ለምን የከፋኝ ሆኜ ልታይ» በሚል እምነት ሳይሆን አይቀርም። አብዛኛው ግን እንዲሁ ያለ ምክንያት ልማድ እያደረገው ይመስለኛል።

በፎቶ ግራፍ ዓለም ጐልተው ከሚታዩት ነገሮች ዋነኛው የማማር ጉዳይ ነው። እዚህ ላይ ምን እመስል ይሆን የሚል ጭንቀት አለ። እንዲያውም ጭንቀቱ ፎቶው ታጥቦ እስኪታይ ድረስ አይለቅም። ፎቶውን ከተነሡም በኋላ መጸጸት አለ። «ይኸ ጐፋፋ ካፖርት ምን አስመሰሎኛል! እስቲ ምን ይባላል ካልጠፋ ነጠላ ዘርዛራውን መልበሴ። አዲሱ ጫማ እያለልኝ ጠማማውን ላርገው! ዘጊ ሹራብ ጡቴን ምን አሳከለው!» ሌላም ሌላም አለ። ሰበቡ ተፈልጎ ከጠፋ ግን «እንኔ ድሮም ፎቶ አይዋጣልኝም» የምትለዋ አባባል መሸፈኛ ትሆናለች።

ዋናው ነገር ግን ቆንጆም ይሁን አይሁን ሁሉም አጊጦና አምሮ ለመነሣት ይጥራል። ጸጉሩን ደጋግሞ ያበጥራል፣ ልብሱን ይመርጣል። የተጨማደደውን ያስተካከላል። ሌላው ቀርቶ የኖረ ማድያቱን ለዚያ ቀን እንዳይታይ መስተዋቱን እሚማጸን ሰው ሳይኖር አይቀርም። እንደ እውነቱ ከሆነ አጊጦ አምሮ (ቁንጅና ደረጃ ድረስ እንኳን ባይሆን) ደስተኛ ሆኖ ከነወዙ ከነ ድምቀቱ መታየት እማይፈልግ ማን አለ? ኑ ፎቶ ተነሡ ሲባል አሮጊቷ ተቅመጥ የከረመውን ሻሻቸውን የተረሳውን ጌጣቸውን ካለብት ፈልገው ብቅ ይላሉ። ሽማግሌውም የአዘቦት ካባቸውና እጀጠባባቸውን አጠላልቀው ዝግጁ ይሆናሉ። ኑ ፎቶ ተነሡ ሲባል ጐስቋላው የዐውደ ዓመት ልብሱን ቀይሮ ከች ይላላ። ተማሪዋ ኮረውዳ ዩኒፎርሙዋን ለማውለቅ ወደ መኝታ ቤትዋ ትሮጣለች። ይኸ ሁሉ አጊጦና አምሮ ለመነሳት የሚደረግ ጥድፊያ ነው።

ሆኖም የፍቶ ጉዳይ በዚህ ብቻ አያበቃም። ያማረውን እንደገና ማሳመርም አለ። አንዳንዱ በውድ ዋጋ የገዛው መስተዋወት (ፍሬም) አልበቃው ይልና በሥዕል ካላሠራሁ ሲል ሌላው ደግሞ በልዩ ልዩ ቀለማት (ቴክሊከለር) ካልስጌጥኩ ይላል። እንዲህ ዓይነቶችን ሰዎች፣ «መልካችሁ እንደሆነ አለ፣ ምነው በማይንቀሳቀስ ነገር ላይ ገንዘብ ባታባክኑ» ብላችሁ ከመጠየቅ ብትቆጠቡ መልካም ነው። ምክንያቱም፣ «ስሞት በዚህ ነው እኮ እምቀበረው፣ በእዚህ ነው የሚለቀስልኝ» የሚል መልስ ልታገኙ ትችላላችሁ። እስቲ

በዚህ ረገድ ፎቶ ግራፍን ወደ ሐውልት በቀላሉ ወይም በርካሽ ማስለወጥ የሚቻል ቢሆን ምን ያህል ሽሚያ ይኖር እንደነበር ገምቱ።

ፎት አነሳስ ሲታሰብ ሳይጠቀስ መታለፍ የማይገባው ሌላው ነገር የካሜራ ቴክኒክ ነው። ወጣቱና ወጣቷ በልብ ቅርጽ ውስጥ ሆነው ይነሣሉ። ፍቅር ላይ ነን አትንኩን ማለታቸው ነው። ልባቸው ደማቅ በሆነ የአበባ ስዕል ከተከበበማ ፍቅሩ በረታ ማለት ነው። በካሜራ ቴክኒክ ፋሲል ግምብ በረንዳ ላይ የሚቀመጡ፤ አክሱም ሐውልት ሥር የሚቆሙም አሉ። እነዚህ እንኳ በቂ ምክንያት የሚኖራቸው ይመስለኛል። የተወለዱበትን ሥፍራ ለማስታወስ ወይም ከታሪካዊ ነገር ጋር አብረው ለመታየት ሲሉ የሚያደርጉት ሊሆን ይችላል። እኔን የሚገርመኝ አውሮፕላን ነጂ ሳይሆኑ አውሮፕላን ፊት የሚቆሙ፣ አይተው የማያውቁት መርከብ ላይ ወገባቸውን ይዘው የሚዝናኑ ወይም ትልቅ ከተማ ከኋላቸው እየታየ የሚነሡ ወጣት የፎቶ ሱሰኞች ናቸው።

እዚህ ላይ በእንስሶች መካከል እንደ ቀልድ ቆም የሚሉ ደፋሮች መኖራቸውም መዘንጋት የለበትም። እንስሳ ስል አንድ ነገር ትዝ አለኝ። ይህችን ጽሑፍ በማዘጋጀት ላይ ሳለሁ አንድ ወዳጄ ጅምሩን አነበበና፣ «አይተህ የማታውቀውን የፎቶ ዓይነት ላሳይ» ብሎ አንድ ሰው ቤት ወሰደኝ። ፎቶው እንዴት ዓይነት መሰላችሁ! አንድ ሽንጠ ረጅም ነብር አለ። ፊት ግን የለውም። በደህና መቀስ ተቀፎ ወጥቶ የሰውየው ጉርድ ክብ ፎቶ ቦታው ተከቶበታል። እንደ ገና ፊቱና የነብሩ አካል አንድ ላይ ሆኖ ፎትቶ ተነሥቷል። መቸም ቆጣ ብሎ ቢነሣም ዕውነተኛ ነበር አልሆነም እንጂ ያደረገው ሙከታ የሚናቅ አይደለም። እስቲ ተመለከቱት፣ ሐሳቡን እንዴት መጣለት?

የቴክኒክን ጉዳይ ካነሣን የፎቶ ማንሻውን ዓይነትና የአንሺውን ችሎታና ልምድ ማሰብ አለብን። ምክንያቱም በትኩረት በርቀትና በሌላም ምክንያት የምጣኔ ስሐተት ሊፈጠር ይችላል። ቦርጭ ሳይኖረው ቦርጫም ሆኖ የሚነሳ አለ። ሳያጥር አጭር የሚሆን አለ። በፎቶ አንሺና በፎቶ ማንሻ ያልታሰበ ሴራ ግንባሩ ተጨማዶ፣ የዓይኑ ቆብ ጠቦ ሰው ገድሎ ያመለጠ ወንጀለኛ መስሎ የሚነሳም ይኖራል። አገር ያወቀው ብልጥ ሰው - እንዲይውም ጮሌ እንበለው - ከሲታ ጉንጩ ያለ ወትሮው ሞላ ብሎ ፈጣጣ ዓይኖቹ በቆባቸው ተውጥው ሩቅ የሚመለከት ዓይነት ሆኖ፣ ፈዛዛ ወይም ሞኛ ሞኝ በመምሰል ሊነሣ ይችላል። መቸም በዚህ ረገድ ሳይለጠጥ የተለጠጠ ሳይጐብጥ የጐበጠ መስሎ የተነሳውን፣ ፊቱ ከጐፈሬው በጣም ያስነበቱን አንገቱን ያጠረበትን ሰው ቤት ይቁጠረው። አፍንጫው ጆሮ፣ አገጭና ሌሎችም የአካል ክፍሎች እንዳልነበሩ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ።

አንዳንድ ፎቶ አንሺማ የሰው ዕድሜ ጨምሮ ቆጭ ይላል። ትልቁ በደል ይኸ ነው - በማንም ፎቶ ተንሺ ዘንድ ይቅርታ የማይገኝለት። በዚህን ጊዜ የማማር አለማማር ጉዳይ እደ ጐን ይቀርና ትኩረቱ ዕድሜ ላይ ይሆናል። እና፣ ምንም ተንኮል ሳያስብ የደንበኞቹን ሽሚዝና ክራባት የነጠላውን ጥበብ ጌጣጌጡ እያስተካከለ «ከአንገትዎ ቀና፣ አዎ፣ እንደሱ ትንሽ ራስዎን ዘንበል እጇጋ ተመለከቱ፣ አትነቃነቁ!» እያለ ለማሳመር ሲጨነቅ ሲጠበብ የቆየ ፎቶ አንሺ ለስድብና ለእርግማን ይዳረጋል። «ወይ ጉድ፣ ቂም አንዳለው ሰው እናቴን እኮ አሳከለኝ! እግዜር ይይለት፣ ገና በሃያ አምስት ዓመቴ የአርባ ዓመት ሰው ያስመስለኝ!»

ታዲያ የዕድሜው ነገር በፎቶ አንሺው ምክንያት የተጨመረ ይምሰለ እንጂ፣ ፎቶ ተነሺዎች በበኩላቸው የዚያኑ ያህል ዕድሜያቸውን መናገራቸው ዞሮ ዞሮ የማይቀር ጉዳይ ነው። መቸም እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የተነሡ ፎቶዎች በንዴት እንደሚቀደዱ ወይም፣ «ኧረ እኔን አይመስልም አትየው......» የተባሉ ከጅ እየተነጠቁ እንደሚደብቁ ግልጽ ነው።

በእርግጥ ፎቶ ግራፍ ሰውን መቶ በመቶ ራሱን አድርጎ ሊያነሣ እሚችል አይመስለኝም። ጥሩ ፎቶ ማንሻም ቢሆን ትንሽ ለወጥ አድርጎ መቅረጹ ስለማይቀር ምን ጊዜም ቢሆን ዓይንን የሚተካ ነገር የለም። ይሁን አንጂ ወፈር ያለ ነጭ ወረቀት ቆርቶ ከኪስ በከፊል ብቅ በማድረግ መሐረብ እንዳለው ሰው መነሣት መቻሉ ሲታሰብ ፎቶ ግራፍ አንዳንዴ ገመና ሸፋኝ ነው ለማለት ይቻላል።

# በሽተኞችና ጠያቂዎች

ዘመድ ወዳጅ የተባለ ጐረቤት ሁሉ ሲያዝንላቸውና ሲጨነቅላቸው መስማት የሚወዱ፣ በቁንጣኑም፣ በድካሙም አይዞሽ መባልን መጽናናትን የምቾት ያህል ሊያረጉት ትንሽ የቀራቸው ዛሬ «ደግ ነኝ» ብለው እንደ ሆነ፣ ነገ «አገረሸብኝ» ማለት ልማድ የሆነባቸው ሌላው ቀርቶ ቀኑን «ደህና ውያለሁ» ቢሉ እንኳን የዛሬውን አዳር እንጃልኝ ብለው ለመተንበይ የማይመለሱ የበሽታው ዓይነት ውጋት፣ ቁርጠት፣ ትውከት ትኩሳት፣ ሁሉ ካፋቸው የማይተፋው አንድ ሴት ወይዘሮ ነበሩ። ታዲያ ጠያቂዎቻቸውም እንደ በሽታቸው የበዙ ነበሩና ውሎአቸውን ሲጠይቋቸው «ኸረ ተይዣለሁ» በሚለው ጀምረው ሁኔታውን በዝርዝር እያጋነኑ ሲያወሩ ቆይተው፣ «አለሁ መቸም እንደ ነገሩ» ብለው ካላስረጉ ወደ ሌላ ጉዳይ መግባት አይሆንላቸውም ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን በተለመደው ኻንጉርጉር አለባበሳቸው ብጭጭ ያለ ቢጫ ቀሚሳቸውን ከአርቲፊሻል ጌጣቸው ጋር አጥልቀው ሰማያዊ ሹራባቸውን ደርበው፣ አረንጓዴ ሻሽ ጆሮአቸው ድረስ አስረው፤ ወተት በመሰለው ነጭ ጫማቸው ላይ እንደሳቸው አጠራር ቀይ «እስቱኪያቸውን» አርገው የስለት ጃንጥላ ዘርግተው ያሳደጓትን ትንሽ ልጅ ያስከትሉና ዘመድ ጥየቃ ለመሄድ ይነሣሉ። ልጅቷ ያረጀው እስቶኪንጋቸው በወረደ ቁጥር ከፍ እያደረገች «እሱን ትተሽ ሸሸንቶውን አትጠሪም!» ስትባል ደሞ በሰላላ ድምጿ እየጮኸች እሳቸውም በታጠፈው ክንዳቸው ላይ የሚያብረቀርቅ ጥቁር ቦርሳቸውን ሳያነቃንቁ እንደያዙ የግዜር ሰላምታቸውን እየሰጡ፣ ያልጠየቃቸውን በሆዳቸው እየተራገሙ ዘመናይ መሳይዋን «ወንዳወንድ መንቃራ» ወጣቱን፣ «ዓይናውጣ ጎፈሬያም» እያሉ መንገዳቸውን ይሄዳሉ።

አንድ ወጣት ተማሪ፣ «እንደምን ዋሉ» ትላቸዋለች ስለምታው አጸፋውን ይሰጡትና፣ «ባገር አለሽ እንዴ ለመሆኑ? ምነው ታምሜ ሳትጠይቂኝ ልጄ? አሳድጌ አሳድጌ?» ይሏታል። ወጣቷም አለመስማቷን ትገልጽላቸወአን፣ «ታዲያ አሁን ተሻለዎት ወይ» ትላቸዋለች። እሳቸው ግን፣ «እንደጠየቅሽኝ! እንደጠየቅሽ!» ብለው መመረር ይጀምራሉ መጨረሻ ልጅቷ ትዕግሥቷ አለቀና። «ተሻለዎት ወይ ብዬዎታለሁ እኮ። መጠየቅ ማለት ይኸ አይደለም?» ብትላቸው ከት ብለው የሽሙጥ ሣቅ ሣቁና «አዎን ልጄ እንዲህ እንዲህ አድርጎም መጠየቅ የለ! ሰው እሚታመመው እቤቱ ነው እንጂ በየአደባባዩ ነው?» አሏትና መንገዳቸውን ቀጠሉ።

መቸም ይኸ ትርክት ከጅምር ልቦለድ የተወሰደ መምሰሉ አያጠያይቅም። የሕመም ነገር እንደ ልቦለድ የሚያዝናና ስላልሆነ፣ ስለ ጠያቂና በስተኛ ለመናገር በጥቂቱም ቢሆን ኮስተር ብሎ ማሰብ አይከፋም። ታዲያ በሽተኛ ከሌላ ጠያቂ አይኖርምና ጠያቂ ቢጠፋ ግን በሽታ አይጠፋምና በነሱው ማንገራገሩ ሳይበጅ አይቀርም።

እኔ እንደሚመስለኝ፣ በሐኪሞች ሊስት የመጀመሪያውን ደረጃ የሚይዙት የብዙ ዓመት የሕክምና ማህደር ያለአቸው በጠንቃቃነታቸው የሚታወቁ ግለሰቦች ናቸው። ጤናቸውን በሚገባ የሚንከባከቡና አስፈላጌውን ክትትል የሚያደርጉ በመሆናቸው ሕመም ነክ በሆነ ነገር ሁሉ በአርአያነት ይጠቀሳሉ። ታዲያ ከመካከላቸው ለሐኪም ሥራ እንቅፋት የሚሆኑ አሉ። «ምንዋን ያምዎታል? መቼ ጀመረዎት?» ሲባሉ የሚሰጡት መልስ ሐተታ ይበዛውል «በእንዲህ ያለ ሆስፒታል ተመርምሬ እገሌ የተባለው ዶክተር አክሞኝ ጠበል ትንሽ አስታግሶልኝ ኦብሬሽኑም ሳይረባኝ፣ አራት ኽምት ሙሉ ራጅ ስነሣ......» መዘብዘቡን ልማድ አርገው ይይዙታል። ለጧቱ ብርድ ልዩ ካፖርት አይኑራቸው እንጂ ቀጠሮ ዝንፍ የማያደርጉ ሆስፒታል አዘውታሪዎች እነሱው ናቸው። አንዳንዱ ንግግር የማያደርጉ ባይ ሠራተኛ «በቃ እኒህ ደሞ ሁልጊዜ እዚህ አይጠፉም» ሲላቸው እንኳን ቅር አለኝ ብለው ደሞ ሁልጊዜ እዚያ አይጠፉም» ሲላቸው እንኳን ቅር አለኝ ብለው አያስታጉሉም። በዚህ ዓይነት ሆስፒታልን እንደ ሁለተኛ ቤታቸው ስለሚቆትሩ ለሐኪም አስተያየት ከመሰንዘር ወደ ኋላ አይሉም። «ያ እሚጠታውስ ፋይዳም የለው፣ ሞክሬዋለሁ» ይላሉ - «እንዳው ምን አለበእት፣ አንተ እንኳን መርፌ ብታዝልኝ.......» ደሞ ኮስተር ብለው።

እንደዚህ ያሉት በዕድሜ ገፋ ያሉ ሕመምተኞች የመታከም ልምድ ስላላቸው ሆስፒታሉን ሁሉ፣ «የአንገት በላይ የአንገት በታች» ብለው ይመድባሉ። የዱሮ ሀኪማቸውን ሐኪም ሲጠሩ ይኖራሉ። ለምሳሌ «ሐኪም ማለት ዶክተር ላምቢ ነበር ምን ያረቃል ቀረ!......» በሚል እምነት። የማስታወስ ችሎታቸውም ከፍተኛ ነው። «ለውርዴ እሱን የሚያህል የለም።» የሐኪም ቤቱን አቅጣጫ በከዘራቸው ያሳያሉ።

በመንደር መርፌ ወጊ የሚያምኑ ሕመምተኞች ደግሞ ሕክምና ሁሉ ያለ መርፌ እሚሆን አይመስላቸውም። የመድኃኒቱን ፈዋሽነ ከዕድል ወይም ከግንባር ጋር ያያይዙታል። የመጀመሪያው መርፌ ካዳናቸው «እጁ ጥሩ ነው» ይሉና ደንበኛ ያበጃሉ። መድኃኒቱ ወዲያው ተከታትሎ አልሠራ ማለት ሲጀምር ግን፣ የራሳቸውን የእምነት መለወጥ ሳያዩ ጣኦት ያረጉት ሐኪማቸውን እጁ ተለወጠ ብለው ያወግዙታል። በመርፌ ወጊያችው ለረጅም ጊዜ ታክመው አንዴ ካመኑ በኋላ በመሐሉ አልፎ አልፎ አልይዝ እንኳን ቢላቸው ሌላ «የጣላቸው» ነገር እንዳለ በማለት ሲፈልጉ ይውላሉ እንጂ ቶሎ ተስፋ መቁረጥ እሚባል አያውቁም። እንዲያውም እምነታቸው በደንብ ከተጠናከረ በኋላ «የኮሶ ዓይነት ምረጥል። በቫይናክና ከካፌኖል የትኛው ይሻለኛል» እያሉ እስከ መጠየቅ ይደርሳሉ። ወይም ገና ሊያማቸው ሲል እንደ ዘበኛ አጥሩ ጋ ያቆሙት ይመስል «ብርድ ብርድ ብሎኛል፣ እገሌን ጥሩልኝ» ማለትን ልማድ ያደርጉታል። ትእዛዙንም በማክበር ብቻ አይወሰኑም። «ተናግሯል እኮ እሱ ራሱ» በማለት በየእድሩ በየእቁቡ ምክራቸውን ይጠቅሱላቸዋል። «በየትኛው ጐኔ ልተኛ?» ማለቱ ቢቀርባቸው እንጂ ከኪኒን መቆርጠም አንሥቶ እንግሊዝ ጨው እስከ መጠጣት ድረስ ያለውን መድኃኒት አወሳሰድ ጉዳይ በየአጋጣሚው በሥልጣናቸው የሾሙትን የግል «ሐኪም» ካላማከሩ አይሆንላቸውም።

የማማከር ነገር ከተነሣ፣ ስለ በሽታና ሐኪም ስለ መድኃኒት ዓይነት ጤነኛውንም በሽተኛውንም ሲያማክሩ እሚውሉ በዚያውም የታከሙ ያህል በወሬው የሚረኩ ግለሰቦች እንዳሉ እናውቃለን። «እንዴት እንዴት ነው የሚያረግህ?» ጥያቄያቸው የሚጀምረው በዚህ ነው። በሽተኛው ገለጻውን ይጀምራል «ራሴን እያቃጠለኝ ሰዓት ሰዓት እየለየ ለሁለት ክፍል እያረገኝ ጅርባዬ በረዶ ምስጋና ይንሳው ለምን ባውዳመት ጠላ ቀመስ ብሎ እንደ ማድቀቅም መከርተፍም ይለኛል........» ነገሩን ከራሳቸው ሁኔታ ጋር ያወዳድራሉ።

በማማከር የሚረኩ ሕመምተኞች ከሁሉም የተሻእልውን አጣርተው እስከዚያው ድረስ ሥራ አይፈቱም። ሐኪም ለሌላው ያዘዘውን ሁሉ «አንድ ቀን ሳይጠቅመኝ አይቀርም» በሚል ተስፋ እየሰበሰቡ ለማስቀመጥ ይጥራሉ። የመድኃኒቶችን ስም ሲያገኙ አስገልብጠው አጽፈው በግል ማስታወሻቸው ላይ በጥንቃቄ ያኖራሉ።

ባዶ የመድኃኒት ብልቃጦችንም ይሰበስባሉ። አንዱ በሽታቸው ሥጋትና ጭንቀት ስለ ሆነ አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያስላፉት የሕመም ዓይነቶች ከነአጀማመራቸው በማጥናት ነው።

ወደ በሽተኛ ጠያቂዎች ስንሻገር ደግሞ ከሁሉም ጐላ ብለው በዓይነ ሕሊናችን ድንቅ የሚሉት በሽተኛ ላጽናና ብለው ሄደው የራሳቸውን ጉዳይ ሲያወሩ መላው እሚመስሉት ናቸው። «መታመምህን እንኳን እገሌ ነግሮኝ ነበር። ግን የኔ ነገር የምታወቀው ነው። በዛ ወጥቼ በዚህ ወርጄ ለራሴም ጤና የለኝ፣ እሱማ ነፍሰ ጡር ናት ያ ሙግት ደሞ ፋታ አልሰጥ ብሎኛል» እያሉ ወጋቸውን ከጀመሩ መመለሻም የላቸውም። በሽተኛው ሰልችቶ ጨንቆት፣ ዓይኑን ጣራው ላይ ሲከድን ሲከፍት መውጫ ቀዳዳ አጥጦ ከጨኸት የዳነ መስሎት ትራስ ጭምሩልኝ.......አስተካክሉኝ ሲል ሁሉ ስሜት አይሰጣቸውም።

በልፍለፉ ከነዚህ ጋር የሚመሳሰሉ፣ ነገር ግን ለስለስ ባለው አንደበታቸው የሚሠጡት ትእዛዝ መሳይ ምክር በደንብ እንዲያደምጥ የሚፈልጉ ራሳቸውን ሐኪም የሚያደርጉ ጠያቂዎች ናቸው። «ታዲያ እኮ መድኃኒቱ አንድ ብርጭቆ ወተት ነበር። ትንሽ ማር በላይዋ ላይ ጣል አርጎ፣ ትንፋሽ ሽው ማረግ። ከተገኘ ፌጦም ተደቁሶ ቢቀባ ለጊዜው ፋታ ይሰጣል። ዋናው ማሩ ነው። በተቀማጭ ውልቅልቅ አርጎ ነው ምቹን ከነ ዘርማንዘሩ የሚነቅለው!» ይህን የሚሉት ኮራ ባለ መንፈስ ስለሆነ «ሰው ይታዘበኛል» የሚል ሐሳብ ዝርም አይልባቸውም። ደሞ ለዚህ የሚረዳ ወፍራ ድምጽ አያጡምና ለመታመን ዕድል አላቸው። መድኃኒት ፍለጋ ግን ሩቅ አይሄዱም። የሆድ በሽታ ከሆነ ባዶ የስፒራይት ጠርሙስ ማየቱ እዛው በዛው ሿ እሚያደርግ እምድኃኒት ያስፈለስፋቸዋል። ሌላ ጊዜ ደግሞ ስፕራይት በአምቦ ውሃ ሊለውጡት ይችላሉ።

ከበሽተኛ ጠያቂያቸው መካከል ያጽናኑ መስሏቸው የመንፈስ ጭንቀትና አጉል ፍርሃንት በሰው የሚያሳድሩ የሕመምተኛውን ቁስል ሳይውቁ ወይም በግዴለሽነት እየነካኩ የሚመርዙ ምን ላውራ ባዮች ናቸው «እኔም እንዳንተ እሞኝ ነበር። በስንት ሥቃየ ንወ የዳንኩት!» ይሉና የበሽተኛውን ቤት፣ በበሽታ ወሬ ይበክላሉ። እንዲህ ዓይነቶቹ «በቃ ጠይቀኸናል፣ ተነሥ ውጣልኝ» ቢባሉ፣ እንዲያውም «ደህና ነኝ፣ እንዳትመጣ» የሚል ደብዳቤ በቅድሚያ ቢጻፍላቸው አሜን ብለው መቀበል የሚገባቸው ናቸው። የነዚህ ተቃራኒ የሆኑ በሽተኛ ችግሩን በጥሞና ሲያዳምጡለት ቀለል እንደሚለው የማይገባቸው የሚያጽናኑ እየመሰላቸው ወይም እንዲሁ ልማድ ሆኖባቸው ሁልጊዜ መቀለድ የሚወዱ ግለሰቦችም አሉ።

ምንም ይሁን ከጠያቂ ንዝነዛ እሚብስ የሕመምተኛ ችግር አይኖርም። «ምንህን ነው? ስንት ቀን ሆነህ? ስትተነፍስ እንዴት ይሰማሀል? ጀርባህን ያቃጥልሃል? ትኩሳትህን?» በማለት ለበሽተኛ የማቃሰት ጊዜ እንኳን ሳይሰጡ አጥብቄ ልረዳ ባዮች አሉ። አንዳንዶቹ ምን እንደሚሉ እያጡ ነው ጥያቄያቸውን የሚያዥጐደጉዱት። ወይም አንድ ነገር ሳይናገሩ ከወጡ በደንብ ያልጠየቁ ሆነው የሚገመቱ ስለሚመስላቸው ነው።

አንዳንዶቹ እንዲህ የሚያደርጉት የራሳቸውን የጤንነት ሁኔታ በድብቅ ማጥናት ስለሚፈልጉና ሕመም ጥርጣሬ ለማረጋጋት ወይም ለማስወገድ ሲሉ ነው። ስለ አተነፋፈሱ ሲጠይቁ ከመልሱ ጋር አብረው ይተነፋሳሉ። ስለ ውጋት ሲያዳምጡ ያመማቸው የሚመስላቸውን ቦታ ጫን ይሉታል።

እስቲ ስታስቡት በአጉል ፍርሃት በሽታ መፈለግ ምን ይባላል!

# ሙዚቃ

ስለ ሙዚቃ አስተያየት ለማቅረብ ወይም ለመተቸት የሙዚቃ አዋቂ መሆን የግድ አስፈላጊ ባይሆንም፣ የዕውቀቱና የችሎታው ባለቤት መሆን በቀላሉ የሚገመት ነገር አይደለም። ምክንያቱንም ከሙያው ጋር አግባብ ያለው ሰው ከኪነጥበብነቱ የሚያሳየውን ተአምራዊ ሂደት በስፋትና በጥልቀት ለመገንዘብ፣ እንዲሁም ከሕይወት ጋር ያለውን ውስብስብና ረቂቅ ተዛምዶውን በሚገባ ለማጣጣም ከማንም ይልቅ የበለጠ ዕድል አለው። ጆሮ ያለው ሁሉ የሙዚቃን ጣዕም ይለያል አይባል። የመስማት ልምዱን ከመመሰጥ ዝንባሌ ጋር ያዳበረ አድናቂ ትችት ሲሰነዝር ይችላል ብዬ አምናለሁ።

በመሠረቱ የሙዚቃ ባለሙያ አይደለሁም። ምንም ዓይነት የሙዚቃ መሣሪያ ተጭውቼ አላውቅም። ዱሮ በተማሪነቴ ሐርሞኒካ መንፋት በሚችሉት ጓደኞቼ የነበረኝ ቅናት ዛሬም ቢሆን ዘመናዊ መሣሪያ የሚጫወቱ ባየሁ ቁጥር ያገረሽብኛል። እንደምንም ብዬ ለመጀመሪያ ጊዜ የሞከርኩት ከሁለት ዓመት በፊት ነበር። አንድ በሀገር ባሕል መሣሪያዎች የታወቀ የሙዚቃ ትምህርት ቤት መምህር የሆነ ወዳጄ ክራር እያስተማረኝ በታላቅ ትጋት ልምምድ ማድረግ ጀምሬ ነበር። ነገር ግን የሱን አመታት ፈዝዤ ሳይ፣ ጣቶቹአ የተለየ ነፍስ ያላቸው ይመስል በስድቱ ጅማቶች ላይ እየሮጡ በህበተ ሲናገሩ አስደናቂ ትርጉም ሲሰጡ ሳይ፣ በጨፌ መሐል አቋርጦ እንደሚጓዝ ጅረት የሚፈሰውን የአምባሰል ዜማውን፣ ልብ ሰርቆ ወደ ሌላ ዓለም የሚያሻግረውን አስገምጋሚ ትዝታውን ዝም ብዬ ተመስጬ ስሰማ፣ ተማሪነቴን እየረሳሁ፣ «ድገምልኝ፣ እንደገና በልልኝ» ማለቱን ብቻ ሥራዬ ብዬ ያዝኩትና ትምህርት አልገባ ብሎኝ ተውኩት።

ከማናቸውም የሙዚቃ መሣሪያ የሚወታና ድምፅ የሚማርከኝን ያህል ከታደለ ጉሮሮ የሚመነጭ ጥሩ የዜማ አሰባበርም ያስደንቀኛል። እዛ ምን አደረሰህ እንዳትሉኝ እንጂ የጥላሁን ገሠሠን ዓይነት ተሰጥኦና ችሎታ እንኳን ባልመኝም፣ ለራሴ ያህል በመጠኑ ለማንጐራጐር ፍላጐት ብቻ ሳይሆን ስሜትና ጉጉትም ነበረኝ። ነገር ግን በመዝሙር ፈተና ከሃምሳ በላይ አግኝቼ እማላውቅበት ድምፅ ዛሬም ስላልተሻሻለ፣ ሞከረኤ አልሆነልኝም። ያኔ በመዝሙር ትምህርት ጊዜ አዲስ ዜማ ባንዴ የመያዝና ሌሎቻችንን የማስጠናት ችሎታ የነበራቸው «ኑ ዘምሩ» ሲባሉ መድረክ ላይ ወጥተው፣ በተጠንቀቅ ቆመው፣ በመረዋ ድምፃቸው ክፍላችንን የሚያሸብሩ ልጆች እንደነበሩ ትዝ ይለኛል። ከኛ በዕድሜ የገፉ፣ ውጡ እንዳይባሉ አንገታቸውን የሚያቀረቅሩ ክፍሉን ሣቅ በሣቅ የሚያደርገ ጐርናና ሸካራ ድምፃቸው የሚያሳፍራቸው የዘመኑ ጐረምሶችም ነበሩ። ይኸን እግረ መንገዴን ማንሣቴ ጥሩ የመዝሙር ልምምድ ምናልባት ለድምፅ ይረዳ ይሆን ለማለት እንጂ የዘመረ ሁሉ የሙዚቃ ሰው ይሆናል የሚል ሐሳብ ለመጠቆም አይደለም።

ሙዚቃ ጊዜ የማይሽራት፣ ቦታ የማይወስናት የዓለም ቋንቋ ናት። የሰውን ልጅ ለኅብረት ሥራ ታዘጋጃለች፣ ታሳትፋለች። ሩቅ ሳትሄዱ የምንጃሮች የውቂያ ዘፈርን አንድ ምሳሌ ሊሆን ይችላል። እስቲ ስታስቡት አናጢው እርሳሱን ጆሮው ላይ እንዳረገ፣ ገበሬው ለበሬው ስም እያወጣ ልብስ አጣቢው ፎጣውን ራሱ ላይ እንደ ጠመጠመ፣ ወፍጮ እምትፈጨው፣ ልብስ እሚተኩሰው፣ እነዚህ ሁሉ ለምን ያንጐራጉራሉ? ሌላው ቀርቶ የእሹሩሩ ዜማ ሕፃን ልጅ ያስተኛል። ሳይንቲስቶቹማ ሙዚቃ ሲሰሙ እጽዋትም ያድጋሉ ይሉ የለ!

በአቀነባበሩ አነስተኛ ግምት የሚሰጠው የሠርግ ዘፈርን እንኳን ለፍቅር መግለጫ ሆነ ለትዳር ምሥረት ምን ያህል አስተዋጽኦ እንደሚኖርው መመልከቱ በቂ ነው። ከጓደኛዋ ወርቅ ተውሳ ወይም አርቲፊሻል ጊጧን ደርድራ የምትዳረው ሙሽራ፣ «እንዳላይሽ እንዳላይሽ ወርቅ አዘብዝቧል በላይሽ» ስትባል፣ እዛው ኩራት

ተሰምቷት በደስታ ብትፈነድቅ፣ «ያረገርጋል ኮፍ ጫማዋ ደረሰ መሄጃዋ» የሚለውን የመሰነባበቻ ግጥም ስትሰማ የወላጆቿን ቤት ዳግመኛ እማትረግጥ ይመስል ከከበሮው ጋር ልብ አመታቷ እየናረ እንባ ቢተናነቃት፣ ሚዜው ይህ ነው ሲሉት፣ «ምን በወጣኝ» ብሎ ሽቶውን ከሰው አልፎ ግድግዳው ላይ እየረጨ ቢጨርስ፣ ሁሉም እንዲያ የሚያደርጉት ያለ ምክንያት አይደለም። ግጥሙና ዜማው በተለይ ዜማው - ልጅነትን ያደገበትን ባህል፣ የቤተሰብ ፍቅርን፣ መልካም ባልንጀራነትን እንዲያታውሱ የሚያደርግ፣ ትዝታን የሚያጠነክር፣ ደስ ከማለት አልፎ በስሜት የሚያከፈክፍና የሚያባባ ብሎ የተቀመጠው የሃምሳ ዓመት አዛውንት ሠላሳውን ወዲያ ቀንሶ ለርሱ የተዘፈነለት እስኪመስለው ድረስ የስሜት እንባውን አቅርሮ በሐሳቡ ተክሊሉን ሲያፋ፣ ካባውን ሲያጠልቅ ሊታየው ይችላል።

ሙዚቃ እንደ ኀዘን፣ እንደ ደስታ፣ ናፍቆት፣ ፀፀት የመሳሰሉትን ረቂቅ ስሜቶች በየመልካቸው ታቀርባለች። ከሁሉም በላይ በሥራ የደከመን አእምሮ ለማደስና ለማዝናናት፣ የዚህን ዓለም ምሬት በችላ ባይነት ለማሳለፍ፣ የምናብ ደረጃን ለማዳብር አዳብሮም የሕይወት ግንዛቤና የአስተሳሰብ ብስለት ለማግኘት፣ አካባቢን ለመቃኘት፣ ተፈጥሮን ለማድነቅ ትልቅ አስተዋጽኦ ያላት ነች።

ለኔ እንደሚመስለኝ በደራሲዎች በድምፃውይንና በመሣሪያዎች ኅብረትና በመድረክ አቀራረብ የምትቀነባበር ብትሆንም፣ ሙዚቃ ተፈጥሮን በሚያጅቡ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በየአጋጣሚው ትታወሳለች። ለምሳሌ ዝናብ ሊመጣ ሲል ሙዚቃ መሰል የሆኑ ነገሮች ያጅቡታል። በአስተውሎት ልብ ብላችሁ ካዳመጣችሁ ውሾች ሲጮሁ፣ ከብቶቹ ሲጠራሩ፣ ነፋሱ የግቢያችሁን ዛፎች እያወራጨ የቤታችሁን ቆርቆሮ ክዳን ብድግ እንደማድረግ እያለ በበረንዳው ክፈፍ በማእዘኑ እየሾለ ሲያፏጭ፣ ከዛ ጠጠር ወይም አሸዋ መሳይ ጣል በተን እያረገ፣ መብረቅ ወዲያው እዚህ እየተሯሯጠ ነጐድጓዱን ሲያከታትለው፣ ነፋስና ቆርርቆሮ ግብስግብ ሲገጥሙ፣ በመሐል ንግግር መሳይ የሚያጉረመርም ዓይነት ድምፅ ስትሰሙ፣ ደሞ ገርበብ ያለው በር ሰው የነካው ይመስል ከፈት ሲል፣ ቀቀቀቀቅ - እንደ መዘግነን የሚል ድምፅ ስትሰሙ፣ ከዛ የዝናቡ እሩምታ፣ ይኸ ሁሉ ተደማምሮ አንዳች ስሜት የሚቀሰቅስ ዜማ ይፈጥራል። ፏፏቴው እየተወረወረ ዘመናት ባሳለፉ አለቶች ላይ ሲያርፍ ፈረሰኛ ውኃ ከወዲያ ወዲህ ሲላጋ፣ የእረኞችን እንጉርጉሮ የገደል ማሚቶ ስታስተጋባ፣ ባሕሩ ቋጥኙን እየተጋፈረ አረፋ ሲደፍቅ ጸጥ ያለውን አየር ንቧ ስትቀዝፈው አሞራው ዛፉ ላይ ተንጠልጥሎ ጬኸቱን ሲለቀው፣ ኩኩ መለኮቱ ራቅ ብላ በጣፋጭ ድምጿ ስታጅበው፣ ይሕን መሳይ ሁኔታ ሲያጋጥማችሁ ግሩም የተፈጥሮ ሙዚቃ ሠማን አትሉም?

ከላይ እንደ ጠቀስኩት ሙዚቃ፣ በተለይም በመድረክ የሚሠራ ሙዚቃ፣ የብዙ ድካም ውጤት ወይም ቅንበር ነው። ለምሳሌ የመሣሪያዎቹ ተራ አጠባበቅ የየብቻና፣ የኅብረት ተሳትፎአቸው የድምፅ አወጣጣቸው ከፍታና ዝቅታ ደረጃ፣ የፍጥነትና ዝግታው መተን፣ የድምፃዊና የተጫዋቾቹ ውዝዋዜ፣ አጀማመሩና አጨራረሱ፣ ወደ ዘፈኑ የመጀሪያ መግቢያ የመመለሱ ሁኔታ ሁሉ ሥርዓቱን የጠበቀና የሚስብ፣ የሚያጓጓ መሆን አለበት። ግጥሙም ለጆሮና ለልቦና የሚጥም ጥሩ መልዕክት ከስሜት ጋር አዋሕዶ የሚለግስ ሊሆን ይገባል።

ስለ ውዝዋዜ ካነሣን፣ ድምፃዊ ብቻ ሳይሆን መሣሪያውን የሚጫወቱት ሙዚቀኞችም አኳኋን ደስ አይላችሁም? እስቲ ገና ሊጀምሩ ሲሉ ልብ ብላችሁ እዩዋቸው። ቅኝታቸውን ለማስተካከል የሚነጋገሩበት የራሳቸው ቋንቋ አላቸው። ጊታር መቺው ጅማቱን ላላ ጠበቅ እያረገ አንድ ሆድ እምትበላ ድምፅ ሲያወጥ፣ ባለ ከብሮው ድምድም፣ ደሞ እንደ ሳክስሮን ጐርናና ድምፁን ሞከር፣ ቀጥሎ ቀጭኗን ወጣ፣ ደሞ ዝም፣ እንደገና ከበሮው ድም፣ እንዲህ እንዲህ ሲሉ ይቆዩና - ስውር ቴሌፎን አላቸው መሰለኝ - ዘፈርኑ ላይ አንድ ጊዜ በድንገት ይወርዱበታል። ከዚያ በሙዚቃው ይመሠጡና ከራሳቸው ጋር የሚነጋገሩ እስኪመስሉ ድረስ፣

እንደ መሳቅ፣ እንደ መኮሳተር እያሉ ውዝዋዜያቸውን በስሜት ይያያዙታል። ባለ ሳክስፎኑ ደረቱን እንፍቶ፣ ባሕር እንደሚቀዝፍ ታንኳ ወይም በቄንጥ እንደሚያሽበሽብ ካህን ትከሻውን ሄድ መለስ ወዝወዝ፣ ቅንድቡን ከፍ ዝቅ እያረገ ኩሩውን መሣሪያ ደርበብ ብሎ ሲጫወተው፣ ጊታር መቺው በሙዚቃው ሂደት ዓይነት ራሱን እየነቀነቀ ወለሉን በእግሩ መታ ሲያደርግ ከበሮ መቺው በሙዚቃው ሂደት ዓይነት ራሱን እየነቀነቀ ወለሉን በእግሩ መታ ሲያደርግ ከበሮ መቺው እየተንጠራራ እየተንቀጠቀጠ ሦስት አራት ነገሮችን እንደ መዝለል እያለ ሲመታ በተለይ እሱ አንድ ቦታ ቁጭ ብሎ የኮርስ ብስክሌት የሚነዳ ሲመስል - ትእይንቱ በጣም የሚያስገርም ነው።

ታዲያ በጥሩ ሥዕል አንጻር ተራ ሥዕል እንዳለ ሁሉ በኦኬስትራው ጩኸትና በመሣሪያዎቹ ኳኳታ ግጥሙና ምልክቱ ተውጦ የሚቀበት ተራ የሆነ የመድረክ ሙዚቃ አቀራረብም አለ። እንደ ዛሬ የቲያትር ምንነት በደንብ ሳይታወቅ ተዋንያኑም ለመድረክ ሳይሠለጥኑ ቲያትር በሚታይበት ወቅት ተመልካቾች ተደስተው እየሣቁ ካጨበጨቡ ወይም በጣም ልባቸው ተነክቶ የማዘን ምልክት ከታየባቸው አንዳንዶቹ ተዋንያን ከሚያስፈልጋቸው በላይ እየደጋገሙ ይጫወቱት ነበር። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ እንደ ቲያትሩ የጐላም ባይሆን በተራ ኦርኬስትራዎችም ላይ ይታያል። ዘፈኑ ሞቅ ሲል ጭብጨባውና ፉቸቱ ሲቀጥል ባለ ጥሩምባው ጥሩምባውን ባለክላርኔቱም ክላርኔቱን ከአፉ አላቆ ቅጥ ባጣ ሁኔታ እንደ ድምጻዊው እግሩን ሲያንቀጠቅጥ እጁን ሲያወናጭፍ ይቆይና ወይ ዘፈኑ የመጀመሪያ መግቢያ መመለሻው ቴምፖ ሲመጣ «ቆዩኝ አንዴ» አይባል ነገር ሁሉም በየፊናው ያልተዘጋጀበትን ለመፈለግ ሲጣደፍ በአግባብ ስሕተት በየፊናው ያልተዘጋጀበትን ለመፈለግ ሲጣደፍ በአግባብ ስሕተት ምክንያት ዝብርቅርቅ ሁኔታ ይፈጠራል። ማለትም መቅደም እማይገባው የመሣሪያ ድምፅ ይቀድማል። ለስለስ ማለት ያለበት ይጮሃል። ከሁሉም ይልቅ ተደበላልቆ ድንገት ከኋላ እንደሚሰማ የሲዮንቺና ክላክስ ማስደንገጡ አይቀርም። መልእክቱም ትርጉሙም የዞረ ድምር እንዳለበት ሰው ንግግር ውሕደት የሌለውና ያልተያያዘ ይሆናል።

በእንግዲህ ዓይነቱ ተራ ኦርኬስትራ መሣሪያዎች ፉክክር የያዙ መስለው ነው የሚቀርቡት። በተለይ ሳክስፎን ግዙፍ ደረተ ሰፊ ሰው ስለሚይዘው እንደሆነም እንጃ ከሌሎች ይበልጥ መጮሁ የማይቀር ጉዳይ ነው። እኋላ በመቀመጥ ችግሩን ልትቋቋሙ እምትችሉ እንዳይመስላችሁ። ቀድሞም ሲሠራ ለመጮህ እንዲችል ነውና ድምፁ ከአዳራሹ አልፎ ተርፎ የሠፈር አስፋልቱ ላይ ያስደንሳል። እኔ በበኩሌ የመሣሪያዎቹን ድምፅ የሚውጥ ብቻ ሳይሆን የሚቆጣቸውም ነው የሚመስለኝ። ታዲያ እሱም ተቆጭውን አንድ ድምጻዊ መመልከት ነው። ተራው ድምፃዊ ገና ኦርኬስትራው ሳይጀምር ማይክሮፎኑን ሲጨብጥ መወዛወዝ ይጀምራል። ከመሬት ተነሥቶ ጣራ ጣራውን ያያል። እረፍት ለማግለጥ ሲል ግን አይደለም፣ ማፈር ብሎ ነገር እሱ ጋ ቦታ የለውም። ወዲያው ደሞ ሰው ይፈልጋል። ስለ ፍቅር የሚያንጐራጉር ከሆነ ፍቅር የያእው ለመምሰል ከመሞከር አይመለስም። ትንሽ ሆድ የሚያባባ ዓይነት ግጥም አፉ ላይ ከመጣለት በቀላሉ አይሳካለትም እንጂ እዛው ቢያለቅስም ፈቃዱ ነው።

ትሩ ፎርም አንሺ ነው - ፎርም አበላሽቶ ለማንሣት። ሁሉንም ነገር በጣም ለማስመለስ ከመጣሩ የተነሳ ራሱንም ሌሎቹንም ሳይሆን ይቀራል። ሆኖም በድምፅ አወጣጡ ረገድ የሄድን እንደሆነ አንድ ጉልህ ጠባይ ይታይበታል። ይኸውም አለዚያ ቀን የማይዘፍን ወይም ዘፈኖች ሁሉ በሚጫወትበት መድረክ ላይ ያን ዕለቱን የሚያልቁ ይመስል በወፍራሙም በቀጭኑም በረጅሙም በአጭሩም ትንፋሽ እያዜመ ያለ የሌለ ችሎታውን ከድምጽሱ ጎተራ አሟጦ መጨረስ ያለበት ይመስለዋል። ስለዚህ ዜማውን በማያስፈልግበት ጊዜ ሁሉ ቢጎትተውና ቢያሮጠው እንዳይገርማችሁ። ብቻ አስቂኝ ነዝሪ ድምፅ እንደሚያወጣ አትጠራጠሩ።

የተራው ድምፃዊ ውዝዋዜ የተለይ ነው። ማሳየት ሲገባው ይኮሳተራል። ፊቱን ቅጭም አርጎ ተመልካቾችን እንዲመሰጡ ማድረግ በሚያስፈልግበት ቦታ ፎቶ ግራፍ የሚነሳ ሰው መስሎ ቁች ይላል። ልቤን ሠወረችው ለማለት ሲፈልግ እጁን ኩላሊቱ ላይ አርጎ እዛው በሽተኛ ይሆናል። ውዝዋዜው ላይ ያለ ምክንያት በዘፈቀደ የሚደረግ ስለሆነ «እግዚአብሔር» የሚል ቃል በግጥሙ ከመጣለት ጣቱን ወደናንተ ቀስሮ እዚያው አዳራሹ ውስጥ ሲፈልገው ይችላል። እግሩን ሲያንቀጠቅጥ በማይታወቅ ዳንስ ወይም እስክስታ ወገቡን ሲሰብቅ ለጉድ ነው ድንገት የማይክሮፎኑን እጄታ ነቅሎ ከተንበረከከማ መመለሻ የማይገኝለት ትልቁን ተሰጥኦውን ጀመረ ማለት ነው።

የተሰጥኦ ነገር ከተነሳማ አንድ ድምፁን እንደፈለገው ለማዘዝ የሚችል የመድረክ አቀራረቡ ምንጊዜም የሚያምርለት ድምፃዊ አንድ ጨዋታ ሲያሳይ በጣም በተጋጋለ ሁኔታ ላይ ሳለ፣ በጭብጨባው መካከል ሳያስበው የማይክሮፎኑ ገመድ ሊጠልፈው ሲል ምንም ባይታወቅበት በዘዴ እንደ ዳንስ አስመስሎ በርጋታ ሣቅ እያለ፣ ገመዱን ሲዘለው ማየቱ ትዝ ይለኛል። ዘፈኑም «አመልካች ጣት» የተሠኘው ነበር።

ብራቮ ከእውነተኛ አርቲስት የሚጠበቅ።

# ጸጉር ቤት

ስለ ፀጉር ቤት ለመጻፍ ጸጉር አስተካካይ መሆን አያስፈልግም መቀስ፣ ማበጠሪያ ቶንዶስ፣ ምላጭ ኮሎኛ፣ ቅባት፣ ፓውደር፣ በኅብረት የሚሠሩት ሥራ! ግማሽ ሰዓት ያህል ቆጥ የሚያህል ወንበር ላይ እየተሽከረከሩ ማየቱ የአስተካካዩን የደንበኛውን፣ የውጭ ገቢውን ሁኔታ መታዘቡ፣ የሚወራውን መስማቱ፣ ሁኔታውን በቅርብ ለማስትዋል ሳይጠቅም አይቀርም። ነገሩን አንድ እርምጃ ከፍ አድርገን፣ ከተመለከተነው እንዳይነሣ የታዘዘ ይመስል አንድ ቦታ ተቀምጦ ነቅነቅ ሲል ሁሉ ተጠንቀቅ ሳይወድ በግድ የለመደውን መልኩን እንደ አዲስ ዝም ብሎ ሲያይ፣ የገዛ ፊቱን የሚያጠናው ሰው ማየቱ ራሱ የሚያመራምር ባይህን ያስገርማል ፡

መቼም የመጻፍ ነገር ልጻፍበት ብሎ የመነሳቱ ግፊት በመስተካከል ላየ ያለሁ መጥቶብኝ አያውቅም እንጂ የጸጉር ቤቶች ተዘዋዋሪ ደንበኛ መሆን ከጀመርኩ ሃያ አምስት ዓመት አልፎኛል። የዛሬው ዓይነት «አፍሮ ስታይል» ሳይመጣ፣ መጀመሪያ «ባርቤሪ» ከዚያ «የጸጉር ቆራጭ» በኋላ ደሞ ተሻሽሎ «ጸጉር አስተካካይ» በመባል ሲታወቅ ሁሉ ነበርኩ። ታዲያ በዚያን ጊዜ «ተማሪ ቁርጥ» በመባል ሲታወቅ ሁሉ ነበርኩ። ታዲያ በዚያን ጊዜ ሻል ሠልጠን ብለናል በሚሉት ዘንድ፣ «በእነ እገሌ ፎርም መቆረጥ ማበጠር» የሚል አነጋገር እንደ ነበረ፣ እንዲያውም አንድ ዛሬ እውቅ የሆነ ዘፋኝ በአዲስ ኸብባ ከተማ «ኤልቭስ ስታይል» በተባለው አቆራረጥ ለጥቂት ዓመታት ምሳሌ ሆኖ እንደቆየ ትዝ ይለኛል ፡

ከሁሉም ከሁሉም ተወልጅጂ ያደግሁባት ሞጆ እንደ ዛሬው ዋናው መንገዷ አስፋልት ሳይለብስ፣ ቢቆጠሩ ሠላሳ እማይሞሉ አምፖሎች ጭል ጭል ሳይሉባት፣ ያኔ ብርቅ አገርን የምናያቸው የመጀመሪያው ሊስትሮና ባርቤሪ ምንጊዜም አይረሱኝም። ዛሬ በአዋቂ ዕድሜዬም ቢሆን ከማዘጋጃ ቤት ፕላን ተሸሽጋ፣ ፊቷን ሠወር ወዳለ አቅጣቻ መልሳ ጉድባ አፋፍ ላይ ወይም ሁኔኛ ቤት ተደግፋ የቆመች፣ በተጣመመና ወጣ ገባ በሆነ ጽሕፈት «ዘመናዊ» ብላ የምትጀምር ተንቀሳቃሽ ኪዎስክ መሳይ በኩል አለፍ ባልኩ ቁጥር ወይም ጸጉሩን ለመቆረጥ ባላበው እጁ ሽልንጉን ጨብጦ በባልንጀሮቹ የታጀበ ሕፃን ባጋጠመኝ ጊዜ ትዝታው ይመጣብኛል።

ጸጉር ቤቶች ሲባሉ በወር አንድ ጊዜ ማማሪያ ቦታዎች ናቸው። ምናልባት ግን «እኔ ጸጉሬን የምስተካከለው ለማማር አይደለም» የሚል ቢኖር አባባሉን ለውጥ አድርጎ «ጸጉሬን አራግፌ ለመገላገልና ምን እንደምመሰል ለማየት ነው» ቢልም እንግባበለንና ይኸ አይቸግርም፣ ማንም ሰው ጸጉሩን ሲቆረጥ ቀለል ይለዋል። ፊቱ ፈካ ይላል። ወዙ ጠራ፣ ደመቅ፣ ልጅነቱም እንደ መመለስ ይላል።

ታዲያ ሲበዛ ማርም ይመራል ለውበት መጓጓት መረኑን ሲለቅ ደስ አይልም። ለምሳሌ አንዳንዶቹ «ያንን አሳጥር፣ አይንን ተወው» የሚል መመሪያቸውን መደጋገማቸው ሳያንስ ስለ ጸጉር ያላቸውን ፍቅር በሻምፑ ዓይነቶች ይጀምሩና ጥያቄና አስተያየታቸውን ያዥጐደጉዱታል። አልፎ አልፎ ደግሞ እውነታቸውን ከምኞታቸው ጋር ቀይጠው እያዩ፣ የሚነቀለውን ጸጉር ባንዳች ኃይል በጣታቸው እሚተክሉት ይመስል በስጨትጨት በማለት ከአስተካካዩ ጋር የማልጐምጐም ግብግብ የሚቃጣቸው፣ ቢችሉ መቀሱን ስጠኝ ለማለት የማይመልሱ አይታጡም።

ፎቶ ሲነሣ ለመዘነጥ ቆርጦ የመጣውንና እንዳሰኘው ካልተጣመምኩ የሚለውን ማስቀየም እንደማይችል ሁሉ እንደዚህንም ዝብ ብሎ «እሺ» ካላሉ፣ «በገዛ ጸጉሬ ምን አገባህ» መባልይመጣልና የሚያዋጣው ዘዴ በመቀድ ኳኳታ እየተከዙ በትእግሥት ማለፉ ነውና። ያም ሆነ ይህ ጥሩ ሆኖ መታየት አያስነውርምና ነገሩን በዚሁ እንለፈው።

በሌላ በኩል ካይነው እሁድ የሚዳር ሙሽራ ቅዳሜ ማታ መታጀብ በጸጉር ቤት አይደል! እስቲ ለምሳሌ፣ ሱፍ ልብሱ ተገዝቶ ሰንጋው ተጥሎ ሁሉ ነገር ተዘጋጅቶ ሙሽራው ሙሽሪትን ሊያመጣ አበባ ተርከፍክፎለት ማርቼዲሱ ሲገባ በግርግር መሐል ፀጉርና ጺም ተረስቶ ቢገኝ ሥርጉ ምን ዓይነት ሥርግ ይሆናል። ትላላችሁ!

ቅድም ካነሣኋት ተንቀሳቃሽ ኪዎስክ ጀምሮ የሽቶው ቅይጥ እስከሚወድቅበት ዘመናዊ የጸጉር ማስተካከያ ድረስ የጸጉር ቤት ዓይነቱ እንደ ከተማችን ይዞታ እንደ ሠፈሩ ሁኔታ የተለያየ ነው። ብዙ ዝርዝር ውስት ሳንገባ - አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል - እንደ ሻይ ቤት ቁራጭ መጋረጃ ከሚሰቀልባቸው እንጀምር። እነዚህ ጸጉር ቤቶች ከጽዳት በአገልግሎታቸው ግን በሙያው መስክ አንዳንዶቹን በማለማመድ ወደ መሐል ከተማ ያሻገሩ ዛሬ ምሁር ሀብታም፣ ዶክተር፣ የሆኑትን በስሙኒ ሲያስተናግዱ የኖሩ መስተካከያዎች ናቸው። ገና ገባ ስትሉ የየቅባቶቹ ሽታ የሆያሆዬውን ዘመን ያስታውሳችኋል። ወደ ግድግዳው ካማተራችሁ ደሞ፣ «ዘ ግሬተስት ስቶሪ ኦፍ ኦል ታይምስ - ዘ ስቶሪ ኦፍ ኤ ጋን ማን ደስትንድ ቱ ኪል ኤንድ ኮንከር እንቲል ሂ ሜት ኤ ውመን» የሚል ዓይነት የአርባ ዓመተ ምሕረት የሲኒማ ቤት ነፋ ለብዙ ዓመት ባለወለታነታቸው ምስክር ይሆናቸዋል።

ሌላው ደግሞ ከዘመናዊ ዕቃዎች እንዳንዶቹን ያደባለቀው ነው። ልዩ ምልክቱ፣ «ለቋቁቻ፣ ለጭርት ለብጉር፣ ለሚነቀል ጸጉር ለፎረፎር፣ የሚሆን ፍቱን የሀገር መድኃኒት አለ» የሚለው ማስታወቂያ ነው። እነዚህም ነገሮች በቢራ ጠርሙስ ቡሽና ቆርኪ፣ በቆረቆንዳ በተከደኑ ጠርሙሶች እና ቢልቃጦች በግልስ የሚታይ ቦታ ላይ ይደረድራል። የእነ ሲሮኮ፣ ክሬም፣ ኮላ፣ ሲናክል፣ ጠርሙሶች፣ ሌላ ቦታ የጠፉት ሁሉ የሚገኙት እዚህ ነው። ወደ ቡና ቤት ሥዕል የሚጠጉ አፍሮ ጸጉርና ትልቅ መቀስ ኖራ በመለስ ቀለም የተሣሉባቸው ጸጉር ቤቶችም አልፎ አልፎ የሚገኙት በነዚህ አካባቢ ነው። እንደ ሌላው ጸጉር ቤት ሁሉ ለመስተካከል ሳይሆን እንዲሁ ያለ ምክንያት ቁጭ የሚሉ ሰዎች እነዚህም አሉ። ለምሳሌ አግዳሚው ላይ ቁጭ ብሎ እግሩን የሚያወዛውዝ ሕፃን ቢያጋጥማችሁ «እስከመእልስ አቆዩልኝ» ብሎ አባቱ ጥሎት የሄደ ሊሆን ይችላል። ነጠላ እየቋጩ፣ ወይም ሹራብ እየሠሩ ደጃፉ ላይ ተቀምጥው ፀሐይ የሚሞቁም አይታጡም።

ያለ ምክንያት ጸጉር ቤት ቁጭ የሚሉ ሰዎች ነገር ከተነሣ፣ ጡረታ የወጡ አዛውንቶችና ደላሎች፣ በቀን ውስጥ ደጋግመው በመምጣትና ለረጅም ጊዜ ቁጭ በማለት ከማንም ይልቅ ብልጫ እንዳላቸው መታወቅ አለበት። አንዳንዶቹ የሚመጡት ለቀጠሮ ሲሆን አብዛኞቹ ግን በመንገድ የሚያልፍ የሚያገድመውን እያዩ የሳምንቱን ወግ፣ ቁም ነገሩን፣ ቀልዱን፣ እድሩን ሰንበቴውን እያነሡ መጫወቱ፣ ጨዋታውም ከጠፋ ዝብ ብሎ ተቀምጦ መሄዱ፣ ሄዶ ቆይቶ ደሞ መምጣቱ ልማድ እየሆነባቸው ነው። በዚህ አካባቢ መፈላለግ እንኳን ባይኖር «ታዲያስ» በሚለው ምትክል «የፈለከው ሰው ነበር» ማለት የተለመደ ነው ፡

ከነዚህ ትንሽ ለየት የሚሉት ጋዜጣና የቆየ መጽሔት ለማንበብ የሚገቡ ነገር ግን ለመቆያ ያህል በጃቸው እንዳንጠለጠሉት ወሬ የማያወሩት ናቸው። እነዚህኞቹ ብዙም ትእግሥት የላቸውም። ቶሎ ተሰላችተው እንደ ማዛጋት ይሉና፣ «እስቲ ይቺን የኮሰኮሰችኝን አንሣልኝ» ገና ከማለታቸው መቀሱን ለቀም በማድረግ በተገኘው ባዶ ወንበር ላይ እግራቸውን አንፈራጠው ጉብ ይላሉ። የእነሱን ያህል ወግ ጨዋታ ሳይጀምሩ ገብተው ሰላምታ እንደ ሰጡ ኮለኛ ራሳቸው ላይ ነስነስ አርገው ካበጣጠሩ በኋል በል ቻው! ብልው ውልቅ የሚሉም አሉ። የትኝኖቹም ይሁኑ የትኞቹ ድንገት በሩን በርግደው ገብተው መስተዋቱን በሣቅ እያነቃነቁ፣ ጢም ከሚላጭ አስተካካይ ጋር እጅ እየተጓተቱ ለማላፋት ከሚፈልጉ ጋጠ ወጥ ወፈፌዎች መቶ በመቶ ይሻላሉ።

መቼም ለእንዲህ ዓይነቱ፣ በሥጋት ብቻ ለበሽታ እሚዳረግ አጉል ቀልደኛ፣ እሚበገሩም ባይሆን ለደንበኞቻቸው ግድ የማይኖራቸው አስተካካዮችም አሉ። ለምሳሌ ሰለ ጤንነት፣ ቤተሰብ፣ ሥራ፣ ትምህርት፣ ስለ ክረምት፣ ስለ ስታድዬሙ ጨዋታ፣ ቲያትር ሲኒማው ሁሉ የማያስፈልግ ተደጋጋሚ ወሬ በማነብነብ በመጠየቅ፣ ያለ ምክንያት በመገረም፣ በመሳቅ፣ በሥራ የደከምውን ተስተካካይ የሚያሰለቹ አሉ። የሰው አንገት ደፍተው መቀስ በጆሮ እያንኳኩ የሞቀ ወሬ ከማጦፍ አልፈው «አስቸኳይ ነው» በሚል ይቅርታ የጢም ሳሙና ሲቀቡ አቋርጠው ስልክ የሚያነጋግሩ አሉ። ደንበኛ ጥበቃ ሲሰለቸው ባለ አንቴውናን ሬዲዮ ሰምቶ ሳይሰማ ከጣቢያ ጣቢያ ዝም ብሎ የሚጐረጉረው ደሞ ሊላው ነው።

ከሁሉም ከሁሉም የሕፃን ጸጉር ማስተካከል ቀላል አይመስለኝም። ገና መቀሱን ሲያይ የሚያለቅስ ሕፃን ይኖራል። ሌላው ደግሞ ማንጅራቱን በየጊዜው ካላከኩ እያለ አንገቱ ዙሪያ የተጠመጠመውን ጨርቅ የሚፈታ፣ ኳስ ብጤ ወይም ሙዝ የያዘ ሱቅ በደረቴ በመስተዋቱ ውልብ ሲል ካልዞርኩ የሚል፣ ቅብጥብጥ ይሆናል። ታዲያ እንዲህ ዓይነቶቹን ሕፃናት እያጫወተ፣ «አባባ ተስፋዬን እየህ?» እያለ ባድኑ እጁ መስተዋቱ ውስት እያሳየ፣ በሌላው የሚቆርጥ፣ የማዝናናት የማረጋጋት ተሰጥኦ ያለው ጸጉር አስተካካይ አለ። በየጸጉር በኢቱ ሌላም ሌላም የሚደንቅ ነገር ይኖራል። ትሕትና ግን የሥራው ጠባይ ነውና እዚህ ውስጥ አይገባም።

# ሲኒማና ቲያትር ተመልካቾች

የሥራ ጊዜው በሚፈቅድለት መጠን ሲኒማ መግባት የሚወድ፣ ነገር ግን የፊልሙን ታሪክ መከታተል የማይችል አንድ የታወቀ ይሳይንስ ሊቅ ነበር። ሐሳብ ስለሚበዛበት ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት የተወሳሰበ የፊዚክስ ፕሮብሌሞችን እንደ ብሎን እየፈታ መግጠም የማያቅተው ሰውዬ፣ ማንም ተራ ሰው ፊልም እያየ ሲደሰት እሱ አልገባ እያለው ይበሳጭ ነበር። በኋላ ለዚህ አንድ ዘዴ ፈለገና የሚያስረዳው ሰው እየያዘ ሲኒማ

*መግባት ጀመረ። እንደዚሁም ሆኖ ለችግሩ መፍትሕሄ አልገኘለት አለ። አንድ ቀን ሁለቱም ፊልም ሲያዩ ሰውዬው እያብራራለት ነገሩ እየገባው ለካ እንደዚህ ነው ሲያዳምጥ ቆይቶ፣ በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ሌላው ተመልካች ሲስቅ ሲያዝን በስሜት ታሪኩን ሲከታተል ዋለና ወደ መሥሪያ ቤቱ ሄደ። እዚያም ሳይንቲስቱ የላቡራቷር ሥራውን ሊጀምር ሲል፣ የፊልም ትርጅማኑን፣ «ቅድም ፊልሙ ላይ ከብቶቹን የዘረፈው የሴትዬዋ የባሏ ወንድም አይደለም እንዴ?» ሲል ጠየቀው። ሰውዬው አዎን ሲል መለሰለት። «ከብቶቹን ያስመለሰውስ የባሏ ልጅ አይደለም?» ሲል ጠየቀ። ሰውዬውም፣ «እሱማ የሴትየዋ ባል ነዋ - ከብቶቹ ሲዘረፉ የሞተው» ይለዋል። በዚያን ጊዜ ሊቁ ተገርሞ ከት ብሎ ሣቀና፣ «ለካ ስለሞተ ነው ያላየሁት» አለው።*

*ሳይንቲስት ሲባል ጢሙን አንዠርጎ፣ ጸጉሩን አጎፍሮ፣ የፀሐይ ብርሃን ሳያገኘው ማይክሮስኮፕ እንደ ጨበጠ ላቦሯቷሩ እስጥ የሚውል ነው ብለው ለሚያስቡ ሰዎች ቀልድ መስሎ ይታይ እንደሆነ ነው እንጂ ነገሩ በእርግጥ የደረሰ ነው። የፊልሙ ታሪክ የማይገባው አልበርት አነስታይን ነበር። «ታዲያ ምን ለማለት ነው ይህ ሁሉ» የሚል ጥያቄ መሰንዘሩ ስለማይቀር ነገሩን እንደ መነሻ አድርጌ ሰል ሲኒማና ቲያትር ቤቶቻችን ተመልካቾች አንዳንድ የተመለከትኳቸውን ነገሮች አቀርባለሁ። በመጀመሪያ የሀገራችን ተመልካቾች እንደ ሳይንሱ ሊቅ የፊልም ታሪክ መከታተል አይችሉም የሚል አቋም የለኝም። ሳይንቲስት በሆንኩና ሲኒማ በቀረብኝ የሚሉ ካሉ ግን ያርላቸው ከማለት በስተቀር ሌላ የማክለው ሐሳብ አይኖረኝም።*

*ከሲኒማ ደንበኞች መካከል ቋንቋውን ወይም የአነጋገር ፈሊጡን ወይም ባህሉን ባለማወቅ፣ ወይም የድርጊቶቹን ጥድፊያ ለመከታተል ባለመቻል፣ ተንቀሳቃሹን ብርሃን ብቻ አይተው የሚወጡ ሰዎች በርግጥ አሉ። አንዳንዶቹ ለሙዚቃው ስሉ የሚገቡ፣ ሌላው ሲስቅ አብረውም የሚስቁ ከንፈሩን ሲመጥ የሚመጡ ሌላው ያዘው በለው ሲል የሚፈነጩ ፉጨት ሲሰሙ የሚያፏጩና የሚያጨበጭቡ ናቸው አንዳንዶቹ ገግሞ ስለ ፊልሙ ሲወራ አይቼዋለሁ ለማለትና የአራዳውን ወሬ ለመቅመስ፣ የሚያውቁትን ሰው ለማግኘት ወይም ከዙረት ከመጠጥ ገንዘብ ከማጥፋት ለመቆጠብ ሲሉ የሚገቡ፣ ኮካኮላውን ማስቲካውን መገዛዛቱን ጨኸቱ ትችቱ ሁሉ ደስ የሚላቸው የታመቀው የሲጃራ የተዋሐዳቸው ናቸው። «ከሷ ጭቅጭቅ ሲኒማ ብገባስ» እያሉ ከሚስታቸው የሸሹ መስሏቸው የሄደው የሚውል ለታሪክ ደንታ ሳይኖራቸው ጥሩ እንቅልፍ ተኝተው እያዛጉ እሚጠጡ፣ ልጃቸውን «አውሮፕላኑ ይውና» የሚል ዓይነት ጨዋታ እሚያጫውቱ የእድሩን ወሬ የመሥሪያ ቤቱን ወሬ እሚያወጉም ይገኙባቸዋል።*

*በቲያትር ረገድ የሄድን እንደሆነ ታሪኩን የመከተል ችግር በብዙ ሰዎች ዘንድ እንደማይኖር የታወቀ ነው። እዚህ የምናየው አንድ ጉልህ ነገር ለብዙ ዓመታት የቲያትር ቤቱ ደንበኞች የሆኑ ተመልካቾች መኖራቸውን ነው። እነዚህ ሰዎች በፋሲካ ድሮ እንደማይቀር ዓይነት እሁድን ከአገር ፍቅር አስታጉለው አያውቁም። ስለዚህ፣ «የአገር ፍቅር ልብሴ ተተኩሷል?» ቢሉ፣ ወንበር ላይ የተለጠፈ ማስቲካ አግኝተው ያለ ምንም ማረጋገጫ ቢቆጧችሁና «ምነው አንተ ውርጋጥ» ብለው ቢደነፉባችሁም እንዳይገርማችሁ።*

*ጥሩ ልብሳቸውን ለብሰው፣ ባርኔጣቸውን አርገው በተላጨው ጉንጫቸው ላይ ፈገግታቸውን ጨምረው በሰዓቷ ከች የሚሉ ሕንፃውን እድነ አደጉበት ቤት ዙሪያው በትዝታ ዓይናቸው የማንከባከቡና ገና ሳትወስዱ ጀምረው ሲመላለሱ የኖሩ ናቸው። ስለ ቲያትር ዓይነት እነሱ ጋ መጨነቅ የለም። ምንም ቲያትር ይሁን እሁድን በቲያትር አዳራሽ ማሳለፍ አለባቸው። እና አንዱን ቲያትር አምስት አድስት ጊዜም ደጋግመው ያያሉ። የታሪኩን ሄደ በጣም ስለሚያውቁና ለመጪው ድርጊት ስለማይጨነቁ የተዋንያኑ ግጥምና አነጋገር እየተጋጋለ መጥቶ ሲያበቃ አንድ አስደናቂ ደረጃ (ጡዘት) ላይ ሊደርስ ነው ብሎ ተመልካቹ ሲጓጓ፣ «መልሱን አታመታም አንተ?» ይሉና ኮካኮላ በሚሸጠው ልጅ ላይ እንደ ብራቅ ይጮሃሉ። ቀረርቶ መድረኩ ላይ*

ከተጀምረም፣ ድምፃቸውን ዝቅ አርገው እንደማቅራራት ይቃጣቸዋል። ታሪኩን በቃል ሊያጠኑ ምንም ያህል ስለማይቀራቸው ተዋናይ ተዋያንትዋን አንድ ነገር ሊያደርጋት ነው ብሎ ሰው በፀጥታ ሲጠባበቅ፣ «አታስቡ - ሲያብል ነው አይገላትም» ይላሉ - አስቀድመው በመናገራቸው ኮራ እያሉ።

የፊልምን ታሪክ መከታተል ከሚችሉ ተመልካቾች አብዛኞቹ ቋንቋውን በደንብ የማያውቁ፣ ወይም የተመጣጠነ ችሎታም ቢኖራቸው ብዙ ከማየት ልምድ የተነሳ ታርኩ የሚገባቸው ወጥቶች ናቸው። ታዲያ ታሪኩ ብቻ ሳይሆን በፊልሙ የሚያጋጥማችውን ዘመናዊ ነገር፣ ለምሳሌ ፋሽኑን፣ አነጋገሩንም አካሄዱን.....እንደ ካርቦን ለማንሣትና በአካባቢያቸው ካሉት ሁኔታዎች ጋር ለማገናዘብ ብዙ ጥረት ያደርጋሉ። ፊልሙ ታይቶ ሰዓቱ ደርሶ ሲወጣ የተቀሰመው ነገር ሁሉ መጥፋቱ አይቀርም እንጂ እንደ ጀምስ ቦንድ ወንዳ ወንድና ቀልጣፋ ሆኖ ለመታየት፣ እንደ ሶፊያ ሎሬይን በቁንጥ እየቀዘፉ ለመራመድ ምኞትና ጉጉት አላቸው። እንዲያውም ውብ ሆኖ የመታየቱ ለብታ የሚጀምራቸው ገና ሲኒማው አዳራሽ ሲገቡ ነው - አካሄዳቸው፣ ፈገግታቸውና አሣሣቃቸው ለወጥወጥ ይላል። የአነጋገር ለዛቸው የፊልሙን ዓይነት መሆን ይቃጣዋል። ሌላው ቀርቶ፣ የጫማቸው አረጋገጥና አበላላቸው ሁሉ ይሻሻላል።

በዚህ ክፍል የሚመደቡት ሌሎች ወጣት ተመልካቾች ደግሞ የሙዚቃ ፍቅር በጣም የሚጠናባቸው አፍላ፣ ጉርምስና የወጠራቸው ስሜታቸው ያልተገራ የመንቀዥቀዥ ባሕርይ የሚታይባቸው ናቸው። ከዛም በዙህ ሲያጠራቅሙና ሲያሟሉ ማንም ሳይቀድማቸው እፊት ባሉት ወንበሮች ላይ እንደ ታጠበ ሸማ እጥፍጥፍ ብለው ይቀመጡና አዳራሹን በጩኸትና በፉጨት ለማሸበር ይዘጋጃሉ። የሚገባ የሚወጣውን ብቸኛውን ወንድና ሴቱን የተመልካቾቹን አረማመድና አለባበስ በቅንዝንዝ ዓይናቸው ይከታተላሉ፣ ያጠናሉ።

እነዚህ የሲኒማ ተመልካቾች ትንሽ ጠብ ብጤ ካዩ አፏጭተው የሚያደባድቡ አዳልጦ የሚወድቅ በጣለልን የሚሉ ካለመዱት ወንበር ጠፍተው የማያውቁ፣ አሿፊዎችና ሸርዳጆች ናቸው። ፊልሙ ሲጀምር ከተዋንያኑ ጋር ፋክክር የያዙ ይመስል አብረው ማውራት ይጀምራሉ። በነሱ አጠራር «ጎበዝ» ወይም «እስታሪንጉ» ብቅ ባለ ቁጥር የሚሠራውን ጀብዱ በጋል ጭብጨባ ይተነትኑታል። «መጥቶብሃል፣ ዞር በል አሁን አትልቀቅ» ይላሉ። እስቲ ስታስቡት ቀድሞ ለተሠራ ነገር ምን መመሪያ ያስፈልጋል? የሚጠሉትንም ተዋናይ የዚያኑ ያህል ያክፋፉታል። «አረመኔ! ትንሹን ምን አርግ ይለዋል?» ወንበሩን በቡጢ፣ ወለሉን በጫማ ይደበድባሉ። አንዳንዴማ እግር ኳስ ሊሆን ምንም አይቀረው። ይኸ እንኳን የስሜት ጉዳይ ነው። ክፉውን መትላት ደጉን መውደድ በፈጠራ ጽሑፍ በተለይም በተውኔት ያለ ነገር ነው። ይሁን እንጂ የሚያደርጉት በታሪኩ በመመሰት ብቻ ሳይሆን ለፊልሙ ድምቀት የሚሰጠው እየመሰላቸው ስለ ሆነ ጤነኛ ተመልካች ከክፉው ተዋናይ ይበልጥ ያናድዳሉ።

በሲኒማ አዳራሾች ከነዚህ ጋር የሚወዳደሩት የለየላቸው አናዳጆች ታሪኩን ከመጀመሪያው አንሥቶ እኪያልቅ ድረስ አስቀድመን ካልተናገርን ሁሉንም ካላስረዳን የሚሉ ግለሰቦች ናቸው። «ቆይ ታየዋለህ......ጎበዝ ይመጣል አሁን በፈረስ......ይው መጣልህ.......ግን አያድናትም ገርሉን.....እሱንም ያሥሩታል ታያለህ.......ያውልሃ አሠሩት። ጀይል ገባ.....ግን እንደታሠረ እሚቀር መስሎሃል.......ያመልጣል.....ምን አለ በለኝ.......ገና ምን አይተህ!» ሲቀባጥሩ ለጉድ ነው።

የገለጸው ሱስ ከባድ የሆነበት ደግሞ ወይ ይጎ ሸማችኋል ወይ የኮታችሁን እጅጌ ይጎትታል። አልሰማ ካላችሁ ግን ጫማችሁ መረገጡ የማይቀር ነገር ነው። ለንዲህ ያለው ቸኮነት መፍትሔው በቀላሉ የሚገኝ እንዳይመስላችሁ። ምክንያቱም ካላጡት ወንበር ፈልገው መጥተው እጐናችሁ ነው የሚቀመጡት።

የሚኖራችሁ አማራጭ ለመናገር ገና አፋቸውን በጃቸው ሲገድቡ ጥላቻኋቸው ሌላ ቦታ ቁጭ ማለት ብቻ ነው - ያውም ካለ። አብዛኛውን ጊዜ ደግሞ ጓደኞቻችሁ ሊሆኑ ስለሚችሉ እነሱ ከሚቀየሙ......በሚል ይሉኝታ ዝም ትላላችሁ።

እንግዲህ አይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም፣ «ሁለተኛ ሲኒማ አልገባም» ኣያሰኝም?

# እረኞች

ሰሞኑን - በተለይም በትንትናው ቀን - ለፍልሰታ ጾም ፍስክ በሚደረገው መሰናዶ እንደ ወትሮው ገበያው ደምቆ ውሎ ነበር። ወደ ሸንኩርትና ቅቤ ተራ ወደ ዶሮ ተራ፣ ቅመማ ቅመሙን ቀጤማው ወዳለበት ብቅ ላለ ተመልካች ጫጫታውና ትርምስምሱ ከመኪናዎች ጋጋታና ትሩንባ ጋር ተደባልቆ ሲታይ መርካቶን እንደ እንጉዳይ የፈላውን ገበያተኛ ለማስተናገድ ዝግጅት ሲያደርግ የሰነበተ አስመስሎታል። የመደብሩ ሻጭ ሱቅ ውስጥ እየተንቆራጠጠ፣ ባለ መደቡም ተላላፊውን በዓይኑ እየተከታተለ ገኘው አንዱን እያነሣ እየጣለ ወደ ሌላው እያማተረ አውቶብስ ተሳፋሪው እየተጋፋ ሌላው ለታክሲ እየሮጠ ሌባው እያማተረ፣ አውቶብስ ተሳፋሪው እየተጋፋ፣ ውር ውር ሲል ሁለት እግር ሁለት እጅ ሲወዛወዝ እነዚህም እዚያም - ቀይ ሻሽ - አረንጓዴ - ደሞ ነጭ ሻሽ - ጥለት - ፎጣ - ጥቁር ጃንጥላ - ሰማያዊ ጃንጥላ - ቢጫ እስቶኪንግ - መነጽር በዓይነቱ - ባርኔጣ ኮፍያ - ቦት ጫማ - ሸሚዝ - አዳዲስ ጫማ - ቺፖሊን በጋቢ ላይ ካፖርት - የዝናብ ጃኬት - (አከላሆማ የሚል እጀርባው ላይ) ምኑ ቅጡ ዓይነቱና ብዛቱ! ደሞ የድምፅ ዓይነቶች - ገንዘብ የጣለ ሲያለቅስ - ያተረፈ ሲፈነድቅ - ሰው የጠፋበት ሲጣራ - ታክሲ ላይ ሊወጣ ስንዝር የቀረው አውቶቡስ እየከታተለ ክላክሱን ሲለቀው - ሌባ ሌባ ባዩ ሲጯጯህ - ሊስትሮው ሲያፏጭ - ሰካራሙ ሲአይቅራራ - ትእይንቱ ሌላ ነበር።

ስለ መርካቶ ብዙ ተጽፎአል። የፋሲካን ዋዜማ የገበያ ሁኔታ ለማጠናከር የሄደው ጋዜጠኛ በዕቃዎች ዓይነት ተማርኮ ለዓመት በዓሉ ያሰበውን ገንዘብ ገብይቶበት መመለሱ፣ ግጥም እገጥማለሁ ብሎ ለ«አብዘርቬን» የሄደው ባለቅኔ ፓርከር እስክሪፕቶውን ማስረከቡ፣ ላንድ ሰሞን የታላቋ ገበያ ወሬ ሆኖ ሰንብቶ ነበር።

እኔ ከማስታውሰው ከጋሪው ዘመን ጀምሮ ከእሁድና ከክብረ በዓላት በስተቀር ገበያተኛና መኪና እንስሳት ሳይቀሩ ሳይጋፉ የዋሉበት፣ ከልደታ ባሻገር ጋብ ይበል እንጂ፣ ክረምት ከበጋ ትርምስምስ ያልታየበት የመርካቶ ቀን ያለ አይመስለኝም። ታዲያ ተሸከርካሪዎች በቀይ መብራት ሲቆሙ ወይም ትራፊክ ፖሊስ ምልክት ሲሰጥ አቋርጠው እንደሚለው ዓይነት ለእግረኞች እርስ በእርስ መተላለፍ የወጣ ደንብ የለም እንጂ አዲስ አበባን በመሰለ ከተማ በየመገበያያው ላይና ሰው በበዛበት ባሉባቸው አካባቢዎች የሚታዩ ሥነ ሥርዓት የጐደላቸው ሁኔታዎች አሉ። አካሄድ አታውቅም ተብሎ አይከሰስም። እንጂ የአንዳንዱ እግረኛ አኳኋን ያስመርራል። ጫማውን ጭቃና ውሃ እንዳይነካው አቀርቅሮ የሚሄድ፥ ሰማይ ሰማዩን እሚያይ፣ ከመሬት ተነሥቶ ፈገግ እያለ ከራሱ ጋር የሚነጋገር። መኪኖች ባለፉት ቁጥር የሚገላመጥ ከሌባ ለመጠንቀቅ ዕቃውን እንቅ አርጎ አላፊ አግዳሚውን በጥርጣሬ እሚያጠና ትርፉን እያሰላሰለ ሄድ ቆም ሄድ ቆም የሚል - እንደ መኪኖቹ ቀለም የእግረኛውም ዓይነት ብዙ ነው።

አንዱ ከየት መጣ ሳይባል ድንገት እፊታችው በሳንቲ ሜትር እርቀት ገጭ ብሎ ይቆማል። ዞር ብሎ ያልፋል ብላችሁ በቆማችሁበት ስትጠባበቁ እሱም ቆሞ ይጠብቃችኋል። ከሩቅ ሥራዬ ብሎ ለሚያይ ሰው በሙሣም ሰላምታ የምትለዋወጡ ሊመስል ይችላል። ሰው ጥቅጥቅ ባለበት መንገድ ላይ ከሆነ ግን የቅምሻ ዓይነት መላተምም አይጠፋበትም። ሌላው እግረኛ በጫማው ረግጦአችሁ ወይም በዚያው ዘንቢል መሳይ ጎሽሚችሁ ያልፋል። ምናልባት ዕቃው በዘንቢል ፋንታ አዲስ ቀለም የተቀባ ሳጥን ከሆነም የልብስ አዘኔታ ብሎ ነገር የለምና ዝም ብላችሁ መንገዳችሁን መቀጠል ነው። የመሸጥ ወይም የመግዛት፣ የመደለል ወይም ካሰቡበት ቦታ ቶሎ የመድረስ ሐሳብ የተጠናወተውማ ዝናብ ካባራም በኋላ፣ ጃንጥላውን እንደ ዘረጋ ይዞ አናታችሁን ሊቧጥጣችሁ ይችላል።

በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፣ በየዋህነት ወይም በግዴለሽነት የእግረኛን ምቾት የሚንቀሳቀሱና ጊዜ እሚያባክኑ ብዙ ሁኔታዎች አሉ። ለምሳሌ፣ ጥግ መያዝ ሲቻል በእግረኛ መተላለፊያ ላይ ቆሞ ማቋረጥ ሰላምታ መለዋወጥ ወይም የሞቀ ወሬ ማውራት.....አንድ ጊዜ ሁለት ሰዎች ተቃቅፈው የመሳሳም ሰላምታቸውን እየደጋገሙ መንገድ ዘግተው ቢያስቸግሩት ሁለቱንም መሐላቸው ገብቼ ለያየኋቸውና፣ «በቃ ሁለታችሁም ደህና ናችሁ ብዬ መንገዴን ቀጠልኩ» ሲል አንድ ግለሰብ ያጫወተኝ በዚህ አጋጣሚ ትዝ ይለኛል። በገዛ ሰላምታችን ምን አስመቀኘህ አለመባሉ ዕድለኛ ነው።

የሚገቡበትን ሲኒማ ቤት ለመምረጥና የቀን ውሎአቸው ለመወሰን ዝም ብለው የሚቆሙ ወይም የትዝታ ጭውውታቸውን መዝገብ ከፍትው የስልክ እንጨት ደገፍ የሚሉ ወጣት ፍቅረኞችማ ለሥራ ለቸኮለ፣ ለሆስፒታል ወረፋ ለሚጣደፍ፣ የፈተና ቀጠሮ ላለበት መንገደኛ አብሻቂ እንቅፋቶች ናቸው። በግር መሄጃ ላይ የጠፉ ዕቃ ወይም ማስረጃ ለመፈለግ ሳጥንና ቦርሳ ከፍተው መንገድ የሚዘጉ አሉ። የቀበሌ አባል ካልሆኑ በስተቀር፣ «ምነው ጃል» ብሎ እነሱን ልጠጋ ማለት ትርፉ «ምን ልትሰርቅ አማረህ?? መባል ስለሆነ ያለው ምርጫ እንዳላዩ ተጨናንቆ ማለፍ ነው።

አዲስ ሙዚቃ ለመስማት በካሤት ሻጮች ደጃች ተሰብስበው ሚደንሱት ወጣቶች መተላለፊያ ያሳጣሉ። ከነርሱ ይበልጥ ግን እንደ በቅሎ አስደንብሮ ወደ መሐል አስፋልት የሚያስሮጠው የዘፈኑ ጩኸት ነው።

እንዲህ ያለው ችግር የመዝናኛውን የመገበያያውን መንገድ ለይቶ ባለማወቅ ወይም ለይቶ ለማወቅ ካለመጨነቅም ይመጣል። ለምሳሌ፣ አንዳች እክል ካላጋጠመው በስተቀር በመናፈሻ ውስጥ ልሩጥ የሚል በሰዎች መሐል መሽሎክሎክ የሚቃጣው ሰው አካባቢውን ለይቶ አላወቀም ማለት ነው፣ ወይም ለያውቅ አልተጨነቀም። በዚህ አንፃር ሕፃን ልጅን የሀገር ልብስ አልብሶ፣ በአንድ እጁ ትንሽ ጭራ በሌላው ኳስ አስጨብጦ፣ ጥድፊያ ባለበት አካባቢ በጥምቀተ ባሕር እርምጃ ዘና እያሉ መሄድ፣ «ኳሱ ተገዛ» እያሉ ማጫወት፣ ፎቶ በያይነቱ ማሳየት አግባብ አይደለም። ምክንያቱም የሌቶችን ምቾት መቀነስ ነው።

የእግረኞች መንገድ ሲዘጉ አለመጨነቅ ራስን የሚጎዳበት ጊዜም አለ። አንድ ጊዜ የማርያም ዕለት ጥዋ ከግድስ የተመለሱ ሴቶች እግረኛ መሄጃ ላይ ቆመው በሆነ ነገር ሲከራከሩና ሲንጫጩ በመሐሉ ጥዋውን ከነጠላው ሌባ ይዞባቸው ሄዷል።

ሆኖም አንዳንድ ጊዜ፤ ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ ስለሚሆን፣ አንዱ በሌላው ችግር ይፈጥራል ብሎ ለመድፈር ያያመችም። ግፊያው ከበዛ ሳያማርሩ መጋፋት ግዴታ ነው - እፊት የሚሄደው ከቆመ መቆም። ከመኪና ጎማ አምልጠው ዘለው የነፍስ ያለህ ሽንኩርትና ቅመም መደብ ላይ የሚወጡ የተከመረ ድንችና ቃሪያ የሚንዱ ሰዎች አልፎ አልፎ መታየታቸው አልቀረም።

እፍንፍን ባለው የዘመን መለወጫ ገበያ ወደ ቅርጫው ቦታ እየተደነፋ የሚሮጥ ሠንጋ ደርሶባቸው በመበርገግ ዘምቢል ውስጥ የተቀመጠው ቅቤ በእግራቸው የሚጨፈልቁም አይተፉም።

ከመኪና አሽከርካሪዎች አንፃር ሲታይ ደግሞ ችግሩ በምቾትና በጊዜ ብቻ የሚወሰን አይደለም። የሞት ወይም የመቁሰል አደጋም አለበት። መንገድ ቁጭ ብሎ ከሚሸጥ ሰው ላይ አድን እብድ ሲጃራ ነጥቆ በመሐል አስፋልት ሲሮጥ፣ ሰውየው ሴክተል በኋላ እብዱ ሲወርውርለት እሱም ከመኪኖች ጎማ ለመዳን ሲጃራዎቹን ሲለቅም፣ ሁለት መኪኖች ድንገት ፍሬን ሲይዙ እርስ በእርስ ሊላተሙ ሲሉ በአጋጣሚ ግን ሁሉም ሳይገጩ ሲተርፉ፣ የአንድ ቀኑ ትዕይንት ባስብኩት ቁጥር ይዘገንነኛል። በዚህ ዐይነት በመኪኖች መሄጃ ግብ ግብ የሚይዙና የሚደባደቡ፣ ሲይቋርጡ የወደቀባቸውን ዕቃ ከመሐል መንገድ እናነሣለን እሚሉ፣ ዘው ብሎ ገብተ ከብት እሚያስወጡና ያለ አግባብ አስፋልት እሚያቋርጡ በተለይ የተጋለጡ ናቸው። በቀላል ግጭት ባዩ ቁጥር ጠብቁ የተባሉ ይመስል ግር ብለው አስፋልት ውስጥ የሚገቡ ወሬ አዳማቂዎችና ፍርዱን እዛው እንስጥ ባዮች ደግሞ ለመኪኖች መጋጨትና ለጊዜ መጓተት ምክንያት ይሆናሉ።

አንድ ቀን ያጋጠመኝ ነገር ትዝ ይለኛል። ወራአቱ ክረምት ነው። ሀብተ ጊዮርጊስ ድልድይ ፋሲል ቡና ቤት ፊት ለፊት ሁለት የቤት መኪኖች ተጋጭተው ሰው ከቧቸዋል። ባለቤቶቹ ሳይሆኑ አይቀሩም ይጨቃጨቃሉ። ሁለት ሰዎች ሾፌሮቹን ያዋክቧቸዋል። እንደ ሰማሁት አንደኛው ታረቁ ባይ ነው። ሌላው እጁን አሥሬ እሚያወራጨው ደግሞ ትራፊክ ጽ/ቤት ሁለታችሁም ምስክር ይዛችሁ ሂዱ ነው አሉ እሚለው። ከገባሁበት ግፊያ ለመውጣት ስሞክር - የሰው ቁጥር እጥፍ ሆነ መሰለኝ - ግራና ቀኝ አስፋልቱን አጥለቀለቀው። አንድ ቆሎ የጫነ አሮጌ ከባድ መኪና በላይ ከወደ መስጊድ ታጥፎ ሲመጣ መንገድ ተዘጋበትና በስንት መከራ ከፊቱ እየሸሸለት ፍሬን ይዞ ቆመ። ሾፈሩ ክላክሱን አከታትሎ ያጮሃል። አጠገቡ ያለው ረዳቱ እጁን በመስኮት አውጥቶ ዞር በሉ እያለ ቆርቆሮውን ይደበድባል፣ ደሞ ወዲያው «ሰው ተርፎአል ወይ?» እያለ ይጠይቃል። «ዚታዋ እሚያህል ነገር ላይ ተቀምጦ እንዴት አይታየውም!» ብዬ ገና ማሰብ ከመጀመሬ፣ አውታንቲው ወሬ ለማየት ከቁልሉ ላይ ለመውረድ አንዱን ጆንያ ረገጥ ሲያደርገው ሁለቱ ተናደና በቆሎው ይንጠባጠብ ጀመር። ያ ደሞ ሌላ ትርኢት ሆነ።

የሽሚያ ዓይነት ሁኔታ ተፈጠረና በቆሎውን ለማንሣት ትንንሽ ልጆች ሲራወጡ ከየት መጣ ሳይባል አንድ ፎጣ የጠመጠመ ባለ ቁምጣ ሰውየ ይዞ እሚሮጠውን ከደህናው ሳይመርጥ በአጭር ዱላ ያተራምሰው ጀመር። መጋፋቱን አጠናክሬ ተያያዝኩት። «የትኛው ነው ጥፋተኛው?» አንድ ሹራብ የለበሰ ወጣት ጠየቀኝ። ዝም ብዬ ስጋፋ አንዲት ልጅ ያዘለች ሴትዮ፣ «ሰው ሞተ እሚሉት እውነት ነው» አለችው። ልጋፋ ወይስ ግጭቱን ለመጣው ሁሉ ላስረዳ! በጣም በሽቁ ነበር «ማሙሽ ጡጦ እንካ» ብሎ አንድ ሊስትሮ ለታዘለው ሕፃን ቆረቆንዳ ሲወርውርለት የአሯሯጧን ነገርና አደነጋገጧን እንኩና ልብ ያልኩት በኋላ ነው። እንደ ምንም ብዬ ግፊያውን ጨረስኩና ወደ አንድ ኪዎስክ ራመድ አልኩ። ልክ ይኼኔ ግው የሚል ድምፅ ተሰማ። ከወደ አሜሪካን ግቢ የሚመጣ ባለሸራ ኤን ትሬ ፊቱ የቆመውን ፎርድ ፒክ አፕ ለትሞታል። ፍይፎርዱ ክላክስ ኮንታክት አድርጎ ኖሮ ጆሮ እሚሰነጥቅ ጥሩንባውን ኧከታትሎ ይለቀው ጀመር። ወሬ አዳማቂው የመጀመሪያውን ተወና ወደዚያ ግር አለ። ወዲያውኑ በክላክሱ ተጠርቶ ከትራፊክ ጽ/ቤት የተላከ ይመስል ኃይለኛ ዝናብ መጣል ጀመረ። ሰው ሁሉ ሲበታተን አራቱ መኪናዎች ብቻ ቀሩ። በኋላ እንደ ሰማሁት አንድ የትራፊክ ሞተር በዝናቡ መሐል ደርሳ ገላገለቻቸው አሉ።

የትራፊክ መብራት በየአስፈላጊው ስፍራ የቆመው መኪኖችን ለማስተላለፍ ብቻ ሳይሆን እግረኖችን ለማቋረጥ ለመርዳት ነው። ታዲያ አንዳንድ ሰዎች ባለ ማወቅም ሆነ በመጠጥ ኃይል ቀዩ ሴብራ እንደ ይባስ ብሎ ደሞ ማቋረጥ ጀምረው መኪኖቹ በረድፍ ሲጎርፉ ግራ ተጋብተው እንደ ሐውልት ባሉበት ቆመው

ይቀራሉ። በዚህ ላይ በሐሳብ ተውጦ ብቻውን የሚነጋገር ኮቱን ካልጎተቱት ዘወር እማይል እግረኛ የጀሮ መነጽር በተሠራ ያሰኛል። «እኔን ድጦ የት ሊገባ» -- እንዲህ ያለው ግድ የለሽማ መሐል መንገድ ላይ የጫማውን ክር ለማሠር ይቃጣዋል። ከፍቅረኛቸው ጋር ሊያቋርጡ ሲሉ እለፉ ብለው መኪናቸውን በሚያቆሙበት ጊዜ በቅናት እሚያኮርፉ ወንድ እግረኖች መኖራቸው ከአንዳድን ባለ መኪኖች ይነገራሉ።

መኪና መንገድ ስለ ማቋረጥ ከትራፊክ ፖሊስ ጽ/ቤት በየጊዜው ትምህርት መስጠቱ ይታወቃል። ምን ያህሉ እግረኛ ሰምቶ በሥራ ላይ እንደሚያውለው አላውቅም። እንዳላወቁ ሆነው ወይም በግድለየሽነት ደንቡን የሚጥሱ - ለምሳሌ መኪና እሚገጩና በገዛ ጥፋታቸው ከሳሽ የሚሆኑ፣ በል ሲላቸውም መንገድ ላይ ተኝተው እንደ አደባባይ ካልዞራችሁኝ እሚሉ መኖራቸወ አዲስ ነገር አይደለም። ምናልባት ለነዚህም ከባድ ዝናብ ሳያስፈልጋቸው አይቀርም!

# ነጋዴዎች

አንድ ገበሬ ከባላገር አዲስ አበባ ለጉዳይ መጥቶ ነጋዴ ወንድሙ ዘንድ ያርፍና አስራ አምስት ቀን በእንግድነት ይቀመጣል። ወንድምየውም ሳይሰለች በጉን እያረደ ሲያስተናግደው ቆይቶ በመጨረሻ ወዳገሩ መመለሻው ሆነና ለመሄድ ሲነሳ ውለታው በጣም ስለ ከበደው፣ «ያደረክልኝን መስተንግዶ ምንጊዜም ልመልሰው አልችልም። ሆኖም ትንሽ እንኳን ደስ እንዲለኝ ደከምኝ ሳትል ስትጥረበረብልኝ ሰሰነበተች ባለቤትህ አንድ መታሰቢያ እንድሰጣት ፍቀድልኝ» ይለውና ሱቅ ውስጥ ከተሰቀሉት ጃንጥላዎች አንዱን እንዲሸጥለት ይጠይቀዋል። እንጋዴውም ሳያመነታ፣ «ለገበያተኞቼ ሃያ ብር የምሸጠው ጃንጥላ አለ፣ አንተ ግን በአሥራ አምስት ብር ውሰደው» ይልና ይሸጥለታል። ሰውዬውም ገንዘቡን ከፍሎ ጃንጥላውን ለወንድሙ ሚስት ያበረክትና ደህና ሁኑ ብሎ ወዳገሩ ይሄዳል። ከሦስት ወር በኋላ እንደገና አዲስ አበባ ይመጣና እዛው እወንድሙ ቤት ያርፋል። ታዲያ በአጋጣሚ አንድ ሌላ ዘመዱን አግኝቶ በወሬ ሬ የጃንጥላው ጉዳይ ይነሣና የዋጋውን ነገር ሲጨዋወቱ እርግጠኛ መሸጫው አሥራ ሁለት ብር ብቻ መሆኑን ይነግረዋል። ገበሬው ይኸን እንደሰማ ነገሩ ይከነክነውና አላስችል ስላለው፣ «የሃያ ብሩን ጃንጥላ ቀንሼልሃለሁ ብለህ በአሥራ አምስት ብር ሸጥክልኝ። አሁን ግን ሰሰማ በየሱቁ በአሥራ ሁለት ብር ይሸጣል አሉ። እውነት ነው?» ብሎ ይጠይቀዋል። ያኛውም፣ «አዎን» ይለዋል። «ግን ለምን እንዲህ አደረግኸ?» ነጋዴውም ፈገግታውን እያሳየው፣ «መቸም ያለፈ ነገር ነውና እውነቱን ልንገርህ። ለባለቤቱ አስበህ መታሰቢያ በመስጠትህ አመሰገንኩህ። ሦስቱን ብር ያተረፍኩት ግን የሷ ምስጋናና ምርቃት ሲደረስህ የእኔ የእናትህ ልጅ ምን ይቅርብህ ብዬ ነው» ሲል መለሰለት ይባላል።

ቆሎ እያዞሩ ከሚሸጡት፣ ቃሪያ ሽንኩርትና ድንች የመሳሰሉትን ከሚደረድሩትና መጻሕፍትና አነስተኛ ጨርቃ ጨርቅ ይዘው በየቡና ቤቱ «ታዲያስ» ከሚሉት ጀምሮ በመለስተኛ መደብር እስከሚቸረቸሩት ከዚያም አልፎ ሸቀጣ ሸቀጦችን በከፍተኛ ችርቻሮ ወይም በጅምላ እስከሚያንቀሳቅሱት ድረስ ያሉት ነጋዴዎች በየጉልቱ በየኪዎስኩ፣ በየአዳራሹ ዋና ዋና መንገዶች ባሉበት አካባቢ በተለይም በመርካቶ እየተዘዋወርን ብንመለከት በማትረፍ ዓላማቸው የሚመሳሰሉ፣ በአሻሻጥና በማግባባት ዘዴያቸው ግን የተለያዩ ደረጃዎችና የቋንቋ አጠቃቀም ያሏቸው ሆነው እናገኛቸዋለን።

ንግድ የራሱ ሰፊ አለም እንዳለው ሁሉ የነጋዴም ዓይነት እንደዚያው ነውና ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ አንዳንድ ሁኔታዎችን ለማየት እንሞክር። መጽሐፍና የሕፃናት ጨርቃ ጨርቅ እያዞሩ የሚሸጡ «የእለት» ነጋዴዎች የአሻሻጥና የማግባባት ዘዴ ከላይ ከጠቀስኳቸው ሁሉ በጣም አነስተኛ ነው። ከመራቀቅ ደረጃ ደርሶ ሳይወዱ የሚያስገዛ አይደለም። እንዲያውም ዘዴ የላቸውም ለማለት ባይቻልም በብዛት ስለሚሰማሩና ድንገት መጥተው በመገተር የሚሸጡትን ነገር ለማሳእይት ዓይን መደንቀል እስኪቀራቸው ድረስ በጃቸው ስለሚዘረጉ ያሰለቻሉ፣ የእረፍት ጊዜ ደንቃራም ይሆናሉ። መሸጫ ቋንቋቸው «ታዲያስ» ከሚለው ቃል አያልፍም። ማናደጃ ቋንቋቸውግን ብዙ ነው «በሉ ርስዎ ተናገሩ፣ እሺ ስንት ይወስዳሉ ዋጋውን እዩት፤ ይኸውልዎት፣ የርስዎን ደሞ ተናገሩ ስንት አሉ? - ምናለ የበኩልዎን ቢናገሩ? ይኸን ያህል በሉና ገምቱ......» እያሉ ይነዘንዛሉ። በዚያ ላይ ዕፅ አሽትቱ እያለ አስማት እንደሚደግም ጢአምም አባጥ ጠንቋይ ዓይናቸውን እያንበላጠጡ መጽሐፉን ዓይን ሥር አስጠግተው ያወዛውዛሉ፣ የሕፃናት ጨርቃ ጨርቅ የያዙም ከሆኑ፣ «እስቲ እሱን ሹራብ» ከተባሉ በብላሽ የሚሰጡ ይመስል ጣል አርገው ያልፋሉ። አይስማማኝም ብሎ ገዥው ሲመልስላቸው «ይኸው አለ ከፈለጉ - ደሞ - የዚህን ዓይነትስ? ይቺ ቢጫዋ አትሆንም› አሁንስ?» በማለት ያለ የሌላውን ልብስ እየጎለጎሉ ልብ ያውቃሉ። አሥር አሥራ አምስቱን የልብስ ዓይነት በነበረበት ቦታ በረድፍ መልሰው ወዲያው መልሰው ወዲያው ሲያስቀምጡት ፍጥነታቸው ያስገርማል። በማይገባቸው ነገር ጥያቄና አስተየት አቅራቢ ሲሆኑ ግን ያበሽቃሉ።

«ይቺ ነች ለሱ ጥሩ» እያሉ ስለማያውቁት ሕፃን ፍላጎት መቀባጠራቸው ምን ይባላል!? ታዲያ ከጠባያቸው ሁሉ ችኮነታቸው ጐልቶ የሚታይ ቢሆንም በሚያዘወራቸው አካቢዎች ያሉትን ሁኔታዎች የመረዳት ችሎታቸው የሚደነቅ ነው። ለስፍራው እንግዳ የሆነውን ሰው ባንዴ ይላያሉ፣ እንደነሱ የንግድ ችሎታም ባይሆን ዋጋ የመተመን ዝንባሌ ያለው ገና ሁለት ሦስት ቃል ወርወር ሲያደርግ ያውቁታል። አብዛኛውን ጊዜ በትላላቅ ጠጅ ቤቶች ስለሚውሉ አንድም ቀን የማያስታጉሉትን ጠጪውች ከነስማቸወ ያውቋቸዋል። የሆነ ያልሆነውን ልብስ ለልጆቹ ገዝቶ በየኪሱ እሚወታትፈውን የጠጅ ቤት ደንበኛ፣ ሁልጊዜ እሚጠጣውን ከሚመጥነው ሳርያን ኮቱን ግጥም አርጎ ቆፎ ባርኔጣውን እንዳደረገ ሪዞን እየገመደ ከጣራው ጋር በዓይኑ እየተነጋገረ መለኪያ እሚመጥነውን በሰዓቷ ገብቶ በሰዓቷ የሚወጣውን ይለያሉ።

የቆሎ አዟሪዎች የመሸጫ ቋንቋ ቆሎውን ማሰየት ነው። የቡና ቤቶችም ሆኑ የጠጅ ቤት ጠጪዎች መተከዣ ዓይነት ስለሚጠቀሙበት፣ ለአጣጪነትና እርስ በእርስ ተገባብዞ፣ ለመጨዋወት ስለሚረዳቸው በገዛም ላዩ ሻጮቹ ልጆች የደስ ደስ ፈገግታ እያሳዩ ሞቅ ያለውን ሰው ልጆቹን ስለሚያስታውሱትና ሆድ ስለሚያባቡ አብዛኛውን ጊዜ የቆሰሎው ገበያ የደመቀ ሆኖ ይታያል። አልፎ አልፎ መስፈሪያውን ቆርቆሮ ጠረጴዛው ላይ ቁጭ ከማድረግ በስተቀር ቆሎ ሻጮች አይነዛነዙም።

ቃሪያና ሽንኩርት ድንችና የመሳሰሉትን ደርድረው የሚሸጡት ደግሞ ቁጭ ብለው የሚመጣውን ገበያተኛ መጠበቅ እንጂ የመግባባት ሁኔታ አይታይባቸውም። እነዚህ ደርባባ የዕለት ነጋዴዎች መካከል ጥቂቶቹ ልጅ እግሮች ሲሆኑ አብዛኞቹ ግን መልኩን ለወጥ ያደረገ የተበሳሳ አሮጌ ጃንጥላ ዘርግተው የሚቀመጡ መፋቂያ እያኘኩ አካባቢያቸውን የሚቃኙ አዛውንት ናቸው።

እስካሁን ከጠቀስናቸው ሁሉ በብዙ መንገድ የሚለዩት የትላልቅ መደብር ነጋዴዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች የመሸጥ ሰፊ ልምድ ያላቸው አክብሮቱንና ትሕትናንውን፣ ሲያሰኛችውም መኮሳተሩንና ኮራ ኮራ ማለቱን ለወጣቶችና ለአረጋውያን ለወንዶችና ለሴቶች እንደ አግባቡ ማዋል የማይሳናቸው ለመግዛት የሚበግረውና የማይበግረውን ዓይነ አዋጅ የሚሆንበትን፣ የማማረጥ ልማድ ያለበትን፣ ገና በአነጋገሩ ወገምገም የሚችሉ ናቸው። ቃላት ሲበዘብት የሚጠራርገውን፣ ዝም ሲሉት ቸል ያሉት ወይም የናቁት የሚመስለውን

በሚያጋዛው ጓደኛው ወይም የናቁት የሚመስለውን በሚያጋዛው ጓደኛ አስተያየት ላይ የሚተማመነውንና የራሱ ምርጫ በልጦ እንዲታይለት የሚፈልገውን በአኳኋኑ ይለያዩ። በተለይ ጮሌዎቹማ አንድ ቀን ያጋጠማቸውን ገዥ ድጋሚ እንዲገዛ ለማድረግ ስለ ሥራው ስለ ቤተሰቡ ደህንነት ደጋግመው ሲጠይቁ ካንገት በላይ መሆኑ አይነቃባቸውም። ከሱቃቸው መርፌ ገዝቶ እማያወቀውን ሰው፣ «አምና መጥተህ ነበር» ብለው እዛው በዛው ደንበኛቸው ለማድረግ የማሳውን ጥረታቸውን ሌላ ነው። ጥርብርብነታቸው እንደ ገዥው ማንነት ከጥሩ የአነጋገር ስልት ጋር በሻይ ወይም በቡና ግብዣ ላይ ይጀመርና ገዥው ገንዘቡን ለመክፈል ሲቆጠር ገና እግሩ ከሱቅ ሳይወጣ ትሕትናቸው ያከትማል። ከሁሉም ሲቆጠር ገና እግሩ ከሱቅ ሳይወጣ ትሕትናቸው ያከትማል። ከሁሉም ከሁሉም ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው እንደየ ሁኔታው አንዳንዴ ደግሞ ለንግዱ ትኩረት ያልሰጡ ለመምሰል ደጅ ደጁን እያማተሩ በዛውም ሌላ ገበያተኛ መምጣት አለመምጣቱን እያረጋገጡ ዕቃቸውን ለመሸጥ የሚጠቀሙባት የመግባቢያ ዘዴ ነው።

እስቲ በገዥና በጮሌ ነጋዴ መካከል የሚካሄድ ክርክርና የማግባቢያ ዘዴ ምን ዓይነት ሊሆን እንደሚችል በንግግር ልውውጥ መልከ እንመልከት።

«ሱሪ አለ?»

«የወንድ ነው የሴት?»

«የወንድ።»

«ስንት ቁጥር?»

«ሃያ ዘጠኝ።»

«ይኸው።»

«እንዴ! ይኸ እኮ ሠላሳ ሁለት ቁጥር ነው።»

«አዎን ሠላሳ ሁለት ነው ቁጥሩ አውቄ ገምቼ ነው የሰጠሁዎት።»

«ይሰፋኛል።»

«መስፋትስ ሊሰፋ ይችል ይሆናል፣ ግን ሱሪ ለቀቅ ሲል ነው ጥሩ።»

«ከዚህ ጠበብ ያለ የለም?»

«ጠባቡ ምን ያደርግልዎታል! ጥበብ ያለ ልብስ ከዕድሜዎ ጋር አይሄድም።»

«ምን?»

«ለጨዋ አለባበስ ጠባቡ አይስማማም ማለቴ ነው።»

«እሱ አዎ፣ ግን ይኸ፣ ሰፋ ይቅርብሽ።»

«ሞዴሉ ነዋ ምን እናርገው ጠባብ አይመጣም።»

«አይ እውነቴን ነው ይመኑኝ ምን መስለዎት - ቢመጣም ያልቃል።»

«ለምን?»

«በቃ አለ አይደለም ወጣቶች ቀጫጭኖች ስለሆኑ ባንዴ ይጨርሱታል።»

«እና ሃያ ዘጠኝ ቁጥር የለም ማለት ነው?»

«መኖርስ ነበረ፣ አልቆ ነው እንጂ።»

«ሌላ ዓይነትስ የለም?»

«እናንተ ብቻ ሦስት ደርዘን ይሆናል የሸጥኩት።»

«ሌላ ዓይነት የለህም ወይ ነው እኮ አምልህ!»

«ምን ዓይነት?»

«ቲትሮን መሳይ።»

«ቲትሮን?......ቴትሮን የለም......ፈላጊ የት አለው ብለው ነው በዚህ በብርድ። ክረምት አይደለም?»

«አዎ ክረምቱስ ገብቶአል።»

«መግባቱ ነው! የዘንድሮው ልዩ ነው እንጂ! ኢያዩትም ሰማዩን፣ የሆነ ጭጋግ ይዞታል።»

«እንግዲህ ልሂድ ዝናብ ሳይመጣ»

«ታዲያስ?.......አይሆነኝም አሉ?»

«አይሆነኝም ይቅር!»

«ቆዩ እስቲ እስቲ ወገብዎን እኮ አልለካሁዎትም።»

«ልገዛ ብለካ ምን ያደርግልኛል ብለህ ነው?»

«ዛሬ ባይገዙ ሌላ ቀን መግዛትዎ ይቀራል? እኛ እኮ የዛሬውን አናይም የወደፊቱን ደንበኝነት ይበልጣል። ለራስዎም ቢሆን የወገብዎን ቁጥር ቢያውቁ አይከፉም።»

«በል እሺ ለካኝ።»

«እኮ፣ ኮትዎን ያውልቁ፣ ሹራብዎን ደሞ ወደ ላይ። አ - አዎ....ሆድዎን ለቀቅ እንደሱ......ሠላሳ ከምናምን.......ሠላሳ ተኩል ነው ልበል?.......ኧረ እንዳውም ሳይበልጥ አይቀርም.......«ምንጊዜም ሃያ ዘጠኝ ነው የሚሆነኝ።» «አይ ልክ ነው.....በኔ ይሁንብዎት -- አይ ልክ ነው......በኔ ይሁንብዎት......አይጠራጠሩ......ለምን መሰልዎት ያን ለታ ሲለኩ ሃያ ዘጠኝ የሆኑት.......እርቦዎች ነበር ማለት ነው። ሆዳችን ባዶ ሲሆን የወገባችን ቁጥር ይቀንስ የለም?»

«ኧረ እኔ እርቦኝም አያውቅ።»

«አይ ረስተውት ነው እንጂ እርቦዎት ነበር። የሰው ልጆች ስንበላ መርሳት በሁላችንም ያለ ነገር ነው።»

«ምን ነካህ ሰውዬ......የራሴን ሆድ የማውቀው እኔ አይደለሁም?»

«እሱስ ልክ ነዎት......ከባለቤቱ ያወቀ ምንድነው እሚባለው.....የእኔ ሜትር ግን አያሳስትም......ያውልዎት በዓይንዎ ይዩት ከፈለጉ። የኔ ሜትር ኦርጅናሌ ነው የጃፓን.......ደሞ ከፈለጉ ራስዎ ለኩ።»

«አዎ ልጄ፣ ሠላሳ አድን ይላል። ግን እሚሆነኝ አይመስለኝም። ካልህ ሌላ ስጠኝ......አለዛ ልሂድ ጊዜ አናጥፋ።»

«ከቸኮሉስ ይሂዱ......ጊዜ ወርቅ ነው.....እንዳውም ሌሎች ሱቆች ሄደው ይዩ ዞረው ዞረው ግን መመለስዎ አየቀርም።»

«በል እንግዲህ ብዙ ስላስቸገርኩህ ይቅርታ።»

«አይ ችግር የለም......ችግርስ የለም.......ሥራችን ነው እኮ፣ ምን ሆኑብኝ። «ግን ለማናቸውም ለምን ለብሰው አይሞክሩትም።»

«ምን ዋጋ አለው......ልኬ አይሆንም ስልህ።»

«ካልሆነዎት ይተውታላ......ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል ብለው ነው። ያውልዎት......እዛ ግቡና ለኩት.....መጋረጃ አለ ያውና......ግድ የለዎትም......መስታወትም አለ......ምን አለ በሉኝ......ልክዎ ባይሆን እቀጣለሁ.....ና ማነህ.......ጀማል......አ ጀማል አለካ ባንክ ሄዷል......ተስፋዬ ና አሳያቸው! ሂዱ ግቡ......ጨርቁን ልጁ ይዞ ይመጣል።»

«እሺ እስቲ.......ከሆነኝ ልሞክረው.......(ጥቂት ይቆይና) ያውልህ ለበስኩት......ግን ሰፍቶኛል እንደፈራሁት። »

«ኧረ በጣም ተስማምቶታል!»

«ምን ይስማማኛል......አታየውም?»

«ልክክ ነው ያለው ስልዎት......ማንንም ጠይቁ....በስፋትም በቁመትም ለርስዎ ሲባል የተሰፋ ነው የሚመስለው......እስቲ እንደገና እዩት በመስታወቱ......አበበ የታል......ና ቆሎ በል!.......መስታወቱን አጽዳላቸው......አንዴ ሄደው ይዩት ግድ የለዎትም።»

«ይኸውልህ......ተርፎ አታየውም።»

«ኦ ፓቴሌቴውን ነው አንዴ እሚሉት.....ይጠባላ?! የአንድ ሴንቲ ሜትር ልዩነት እኮ ቀላል ነው። አሁን በደቂቃ እናስጠብብልዎታለን ዋናው ነገር እንኳን ተስማማዎት እንጂ።»

«አይ በሱስ በኩል ቅሬታ የለኝም......ጥሩ ነበር።

«ታዲያስ? እኔስ ያልኩት ይሄን አይደለም?......በተረፈ በራሳችን ሒሳብ ማስጠበቡ የኛ ፋንታ ነው....ምንም አይደል የወደፊቱ ስለሚበልጥ አራት ብር ብንጎዳ ቅር አይለንም.......ደንበኛ ከሚቀየም በሚል መንፈስ ነው። መቼስ ምን እናርግ። ና ካሣ!......ዘበርጋ ሱቅ ወስደህ አስጠብብላቸው.....ሒሳብ በኛ ነው......ብለው......ቶሎ በል ያዝ......በጥሩ ሁኔታ ይሥራ በለው ታዲያ......አረፍ በሉ እዛችጋ። እኪመጣልዎት.....አሁን በደቂቃ አሠርቶ ይመጣል.....ፈታን ነው ልጁ......ለርስዎስ ምን ልስጥዎት እሜቴ? ወንድሜስ ምን ፈለግህ?»

እና፣ ገዥው በብዙ ንግግር ይዳከምና፣ ለማሰብ ፋታ አጥቶ ዓይኑን ፈዘዝ አድርጎ፣ ግራ ተጋብቶ ዝም ብሎ ቁጭ እንዳለ፣ ጮሌው ነጋዴ የያዘውን አጀንዳ ፈጽሞ ይቀመጡ ብሎ በጋበዘው ፎቴ ላይ መቀመጥ አለመቀመጡን እንኳን ለማየት ሳይቸገር ሲያኙጐደጉድለት የነበረውን ቃላትና ፈገግታ ለሌሎች ገዥዎች አዛውሮ ወትሮአዊ ማግባባቱን ሲጀምር፣ ሱሪው ጠቦ ይመጣና በካኪ ወረቀት ትሎ ተጠቅልሎ፣ እጁ ላይ ያርፍና ልብስ ሰፊው በለወጠው ሱሪ ዋጋ ልከራከር ማለቱ በገዛ እጅ ቅሌት ማመጣት ነውና ሱሪው ከተፈላጊው በላይ ቢጠብ፣ ቢያጣብቅ፣ ወይ እንደ በፊቱ ቢሰፋ ወይም ቢጠብ፣ ቢያጣብቅ፣ ወይ እንደ በፊቱ ቢሰፋ ወይም ልክ ሆኖ ኋላ ኪሱ ቢሰወር በፍዝ አደንግዝ ወፍራም የነበረው ጨርቅ ቢሳሳ፣ ድንገት የአንደኛው ጐኑ ቀለም ደብዛዛ ቢሆን፣ ገዥው ምን እንደሚሰማው እንዲያው ዝም እንዲያው ዝም ነው!

# ዕድሜ

በሀገራችን «ዕድሜ መስተዋት ነው» የሚል የቆየ አነጋገር አለ። በልደትና ሞት መካከል መጀመሪያ ሕፃንነት ከዚያ ጉርምስና ወጣትነት አዋቂነት፣ ሽምግልና፣ እርጅና፣ ሁሉም በየተራው ወቅቱን፣ እየጠበቀ ይመጣል። የልጅነት ክፍለ ዘመን በየአጋጣሚው የሚታወስ እንደገጠመኙ ብዛትና ማነስ ጥሩነትና መጥፎነት እንደ ትዝታው ትራትና ደብዛዛነት የሚናፈቅ ወይም የሚዘገንን ሊሆን ይችላል። የአሳዳጊ ወይም የወላጅ ፍቅርን አግኝቶ በተስማሚ አካባቢ ከሚወዱትና ከሚግባቡት ባልንጀራ ጋር ማደግ፣ ሲነጋ መቦረቅ፣ ጀንበሯ ስታዘቀዝቅ ገና ደንገዝገዝ ሲል እበኢት መክተት፣ ሳያስቡ ሳይጨነቁ መተኛት፣ ወፍ ሲንጫጫ መነሣት፣ እንደገና ቡረቃ - ይኸን ይኸን ሲያስቡት መልካም ትዝታው ከልብ አይተፋም። በችግርና መንገላታት በብቸኝነትና ጭቆና ሕመምና ጉስቁልና ማደግ ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ሊሆን ይችላል።

ወደ አዋቂነቱ የሚያሸጋግረው የወጣትነት ዘመን ጉርምስናን በመጠኑ የሚቀላቅል ይሁን እንጂ ከ«ሠርግ ሠርግ» ጨዋታ በደረጃው ከፍ ያለ የሕልም ዓለሙ ዓይነት ምኞት እውነተኛ መልኩን የሚያገኝበት፣ የተስፋ ቡቃያ የሚሸትበትን፣ ልበ ሙሉነት ገኖ ቤተሰብ ለመመሥረት ዓላማን በተግባር ለመተርጐም ይዘጋጁበታል። አካባቢን በሚገባ ማወቅ በጎውን ከክፉ መለየት ይጀመርበታል። የሀገርና የወገን ፍቅር ይጐላበታል።

ከዚህ በኋላ ያሉት ወቅቶች መጃጀት እስኪመጣ ድረስ፣ የቤተሰብና የማኅበረሰብ ኃላፊነትና አመዛዛኝነት ትእግሥትና እርጋት የሚታይባቸው ዕውቀት የሚዳብርባቸውና ብስለት የሚገኝበት ናቸው። እዚህ ላይ በጣም የሚገርመው፣ የመጃጀት አጭር ወቅት ድንገት ሲመጣ ከዓመት ዓመት እየተካበ ተከምሮ የኖረው ሁሉ በአእምሮ ሚዛን መቃወስ ባንዴ ፈርሶ ወደ ሕፃንነት የመመለሱ ነገር ነው። መቸም በዚህ ጊዜ ዕድሜ መስታወት መሆኑ ይቀርና ጭቃ ማቡኪያ ይሆናል። እንዲሁም ሲሆን የሰውን ልጅ በሕፃንነቱ ልዩ መዓዛ ሰጥታ ከማቆንጀት አልፋ ተርፋ የአህያ ውርንጫ የምታሳምረው ተፈጥሮ በገዛ ሥራዋ ላይ አስቀያሚ ሣቋን መሣቅ ትጀምራለች።

በልደትና ሞት መከካል ስድስት ደረጃዎች መኖራቸውን ዘርዝሬ በአጠቃላይ መልካቸው ባጭሩ ለማሳየት ሞከሬአለሁ። አሁን ደግሞ ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ ለኔ ድንቅ ሆነው የሚታዩኝን አንዳንድ የዕድሜ ገጽታዎች አቀርባለሁ።

ዕድሜ በጥቂት ደረጃ ጊዜም መርዘም ማጠር ይለያል እንጂ መምጫና መሄጃው ይህ ነው ተብሎ ተለይቶ የማታወቅ፣ እንደሚያሳስቅ ውኃ ቀስ እያለ የሚወስድ፣ እንደ ንጋት ውጋጋን ሳያስቡት ደራሽ የሆነ፣ ለማንም የማይመለስ፣ ምንም የማይበግረው ኃይለኛ ባላጋራ ነው። ከሞገደኛ ወይፈን ጋር ይታገል የነበረውን ክንድ ያዝላል። በጦር ተወግቶ ፍንከች የማይለውን ጡንቻ ያሚሸሻል፡ አቀበት የሚያፈናጥረውን፣ ጉድባ እሚያዘልለውን፣ ገደል የማያሻግረውን ጉልበት የሚሟል። ገና ሲቆሙ ያብረከርካል። ልራመድ ሲሉ ያንገዳግዳል። እንደ አንበሳ የሚያስገርመውን ድምፅ ሰላላ ያደርጋል። ማራቶንን ድል ያደረገው አትሌት እርምጃውን እየቀጠረ የአስረኛ ፎቅ ደረጃ የሚወጣ ሲመልስ - በሺህ የሚቆጠር እየቀጠረ የአስረኛ ፎቅ ደረጃ የሚወጣ ሲመስል -- በሺህ የሚቆጠር ተመልካች ሲያጨበጭብለት እግር ኳስ ተጫዋች ኳሷን ቀጥ የሚያደርገው ደረቱ ሰምጦ ወገቡ ጎብጦ ከተቀመጠበት ለመነሳት ከዘራ ሲፈልግ -- ብዙ ዓመት የፃፈ እጅ ሲንቀጠቀጥ፣ የስንቱን ልብ አመታት ሲያዳምጥ የኖረ ሐኪም ጆሮ ሲደነቁር፣ ዕድሜ የማያሸንፈው ኃይል የለም። ተፈጥሮ ዳግም ለማትሰራው ውበት እንኳን አይመለስም፣ የለመለመ ቁንጪ አትንቱ ወጥቶ፣ ኩሩ

አንገቷ ተሸብሽቦ፣ ጡቷ ከቦታው ጠፍቶ፣ እንደ እንጨት ደርቃ ፊቷን በነጠላዋ ከለል አድርጋ በአጠገባችሁ ብታልፍ «እድሜ ጨካኝ ነው!» አትሉም?

በሌላ በኩል ካያችሁት ደግሞ እድሜ ሲጋስ የሚሆንበት ጊዜ አለ። ጥሩ የማህበረሰብ ዳኛ ለመሆን የተጣሉትን ለማስታረቅ፣ የተፋትን ለመምከር ትዕግሥትና ጥንቃቄን ለማስተማር ዕድሜ ሁልጊዜም ባይሆን ተፈላጊ ነው። ይህ የሚሆነው ከራስም ሆነ ከሌሎች ስህተት የመማርና ብዙ ከማየት የማወቅ ገጠመኝ ሰለሚኖር ብቻ አይደለም። የማህበረሰባችን ልማድ ለአዛውንቱ የመከበር ፀጋን ስለሚያስገኝም ጭምር ነው። ለዚህ ሁኔታ ድጋፍ የሚሆን ዝግ ብሎ መናገር፣ ያስተሳሰብ ደርባባነት፣ እውነተኛነት፣ የቋንቋ አጠቃቀም፣ ዝምተኛነትና እነዚህን የመሳሰሉ ስጦታዎችም አሉ። ዡርገግ ያለ ሽበት ሳይስቡት ድንገት ከተቀመጡበት ያስነሳል «ኖር» ያሰኛል።

ታዲያ በማበጠሪያ ሽበቱን እያሳመረ አረጋዊ ለመምሰል የሚሞክር አንዳንድ የሸማግሌ አስመሳይ መኖሩም መታወቅ አለበት። ለዚህም እሩቅ ሳትሄዱ ገደል በሚያህል ቁመናቸው ሽበታም ጒፈሬያቸውን ዙሪያውን ተከርክመው፣ በአርበኛ ሞድ ቀጥ አርገው አበጥረው፣ ካስፈለጋቸው ወፍራም የዝናር ቀበቶ ታጥቀው በዛ ላይ ዳዊታቸውን አንግበው በጦር ሜዳ እንደቆሰሉ ሁሉ እንክስ እያሉ በየቡና ቤቱ የሚዞሩትን ለማኞች ልታዩ ትችላላችሁ። ምናልባት በእንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚ የምትጎነጩት ቢራ ሆዳችሁን አባብቶት ወይም በሌላ ምክንያት ዕድሜያቸውን ብትጠይቋቸው እንድታዝኑላቸው አሥሩን ዓመት ጨምረው ይነግሩአችኋል።

በእነሱ ላይ ብቻ ሳይሆን ስራ ለመቀጠር እድሜያቸው ባልደረሰ ወጣቶችና ታሪክ ማጣፈጥ ደስ በሚላቸው ሰዎችም ዘንድ እድሜ ብዙ አድርጎ መናገር የተለመደ ነው። በተለይ ታሪክ አጣፋጮች በጋቢ ላይ ኮፖርት ደርበው ካስክ ባርኔጣውን አድርገው ጅማቱ የረገበ ክራር መሳይ ያንጠለጠሉና ከመደር መንደር በመዞር ሪዛቸውን እያፍተለተሉ ያጠኑትን የታሪክ ዓይነት ከነ ዓመተ ምሕረቱ እየጠቀሱ ሲያወሩ፣ እፊታቸው ቆሞ የሚከራከራቸው አይገኝም። ታዲያ በየጣልቃው «እኔ ያነ አውቃለሁ። ኧረ ጒረምሳ ነኝ! ከነ እገሌ ጋር ውያለሁ። ማለት ይቀናቸዋል። ወይም በአጋጣሚ የአስራ ሁለት ዓመት ልጅ እቅርባቸው ካለ «እሱን አህላለሁ ያኔ አሁን ይኸ ልጅ አያውቅም ትላላችሁ» ይሉና የሚፈሩትን ክርክር በቅድሚያ እያስተማመኑ ያነጋገር ቅመማቸውን በወሬያቸው ላይ ነስነስ ያደርጋሉ። «ኅዳር ማርያም ነው ቀኑ! ሐሙስ

ይሐ ያለፈው ኅዳር!»ወሩና ቀኑን ከነ ዓመተ ምሕረቱ ይጠቅሳሉ። ታዲያ እሚገርመው ጥቂት ቆይተው የራሳቸውን እድሜ ሲናገሩ ማስላት ባለ ማወቅ «ያይን ምስክር ነበርኩ» በሚልበት የታሪክ ወቅት ሳይወለዱ የሚቀሩበት ጊዜ ነው።

የእነዚህ ተቃራኒ የሆኑ እድሜያቸውን የሚያሳንሱ ወይም የሚደብቁ ሰዎች ደሞ አሉ። በአጠቃላይ በአገራችን የተወለዱበትን ጊዜ መመዝገብ የተለመደ አይደለም። እና አቆጣጠሩ አስተማማኝ አይሆንም። ለምሳሌ፣ «የምባቦ ዘመቻ ጊዜ ጣሊያን ሲገባ የኅዳር በሽታ ጊዜ እገሌን አህላለሁ ለትዳር ደርሻለሁ» በሚል ዓይነት አቆጣጠር እርግጠኛውን ማወቅ አይቻልም። ይሁን እንጂ «ስንት ዓመትሽ ነው» ስትባል «የመንግሥቱ ነዋይ ግርግር ስንት ዓመት ሆነው?» ብላ፣ «ሃያ አንድ» የሚል መልስ ካገኘች በኋላ «ያኔ አልተወለድኩም» ያለችው ወጣች የተሳሳተች እንዳይመስላችሁ።

በዚህ አጋጣሚ አንድ የሲኒማ አዘጋጅ «እንዴት አድርገህ ነው የተዋናዮችህን ትክክለኛ ዕድሜ ማወቅ የምትችለው?» ሲሉ ጋዜጠኞች ጠየቁት። ሰውየው ጥቂት አሰበና፣ «በጣም ቀላል የሆነ ዘዴ እጠቀማለሁ» አላቸው። «እንዴት» ቢሉት «መጀመሪያ ተዋናይቱን ስንት ዓመትሽ ነው ብዬ እጠይቃታለሁ። ቀጥዬ ጓደኛዋን

ስንት የሚሆናት ይመስልሻል እላታለሁ። ከዚህ በኋላ ሁለቱን ደምሬ ለሁለት አካፍላለሁ።» ሲል መለሰላቸው ይባላል።

በአንዳንድ ሁኔታዎች ጡረታ ላለመውጣት ሲባል መቼም ማስረጃ አይገኝም በማለት ዕድሜ ይቀነሳል። «ገና ብዙ ዓመት እኖራለሁ» በሚል ራስ ማታለልና ህይወት ማባበልም ይደረጋል። አብዛኛውን ጊዜ ግን «ሽማግሌ» ወይም «አሮጊት» ላለመባል ከጓደኛ በታች ሆኖ ላለመታየት በውበት ደረጃ «ያው እንደ ዱርዬ ነኝ» የሚል ስውር መልእክት ለማስተላለፍ ሲባል የሚደረግ ነው። አለበለዚያማ የመጀመሪያ ልጅን «እህቴ ነች» ማለት፣ ወጣት ሳይሆኑ ወጣት ፊት «ልጅነቴን ይቅጨው» ብሎ መማልን ምን አመጣው? ከገጠር በአሥርና በአሥራ አምስት ዓመት ዕድሜ መጥቶ ከሰባት ዓመቱ ከተሜ ጋር አብሮ ተምሮ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ጨርሶ ሲጠየቁ፣ «የትምህርት ቤት ጓደኛዬን አታይም!» ማለትስ?

የዕድሜ ነገር አንዳንዴ ሊገመት ቢችልም የዚያኑ ያህልም የሚያሳስትበት ጊዜ አለ። አንዳንዱን ቁጭ ብሎ ስታዩት ግንባረ ኮስታራና ሽብቶ መላጣ በዚያ ላይ ትልቅ ጢም ያለው ሆኖ «ጠና ያለ ነው» ብላችሁ ስታስቡ ድንገት ብድግ ብሎ በቅልጥፍና ሲራመድና ሲቀርባችሁ ልጅ እግር ሆኖ ታገኙታላችሁ። አንዳንድ በቅርበትም ቢሆን ስታዩት ጸጉሩ በመላጊያ ቢሉት ፈቀቅ እማይል ዓይነት ሆኖ፣ እንደ ኩላሊት ልስልስ ያሉት፣ የተላጩ ወዛም ጉንጮቹና ክብ ፊቱ የዓይኖቹ ብርሃን ፈጣንነታአቸው ደሞ ፍልቅልቅነቱና ሳቂታነቱ ሁሉም ተደማምሮ ልጅ አስመሰሉት ተነሥቼ ልሂድ ሲል ግን እዛው በዛው ተደማምሮ ልጅ አስመስሎት ተነሥቼ ልሂድ ሲል ግን እዛው በዛው ሥርቼ ተግተርትረው እግሮቼ ሲንቀጠቀጡ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ዕድሜው ሲጨምር ታዩታላችሁ።

በተለይ በጸጉር ማስተካከያ ቦታዎች ይህ ሁኔታ አልፎ አልፎ ይታያል። በኔ ግምት ሁልጊዜም ባይሆን የቁመት ማጠርና መርዘም (ከራራነትና ጀውላላነት) ውፍረትና ቅጥነት አለባበስ የሥራ ዓይነት በደረጃው ይለያዩ ለተሳሳተ ግምት ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። ይሁንና በተሳሳተ ግምት ዕድሜ የጨመሩ መስሎ መታየት ዕድሜን ስለማይጨምር ነገሩ ሊከነክን አይገባም። ይልቅስ ሊወገድ የገባው አካል ሁሉን እየተናገረ በገሃድ እያሳየ ለመቀነስ ከንቱ ሙከራ ማድረጉ ነው።

አቶ ሐዲስ አለማየሁ በጻፉት «ፍቅር እስከ መቃብር» በተባለው ልቦለድ ውስጥ የፊታውራሪ አሰጌና የሰብለ ወንጌል ጋብቻ ከቀረ በኋላ አንድ ቀን ጨዋታ ተነሥቶ ሲያወሩ ወይዘሮ ጥሩ ዓይነት የዕድሜ ልዩነት ቁሞ ነገር የሌለው መሆኑን ጠቅሰው በሳቸውና በባላቸው መካከል የሃያ ሰባት ዓመት ልዩነት መሆኑን በኩራት በተናገሩ ጊዜ ፊታውራሪ መሸሻ ተቆጥተው፣ «ቀድመሽ የራስሽን ዕድሜ እወቂ! የሰው ዕድሜ አውቃለሁ ብሎ የማያውቁትን ነገር ለማዋለድ ከመቸኮል የራስን እድሜ ማወቅ ነው። እንዲያው እኮ የዲማውን! በዚህ ብቻ አይምሰላችሁ። በሌላውም ሁሉ እንዲሁም ዝም ብላ ነገር ማባዛት ትወዳለች፣ ሥራዬ ብላ ይዛዋለች። ታዲያ እኮ 27 ዓመት ትላላች እንጂ በመላችን የ25 ዓመት ልዩነት መኖሩን እንኳን እንጃ» ይላሉ።

የፊታውራሪ መሸሻ ስሕተት ለሰብለ ወንጌል ሠርግ እየሰባበሩ እንደገጠሙት ግጥም ከየዋህነት የመነጨ ነው። ወዲያውም የልቦለድ ዓለም ሰው ናቸው። የገሃድ ዓለም ያሉት ናቸው የሚገርሙ። አስገራሚ መልስ ከመስጠታቸው በላይ አስገራሚነቱን ዞር ብለው እንኳን ባለማየታቸው። ለምሳሌ ሰውዬው ሠላሳ ዓመቱ ነው። የሥራ አገልግሎት ዘመኑ ደግሞ አስራ ስድስት። ሥራ ሲጀምር የአስራ አራት ዓመት ልጅ ነበር ማለት ነው።

የሚወዱትን ዕቃ ጥሩነት፤ ወይም ምትክ የማይገኝለት መሆኑን ለመግለጽ «የጥንት ነው! እስቲ ገምት። አያቴ የጠጡበት ሲኒ፣ ቅድመ አያቴ የገዙት ሳጥን» እያሉ የአሮጌ ዕቃ ዕድሜ ሲያራዝሙ የራስን ማሳነስ ምን ይባላል?

ዕድሜ መስተዋት ነው። «የከርሞ ሰው ይበልህም» ጥሩ ምርቃት ነው።

# የዚህ ዓለም ጨዋታ

ይህች አለም መድረክ ናት.
ወንዶችም ሴቶችም የሚተውኑባት።
ሁሉም በትርኢቱ ይገባሉ ይወጣሉ፣
በጊዜያዊ አድማቂነቱ ያንኑ መድረክ ያስውባሉ።
አንዱ ሰው እንኳ በዓቅሙ ባለችው ሕይወት መጥኖ
ጨዋታውን ይጫወታል ለብዙ ትርኢቶች ጊዜውን ሸንሽኖ።
ከዓለም መዝገብም ይፋቃል፣ የሁሉም ወኪል እሱ ሆኖ
የራሱን ያህል ሰባት እጥፍ የዘመን ድርጊት አከናውኖ።

ሼክስፒር /አዝ ዩ ላይክ ኢት/

ሼክስፒር የዚህን ዓለም ጨዋታ በቲያትር መድረክ መስሎ በጥቂት መስመሮች ብዙ ነገሮችን አሳይቶናል። ዋና ዋናዎቹን ለመዘርዘር ያህል......ማስመሰል፣ ለሙብለጥ መጣር፣ በልጦ፣ ለመገኘት ማታላል፣ ለመታለል ጨዋታውን መጫወት። ባለቅኔው ከዚህም በላይ የዓለማችንን የሩጫ ትዕይንት ውጣ፣ ውረዱን የወድድሩን ፍትጊያና ሽኩቻ......ከሰው ልጆች ደካማነት ጋር አያዛመደ በብዙ ቅኔዎቹ ገልጾታል።

የዓላማችን ጨዋታ በሁሉም የምድር ማዕዘን በነጩም በጥቁሩም በዓረቡም በአስኪያዊም፣ በሠለጠነውም ባልሠለጠነውም በለሙትና ባልለሙት አገሮች ለተለያዩ ዓላማዎች በተመሳሳይ ሁኔታና አንዳንዴም መልኩን እየለዋወጠ ይካሄዳል። የሬኔሳንሱ ፈላስፋ ኒኮሎ ማኪያቬሊ «ዘ ፕሪስን» በተሰኘው መጽሐፉ አገር ለመግዛትና በሥልጣን ላይ ለመቆየት የዚህ ዓለም ጨዋታ ምን ያህል አስፈላጊ በሥልጣን ላይ ለመቆየት የዚህ ዓለም ጨዋታ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ይተነትናል። «ከፋፍለህ ግዛ» ከሚለው ጀምሮ የተለያዩ ምክሮችን ለገዥው መደብ ስለሚሰጥ በጥቅሉ ሰዎች ሠይጣን አድርገው ይቆጥሩታል። አሁን አሁን ግን የጥበብ ሰዎችና የታሪክ ፕሮፌሰሮች በዓለማችን ላይ የማይቀረውን ወይም ሊደርስ የሚችለውን ከጥንቱ እውነታ ጋር አያይዞ የተገዥዎችንም ፍጥነትና ሥነ ልቦና ይዞታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የጻፈ የፖለቲካ ፈላስፋ ስለሆነ ዝም ብሎ በደፈናው ጋኔል (ዲያቦሊካል) ተደርጎ መፈረጅ የለበትም.....ሲሉ ይመካከሩበታል። ይሄንን እንደ መግቢያ አድርጌ የማነሣው ማኪያቬሊ በዚህች ጽሁፍ በምሳሌነት ብቅ ስለሚል ነው።

የዚህ ዓለም ጨዋታ የሚጀምረው ከድፍረት ነው። «ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም» የተባለው ድሮ ነው። የዛሬው ሕብረተሰብ ወይም ትውልድ ግን «ጭሱ ባይታይ ደፋሩ ይታያል» ብሎ የሚያስብ ስለሆነ የዱሮውን «ተረት» ሽሮ የራሱን የማይታይበትን መንገድ የሚቀይስ ነው። ለዚህ ግዜና ዘመኑን ቴክኖሎጂውን ፊልሙን ቪዲዮውን.....እና ባጭሩ ፍጥነትና ብልጠት የሚጠይቀውን ሁሉ በትልቅ ግምት ውስጥ በማስገባት የዛሬ ደፋር «ጭስ» የሚለው ቃል መዝገበ ቃላት ውስጥ መኖሩን እንኳን አያውቅም። በግድ ታውቃለህ ብትሉት እንኳን አይገባውም። ዋናው ቁም ነገር «ሕይወት እንዲቀና ተቃንቶም እንዲሰምር የኑሮን ዝግ ዋሻ እንዴት ፈንቅዬ ልግባ?.......» የሚለው ጥያቄ ነው። ይህ ጥያቄ ደግሞ ወደድንም ጠላንም የዓለማችንን ጨዋታ በድፍረት ሀ ብሎ ለመጀመር ይጋብዛል።

ድፍረት ወይም ደፋርነት ለዓለማችን ጨዋተኛ የመጀመሪያው መመሪያ ይሁን እንጂ ሌላውን ወይም ሌሎችን ሳየምስል ብቻውን ለተግባራዊነት የሚበቃ አይደለም። «ሌሎቹ ምን አደረጉ? ሥልጣንም ይሁን ሀብት ወይም የሕብረተሰብ ተሰሚነት እንዴት እዚህ ላይ የሚለውን ጥያቄ ይዞ አቅዶ መሄድ መቻል አለበት። እዚህ ላይ ሌሎችን መምሰል ብቻ ሳይሆን አስመሳይነትም ከአጋፋሪዎቹ መቅመስና መልመድ መለማመድ አለበት። ማኪያቬሊ «አንድ የአገር መሪ ከሱ በፊት የነበሩት ምን እንዳደረጉ እንዴት እንደተሳካላቸው ወይም እንደከሸፈባቸው ማየትና ማጥናት አለበት» እንዳለው መሆኑ ነው።

ለዚህ ዓለም ጨዋታ ከማንም በፊት ቀድሞ ትልቁን የምክር ሚና ያስቀመጠው ማኪያቬሊ «ቀስ በቀስ እንቁላል ዶሮ ይሆናል» የሚለው ተረታችንን ሳይሰማ መሞቱ ጥሩ ይመስለኛል። ቢሰማ ኖሮ......«ከሆነ አጋጣሚ ዶሮ መሆን ባይችልም ከዐላማህ ውልፍች አትበል፣ ዶሮ የሚመስል ሥጋ ብታቀርብለት ሕብረተሰቡ አሜን ብሎ ስለሚቀበልህ ሥጋ አይግባህ......» ሲል ይችል ነበር ብዬ እገምታለሁ። «ውሸት መስማት የሚወዱ ሰዎች እስካሉ ድረስ እየዋሸህ ግዛቸው» የሚል ፈላስፋ የሚጠላም ቢሆን የዓለማችንን ሐቅ ፍንትው አድርጐ መናገሩ የሚካሄድ የሚጠላም ቢሆን የዓለማችንን ሐቅ እየዋሸህ ግዛቸው» የሚል ፈላስፋ የሚጠላም ቢሆን የዓለማችንን ሐቅ ፍንትው አድርጎ መናገሩ የሚካድ አይደለም። ላለማችን ጨዋታ ፈር የቀደደ በመሆኑ ለተንኮታኮተው አጽሙ ይቅርታ ባደርግለት ደስ ይለኛል። እውነተኛ ፈላስፋነቱ ግን አከብርለታለሁ።

ያገራችን ጨዋተኛ የብልጠት ተሰጥኦ በተፈጥሮው ባይኖርውም ከአካባቢው ከታላላቆቹና አርአያ ይሆኑኛል ከሚላቸው ሁሉ አሰባስቦ መማርና ተግባር ላይ ማዋል የሚለምደው ገብዘብ ለማግኘት ከዚያም ቀጥሎ ለሚመጣው ጥሩ ጥሩ ነገር እንደምንም ዜጋ በሼክስፒር መድረክ ቀርቦ ፋንታዬን እፈልጋለሁ ማለት ሲጀምር ነው። በመሠረቱ ግዜያዊ ይሁን ራቅ ያለ አመለካከት ሊኖረው ይችላል። መጽሐፍ ያነባል ግን እንዳትሉኝ ማንበብ ስለማይችል ወይም የሚያነበው አጥቶ አይደለም። ዓላማው ህብረተስቡን አታልሎ ከመጠቀም ብዙ እርቀ ስለማይሄድ በመሆኑ እንጂ የዘመናችንን ሰይጣናዊ እንቅስቃሴዎች የሚያስተጋቡ ልቦለዶችን ትኩረቶች ሰጥቶ በእቅድ ዚቆዝምባቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ አካባቢዎች ሁሉ መቆጣጠር ይችል ነበር።

ለዚህም ዓለም ጨዋታ ድፍረት፣ መምሰልና ማስመሰል፣ ህብረተሰቡን ማወቅና ዓላማ ላይ ማነጣጠር እንዴት አስፈላጊ እንደሆኑ ተመልክተናል። ከነዚህ ጋር......ገንዘብ፣ ክብር፣ ፍቅር፣ ዝና፣ ከተቻለም ስልጣን.......አብሮ መሄድ እንዳለበት ግልጽ ነው። በዚህ ላይ ደግሞ ዝንት ዓለም የተገነባውና ፈርሶ የማያውቀው «ውሸት» የተባለው ሐውልት አለ። ታዲያ ይህ ሁሉ እንዴት ይሳካል? ሳቢ ኃይል (ወይም መስህባዊነት) ይባላል። ፈረንጆቹ ካሪዝማ የሚሉት ነው። ለምሳሌ ለብዙ ሰዎች ንግግር ሲያደርግ በእጆቹ መወናጨፍ በዓይኖቹ መንቀልቀል በትከሻውና በጭንቅላቱ መወዛወዝ አፍ የሚያስከፍት.......በል ሊለውም ከመቀመጫ የሚያሥነሣ፣ እናም በሰላ አንደበቱ «ለካ ይሄም ነበረ?!» እያሰኘ......ሲፈልገው እዛው በዛው

የሚያፍነከንከ......ሲፈልገው እዛው በዛው የማያስለቅስ ሰው ካሪዝማ አለው ይባላል። በጣም አናሳና ጊዜያዊ ደረጃ የሚሠጠው ቢሆንም ሴትን ልጅ በፈገግታው በቁመናውና በሰባኪነቱ የሚያምር ሆኖ ዓይኗን እስክታንሸዋርር ድረስ ማማለል የሚችልም የሚያምር ሆኖ ዓይኗን እስክታንሸዋርር ድረስ ማማለል የሚችልም ሰው ካሪዝማ አለው። ሕብረተሱን ወይም የአካባቢውን ሰዎች እንዲያ የሚያደርግ ሰው ግን ከነዚህ ሁሉ ይለያል። የዚህን ዓለም ጨዋታ የሚያውቅ ነው ማለት ነው።

ካሪዝማ ማለት የመሳብ ኃይል ማለት ነው። ይሄ ችሎታ ያለው ሰው በነገሩ ሁሉ አስቦበት፣ ጊዜና አካባቢውን በመጠቀም አርቲፊሻል ሁኔታዎችን የማፈጥር ከአለባበስ ጀምሮ አካሄዱን ከተጠና ፈገግታ ጋር እያቀናጀ.....ጊዜው የሚጠይቀውን «ዘመናይነት» በማስመሰል ጥበቡ እንዲታይ አድርጎ ሌሎችን በቁጥጥሩ የሚያውል ነው። ይሄንን ዓይነት ሁኔታ በመሠረቱ በሥራ ፈቶች፣ እድሜ በከዳቸውና ትናንት እነዲህ ነበርኩ በሚሉ ሰዎች፣ የዝና ባቡር ጥሏቸው ሄዶ ባዶአቸውን በቀሩና......በለማኞች ሳይቀር ታያላችሁ። በመሆኑም ጠብቆ ባልታሰበም ቦታ እንደሚኖር መታወቅ አለበት። ሕብረተሰብ ሲባል እንደምን ተሐዋሲያን ሁሉ ነገር ይነካካዋልና!

ለዓለማችን ጨዋታ አስፈላጊ የሆነው መስሕባዊነት የትሪያንግል ወይም የፒራሚድ ቅርፅ እየሰራ የሚሄድ ነው። ነገሩ ሁሉ ከዚህ ይጀምራል። ለምሳሌ በህንፃ ግንባታ ቆፋሪውን ድንጋይ አቀባዩ ጠራቢው ግንበኛው ፎርማኑ መሀንዲሱ ኮንትራክተሩ ባለቢቱ.....እያለ ወደ ላይ ሲወጣ.....የህሊናው ኩራት የማንነት ጥያቄው እበልጣልሁ የሚለው ሥነ - ልቦናዊ እርካታ......ሁሉ ጊዜውን እየጠበቀ ይመጣል። ቆፋሪውና ድንጋይ አቀባዩ የደላቸው መስለው በጠላና ጠጅ በኢት ሲምነሸነሹ ኮንትራክተርና ባለቤት ክብር በሚጠበቅበት ቦታ በውስኪና ጮማ የራሳቸውን የብልጠት ጨዋታ ይጫወታሉ ፡

ለመሆኑ የዚህን ዓለም ጨዋታ የሚያውቁና ለዓለማቸው ተነሳስተ ተግባር ላይ የሚያውሉ ሰዎች ምን ዓይነቶች ናቸው? ብዬ ሳስብ ጌጣጌጡ ሽቶው፣ ዶይድራንቱ ውድ የእጅ ቦርሳው የሚያብረቀርቀው ሰዓት ከብይ የሚበልጠው የጣት ወርቅ ይታየኛል። ሶስት የብዕር ዓይነቶች የተደረደሩበት ዘመናዊ ኮት አስፋልት የሚገላምት ጫማ፣ ፀጉር አይቶ የማያውቅ ጉንጭና በቆሎ እሸት የሚያስንቅ ጥርስ......ሌላው የምናብ ምልክት ይሆንልኛል። ታዲያ በዚህ ሁሉ ካሪዝማ አጃኬ ባልና ሚስት አስታርቆ በከፍተቱ መግባት.....መጽሐፍ ቅዱስ ለመታሰቢያ ሰጥቶ ከዐሥሩ ትዕዛዞች መሀል ቢያንስ ሁለቱን መጣስ - እንዴት ሊታሰብ ይችላላ?! ቸር፣ አሳቢ፣ መካሪ፣ አልሁልህ በይ፣ ለችግር ደራሽ፣ አድናቂ ሆነው ከቆዩ በኋላ.....በዘመናችን ቋንቋ «የጥሩ ወዳጅነት ማኖ አስነክቶ»..... እምነትና ክብርን ለውጦ ተቃራኒ መሆን እንዴት የእውን ሊመስል ይችላል?!

ምንም ይሁን ምንም የዓለማችን ጨዋተኛ ለዓለማው የሚያግዙት ብዙ ነገሮች አሉት። መነሻ ገንዘብ የመጀመሪያው ነው። ከገንዘብ ቀጥሎ ቴሮዞ መመልመል ይመጣል። በአመዛኙ ይህንን ሚና ከጓደኛም ይበልጥ ሴቶች ይጫወቱታል። ዋናው አጋዥ ኃይል የሚሆንለት ግን ፎቶ ግራፍ ነው። ፎቶ ግራፍ በጥሩ አለባበስ ያሸበረቀውን መዳብ ያጠለቀውን ወርቅ እያስመሰለ፣ ቦርጫሙን ሸንቃጣ መልከ ጥፉውን ቆንጆ እያደረገ፣ ከንፈርና አፍንጫ እያስተካከለ......የሌለ ካሪዝማ እየፈጠረ........የአታላይ ባህሪ ያጎለብታል። ፎቶ የሰው ፊት ለመለወጥ ብቻ ሳይሆን ነጭ ወረቀትን መሀረብ አድርጎ ስለሚያሳይ ለእነዚህ ሰዎች ጨዋታ ጠቃሚና አቋራጭ ዘዴ ነው።

ለፎቶ ግራፍ የሚባለው ጥበብ በብዙ መልኩ ሲታሰብ የጠቃሚነቱን ያህል ለዚች ዓለም አስገራሚ የጨዋታ መድረኮች ብዙ አስተዋጽኦ ሲያደርግ ኑሯል። ንጉሶች፣ ንግሥቶች በልዩ ልዩ አብረቅራቂ ሜዳሊያና ቁልፉ ቁልፎች ወርቅ ቅብ ሠንሠለቶችና ጌጣጌጦች ተኮፍሰው ተቆጥተው ይነሣሉ። ዓለማችን ከአጼዎች

ሙሉ በሙሉም ባይሆን ከተገላገለች በኋላ የመጡት ደሞ ጺድቅና ፈላስፋ በሚያስመስል ካሪዝማና ሙስታሽ ታጅበው «ከእኔ ትእዛዝ አታመልጡም» የሚል ዓይነት ድባብ ተጐናጽፈው ይቀረጻሉ። በተዋረድ የሚገኙት ባለሥልጣኖች ደረጃቸውን እየጠበቁ ታሪካቸውን ያሣምራሉ። በእንዲህ ዓይነቶቹ ቀረጻዎች መሥህባቸው (ካሪዝማቸው) ትኩረት የሚያደረገው በሥነ ልቦናዊ ማስፈራራትና አስተዋይ ሆኖ በመታየት ላይ ነው።

ፎቶ የሚያመነጨው ካሪዝማ ማንንም አድናቆትና ክብር ፈላጊ አሣፍሮ አያውቅም። የላላቅ ቤተሰብ አንጋፋ አባቶች የአልማዝና ወርቅ ባለቤቶች፣ የፖለቲካ አቀንቃኞች.......ተጠቅመውበታል። የሃይማኖት አባቶች ከዚህ በገነነ ሁኔታ ለመቀረጽ በላያቸው ላይ የሚሸከሟቸው ነገሮች ደረታቸው ላይ ከሚንዠረጋገው ፂምና ጥቁር ኮፊያ ጋር ተዳምረው የሚሠጧችው ግርማ ሞገስ ከቶውንም ምድራዊ ፍጡራን አያስመስላቸውም። የፎቶ ካሪዝማ ጨካኙን ደግ ተንኮለኛውን ብሩክም ደደቡን ዓዋቂ ንጹሐን ወንጀለኛ አስቀማኢይውን ቆንጆ ማድረግ ሳያንሰው ሽማግሌና አሮጊቶችን ወጣት በማስመሰል በሰብእና ላይ ከንቱ ደስታና አስቀያሚ ሽንገላ የሚያመልጡት ዱሮ ዱሮ በሥዕል እንደሚታዩት ፈላስፎች ጠውላጋ ፊታቸውንና የተንጨባረረ ጸጉራቸውን ለመለወጥ ከቶውንም ሳይቸገሩ ተፈጥሮአቸውን ሳያስቡ ኩስስ ብለው የሚነሡት የሳይንስና የጥበብ ሰዎች ብቻ ናቸው።

# ጩኸት

ጠዋት የሚጀምረው በጩኸት ነው ቀኑ ሲታጀብ የሚውለው ከጩኸት ነው። ምሽቱ ለሌቱ ቦታ የሚለቀው አየሩን በጩኸት ሲያተራምሰው ከቆየ በኋላ ነው። ጩኸት ባደጉትና ባላደጉት አገሮች ያለ ቢሆንም መነሻው ይለያያል። በምዕራባውያንና በአውሮፓ ታላላቅ ከተሞ ለማረፍና ለመነሣት ወረፋ እሚጠብቀው አይሮፐላን ሰማዩን እየሠንጠቀ ነጐድጓዱን ይፈታተናል። አንደኛ ታክሲዎች ሰውና ምርት ለማጓጓዝ ተሠልፈው ተራ የሚጠብቁት መርከቦችና ጀልባዎ ባሕሩን ሲቀዝፉት ሞተራቸው የሚተፋው ድምፅ ከአየሩ ጋር ይደባለቃል። መኪኖች እንደ ጉንዳን ተከታትለው ሲበሩ ጥሩምባቸው በሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎች ዙሪያ እያንባርቀ ሲያስተጋባ.......የጩኸቱን መጠን መገመት ይቻላል። ቴክኖሎጂ ያመጣው ነውና መቻል ነው። ሆኖም በነዚህ አገሮች ጩኸ ያደከመው ስውነት ጠግቦ ሲያድር ለጠዋቱ ሥራና ውጣ ውረድ ስለሚዘጋጅ በጥሩ ዓላማና ኑሮ ጩከትን ይቋቋማል። እኛን በመሠሉት አገሮች ግን ሁኔታው የተለየ ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ ጩኸት የሚበረታው በመርካቶና በአውቶብሶች መናኸሪያ አካባቢ ነው። የመኪናው ጥሩምባ የአውቶብሱ የታክሲ፣ ወያላው የማያቋርጥ ድምፅ ከሙዚቃ ቤቶች ድብልቅልቅ ጩኸት ጋር ሲዳመር መንገደኛውን ማደናገር ብቻ ሳይሆን ጆሮ ያሳምማል። የመርካቶ እንግድነት ቢሄድ የለመደውን ስለሚያጣ አንዱ ቀን ሁለት መስሎ ሊረዝምበት ይችላላ።

የሰካራሞች ሴተኛ አዳሪዎች ጐዳና ተዳዳሪዎች.....ጩኸት በመርካቶ ጨለማ መስማት የለመደ ጆሮ ጭር ጭር ባለ አካባቢ እንቅልፍ አያስተኛም።

ቡና ቤቶች እንደ ሙዚቃ ቤቶች የዘፈን ጩኸት ምልክታቸው ነው። ችግሩ ለሚገባው ደንበኛ ራስ ምታት ይሁን እንጂ እዚያ ለሚሠሩት እንደ በርበሬ ወፍጮ ሠራተኛ ተዋህዶአቸው በፍፁም አይሠማቸውም። በተለይ ድራፍት ለመቅዳት የተመደቡ ሰዎች ሙዚቃው በጣም ካልጮኸባቸው ድራፍቱን በፍጥነት

በቅልጥፍና መቅዳት የሚሳካላቸው አይመስለኝም። ቡና ቤቶች ውስጥ፣ በሚያፈልገው አጋጣሚ ቢሆን በሞባይል የሚጠቀሙ ሰዎች ይበዛሉ። ሞባይል ለቁም ነገር የመጥቀሙን ያህል ለጉራም ለፋሽንም ስለሚውል ያለ ካርድ የማይውሉም አይጠፉም። የአንዳንዱ ሰው ድምፅ የጠፋ ጓደኛ ለመፈለግ ከፍ ብሎ የሚለቀቅ ዓይነት ሆኖ በተለይ ምግብ እየበላ ላለ ሰው ትንታ አለማስከተሉ ያስገርማል።

ማንኛውም ነገር በድንገት ሲከሰት ያስደነግጣል። በድንገት ጩኸት ሲደመጥ ግን ይበልጥ ያስደነግጣል። ታክሲ ውስጥ ጉዳያችሁን በጥሞና እያሰባችሁ ስትሄዱ ከኋላችሁ «ሃሎ.....» ብሎ የማያንባርቅ ሰው ያስበርግጋችኋል። ዘወር ብላችሁ ካያችሁት ደግሞ በሕይወቱ ስልክ ደውሎ የማያውቅ ሊመስላችሁ ይችላል። አንዳንዱ ሰው ሞባይሉ ሲጮህ የተቀመጠውን ሰላማዊ ሰው እየረጋገጠና በር የቆሙትን የሚገቡትን.....እየበረጋገደ እድኒ ተዋናይ ወዲያ ወዲህ እየተንጐራደደ በጩኸቱ መረበሽ የለእብትም። ነገሩ በተደጋጋሚ በጋዜጦች ተነሥቷል። ችግሩ ሕግ ይውጣለት የሚባልም ባይሆን አሳሳቢነቱ የሚያጠያይቅ አይደለም።

በአውደ ዓመት ሰሞን ታክሲ ውስጥ የሚጫኑ ሙክቶች ግን በዋጋ ድርድር ካልሆነ በስተቀር ስለ ጩኸታቸው ማንንም አሳስበው አያውቁም። አንድ ቀን ትዝ ይለኛል..... ተሣፋሪዎች በፀጥታ ቁጭ ብለን በምንጓዝበት ወቅት.... ባለቤቱ አፉን አፍኖት የቆየ ፍቅየል ሰውየው ዘንግቶ ለቀቅ ሲያደርገው ከኋላችን ድንገት በኃይል ሲጮህ እንዴት እንዳስደነገጠን እስከዛሬም ይገመኛል። ፍየል ከእንስሳት ሁሉ እንደ ሰው በተለይም እንደታነቀች ሴት የመጮህ ተፈጥሮ አለው። ባለፈው ፋሲካ ወደ ሆቴል የሚሂዱ አራት ፍየሎች (ሁሉም ፈነዱ የደረሱ ሙክቶች) ውይይት ታክሲ ላይ ተጭነው መኪናው ከአውቶብስ ተራ ቁልቁል ሲወርድ እንዴት ሠፈሩን እስከ ሰባተኛ ድረስ በጩኸት እንዳሸበሩት አይረሳኝም። ሁኔታውን ልብ ላለ ሰው ዓይናቸው ወደ መንገደኞች እያጉረጠረጠ «አስጥሉ» የሚል ዓይነት ዑውታ የሚያቀልጡ ይመስሉ ነበር።

የሰው ጩኸት ሳያንስ የቤት እንስሳቱ መጨመር ያስገርማል። ለምሳሌ ድመት ሌላዋ የጆሮ በሽታ ናት። የሠፈሬ ድመቶች በመልክ ማማርም ሆነ በሌሊት ዙረት የሚስተካከላቸው የለም። አይጥ መያዝ ከተዉ ቆይተዋል። የአይጥን ሥራ በመሻማት ግን በየቤቱ እያንጐዳጐዱ ሥጋ ከመሥረቅ አልፈው ተርፈው እህል እየደፉ ሕብረተሰቡን ማበሳጨት ጀምርዋል። ድመቶች በጩኸት ደረጃ ዛሬ አይጦችን በእጥፍ በልጠዋል።

እውነት ለመናገር.....አይጥ የምትረብሸን ድምፅዋን አጥፍታ ነው። ያም ግፋ ቢል እንቅልፍ ነው ያሚያዘገይብን። ድመት ግን.....በቀትር ፀሐይ ጣራችን እንደ ነጐድጓድ እያንጓጓች ጥይት የተተኮሰ እስኪመስለን ድረስ ከባድ ድንጋጤ ላይ ትጥለናለች ፈረንጆች የኛን ድመቶች አገራቸው ቢያስገቡ ኖሮ.....እንዴት ቤት ሊገለብጡና ግድግዳ ሊንዱ እንደሚሞክሩ.....በግብረ ሥጋ ሲማግሩ እዝግናኝና ሰቅታጭ ዋይታና ትርምስ እንደ ሚፈጥሩ....... በመመልከት ስለ እንስሳት የብልግና ወልጀል ቢያንስ ውይይት ሊያካሂዱ የሚገደዱ ይመስለኛል

ከለማዳ እንስሳት ሁሉ ይሻላሉ የሚባሉት አህያና ውሻ ናቸው ይሁን እንጂ፣ እነዚህን እንፈርጃቸው ካልን አህያ ጀርባውንለማከክ ሲገላበጥ፣ ወይም ተፈጥሮ የጣለብትን ፍላጐት የሰው ልጆች ሲከለክሉት......ኡኡ ለማለት ያህል ብቻ እንደሚጮህ እናውቃለን። ውሻም ቤቱና ባለቤቱን ለመጠብቅ ይጮሃል። ድመቶች ግን፣ ከልጅነቱ እንደማልወዳቸው ባውቅም፣ ከጠጅ ቤቶች ጣራ ጀምሮ ግድግዳ እየሸረሸሩ ማውካካትና በአስቀያሚ ድምፅ እየተቀባበሉ መዳራት የሚወዱ......ጩኸት ፈጣሪዎች ናቸው።

የመዲናችንን ጩኸት ከፍተኛ ደረጃውን የሚይዘው ሕግ የሚያውቃቸውና የማያግዳቸው ድርጅቶች አስፋልት እየተከተሉ ከሠፈር ሠፈር እየዞሩ በማይክሮፎን ሲያንባርቁብን ነው። በዚህ ረገድ አንደኛነቱን እስከዛሬ ያልተነጠቀው የአምቡላንስ አገልግሎት ነው።

አምቡላንሶች በሽተኞቻችን ሆስፒታል ለማድረስ አገልግሎት እንደሚሠጡ ብናውቅም፣ አስፈላጊ ባልሆነ ጊዜ መኪኖች መንገድ እንዲ ለቁላቸው ሆነ ብለው ያደርጉታል የሚል ሐሜት ሠምተናል። ብሔራዊ ሎተሪ አስፋልት ከረገጠማ አሮጌ ፎቅ በንዝረት ለመናድ የማይመለስ ዓይነ የእስክስታው አቀንቃኝ ከብሮ ሙዚቃ ሁለት ሶስት ቀበሌ ያዳርሳል። የእስክስታው አቀንቃኝ የሆነችዋ የሎተሪውን ዓርማ ወፍዋን የምታክለው ልጅ እንኳ ብዙ ሜጋ ቶን ድምፅ ሳታወጣ የምትቀር አይመስለኝም። ምን ዓይነት ፍቃድ እንዳሏቸው የማይታወቁ የኃይማኖት፣ የኤች. አይ. ቪ. የክትባት ሰባኪዎች ጆሮ በሚበጥስ ጩኸት ያዋክቡናል። ሌላው ቀርቶ......ስሙን መጥቀስ የማልፈልገው የሃይማኖት ድርጅት መጽሐፋችንን ግዙ ማለቱ ሳይበቃው ፊልማችንን ግዙን እያለ ቪድዮ ቤቶችን በጩኸት ሲጫረት ተመልክተናል።

ይሄ ሁሉ ተደማምሮ......በጤንነት ላይ ሊያመጣው የሚችለው ጉዳት ባይጠናም ሊጤን ይገባዋል እንላለን። በአሜሪካ ቨርጂኒያ ቴክ ዩኒቨርሲቲ ግድያ ከተካሄደ በኋል «አሥራ አምስት ሚሊዮን የአዕምሮ በሽተኞች ኢትዮጵያ ውስጥ አሉ» የሚል የጥናት ውጤት በቴሌቪዥን መሰማቱን አስታውሳለሁ። ምናልባት ደሞ አንድ ቀን ጩኸት በሰው ልጆች ጆሮ ምን ዓይነት ጉዳት እንደሚያስከትል......ወይም ለሥነ ልቦናዊ ደህንነት ምን መጥፎ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው.....በውጭ ተመራማሪዎች አንዳች ጥናት ተደርጎ ውጤቱን እንሠማ ይሆናል። ስከዚያው ግን ለማሕበራዊ ውይይት ርዕስ ሆኖ የሚቀርብበትን አጋጣሚ ብንጠብቅ መልካም ይመስለኛል ፡

ድምጽ የሚባለውን ነገር ሳስበው ለሙዘቀኞች ከፍታ፣ ለፍቅረኞች ዝቅታ፣ ለቢሮ ሰዎች በተለይም ባለሥልጣኖች መካከለኛ.....እየሆነ ለመገልገያነት እንደሚውል አውቃለሁ። ከነዚህ የሚለየው «ጩኸት» የምንለው እንዴት ሊጐዳ እንደሚችል አይተናል። መቼም አንድ ነገር ጐጂም ቢሆን በትንሹ ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያቅትም። ለመሆኑ ጩኸት ሰውን የተቀመበት ጊዜ አለ? እዚህ ከደረስን በራሴ ላይ የደረሰ አንድ አስገራሚ ገጠመኝ አቻውቻችሁ ጽሑፌን እደመድማለሁ።

ጊዜው ከዓሥር ዓመታት በፊት ነው። ብርሃንና ሰላም ሰባተኛ ፎቅ ላይ ፕሬስ ድርጅት ለሥራ አድን ቀን በዕለተ - ዓርብ በጣም የምፈልገው ጽሑፍ ስለ ነበረ አሥራ አንድ ሰዓት ቢሮዬን ከፍቼ ገባሁ። ጽሑፉን እያገላበጥኩ ሣለሁ ጸሐፊዋ ቢሮዋን ቆልፋ ደርጃዎቹን ስትወርድ ተሠማኝ። ያለሷ ምንም የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኛ እንዳልነበረ አውቃለሁ። ሥራዋን ጨርሳ መሄዷ ነው.....አልኩ በሆዴ። በኋላ ግን የሆነ ነገር ጥርጣሬ ውስጥ ጣለኝ። ሳስበው ነገ ቅዳሜ ከነገ ወዲያ እሁድ ነው። ሥራ የለም ማለት ነው። ይብስ ብሎ ደሞ ሰኞ በዓል ነው። ወዲያው ተነሣሁና ጽሁፉን ኪሴ ቶሎ ከትቼ ወደ ኮሪደሩ ሮጥኩ።

ራሴ በማውቀው ምክንያት ረስቼ ነእብር እንጂ ወደ ስድስተኛ ፎቅ (የሕትመት ክፍል) ለመውረድ አንድ ትልቅ የመስተዋት በር አለ። እና ልክ በሩጋ ስደርስ ሰው የሌለ መስሏት ለካ ቆልፋለች። ቆልፋ ስትወርድ ነበር የሠማኋት ማለት ነው። ጉዴ ፈላ......ከማለት በስተቀር ምንም ሌላ ያሰብኩት የለም። ሶስት ቀን ሰባተኛ ፎቅ ላይ ቀኑን ውዬ ሌሊቱን ላድር ነው። ምን ላድርግ? ተጨነቅኩ። ይሄን ጊዜ ጸሐፊዋ ታች ደርሳለች። አንድ ደቂቃ እንኳን ማጥፋት የለብኝም!

አንድ እግዚአብሔር የባረከው ሐሳብ መጥቶልኛል። እይሚያድነኝ አንድ መፍትሔ ጩኸት ብቻ ነው። መስኮቱን ከፈትኩና ወደ ታች መጮህ ጀምርኩ። የማተሚያ ቤቱ ሠራተኞች፣ ዘበኞች፣ ጽዳት ሠራተኞችም

የወረቀት መዓት እንደ ቴሌ ካቦ የሚገፉ ነጫጭ ካፖርት የለበሱ ሴቶች ሁሉ......ሠይጣን ከሠማይ የተነገረ ሳይመስላቸው አልቀረም። እኔ መጮኼን ቀጠልኩ። ያለ የሌለ ድምፄን ዱሮ ጐረምሳ ሆኜ የነበረኝን ኃይል ሁሉ አሰባስቤ እጣራለሁ......እጣራለሁ ጸሐፊዋ አንደኛውን ፎቅ ጨርሳ የግቢውን አሥፋልት በታኮ ጫማዋ ስትቀጠቅጠው ባየሁ ጊዜ ጐሮሮዬ ራሱ ባልጠበቀው መንገድ የራሱን የተለየ ታምር ሊሠራ ቻለ። ያለ የሌለኝን ከባድ ድምፅ እንደተጠቀምኩ ዘወር ብላ አካባቢዋን ስትቃኝ አየሁዋት። ከዚያ በኋላ......ምን ብዬ ልንገራችሁ?......«እኔ ነኝ......ከሰባተኛፍ ፎቅ......እኔ ነኝ.......እኔ.....» ቀና አለች። ቀና ብላ ስታየኝ ሰሀራ ምድረ በዳ ላይ ለሂሊኮፕተር ምልክት እንደሚሰጥ ሰው እጄን አውለበለብ። ዕድሜ ለጩኸት! በሩ ተከፍቶልኝ ከሰባ ሁለት ሰዓታት እሥር በቤት በጤና አምልጬአ ነገሩ ሁሉ በዚህ ተደመደመ ፡

ለመሆኑ.....ሶስት ቀን ውዬ ባድር ምን እሆን ነበር!? ጤነኛ ሆኜ ብተርፍ እንኳ የራሴ ጋዜጠኛ ጓደኞች በኢንተርቪው እንዴት ያጣድፉኝ እንደ ነበር አይታያችሁም? «ስልክ መወድወል አትችልም ነበር?» ብላችሁ እንዳሰባችሁ ገና ዱሮ ገብቶኛል። ጸሐፊዋ የለች....ኦፕሬተሯ የለች.....ለቀጥተኛ (ዳይሬክት) ስልክ የታደሉ ጥቂቶች ናቸው። ለመቶ ሀያና ለሌሎች ፈገግታ ዓምዶች የራሱን ወገን ማጋፈጥ ደስ የሚለውና አሰፍስፎ የሚጠብቀው ጋዜጠኛ ሁሉ.......የኔን ዓይነቱ ጡረተኛ ድምፅ የለውም። ጩኸት አያውም። ቢያውቅም ኃይል ስለሚያንሠው አድማጭ አያገኝም።

# በዓልና አዲስ አበባ

እስከ ዛሬ የሚሊኒየማችን ዋዜማ ድረስ ከሁለት መቶ የማያንሱ የሃይማኖት በዓሎች አሳልፌያለሁ። ቅበላዎች ዳግማይ ትንሣኤዎቹ ሳይቆጠሩ ማለቴ ነው። አገራዊ በዓሎች ከባንዲራ ጋር እንጂ ከኑሮ ውጣ ውረድ ስለማይያያዙ እዚህ ውስጥ አይገቡም። እንደ ዘንድሮው ፋሲካ ትኩረቴን የሳቡት በዓሎች ጥቂቶች ናቸው።

አዲስ አበባ ሁሌም ንግድ ላይ ናት። በበዓላት ሰሞን ግን የተለየ ሁኔታ ይታይባታል ዶሮዎች፣ በጎች፣ ተደጋግሞ እንደሚነገረው ቅጥ ባጣ ሁኔታ ሲንገላቱ መመልከት የሁልጊዜ ትዕይታችን ሆኗል። አሳዛኝ ገበናችንን ከቱሪስቶች መሳለቂያ ካሜራ ልናስወግድ መሞከር ይቅርና በእምስተዳድርም ሆነ በሕብረተሰብ ደረጃ መወያያ ርዕስ ልናደርገው አልቃጣንም። የደን ሀብትን መጠበቅና መንከባከብ ተገቢ ቢሆንም እንደገና ለሚበቅለው የገና ዛፍ ምን ያህል የአዞ እንባ እንዳፈሰሰ ዓመታቱ ሁሉ ይመሰክራሉ። እንስሳቱን በተመለከተ ገና ታርደው የሚበሉ ስለሆነ ምን አደከመን የምንል ይመስላል።

በዘንድሮ ፋሲካ ከየክልሉ ጋዝ በተቀባና አቧራ በለበለ ሊዎንቺና አውቶብስ ታጭቀው፣ ንፋስ ላባቸውን እየነቀለና መንቆራቸውን እያደረቀ፣ በፀሐይ ሐሩር እያለከለኩና እየተንጫጩ ወደ መዲናችን የሚጓዙት አዕዋፍ ቁጥር ልክ አልነበረውም። ጅቡቲና የሐዲድ መስመር ከተሞች ከፍተኛ አምራቾች ቢሆኑ ኖሮ የባቡር ፍርጎዎች ሁሉ ዶሮ ዶሮ ሲሸቱ ይከርሙ ነበር ያሰኛል።

በግና ፍየል እንኳን በዓውደ ዓመት በአዘቦቱም ቀን ሲሮጡ የሚውሉ ናቸው። በውፍረት ሊፈነዱ የደረሱ የሚመስሉ የቅርጫ ሰንጋዎች እንደመኖራቸው ሁሉ......አጥንታቸው የሚቆጠር፣ በግድ እየተጎቱና እየተገፉ የሚሄዱ ያረጁ ያፈጁ በሬዎችም በየጉራንጉሩ አይተናል። የእህሉ፣ የቅቤው፣ የቅመሙ፣ ከሁሉም በላይ

የሉካንዳው ርብርቦሽ ቢያወሩት ያሰለቻል። የዋጋውን ነገር ሚዲያው ሁሉ የሚገልጸው ነውና መዘርዘሩ አስፈላጊ አይመስለኝም።

በዓል በመጣ ቁጥር ቤት መለዋወጥ ዓይነተኛ ልማዳችን እየሆነ መጥቷል። በተለይ ነጋዴው ሥራውን አዲስ ለማድረግ ሳይሆን ለማስመሰል ጥረቱን የሚጀምረው ገና ከበዓሉ ሣምንታትን አስቀድሞ ነው። የሱቁን ወይም የምግብ ቤቱን፣ ካፌውን ወዘተ......ቀለም ይለውጣል። «በአዲስ መልክ ስራ ጀምረናል.....» የሚል ዓይን የሚስብ ጽሑፍ ያረፈበት ጨርቅ ይሰቅላል። በዓልን ብቻ ጠብቆ አዲስ ነገርም ታስቦ፣ ተግባራዊ ሲሆን ያው የዱሮው መሆኑ እንዴት ለራስስ ትዝብት አይሆንም? ያሰኛል።

በመኖሪያ ቤትም ደረጃ ምንም ያልደላቸው የእኔ ቢጤዎች አዲስ የቤት ዕቃ ሳይኖራቸው ሶፋው ተዟዙሮ ቢፌው ወደ ሌላ ግድግዳ ተገፍቶ ፎቶ ግራፉ የላዩ ወደ ታች የታቹ ወደ ላይ ተሰቅሎ፣ በል ሲለው ወለሉና ግድግዳው ታጥቦ፣ እቅለም ባይቀበም ኮርኒሱ በረጅም መጥረጊያ ፀድቶ.....እንዲታይ ያደርጋሉ። አልፎ ተርፎ የግቢው ቆሻሻ፣ የወደቀ ወረቀት ሳይቀር ይለቀማል። አጓጉል የበቀለ ሣር ይነቀላል። በክረምት መግቢያ ያልተደረገው የበይ ቁፋሮም ይካሄዳል። ሁሉም የድሮ ሆኖ መጋረጃው ይታጠባል። አልጋ ልብሱ፣ ጠረጴዛ ልብሱ ይታጠባል። ምናልባት ግን ቴለቪዥኑ፣ እስም ከሌለ ሬዲዮና ቴፑ አዲስ ጨርቅ ይለብሳል። በእንዲህ ያለው ሁኔታ ምንም አዲስ ነገር ላይኖር......ሆነም ቀረም እንዲባል፣ ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ዓይነ......የበዓል ዋዜማ «ተመስገን» እየተዘመረለት ይደምቃል ፡

ይህ እንዲህ ቢሆንም.....ብዙ ክረምቶችን አሳልፋ ቀለሟ የተላጠ፣ ጥቀርሻ መሣይ ቆርቆሮዋን ድንጋይ ጎማ፣ የብስክሌት ስብርባሪ የተጫናት፣ በአሮጌ ሣንቃዋ ከፍተኛ የቆሻሻ ዓይነቶች ያጠራቀመች......ጣውላ ግድግዳዋ ያዘመመ....ጡረተኞች ያሚያዘወትሯት.....«ፀጉር ቤት» የሚል ጠማማ ታፔላ የተሰቀለባት አሮጌ ኪዮስክ......ቢያጋጥማችሁ ለዚያን ቀን ብቻ በፅጌረዳ አታክልት መሃል ደርቃ የቆመች የሎሚ ዛፍ ልትመስላችሁ ትችለለች።

አዲስ አበባ ግን ሁሌም በንግድ ላይ ናት። የአፍሪካ ዩኒየን መዲና ብቻ እንዳትመስላችሁ። ከክልሎች መናኸሪያነትም አልፋ የአፍሪካ ትልቅ ገበያ ባለቤት ተብላለች። ምርቷ በጣም አናሳም ቢሆን ከውጭ የምታስገባቸው ዕቃዎች የመብዛታቸው ሁኔታ ሲታይ ደግሞ እቴጌ ጣይቱ መጀመሪያ «ፊንፊኔ» ብለ እንደሰየሙዋት ዛሬም በንግድ ሩጫ የዓለም ኮከብ ለመሆን ፊን ፊን የምትባል ትመስላለች። ጫት ተራው ወደ መገናኛ ገርጂ ተሻግሮ በቦሌ በኩል የንፋስልክን አካባቢ አጥለቅልቋል። እንጦጦን አየር ጤናን፣ ፒያሳን አሥመራ መንገድንና ወሎ ሠፈርን ሳይቀር አልብሶታል ፡

የጫት ንግድ ብሎ ብሎ ዘብኛና አስተናጋጅ የምያሥፈልግበት ቪላ ቤት ውስጥ እየተጧጧፈ ነው። የጫት ጎጂነት በሬዲዮ በሚሰማባቸውና የሙሽራ ጫጉላ ቤት በመሰሉ ዝግ ክፍሎች ውስጥ......የዱባይ ሽቶና የሊባኖስ ከርቤ በሚያውዱባቸው ምንጣፎች ላይ ጥሩ መዋያና የቢዝነስ ምንጭ ሆኗል። የቦይንግ እየወረዱ ሻንጣቸውን ወደ ቤት ልከው የሚፈርሹ ዓይናማዎች ራሳቸው የሚመሰክሩት ነው።

የወጣቶች ጊዜ ማሣለፊያና መዝናኛ ቅድሚያ ይሰጠው ብለን ነው እንጂ ገበያው በሁሉም አቅጣቻ እየደራ መሆኑን ዘንግተውነው አይደለም። የአዲስ አበባ ባለ አደራ ቦርድ አላየውም እንጂ የከተማችን ገበያ ከአትክልት ተራ ቆሻሻ ሥፍራ ተነሥቶ አቡነ ጴጥሮስ ሐውልትን አልፎ በመስተዳድሩ በራስ በኩል በጊዮርጊስና በዱሮ ውቤ በረሃ በኩ ሣህን፣ ብርጭቆ፣ ማንኪያ፣ ሸሚዝ፣ ካልሲ.......ምኑ ቅጡ በአራቱም ማዕዘን ከቻይና እስከ ቱርክ የሚደርሱ የሸቀት ዓይነቶች ተደርድረው መንገደኞችን የሚፈታተን የዕቃ ክምር በተለይ በበዓል ሰሞን የሚፈጥርው ችግር ይታያችሁ።

አዲስ አበባ ነገር በማስገባት ብቻ አትመለስም፡፡ «ምናለሽ ተራ» ሄዳችሁ ብታዩ አሮጌው ታድሮ ስለሚሸጥ የገበያተኞች የተጧጣፈ ትዕይንት ያጋጥማችኋል......ለምሳሌ.......የተለያዩ ካልሲዎች ዓይን የሚስብ ልዩ ቀለም ያላቸው ካናቴራዎች ባንዲራዎች የሚያስታውሱ ኮፍያዎች ከምግብ ጉርሻ ቀጥሎ የሚሸጡ ናቸው፡፡ አንድ ሰው የሚያጠልቀው ጫማ አንደኛው እግር የቻይና ሌላኛው የታይዋን ሊሆን ይቻላል፡፡ መነፅር አንዱ ሰማያዊ ሌላው ጥቁር ቢሆን ያስኬዳል፡፡

በተለይማ በዓል ከሆነ.....ብዙ ከዋክብ ስላለ ቦታውን ያልተለማመደ ሰው በድንገት «ምናለሽ ተራ» ቢሄድ ነጋዴዎቹ የአካል ጉዳተኛ ሳይሆን መስሏቸው...... ያላሰበውን ዓይነት ጫማም ይሁን ልብስ እንደሚሸጡለት መጠራጠርም የለበችሁ፡፡ የእግር ልክ ቁጥር የሚባል ቆዳ ወይም ጎማ.....ተሞርዶ የሚያስካክልበት ሁኔታ አለ፡፡ አንዱን የዚያ ገበያ ቦታ ሻጭ እንደጠየኩት ከሆነ፣ ወንድ የሚለብሰው ሙታንታ እዛው ባሉ የመርፌና ክር የእጅ ስፌዎች ተለዋውጦ ለሴት ጡት መያዣ ይሸጣል፡፡ ይገዛል አሉ፡፡ አርቴፊሺያል እጅ ከተራ ላስቲክ በተሠራ ጓንት (ግሎቭ) ውስጥ እየሆነ ለምስኪን ለማኞቻችን ይሸጣልም ከተመኘኖች ሳልቮጁ ሲወደድብን ወደ «ምናለሽ ተራ» እንሂድ ይሆን? እላለሁ፡፡ አሳቡን ወደድነውም ጠላነውም.......የሚያስገርም አይመስለኝም፡፡ ዱሮስ ቢሆን......ምን የማይሆን ነገር አለ?

ኧረ ይቺ ጉደኛ መዲና ጨካኝ ናት፡፡ በአራት ኪሎ በአራዳ (ባሻ ወልዴ ችሎት አባታችን ሠፈር ዶሮ ማነቂያ፣ ገዳም፣ ሠፈር ሳይቀር) ሞቅ አድርጋ የጀመረችውን የነጋዴ ባህርይ ጣልያን አዲስ አበባ ከተማን ገበያ አድርጎ ሲቆረቁር ሁሉ ድምፅዋን አጥፍታ ተባብራለች፡፡ ከዚያን ዘመን ጀምሮ ያካበተችውን ልምድ በተለይ በበዓላት ሰሞን፣ እጥፍ ድርብ ሁላችንም ነጋዴ ለመሆን የምናደርገውን መፍጨርጨር አውቃ እየተሳለቀችብን ይሆን? ማን ያውቃል፡፡

እንዴት እንደሆነ አላውቅም እንጂ.......ኢትዮጵያውያን ስንባል ተማርንም አልተማርንም ኖርንም አልኖርንም......መሸጥ መለወጥ ተጠናውቶናል፡፡ ብዙ ጊዜ እንደኔ ጡረታ የወጡ ጓደኞቼ ስለ ጤንነት ካነሱ በኋላ «ታዲያስ? እንዴት ነው?» የሚለውን ተነጋግረን ብዙም ሳንቆይ «ስማ እንጂ፣ ዛሬ እኮ በአበል መኖር አልተቻለም፡፡ ለምን ሌላ ሌላ ሥራ አንሠራም?» ውስጠ ታዋቂ መሆኑ ይገባኛል ፡፡ እኔም ይሄ ዓይነቱ አነጋገር ወዲያው ይጋባብኝና ላጋጠመኝ ጡረተኛ አስተላልፋለሁ፡፡

አዲስ አበባ ግን፣ እንኳንስ ሁነኛ መዋያ የሚያጣውን ጡረተኛ ይቅርና ከውጭ የሚመጣውን ኢንቬስተር «አርፈህ ቁጭ በልና ነግድ» ብላ በመስሕብዋ ጉያ ማስገባት የሚያቅታት አይደለችም፡፡ ታዲያ ይሄንን አልኩ እንጂ......ገና ከገጠር ቅሉን ጨርቁን ጠቅልሎ የሚነሳ ዜጋ ሁሉ «መነገድ» የሚለውን ቃል ብቻ እያሰበና በሆዱ እያነበነበ.....ሲጓዝ ደራሽ ውሃውን፣ ጎርፉን፣ ሐሩሩን የማያስታውስ እንኳን አይመስለኝም፡፡ ይሁን እንጂ ይቺ ጉረኛ መናኸሪያ የሚላስ የሚቀመስ አታጣምና.....በእናትነት ዜማዋ አባብላ፣ እንባውን አድርቃ፣ በሌላ የንግድ ፕሮግራም እንዲሠማራ ታደርገዋለች፡፡ እውነትም እኮ......የሁላችንም መሰብሰቢያ ስለሆነች አኩርፋ ፊት ካልነሳችን መግቢያ፣ መውጫችንም ነች፡፡

የአዲሳባ ሰው ሲባል፣ እንኳን በበአላችን በአዘቦቱም ነጋዴ መሆኑን ማንም የሚክድ ሰው የለም፡፡ የቢሮ ሠራተኛም አስተማሪው፣ ተማሪው፣ ቆንጆዋ ፀሐፊ፣ ደላላው፣ ባለሥልጣኑ፣ ተላላኪው፣ ሴተኛ አዳሪዋ፣ ጡረተኛው፣ ታክሲ ነጂው፣ ሁሉ ይነግዳ፡፡ ሩቅ አትሂዱና......አድኒት ግቢ ድንገት ባንድ በኩልዋ ተበርቅሳ፣ ስኳር ሻይ ቅጠል፣ ኮካኮላ፣ አፖፕ.....የሚመጠጠው የሚላሰው.......የሚሸጥበት አንድ ትንሽ ቤት ውስጥ......በአጭር መስኮት አንገትዋን ብቅ አድርጋ «ምን ፈለጋችሁ?» የምትል ትንጥ ብልጥ ልጅ ካያችሁ የንግድ ሀሌታው ጀመረ ማለት ነው፡፡ ደግሞ እዚያው ቁጭ ብለው ሻሻቸውን ወደ ላይ ገፋ እያደረጉ ነጫጭ

ጠጉራቸውንየሚደባብሱ አዛውንት ሴትዮ ካሉ የንግዱ ሂደት በእግሩ ሊቆም ነው ማለት ነው። ከትንሿ ሱቅ ፊት ለፊት ኳስ የሚያነጥሩ ልጆችም የነፉትን ፊኛ አዲስ አስመስለው ለመሸጥ ዘዴና መንገድ የሚፈልጉ......የወደ ፊት ነጋዴዎች ናቸው። ያሳለፍነው የፋሲካ በዓልና ስግደታችን ይቅር ይበሉኝ እንጂ......እንኳን ጤነኛው ለማኙም ነጋዴ ነው።

# ስብሐት ገ/እግዚአብሔር.....እኔ እንደማውቀው

ሰው በፈጠራ ሥራ በገጸ ባሕርይነት ይሣላል። በተለይ በልቦለድ ከሌሎች ተውጣጥቶ ከሚፈለገው ድርጊት ጋር ተቀነባብሮ ርሱን እንዲሆን ይደረጋል። የሚያቁት ሰው ግን በቁሙ እንዳለ እንደሚያቁት ተደርጎ ይቀረፃል። በቃላት ፎት እንደ መነሣት ማለት ነው። በሕይወት እያለ የሚቀረጽ ሰው አድን የሚደነቅ ባሕርይ ያለው ሊሆን ይችላል። በሙያው ምን ዓይነት ተሠጥዎ ችሎታ ልምድ አለው? ለሙያው ፍላጎት፣ ፍቅር ጥረት.....ምን ይመስላል? የተፈጥሮ ጠባዩ፣ ለነገሮች ያለው አመለካከት እምነቱና አስተሳሰቡ......በጠቅላላው እንደ ማንኛውም የሰው ልጅ ራሱን የሚያደርገው ማንነቱ.......በብዕር ሲዳሰስ ለጸሐፊው ትዝታ መግለጫ ለድናቂዎቹም ብሩህ እይታ ማሳሰቢያ ይሆናል።

ስብሐት ገብረ እግዚአብሔርን በሰባዎች መጀመሪያ አካባቢ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የባህል ማዕከል ተጋብዞ ስለ ድርሰትና ደራስያን ንግግር ሲያደርግ ለመጀመሪያ ጊዜ እንዳየሁት ትዝ ይለኛል። ቀልዶችን በመሃሉ ጣል ጣል በማድረግ ስለ ውጭ አገር ደራስያን ማንነትና የነበረችውን ችግር......እና ደራሲ ማለትምን ዓይነት ሰው እንደሆነ ሠፋ ያለ ገለጻ አደረገልን። አነጋገሩ እጥር ምጥን ያለና ሲናገር ዘና ብሎ የሚያዝናና፣ ቁም ነገሮችን በቀልድ መልክ እያዋዛ የሚጠቋቁም መሆኑን ተረዳሁ። ዛሬ በማዕከሉ የተቀረጸው ድምፃቸው ይኑር አይኑር የማላውቅም ብሆን በሱ አቀራረብ ላይ በዕሉ ግራም ተጨምሮበት ጥሩ ጥሩ ፕሮግራሞች እንጋበዝ እንደ ነበር አስታውሳለሁ ፡

የሥብሐት ጽሑፎች ከዚያ በኋላ እየፈለኩ ሳነብ (ለምሳሌ መነን የካቲት፣ ቁም ነገር፣ ለዛ፣ ፈርጥ.......ጋዜጦች በተለይም አዲስ ዘመንና ሄራልስ ወዘተ.....» ከአፃፃፉ ዘዬ (style) ጋር እየተዋወኩ......በመቀጠልም ወጎችን አጭርና ረጅም ልብ ወለዶቹን በማጣጣም እያነበኩ ደራሲውን እያደነቅኩ ሄድኩ። የሥብሐት አፃፃፍ ቀላልና ግልስ ሲሆን አንዳንዴ ግን ከባድም ነው። አረፍተ ነገሮቹ አይንዛዙም። እጥር ምጥን ያሉና አዝናኝነት የተላበሱ ናቸው። ይሄንን ስል «አፃፃፉ ሁሉ ከባድ ነው አይባልም» የሚሉ አንባብያን መኖራቸውን ዘንግቼ አይደለም። ለኔ እንደመሰለኝ ይህ ሁኔታ የሚከሰተው የራሱ ዘዬ (style) ከይዘቱ ጋር በሚኖረው የአስተራረክ ሂደት የተነሣ ነው።

ማንኛውንም ደራሲ በየትም አገር ላይወድ የሚከተልው የአተራረክ ስልት አለው። በሄሚንግዌይና ሞፓሳ ቀላል አጻጻፍ አንጻር እነ ፎክነር፣ ካፍካና ሄንሪ ጀምስ አሉ። ከነሱ በበለጠ ሁኔታ ከባድ ትረካ (በተለይም ምስልልስ ወይም ዲያሎግ) በመጠቀም እንደ እንቆቅልሽ ፍታው የሚያሰኝ አስቸጋሪ እይታ የሚፈጥሩ ጀምስ ጆይስና ቨርጂኒያ ውልፍን የመሰሉ ደራስያን አሉ። እነዚህ ላይ ወደድንም ጠላንም «ኪነት ወደ አንባቢ ደረጃ ካልሄደች አንባቢ ወደሷ ይሂድ» የሚለውን የአርት መፈክር ማስታወስ ሊኖርብን ነው። ይህ እንዲህ ቢሆንም ተደጋግሞ በርጋታና ማስተዋል የሚነበብ እንጂ ልቦለድ ይኑር ማለት አይደለም።

ሥብሐት አንዳንዴ ከበድ ያሉ ልቦለዶችን በሚጽፍበት ጊዜ በሐሳቦች መካከል ተለቅ ያለ ክፍተት ስለሚተው «አይገባም» ለማለት የምንበቃው በአነባበብ የለመድነውን መሸጋገሪያ ጠብቀን ስለምናጣ ይመስለኛል። በአንዳንድ ፊልሞች ላይም የሚታየው ይህን መስለ አተራረክ የሚመነጨው አንድም ጽሐፊው ከለመደው የግል ዘዴው አልያም ይዘቱ በራሱ ከሚጠይቀው ሄደት የተነሣ ነውና የደራሲና የአንባቢ ግብብነት ከግምት እንዲገባ ያስፈልጋል ፡

ሥብሐትን በሥነ ጽሑፍ ምሽትና በአጻጻፍ ከተዋወቅኩት በኋላ ከዳኛቸው ወርቁና በዓሉ ግርማ በስተቀር ከሌሎች ደራስያን የሥነ ጽሑፍ ሰዎችና መምህራን ጋር በምናደርገው ውሎ ይበልጡን ተቀራረብንና በድርሰት ዓለምም ሆነ በጓደኝነት እየተግባባን መሄዳችን ቀጠልን። እና ስለ ማንነቱ ማለትም የግል ባህርይው አመለካከቱ፣ አስተሳሰቡ እያስተዋልኩ......ከሁሎችም መመልከቻ መነጽሮች አንዲቷን ለኔ ደህናና አመዛዛኝ የሆነችዋን አጥልቄ......በሃያ አምስት ዓመታት እይታ ይቺን ቁንጽል ጽሑፍ («ማስታወሻ» ን ሳላነሣ) ለመፃፍ በቃሁ።

እንግዲህ አሁን «ሰውዬ ምን ዓይነት ሰው ነው?» በሚለው የአገሬ ሰው፣ ነጋዴም ሆነ ምሁር፣ ቄስም ሆነ ወግ......ጠራቂ፣ አንባቢም ሆነ ገምጋሚ......መላልሶ በሚጠይቀው ጥያቄ ልጀምርላችሁ። ለኔ ስብሃት ማለት «በተፈጥሮዬ ራሴን ነኝ» የሚል ውስጤም ውጭዬም ፍጥረቱም እንደ ማንም ሰው ሆኖ.......ነገር ግን ባለኝ ነፃነት የማንም ነኝ» በሚል አስተሳሰብ የሚኖር፣ ሌሎችን የማያስቀይም፣ ሊዘልፉት ሲኮንኑት ምድራዊ ኩሽት የማያምን.......ሰው ነው። ይሄንን ጽሑፍ ቢፈረድልንም ቢፈረድብኝም «እኔ» ብዬ ነውና የጀመርኩት......እኔ እስከማወቀው ድረስ ሰዎችን በክፉነታቸው ሲቃኝ ወይም ማኅበራዊ ሤራ ውስጥ ራሱን ጀቡኖ ሲዶልት አይቼው ሰምቼውም አላውቅም። ቲፎዞ ለምሳሌ ገና ድሮ ቢገባኝ ተኩራርቶ በሌላው ተመክቶ፣ እበልጣችኋለሁ ብሎ እንደ ውስጠ ባዶ «ምሁራን» ሲናአር አልሰማሁትም። በመሠለሎቹ ላይ ሲፈርድ ከነኢ ያነሰ ነው በሚል ትምክህት ሲንቅ.... ይሄን የሚመስል ሁኔታ በበኩሌ አላጋጠመኝም። በነዚህና በሌሎችም ምክንያት.....ቅንና ሰው አክባሪ፣ ጥሩ አዳማጭ፣ ሙብትና ነጻነት ከሁላችንም በላይ የሚገባው ማንም እንደሚያውቀው ጥሩ አንባቢና ተመራማሪ እንዲያውም በአገራችን አሉ ብዬ ከምፈርጃቸው በጣም ጥቂቶቹ መካከል ሀገራዊ ምሁር (ኢንተሌክቹዋል) የምለው ሰው ነው።

ምን ያህል እንዳጋነኩት ዓይነት አድርጋችሁ የምታስቡ እንደምትኖሩ ይገባኛል። ቮልቴር እንዳለው «ሐሳብ የመግለጽ ሙብት እስካለኝ ድረስ» ግን ትታገሱኛላችሁ ብዬ አምናለሁ። ይቅርታ አድርጉልኝና አሁን ወደ ሌላ አሳብ መተላፍለፌ ነው። በአማርኛ ቃል አጥቼለት ነው እንጂ በእንግሊዝኛ «wit» የሚሉት የዓለማችን ደራሲያን ሁሉ የሚደነቁበት አንድ ትልቅ ተሰጥዎ አለ። ለጊዜው «ዊት» እንበለውና እነዚህን አባባሎች አንዴ እንመልከት

«ዊት በአነጋገር ውስጥ የሚገኝ ምግብ አይደለም፣ ቅመሙ ነው»

ዊልያም ሃዝሊት

«ዊት ማለት በተፈጥሮአችን ውስጥ ቢኖርም ብዙ ጊዜ የታሰበ ነገር ቢሆንም፣ አንዴ እንደ እሩምታ ዝናብ ሲወርድ አንጀት አርሶ አድናቆት የሚፈጥር አነጋር ማለት ነው»

አሌክሳንደር ፓፕ

«ዊት አለኝ ከሚል ደደብ ሰው ይልቅ፣ ደደብ ሆኖ ዊት አለኝ የሚለው ይሻለኛል»

ዊልያም ሼክስፒር

እነዚህ ያነሳሁላችሁ ስለ ሥብሐት «ዊል» ልነግራችሁ ፈልጌ ነው፡፡ ከተፈጥሮው ሁሉ፣ ከነገረ - ሥራው ሁሉ የሚናገረው አያጣም፡፡ ለምትጠይቁት ሁሉ መልስ አለው፡፡ ለማትጠይቁት ደግሞ ዝምታ፡፡ ለኔ በጣም የሚያስቸግረኝ መታገስ ነው፡፡ እሱ ሰዎች ሊዘበዝቡ ቢውሉ ዝም ብሎ ያዳምጣል፡፡ ቁንጫ ቢቆነጥጠው እንኳን «አንዴ ቆዩ» አይልም፡፡ ማዳመጥ ነው፡፡ ጥሩ ምክንያትና ደርስ ያልያዘ አነጋገር (ወይም አስተሳሰብ) ከመጣ ግን እንደ ፊታውራሪ መሸሻ የሚቆም ቀንድም ባይኖረው ምላሱ ከመቅጽበት ትሾላለች፡፡ ዝግተኛዋ ደካማዋ ለጥቂት ደቂቃ ትሞጣሞጣለች እንጂ ወዲያው ትበርዳለች፡፡ በይ ሲላት ደሞ ቱግ ትላለች፡፡ ይሄን ባሕርይውን ማንም ሀብታም ዝነኛ ወይም ባለሥልጣን አያስጥለውም፡፡

ሥብሐት ማለት ግሎ የሚበርድ ብረት ይሁን እንጂ ሰዎችን ማስተዋል ሲፈልግ ከፍ ዝቅ እያእል እንደማይጠፉ ሻማ መብራት ነው፡፡ በወስፌ ዓይኖቹ እያፈራረቀ እያየ፣ አካባቢውን ሁሉ እየቃኘ ምንም ሳይናገር የሚጽፈውን ነገር በሆዱ ይጽፋል፡፡ ኮሥሥ ባለችው ቁመናው ብድግ ብሎ እያዘገመ ወጣ ሲል እንኳ በሰላ አእምሮው ለጎረምሳ የሚሰወር ነገር እንኳን አያመልጠውም፡፡

እውነት ለመናገር ሥብሐት ገብረ እግዚአብሔር ትግሬ ሆኖ የትግሬዎች ሁሉ ዲሞክራት ነው፡፡ አድን ቀን ጓደኛዬ ቤት ቁጭ ብለን የትግርኛ «ተሐድሶ» ስናይ «እነዚህ ደግሞ ውዝዋዜያቸውን አይለዋውጡም» ማለቱ ትዝ ይለኛል፡፡ ለኔ እንደሚገባኝ የትግርኛ ባህላዊ አቀራረብን ጠላ ማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም የኢትዮጵያን ብሔር ብሔረሰቦች የተለያዩ ባሕላዊ ውዝዋዜዎች ይወዳሉ፡፡ የባሕል ዓይነቶችን በኪነት ዕይታ እንደሚያደንቅ ያጫውተን ስለ ነበረ አመለካከቱን «ያደግክበት ቋንቋ ትግርኛ ሆኖ ሳለ ለምን በትግርኛ ልብ ወለድ አልፃፍክም?» ተብሎ በቴሌቪዥን ሲጠየቅ «ተከፈሪ መኮንን ት/ቤት ጀምሬ አማርኛ ለመድኩ፡፡ የምጽፍ እስከሆነ ድረስ በለመድኩትና በሚመቸኝ አማርኛ ቋንቋ ብጽፍ ምናለበት?» ያለ ሰው ነው፡፡ እና......አትጠራጠሩ፡፡ ኮሥሥ ብሎ ብታዩትም ከክርስቶስ ጋር የመሳሰለ......ደራሲ፣ የውስቱን ደፋር አቋም አያሳይም ትላላችሁ?!

ዛሬ መቼም ለይቶልኛል፡፡ ሙሉ ቀን መለሰ እንደዘፈነው ዘፈን «ገና ብዙ አለብኝ፡፡» አንዴ ጀምሬያለሁና ልፍለፋዬን ልቀጥል ማለቴ ነው፡፡ «ዊት» ሲባል የእዚያው በዚያው ድንቅ አባባል መሆኑን ቀደም ብዬ ጠቅሼላችኋለሁ፡፡ ጆርጅ ብርናንድ ሾው፣ ዊንስተን ቸርቺል ሳሙኤል ጆንሰን አብርሃም ሊንከን የታወቁበት ተሰጥዎ ነው፡፡ ታዲአይ ሥብሐት በራሳችን ደረጃ እኛኑ የምትመስል የራሱ «ዊት» ያለው ቢሆን ምን ያስገርማል? ለነገሩማ የቅዱስ ያሬድ ዜማና የግዕዝ ቅኔ ብቸኛ ሀብቴ ነው በምትል አገር ከዚያም በላይ ቢጠበቅ የሚስገርም አይሆንም ነበር፡፡ እና ሥብሐትን ከነመንግሥቱ ለማ ገር በሚጋራው የሰላ አንደበቱ ነገር ሰምቶ ነገር በቅጽበት ጣል ሲያደርግ የዋዛ ሰው አይምሰላችሁ፡፡ ትንሽ ልዩነት አለው ቢባልም የዚያ ምክንያቱ ተፈልጋ ተፈልጋ በግድ አለሁ የምትለው እንደ መንዜዎች ኅተት ብላ የምትወጣው ድምፁ ናት፡፡ በቀልድም መልክ ይሁን፡፡ እንደፈለጋችሁ ተመልከቱት፡፡

ጥቂት ምሳሌዎች፡፡-

አለባቸው፡፡ «ሞት ትፈራለህ ይባላል......»

ሥብሐት፡- አንተስ?

====

ጠያቂ፡- «ታዲያ ለምን በግልጽ አልነገርኩውም?»

ሥብሐት፡- ሰው ነኛ!

ጠያቂ፡- «ያልኩትን አንዳችሁም አልሰማችሁም። ልክ ነኝ?»

ሥብሐት፡- ገና ሳትናገር ያወቅከው ነገር ነበር!

====

ከመሃላችን አንዱ - «የሷን ውበት ለማወቅ ዓመታት ይፈጅባችኋል.....»

ሥብሐት፡- በአቋራጭ ነግረኸናል።

====

አንዱ ጠጅ ጠጪ- «እኒህ ሽማግሌ ጠጅ ቤት ዘላለም ያነባል»

ሥብሐት፡- እናትክን.....ሂድና ሚስትህን አንብቢ በላት።

====

ፋሲካ ኬክ ቤት የጋበዘው ወጣት -- «እኔ ኬክ ብጋብዝህ ይሄ ጓደኛዬ ጭቅና ጥብስ ሙሉ የበግ ቅቅል ነገ ይጋብዝሃል።»

ሥብሐት፡- ደፋር ነው እንዴ?!

====

ቴሌቪዥን ሲያዩ አድኑ ላውራ ባይ -- «ለኃይሌ ገብረ ሥላሴ ይህንን ሁሉ ዝጅግት ያደረጉ......በፊዚክስ በኬምስትሪ ወይም በሥነ ጽሑፍ ኖቤል ሽልማት ለሚያገኝ ኢትዮጵያዊ እንደዛ ያደርጋሉ?»

ሥብሐት፡- ምን በወጣቸው!!

====

አስተያየት ሠጪ (መንገድ እየሄዱ) - «አሁን ይቺ ከይሲ ሽርሙጣ በባህላችን እንግዲህ ተገልባ መሄድ አለባት?»

ሥብሐት፡- አይነ ሥውር አባት ቢኖራትስ? የምታስተምራቸው ወንድሞችና እህቶች ቢኖርዋትስ?

====

አንድ የቅርብ ጓደኛው ቆንጆ ሴት እያየ ሲሴድ - «ውይ ጋሽ ሥብሃት አላየሁህም እኮ.....»

ሥብሐት፡- ቀጥል መንገድህን! እኔን ነገ ታገኘኛለህ።

=====

የሥራ ጓደኛው ሰባት ፎቅ ሲወጣ - «በየፎቁ ቆም ብዬ ፖስተር የማየው ከድካም ለማረፍ ብዬ ነው።»

ሥብሐት፡- ለምን ይህን አታእይውም (ባዶውን ግድግዳ እየነካ)

====

የቢሮ ጸሐፊ - «ምነው ጋሽ ሥብሐጥ?!

(ሱሪውን በገመድ አስሮ አይታው)

ሥብሐት፡- ቀበቶዬን ለጊዜው አጥቼው ስለቸኮኩ ነው። ምነው? ይሄም እንደ ቀበቶ ያገለግላል።

=====

ጓደኛው፡- «ምን አስቸኮለህ?»

ሥብሐት፡- ቀጠሮ እንዳላፈርስ

====

ጓደኛው፡- «ወንድምህ ዶክተር ተወልደ አሥመራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ሆኖ ለተመራቂዎች ያደረገው ንግግር ግሩም ነበር። የሥነ - ጽሁፍ ችሎታ እንዳለው ያስታውቃል!»

ሥብሐት፡- ታፊያ ደራሲ አይሆንም ነበር!

====

ግብዣ ላይ ያጋጠመው ሰውዬ፡- «ኬሚስት እህት አለችኝ አረቄ ትጠምቃለች» ብለሃል አሉ እውነት ነው?»

ሥብሐት፡- ውሸት ነው። አሁን ግን አንተ ብለሃል።

=====

ዳኛቸው ወርቁ፡- «ደርግ አሥር ሰው በአንድ ጉድጓድ ሲቀብር አይቼ አልጻፍክልህ ብሎኛል። አንተ እንዴት ነው የሚፃፍልህ?»

ሥብሐት፡- ዓመት ባሎች ስለሚመጡብኝ።

======

አንድ ገጠሬ ያወራለትን ጓደኛው ሲነገረው፡- «ሰውዬው ቀበሌ እንደተሰለፈ አንዛርጧል። እፊቱ የቆመውን በጥፊ አለው። ይሄ - ነፃ ወጣ። በዚያኛው ተሳቀ ብሎ አጫወተኝ። እስቲ ስለ ፈስ የሠማኸው ካለ ንገረኝ።»

ሥብሐት፡- ሰውዬው እቀመጣለሁ ሲል ተሳታቸው። ብድግ አሉና ወደ ወንበሩ እያዩ «ማነው እዚህ ፈስ የተወው?» አሉ።

====

የሠርጉን ፎቶ ያየ ሰውዬ፡- «ለምንድን ነው እንደ ሙሽራ ያልለበስከው?»

ሥብሐት፡- ሠርጉ እኮ የኔ ነው። አንተ ምን አገባህ?

====

ጓደኛው፡፡- «ማንጎ እንዲህ እየጣፈጠ ድንጋዩ ለምን ትልቅ ሆነ?»

ሥብሐት፡- ጥፍጥናውን ከሱ ነዋ የሚያገኘው። አንተ ትሰጠዋለህ?

====

የቅርቡ ዘመዱ፡- «ሰዎች እንደ አለቃ ገብረ ሐና ሊያደጉህ ይፈልጋሉ ሲባል ሠምቼ.....»

ሥብሐት፡- በማ ዕድሌ!

====

ጓደኛው፡- «አሜሪካ ሄደህ ነበር አሉ፣ እውነት ነው?»

ሥብሐት፡- አዎ ስንት ዓመት የየህስ አትለኝም? - አንድ ወር!

====

የቴሌቪዥን ጠያቂ፡- «እርስዎ የብልግና ነገር ብቻ ይጽፋሉ ይባላል። ስለዚህ ነገር ምን አስተያየት አለዎት?»

ሥብሐት፡- አንተ ብልግና አልከው። እኔ ግን የነበረውን እንደነበረ ነው የጻፍኩት። በሸወርኒ የዘመኑ ሰው እንደሚነጋገረው አይደለም ማለቴ እንው። የመነጋገሪያ ወቅቱ ሲመጣ ግን ሁላችንም እንግባባለን።

# ጡረታ ወይስ ማሕበራዊ ዋስትና?

ቃላት ፈጣሪው ማን እንደሆነ በውል ባይታወቅም ልመዱት ብሎ ለሕዝብ የሚሰጠው ግን ገዢው አካል /መደብ/ መሆኑ ግልጽ ነው። ለምሳሌ በኃይለ ሥላሴ ዘመን በሚኒስቴር ደረጃ «ጡረታ» ተባለ ደርግ መጣና ቃሉ ሲያሻሽል «ማሕበራዊ ዋስትና» አለው አሁም በኢ.ሕ.አ.ዲ.ግ እንዲያው ቀጥሏል። ስለዚህ ቃላት ይወጣሉ፣ ይሠጣሉ። ተቀባዩም ያንኑ እየለመደ በሕይወቱ ዑደት ላይ መጓዙን ይቀጥላል። ለመሆኑ ለመነሻ ያህል ከቃል አወጣጡ ብንነሣ እንኳ ጡረታና ማሕበራዊ ዋስትና ምን አንድ ያደርጋቸዋል? ወይስ ምን ይለያያቸዋል? ብለን ብንጠይቅ። ይኼንን መልስ እኔው ልንገራችሁ። በፊደል ቅርጽ ከመለያየታቸው በስተቀር ምንም በማያሻማ መንገድ ሁለቱም አንድ ናቸው። ምናልባት ግን......ለወደፊቱ አንዱን ቀን ሌላ ቃል ይወጣል ብላችሁ ካሰባችሁ «የአዛውንቶች ሕብረት» ወይም «የአረጋውያን አለኝታ» የሚል ዓይነት ይሆናል። በእነኢህ ቃልት ላይ «ኮሚሽን» ወይም የዱሮው ከናፈቃችሁ «ሚኒስቴር» የሚለውን ከጨመራችሁበት ጥሩና ወሳኝ ቃላት አማርጣችሁ ፈጠራችሁ ማለት ነው።

እኔ ሳይቸግረኝ ወደ ቃላት ሁኔታ ገባሁና ነው እንጂ አሳቤስ ዝም ብዬ «ጡረታ.....» የሚለውን ይዜ ገር ገሩን እያዋዛሁ ላጫውታችሁ ነበር። ዋዛ ነገር ግን ሁሌም ባይሆን አንዳንዴ ቁም ነገር ኣያጣውምና ያን ያንን እንደፈለጋችሁ እዩት። ቢሆንም.....እዚህ ላይ ጡረታ ባሁኑ ዘመን ምን ማለት እንደሆነ በትንሹ እንናገር.......እኔ ትጦራልች። ልጅ እናት አባቱን የሚጦረው ዲቪ ደርሶት አሜሪካ ሲሄድ ነው። አባትና እናት ደርሷቸው ከሄዱ ግን እነሱ ራሳቸው ምነው ልጅ በሆንኩ የሚሉ ይመስለኛል። እዚህ በአባት ጡረታ አበል የመነመነች ዶሮ እያጣጣሙ የበሉ ልጆች ውጭ አገር ሄደው ባይጣፍጣቸውም የፈረንጁ ትልቅ ዶሮ /ከፈረደባቸውም ተርኪ/ በጣም ትልቅ ዶሮ አድርገው ቢያዩ ምን ያስገርማል? «ያላዩት አገር አይናፍቅም» ቢባልም «ያላዩትን አገር ዲቪ ያስናፍቃል» የሚለው ደግሞ ዘመነኛ ምሳሌያዊ አነጋገር ሊሆን ይችላል።

ይሄን ያልኳችሁ ያለ ምክንያት አይደለም። እኔ ጡረታ ስወጣ ዲቪም ሆነ የሚናፍቅ አገር አልታየኝም። ይልቁንስ «እንኳን ለዚህ አበቃህ» የሚል ነገር ያልተጻፈበት የመሥሪያ ቤት ደብዳቤ ገና እንደደረሰኝ ራሴው ፈጥሬ ከቀድሞ የተሻልኩ አዛውንት የሆንኩ መሠለኝ። አካሄዴ ራሱ ሳላስበው ተቀየረ። ሠልፍ ላይ እንደለመደ ወታደር ቀጥ ጠንቀቅ እንደ ማለት እግሮቼም የዱሮ መወላገዳቸውን ትተው ቀጥ ጠንቀቅ እንደ

ማለት ይቃጣቸው ጀመር። ጡረታ ወጥቼ መሥሪያ ቤቴን ስሠናበት እንደ አስናቀች ወርቁ ሻይ ቡና ያለኝ ባይኖርም የፐሬስ ድርጅት እድርተኞቼ አዋጥተው የአንገት ሀብል ስለ ሸለሙኝ ሞራሌ ከፍ ብሎ ነበር።

ዱሮ የአራት ኪሎ ግሪኮች የሚያደርጓትን ባለ ባልና ሚስት ኮፊያ አልገዛሁም እንጂ «ሠፊ ናቸው አያምሩም» እያልኩ አሮጌ ቁም ሣጥኔ ውስጥ የረሳሁዋቸውን ሱሪዎች፣ ከረቫቶች፣ ባለቁልፍ ወፍራም ኮት፣ ሹራቦች፣ ሰደርያ፣ ካፖርት ሳይቀር........ፈላልጌ ለጡረታ ዘመኔ አፀዳድቼ አዘጋጀሁ። ለምን እንደሆነ አላውቅም - ዱሮ ያልናፈቀኝ ጡረታ አዲስ ነገር የሚያመጣልኝ መሠለኝ።

ይህም ብቻ አልነበረም፣ እንደ አብዛኛው ጡረተኛ የተለያዩ ኪሶች ያሏትን የአንበሳ ምስል የተቀረጸባትን የቆዳ ቦርሳዬን ሣጥኖቼን ሁሉ በርብሬ ፈልጌ አገኘሁ። መቼ እንደገዛሁዋት ዳርማር ይሁን አስኮ ትዝ አይለኝም። ብር ለመደበቅ ግን እሷን የመሠለ የኪስ ቦርሳ የለም። መቼም ሁሌም ባይሆን ጠንቃቃ ጡረተኛ ከጓደኖቹ ጋር ድራፍት ሂሳብ ላይ መሸዋወዱ አይቀርምና ከአንድ ብር አንስቶ እስከ ሃምሳ ብር ኖት በተለያዩ ኪሶች ለማስቀመጥ የኔ ዓይነቷ ቦርሳ ጠቀሚታ ጫት ሻጮች በየሠሌኑ በየግድግዳውና አሮጌ ወረቀቶች ትላልቅ ኩባይዎች ውስጥ ከሚደብቁበት ሁኔታ የተሻለ ነው።

ከወጣትነት ወደ ጐልማሳነት ያለፍኩበት ዝመነ ምንም ስሜት ያልሠጠኝ ሰውዬ ወደ ጡረታ መሸጋገሬ እንዴት እንዳስፈነደቀኝ እስከ ዛሬም አይገባኝም። የሚመጣው ሕይወት ብሩህ ሆኖ የታያኝ ያኔ ነበር። እንደውም ጡረተኞች በብዛት ወደ ሚገኙበት አንድ መሀል አራዳ የታወቀ ቡና ቤት /ሆቴል/ በዚያው ሰሞን ሄድኩ። ደሀብ ሆቴል የሚባል ገና ዩኒቨርሲቲ ስማር የማውቀው ጨል ቤት ነው። ስገባ አንድም ባዶ ወንበር አልነበረም። ሆኖም የተለመደ መሆኑን አውቅ ስለ ነበር ከበረንዳው ትንሽ ዝቅ ብሎ በሚታየው የደረጃ ድንጋይ ላይ ከመሀላቸው ሄጄ ተቀመጥኩ። ግራ ቀኝ ያሉትን ስመለከት ሽበታቸው - አንደበታቸው - ትሕትናቸው ሁሉ እየማረከኝ ሣል ወሬያቸው አልጥመኝ አለ። አንዳንዱ ስለሚያዋውለው ቤት ያወራል። አንዳንዱ የቤት ሠራተኛ - ዘበኛ - ታማኝ የሆነ፣ የዲስ አበባ የማያታልላት ጥሩ ጉልበት ያላት.......እያለ አጠገቡ ላለው ያወግጋል። በሬያቸው መከከል የሚጠብቁት ሰው እንዳለ ገምቻለሁ። «ተወኝ እባክህ........የዘመኑ ቀጠሮ.......» እያሉ የሚያልጐመጉሙም አሉ።

ከነዚህ ሁሉ ጆሮዬን የሳበው የሁለት አዛውንቶች ጨዋታ ነበር። ወሬውን የጀመሩት ሰውዬ የተጣጠፉ ቀይ ክላሴሮች ይዘዋል። ሰማያዊና ጥቁር ስክሪፕቶ ኮታቸው ላይ በግልጽ ይታያል። በተቀመጡበት ድንጋይ ላይ ፍትሐ ብሔርና ወንጀለኛ መቅጫ አሮጌ መጽሐፍ አለ። ከአወራራቸው እንደሰማሁት በሕግ ጉዳይ ላይ የተሰማሩ ናቸው። በጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውስጡን ሳልፍ የማያቸውን ባልና ሚስት የሚያስታርቁ ወይም ለፍርድ ቤት ያላቸውን ጉዳይ እየጻፉ ሰላማዊ መድረክ የሚያዘጋጁትን ዓይነት ሰዎች ይመስላሉ።

«እኔኮ አንቀጽ እየጠቀስኩ ጽፌ ላስረዳቸው እሷ ከት ከት እያለች ትስቃለች» አል ባለክላሴሩ ወሬ ጀማሪ።

«ምን አባክህ የዛሬ ጊዜ ባልና ሚስት.......» አሉ አጠገባቸው የተቀመጡት ሰውዬ።

«የባልየውስ አይገርምህም?»

«መቼ አየሁትና ይገርመኛል» አሉት አቀረቀሩ እኒያኛው

«ይኸውልህ.......መቼም ከልጅነትም ባይሆን ገና ጐረምሳ ሆኜ ታውቀኛለህ......እኔ ከሚስቴ ሳልታረቅ መሞቷ የሚቆጨኝ ሰው ታረቁ እያልኩ በሽምግልና ስወትውት......ከሁለት አንዳችን ስንሞት ነው የምንታረቀው ይበለኝ?!»

«ታዲያ ላንተ ካሰቡ አንዳቸው መቼ እንደኢሞቱ አልጠየቅካቸው?»

«አይ አንተ ደሞ ዕድሜ ልክህን እንደቀለድክ ነው» አሉ ባለክሴሩ

«ዕድሜ ልኬን ባውቅማ መቼ እዚህ ዱሮ ሥሠራ ባኖርኩት ሥራ አዲስ ተቀጣሪ ለመሆን ደላላ ተጉልቼ እጠብቅ ነበር!» አሉና ከፉሪ ተራራ አናት ላይ የተንጠለጠለውን የዳመና ቁልል አሻቅበው እያዩ ተከዙ። እኔም የመጀመሪያ ዕለት ጡረተኛ ኩራቴን እነዳነገብኩ ትነስቼ ወደ ምሄድበት ሄድኩ።

ጡረተኛ ሲባል መቼም ቢሜ ደብተሩን እየተማፀነ አበሉን እስኪሞት ድረስ መቀበል ዋና ሥራው ነውና የጀመሪያ አበሌን ስቀበል ያጋጠመኝን ላጫውታችሁ።

እኔ ገና ደብተሩን ከመቀበሌ ራሴን የጠየኩት ጥያቄ ነበር። ለምን የጣት አሻራ ፊርማ እንደሚያፈልግ እንኳ የነገረኝ ሰው አልነበረም። ምናልባት ግን......በቆየውና ዘመናትን ባስቆጠረው ዛሬም ባልተሻሻለው አሠራር ላይ ችግር ይኖር እንዴ? ብዬ አሰብኩ። አሻራ የሚፈልግ ፖሊስ እንጂ እንዴት ጡረታም ይባል ማሕበራዊ ዋስትና........ይሄ ነገር ሊያስፈልገው ይችላል?.......እያልኩ ሳለሁ «የመጀመሪያውን ደብተር ይዘህ ሂድ እንጂ ምን አገባህ» አለና የጭንቅላቴ ግማሽ ጐን ነገረኝ።

የጡረተኛ ጊዜዊ ኩራቴን አሁንም እንዳነገብኩ አበሉ ወደ ሚሰጥበት ሄድኩ። ገና እንደገባሁ ብዙ ሰዎች በአግዳሚ ወንበሮች ላይ ተቀምጠዋል። ቦታዬን ፈልጌ ቁጭ ካልኩ በኋላ የወደፊት ጓደኞቼን ቀስ ብዬ እመለከት ጀመር። የሐዘን ልብስ የለበሱ ሴቶች ልጅ እግር፣ መካከለኛ ዕድሜ ላይ ያለች ደሞ አዛውንት የሆኑ......በሰዎች ተደግፈው የመጡ ዐይናቸው የደከመ - አንካሳ ሆነ ለአበሉ ሲሉ ማንከሳቸውን ለጊዜው እንደማይታወቅባቸው የሚያደርጉ መሆናቸውን ተመለከትኩ። በአንድ የዓይን እሩምታ ሳያቸው ግን አብዛኖቹ ውስት ውስጡን ደስ ያላቸው ቢሆኑም አበል ለመቀበል ሳይሆን በአኳኋናቸው አቤቱታ ሊያቀርቡ የመጡ ይመስላሉ። የሚገማችሁ ግን ያን ያንን ካየሁ በኋላ ለምን እንደሆነ ባላውቅም የራሴ ዕድሜ መግፋት ያ ቅድም ያልኳችሁ የቅልጥፍና አካሄዴ ተጨምሮበት ነው መሰለኝ ከኖርኩበት ዕድሜና ቅልጥጥ ያለ እውነት አፈትልኮ ቢያንስ ስድስት ወይም ሰባት ዓመት የቀነኩ መስሎ ተሠማኝ።

አቤት! ጡረተኛ መሆን! «አያድርጋችሁ»? እንዳይባል እርግማንም ምርቃትም ነው ነው። ነገሩ ያለው ግን ከሁለቱ አባባል መካከል ነው በደንብ ለማሰብ ምንም ጊዜ አላገኘሁም። «ሚሊቴሪ በዛ በኩል ሲቪል በዚህ በኩል» የሚል ድምፅ ስሰማ ብግድ አልኩ። መነሣቴን እንጂ የት እንደምሄድ ወይም እንደምቆይ በፍጹም አላውቅም ነበር። ልጅ እግሮች - አሮጊቶች ሽማግሌዎች ተነሣን እንጂ የሠልፉን ሥርዓት የሚያውቅም የለም። እንዲያው ብቻ እየተተራመስን ሠልፍ የሚመስል ነገር አየንና ቦታ ቦታ ያዝን። በትርምሱ መሀል አንድ ሽበት የተጐናጸፉ ሴትዮ ጀርባ ቦታ ቦታ ያዝን። እንዴት እንደሆነ እስከዛሬ አልገባኝም። ዘወር አሉና «ሚሊቴሪ ነህ እንዴ አንተ?» ብለው ጠየቁኝ። እኔም ቶሎ ብዬ «ገና የመጀመሪያ ቀን ጡረተኛ ነኝ» አልኳቸው። «እይ.......አንተማ ሲቪል ነህ ማለቴ ነው ቦታህ ሌላ ጋ ነው» ሲሉኝ ቅጥ ያጣው ሠልፍ አናዶኝ ትቼ ለመሄድ ቃጣኝ።

ወዲያውኑ አድን ደርበብ ያለ ጥሩ ሙሉ ልብስ የለበሰ ሰውዬ በመሰብሰቢያ የቀበሌ አዳራሽ ሳናስበው ብቅ አለ። «ዝም በሉ እስቲ ሁላችሁም!» አለ ወፍራም አጀቹን በጭብጨባ እየመታ። የአፍዝ አደንግዝ ዓይነት ከኔ ጀምሮ ሁሉማ ጭጭ ማለት ጀመረች። ስታዩት ድምፀ መረዋ ሊያክል ምንም አይቀረው። ደግሞ ከቁመቱ ጋር ደስ የምትል ትንሽ ቦርጭ አለችው። «በየምድባችሁ ተሠለፉ! ቶለ በሉ!» ብዬ ሲናገር ሁላችንም በየቦታችን ጸጥ ብለን ቆምን። ከዚያ በኋላ ከኮሚሽኑ ከመጡ ሰዎች ካርዶቹን ተቀበለና ስም አንድ በአንድ ይጠራ ጀመር። «ለካ የጡረታ ሰዎች ካርዶቹን ተቀበለና ስም አንድ በአንድ ይጠራ ጀመር። «ለካ የጡረታ ስዎች እንዲህ ያለ ቀልጣፋ አስተባባሪ አላቸው?» ብሎ እንደ መገረም አድርጎኝ አስተውል ጀመር።

ስማችንን ፈጠን ፈጠን እያለ ሲጠራ የእኔ ስም ላይ ደረሰ፡፡ «መስፍን ኃይለማርያም» አለ ጮኽ ብሎ፡፡ ዱሮም ቢሆን የአባት ስም ሲሳሳት እከፋለሁ፡፡ ደሞ ዕድሉን ካገኘሁ ይታረምልኝ ከማለት ወደ ኋላ አልልም፡፡ ስለዚህ ዱሮ እንደ ለመደብኝ ወደ አስተባብሪው ሰውዬ ጠጋ አልኩና፡፡ «የአባቴ ስም ሀበተማሪያም ነው እኮ» አልኩት - ገራ ተባ ብዬ፡፡

ቀልጣፋው የአዳራሹ አስተባባሪ በጆሮው የተነፈስኩለትን ከሰማ በኋላ አፉን ወደ ጆሮዬ ሲያስጠጋ፡፡ «ጡረታ ኮሚሽን ወይም ማሕበራዊ ዋስትና ምን አሳስቦኝ ይሆን?» የሚል ሥጋት ገባኝ፡፡ እሱ ግን በጆሮዬ ያንሾሾከው ሌላ ነገር ነበር፡፡ «እባክዎን ችግር አይፍጠሩብኝ፡፡ እኔ አውቃለሁ፡፡ ሀብተ ማርያምም ሆነ ወልደ ማሪያም አበልዎን ዝም በሉና ይቀበሉ፡፡ ጣጣ አይፍጠሩ» አለኝ፡፡ ለካ እኔ የጡረታ ኮሚሽኑ የመሰለኝ ሰውዬ ራሱ የደርግ ሻለቃ ጡረተኛ ነበር፡፡

የመጀመሪያ አበሌን ከተቀበልኩ በኋላ ደንበኛ ሆንኩ፡፡ ወሩ ወራትን ሲቆጥር መሰብሰቢያችንን ሰዎቹን ሁሉ እየተላመድኩ ሄድኩ፡፡ በመጀመሪያው ዕለት የድሮ ጓደኞቼን በማግኘቴ ደስ ብሎኝ ነበር፡፡ ቀስ እያልኩ እያየሁ ስሄድ «ጋዜጠኛው» እያሉ የሚጠሩኝም አጋጠሙኝ፡፡ ዝም ብዬ ከምይዘው ጋዜጣ በተጨማሪ ዋስትና የሚባል ጋዜጣ መኖሩንም አውቄ ደንበኛ ሆንኩ ጋዜጠኛ ተብዬ መታወቁ እየገረመኝ ሣለ አንድ የሕክምና ዶክተር ጡረተኛ መሆኑን አየሁና የምይዛቸው ጋዜጦች ከሱ ቦርሳ ጋር ማወዳደር እንደማልችል ተገነዘብኩ፡፡

በዚህ አጋጣሚ ጡረተኛ ሲባል ወረተኛ መሆኑን ልገልጽላቸው እፈልጋለሁ፡፡ እኔን በጋዜጠኝነት ሲክቡኝ የነበሩት ሁሉ ወደ ዶክተሩ ግልብጥ አሉ፡፡ እኔ እንደ ሆንኩ የጡረተኛ ኩራቴን እንደያዝኩ መሄዴን እንደ ክብር ቆጥሬው ነበር፡፡ ጋዜጣ የሚለው ቃል ደጋግመው ሲያነሱ ቆይተው የማልጠቅማቸው መሆኔን ባውቅም የዓለም ወሬ የሚጠይቁ መሰሎኝ ነበር፡፡ እነሱ ግን የሚስቡትም ሆነ የሚጨነቁት ካሸሪው አበሌን ሳይከፍለኝ ተነሥቶ ይሄዳል ወይ.......የሚለው ላይ ነው፡፡

ጡረተኛ መሆን መመረቅም መረገምም ነው፡፡ ዶክተርም ይሁን ግንበኛ፣ ባለስልጣንም ይሁን ሠርቶ የደርግ ሻምበል ወይም ጽዳት ሠራተኛ ሁሉም......አበል ሲቀበል በቀኝ አውለኝ እያለ ሲያጣም «ምን በደልኩህ?» እያለ የሚኖር ነው፡፡

እና......እየለመድኩ እየለመድኩ ስሄድ ብዙ ወሬ እሱማ ጀመር «የማሕበራዊ ዋስትና እኮ ሰባ ሁለት ሚሊዮን ብር እተረፈ» የሚል ዓይነት እውነት ለመናገር እኔ ራሴ በጆሮዬ ሠምቼዋለሁ፡፡ ያንን ከሠማሁ በኋላ ጋዜጠኛው ጡረተኛ እውነት ይሁን ውሸት ባላውቅም የራሴን ልብ ወለድ ጨማመርኩበት፡፡ የሚያስቀምጡትን ፋይልም ስነድም በሐሣቤ አየሁና በልብ ወለድ ጭንቅላቴ እንደዚህ የሚሉ መሠለኝ፡፡

«የሞተ - የኮበለለ - ሲጠራ የቀረ - ወንዝ የወሠደው - ሊስት ውስጥ ስሙ የሌለ - ቢኖርም ቀርቦ ያላመለከተ - ስሙ ሲለወጥ ያልተናገረ - ሐኪምም ጠበልም የማያውቀው» የሚል ዓይነት፡፡ ደሞ እንደ ሠማሁት ከዚህ የሚብስ ዓለም ያልደረሰበት ሰነድ አለ አሉ፡፡ ጥቂቱን ለመቀነስ «ያበደ - ፎርም ያልሞላ አድራሻው ያልታወቀ - አውሬ የበላው - ፎርም ሳይሞላ ቆይቶ የመጣ - አለ ሲባል በዕድር ምዝገባ ሞቷል የተባለ» ሌላም ሌላም፡፡

ለማንኛውም ይሄንን ጽሑፍ መቋጨት ያለብኝ ይመስለኛል፡፡ ገና ከመጀመሪያው ጡረታ ወጣህ ስባል ምን ያህል ኩራት ተሠምቶኝ እንደ ነበረ አጫውቻችኋለሁ፡፡ በኋላ ግን ሁኔታዎችን ከተስፋ ጋር ላይ ቆይቼ ሣለሁ አንድ የሚገርም ነገር በዚያው አዳራሽ አጋጠመኝ፡፡

ሴትዮዋ አበላቸውን ይቀበሉና ወደ ግድግዳው ይዞራሉ። አስራ ሁለት ዓመት የማይበልጠው ልጅ እሥር እሥራቸው ይላል። ለምንድነው ወደ ግድግዳ የሚዞሩት ብዬ ራሴን ጠየቅሁ። ለካ.....ነገሩ ሌላ ነው። ሴትዮዋ አበላቸውን ከተቀበሉ በኋላ ገንዘብን በሆነ ነገር ጠቅለል ያደርጉና በስስ ፌስታል ከተው በደረታቸው ወይም በጡረታቸው መካከል ያስቀምጣሉ። ወደ ግድግዳው የሚዞሩት ይሄንን ለማድረግ ነው። ትንሹ ልጅ የልጅ ልጃቸው እንደሚሆን ብገምትም ጠባቂያቸው መሆኑን ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም። እሳቸው ወደ ግድግዳው ዞረው ጸሎት የሚያደርጉ እየመሠሉ ገንዘባቸን ሲያስቀምጡ ልጁ ፊቱን ወደኛ አድርጎ እየመሠሉ ገንዘባቸውን ሲያስቀምጡ ልጁ ፊቱን ወደኛ አድርጎ አይኑን ከግራ ወደ ቀኝ ደሞ በተቃራኒው እያዟዟረ አንድ በአንድ ሲመለከተን ብታዩት......ትልቅ ባለሥልጣን ወይም ሀብታም የሚጠብቅ ዓዋቂ ሰው /ቦዲ ጋርድ/ ይመስላል። ሁኔታው ደስ ስላለኝ ጠጋ ብዬ ላወራው ፈልጌ ነበር። ልጁ ግን ከላይ እስከ ታች ትክ ብሎ አየኝና። «አንተን አያገባህም» በሚል ዓይነት ተግባቢነት ሳይታይበት የአዛውንቷን ሴትዮ እጅ ያዝ አድርጎ ተያይዘው ወጡ። በሌላ ቀን የሚቀበሉትን አበል በጣታቸው ፈርመው ሲቀበሉ ጠጋ ብዬ ሳይ አስራ ሰባት ብር ከሀምሳ ሳንቲ ነው።

# ሦስቱ ክፉ ቃላት

ምን ዓይነት ዕድል እንዳለኝ አላውቅም። የሎተሪ ቲኬት ቢያንስ 40 ዓመት ያህል ገዝቻለሁ። ሐኪም ቤቶች፣ መሥሪያ ቤቶች መብራት ኃይል፣ ኢሚግሬሽን ቀበሌ.......ሁሉ ሄጃለሁ። ከአገር ውስት ገቢ በስተቀር ያልደረስኩበት አጋጣሚ ያለ አይመስለኝም። ዕድልም ሆነ ተራ የሚሉት ነገር ደርሶኝ አያውቅም። ሌላው ቀርቶ ከትልልቅ ሰዎች ጋር ጠጅ እየጠጣሁ በማመሸበት ጊዜ ለፋሲካ ከዕጣ የሚዞር ሙክት ይደርሰኛል ብዬ የሁለት ብር ቲኬት የገዛሁት ምሽቶች ተቆጥረው አያልቁም። በእርግጥም በዚህ በዚህ ረገድ ሰመረልኝ የምለው ነገር የለም።

የሚገርማችሁ ግን ከላይ ከዘረዘርኳቸው ተቃራኒ የሆኑ ነገሮች ላይ ዕድለኛ እሆናለሁ።

ለምሳሌ ነፍስ የላትም የምትባል ትንሽ ኪዎስክ ውስጥ ስገባ (ፀጉር አስተካካይ ቤት ወይም ሽሮ በኢት ልትሆን ትችላለች) ግድግዳው ላይ ዓይኔ ያርፍና በጉርምስና ዘመኔ የነበረውን አሜሪካዊ ተዋናይ፣ ወይም ኃይለ ሥላሴ የገናን በዓል ሲያከብሩ፣ ንጉሥ ሰለሞን ቀርቦ በአዲስ አበባ ዘመን ላይ ዓይነት ፎቶዎች ያጋጠሙኝና......መመልከት እጀምራለሁ።

በተለይ መፀደጃ ቤት ንጹሕ ሆነው የተጣሉ የዱሮ፣ የትናትን፣ የዛሬ ቅዳጅ ወረቀቶች ያጋጥሙኛል። እውነት ለመናገር.....ፕሬስ ድርጅት ለሥራ «አንድ ቀን» በሚል ዓምድ ላይ እፅፍ ነበር። ልጆች ስኳርም ይሁን ሌላ ነገር ገዝተው ሲመጡ «ይኸውልክ አባዬ ፎቶክ» ያሉኝ ጊዜ አለ። እኔ ራሴ የሆነ ነገር ጠቅልዬበት ስፈታው የራሴን ፎቶ አግኝቻለሁ።

ይሄን ይሄንን የሚወራላችሁ ዋና ዋናውን የዕድል ቁልፍ አግኝቼ ባላውቅም ትናንሽ የሚመስሉ (ወይም የሆኑ) ነገሮችን በአጋጣሚ የማግኘት ገጠመኙ አለኝ ፈልጌ ነው።

የገጠመኝ ነገር ከተነሣ ስለ ሦስቱ ክፉ ቃላት ከመናገሬ በፊት ለዚህች ጽሁፍ መነሻ የሆነኝን ላጫውታችሁ እፈልጋለሁ። መፀዳጃ ቤት ዝም ብሎ የተጣለ የጋዜጣ ቁራጭ አገኛለሁ። አርዕስቱን ሳየው «የስካር ዓይነቶች»

ያላል። እንደ ዛሬው ሳይሆን ከሕይወቴ ሁለት ሦስተኛውን ባሳለፍኩት ዕድሜዬ የማውቀው ነገር ነበርና ትኩረት ሰጥቼ አነበብኩት። «ሦስቱ ከፉ ቃላት» ብዬ ለመጻፍ ያነሳሳኝ እሱ ነው።

በመጀመሪያ ስካርን ከነጠንቁ የሚተነትነው ወርቀት ምንጩ ምን እንደሆነ አይታወቅም። ተቆርጦ ወድቋል። መሠለኝ አይታይም። ስካሩ የተመሰለው በዱርና በቤት እንስሶች ነው። ለምሳሌ «የጦአ ስካር፣ የአንበሳ ስካር......እንዲህ እንዲህ ያስደርጋል......» የሚል ዓይነት ነው። ዝርዝሩ ማንሣት መቼም የማይሆን ነውና.....የስካርን ክፉነት ከተጠቀሱት ምሳሌዎች ከአንዳንዶቹ ተነሥቼ ትንሽ ላውራላችሁ።

«የበግ ያስኮራል፣ ያንቀባርራል፣ የስጀንናል። ከሱ በላይ ሰው የሌለ ያስመስለዋል» ይላል እኔ ለምን ይሄ ሁኔታ የበግ ስካር እንደ ተባለ አይገባኝም። በግ ኩራተኛ ነው፣ ቀብራራ ነው ያለው ማነው? ከአንገቱ ቀና ብሎ ለነገው እርድ ከመዘጋጀቱ በስተቀር በግ ተጀንኖም ሆነ ተንቀባርሮ አያውቅም። እንዲያውም ክርስቶስ የዋህ ያደረገው በትህትና የመሰለው እሱን ነው። ለመኩራቱና ለመንቀባረሩ አወራ ዶሮ አለ አይደለም ወይ?»

«የዝምተኛ ስካር አያናገርም......» ይላል ያ ደግሞ የቀጭኔ ስካር ቢባል ይሻላል። ምክንያቱም ቀጭኔ ድምፅ የላትም።

«የአልቃሽ ስካር ያስለቅሳል......አዬዬ ያሰኛል» ይላል። ለምን የአዞ ስካር አልተባለም? በእንግሊዝኛ «Corocodile tears» ይባላል።

«የቀበሮ ስካር ራሱን በራሱ ለመቆጣጠር ይጠነቀቃል.....» ተብሎም ቀርቧል። ለኔ እንደሚገባኝ ግን በተረቶቻችን ተለምዶ ነው እንጂ በብልጠት ጦጣን የሚያህል የለም።

«የፍየል ስካር ፍትወትን ያበዛል፣ ያንቀዠቅዠል፣ ያቅበዘብዛል......» ተብሏል። ፍየል ቀዥቃዣ በመሆኑ ምክንያት ለዚህ ምሣሌነት መዋሉ አስገርሞናል። ምናልባት ገን ደርግ «የፍየል ወጠጤ ትከሻው ያበጠ......» ሰላለ ይሆን? ያም ቢሆን እኮ......ደርግ ዱሮ የተዘፈነውን አርጉልኝ አለ እንጂ ስለ ፍየል ቅንጣት ታክል ፍልስፍና አልነበረውም። ለማናቸውም ዝንጀሮና ድመት እያሉ ረጅም አንገቱን ለሰው ልጆች ቢላዋ ያዘጋጀ ፍየል የፍትወት ሥጋ ምሣሌ መደረግ የለበትም። አዲስ አበባችን በቆሻሻና በሰባራ ቱቦ እየገማች ከመሄዱ የተነሣ በጣራችንና በየፈራችን እያላዘኑ የሚሸኮረመሙትን የድመቶች ዓይነ ምድር በሆዷ ችላ ትኖራለች እንጂ ሽርሙጥናቸዋንስ በሚገባ ታውቃለች። በነገራችን ላይ......ዝንጀሮ ከቀናተኘነቱ የተነሣ......እጁን ሚስቱ ብልት ላይ አድርጎ እንደሚተኛ አዳኞች ሁሉ የሚያውቁት ነው። ስለዚህ ምስኪን ፍየልን እንደሚተኛ አዳኞች ሁሉ የሚያውቁት ነው። ስለዚህ ምስኪን ፍየልን ጮማ ነው፣ ቁርጡ ይጣፍጣል፣ ኧረ የፍየል ሥጋ..... አያላችሁ ብሉት፣ አኝኩት፣ ሰልቅጡት፣ ቆርጥሙት እንጂ ያለ ስሙ ስም አትስጡት።

ለማንኛውም «ስካር» ን ከፉ ከምላቸው ቃላት የመጀመሪያ አድርጌዋለሁ። ከላይ ከተተነተነው በተጨማሪ ጥቂት ልጨምር ብል.....የሀብትማ ስካር፣ የድሀ ስካር፣ የሞኝ ስካር፣ የብልጥ ስካር.....እያልን ክፉነቱን ማሳየት እንችላለን። ነገሩን በአጭሩ ላድርገውና.....ሀብታም ቢሰክር ከጠዋቱ አሥራ አንድ ሰዓት ተኩል ላይ አይጦች ይቀስቅሱታል፣ አሥራ ሁለት ላይ ወፎች በጣዕሙ ዜማቸው ያጅቡታል። እሀ ቢሰክር ድንጋዩን ተንተርሶ ሎተሪ ሲደርሰው ጥሩ ሕልም አይቶ እሱም አሥራ ሁለት ሰዓት ግድም ብንን ብሎ ወደ ሽቀላው ይሮጣል። ሞኝዋ ሰካራም የብልጡን ክንድ እንደተንተራሰች፣ ከአትላንት ያስመጣላትን ውስጥ ልብስ የትልቅነት ምልክት አድርጋ፣ በቅርብ ያለውን ዲቪ ረስታ.....ከብልጡ የሚቀርባልትን ሕስብተ - መና እያሰበች ቦስተንና ዋሽንግተን ዲሲን በሐሳብዋ ዞራ ዞራ.....ሲነጋጋ ኢትዮጵያ ትመለሳለች።

ሁለተኛ «ክፉ» የምለው ቃል ኩራት ነው። ኩራት ስንል የሕሊና ኩራት ወይም (pride) ማለቴ አይደለም። ይሄ የስዕብናን መደፈር የማይፈልግ ዜግነትና ሃገራዊነትን በተራ ድፍረት የሚያስነካ የኩራት ዓይነት ነው። ከዚህም ጋር ራስ መቻልን፣ ይበልጡኛል ብሎ አለማጎብደድን.....እና ሌላም ሌላም ያካትታል። በሌላ አነጋገር ሕሊና የሚፈቅደውና ያመነበት ነውና በሙሉ ልባችሁ ትደግፉታላችሁ።

ይቅር በሉኝና «ክፉ» ብዬ በሁለተኛ ደረጃ የማስቀምተው ኩራት ከዚህኛው በጣም የተለየ ከንቱነት መሠረት ላይ በባዶ ኑሮም በባዶ አስተሳሰብም በልፅጎ ፍፁም ሊለወጥ የማይችል....አሳዛኝና ሕብረተሰብ ጎጂ......የሆነ ዓይነት ኩራት ነው። ታዋቂው እንግሊዛዊ ባለ ቅኔ አሌክሳንደር ፓፕ ስለ ኩራት እንዲህ ይላል፡-

«Of all the cause, which conspire to blind man's erring judgement, and misguide the mind, what the weak head with strongest bise rules, is pride, the never failing vice of fools.»

«የሰው ልጅ ሚዛናዊ - ፍርድ የሚያቃውስ፣

አንጎልን አንሸዋርሮ አስተሳሰብ የሚያፋልሱ፣

ከማንም ከማንም አድመኛ፣ ከእውነተኛ ጉዳዮች የሚስብ......

ደካማና ተራ አዕምሮ፣ በቀላሉ ገዝቶ፣ ጠንክር በርታ እሚለው፣

በቃኝን ያማያውቅ የተንኮል መሣሪያ፣ የቂሎች ኩራት ነው።»

አሌክሳንድር ፓፕ (ወጎች በትችት ላይ)

ለመሆኑ ኩራት ማለት ምንድን ነው? ኩራት በመሠረቱ የሀብትም የድህነትም ጠር ብዬ አምናለሁ። ምክንያቱም የሚኮራ ሰው ሀብትን እየናቀ፣ ድህነትም እየተጠየፈ.......ይሄድ ይሄድና.....በመጨረሻ.....በሁለቱ መካከል እግሩን አንፈራጦ ቆይቶ ይቆይና እንደገና ወደ አንጡራ ሀብቱ ወደ ኩራቱ ይመለሳል። ይሄ እንግዲህ ገንዘብን ለማግኘት፣ ከሌላው አላንስም የሚለውን የሚመለከት ነው።

ሌላ ደግሞ የምናውቀው የኩራት ዓይነት አለ። ይሄኛው ከሁሉም በላይ ክፉ የምለው ዓይነት ነው። ይሄንን ለማጤን ከፈለጋችሁ የከበደ ሚካኤን «እሮሮ» የሚል ግጥም አንብቡ። «አባቴ እዛ ነበረ፣ አያቴ ኣ ተቀበረ አትበሉ......» የሚል ዓይነት አስተሳሰብ የያዘ ነው። ከዚህ ላይ ማብራራት ለዚህ ጽሑፍ አይሆንምና......ይሄ የኩራት ዓይነት በአንድ በኩል «ከእገሌ ተወልጃለሁ.....አባቴ፣ እናቴ እንዲህ ዓይነቶች.......ነበሩ ወይም ናቸው» የሚል ዓይነት ነው። የፊውዳልም የዘመናችንም ትዕይንት ግን ደረጃአው ይለያል እንጂ ኩራት አልተለየውም። ኃይለ ሥላሴ ትምህርት በሚያበረታቱበት ዘመን «ከትልቅ ተወልጃለሁ ማለት ሙያ አይደለም፣ ራስን ለትልቅ ሙያ መውለድ እንጂ» ያሉት ያለ ምክንያት አይደለም። «ኩራት ውድቀትን ያስከትላል» ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። «የኮራ የኖረ እንደ ኮራ ይሞታል» ይላሉ አረቦች።

የሚያኮራ ሰው ሌሎችን በመናቅ ጊዜያዊ ደስታን ያገኛሉ። በመለጡን አያምንም። ከአንገት በላይ የሚያደርገው ወይም ሆዱ እያወቀ ራሱን የሚያታልልም ቢሆን እየለመደው እየተላመደው ይሄድና ሁለተኛ ተፈጥሮው ይሆንበታል። ልላቀቅ ብሎ ቢሞክርም እንኳን ከባድ ይሆንበታል። ኩራት የሌለን ነገር ያለ ለማስመሰል ሆን ተብሎም ይደረጋል። መልክ የሌላቸው ሰዎች፣ ከትምህርት ደረጃ በጣም ዝቅ ያሉም ሥራ የማይወዱና ዓላማ የሌላቸው..... በጥቅሉ ሳይሆን አንዳንዶቹ በኩራት ይጠቃሉ። በዚህም የተነሣ ጓደኞቻቸውንና ዘመዶቻቸውንም እንዲያውም ሕብረተሰቡን ይጠላሉ። ያልበደላቸውንም፣ ሊበድላቸው ያላሰበውንም ይርቃሉ። ይሄ ሲገርመን ጥሩ ኑሮ ያላችወ አንዳንድ ሰዎች በምኑም በምኑም ዝቅተኛ ያልሆኑ

ሰዎች ከሕብረተሰቡ የተገለለ ጎራ ለመፍጠርና «ውስጣቸው» እንዳይታወቅ ከመፈለጋቸው የተነሣ ብቻ..... በብዙ መልኩ በር እንዲሆንላቸው ኩራታቸውን ሲማፀኑ ይታያሉ። በብዙ መልኩ ሲታይ ኩራት ሽፋን እየሆነ ማሕበራዊ ግብብነትን እንደሚያደናቅር የታወቀ ነው ፡

ሦስተኛው ክፉ ቃል ቅናት ነው ብዬ አስባለሁ። ቅናትን ሳነሳላችሁ የክፉ ቃላቶች ሁሉ ክፉ መሆኑን እያሰብኩ ነው። የጽሑፌ መጨረሻ ላደርገው የፈለግኩትም በዚህ የተነሣ ነው። ልብ በሉ ግን። እዚህ የማነሳው ቅናት መንፈሳዊ የሚባለውን አይደለም። ለደግ የሚቀና እግዚአብሔር የወደደው ነው። እኔ ግን ሳስበው እግዚአብሔር ፍቅርን ሲፈጥር ሠይጣን በልዩ መንገዱ ተሹለክልኮ ሳይታይ ሳይሰማ ቅናትን የፈጠረ ይመስለኛል። አለዚያማ ለምን ሰው የሚወደውን ይገድላል? አለዚያማ ሰው ለምን ፍቅረኛው ቆንጆ ሆና እንዳትኖር ይፈልጋል።

ለመሆኑ ቅናት የሚባለው......ቅፍርን አስታክኮ፣ በሠይጣን እንኮኮ እየተባለ ታዝሎ የሚመጣ የምድራችን ጉዳጉድ የሆነ ከይሲ ክስተት ምንድን ነው? እነ ሙሉቀን መለሰ የገጠር ግጥማቸውን አሰባስበው በጥሩ ድምፃቸው «ወይ በሞተችና ተዝካርዋን ባስበላኝ» ሲሉ እዚችው ያልሞተች አፈር ላይ ቁጭ ብለን አዳምጠናል። ዘፈኖቻችን ደግሞም ፊልሞቻችን ጽልመታዊ የሆነ ከዳሽኝ፣ ዓይነት ሂደት እያዘዙ ፍቅርን እያጨለሙ፣ በል ሲላቸው ማጠንጠኛቸውን በግድያና በፖሊስ ጋጋታ (ባለፈው የቀበሌ አብዮት ጥበቃ እንደነበረው) እያደረጉ...... ሠይጣናዊ ቅናትና በተዘዋዋሪ መንገድ ሲያጎላምሱ እናያለን። አልፎ ተፍሮ ሚዲያችን «ቅናት ከሌለ ፍቅር አለ እንዴ?» የሚለውን አስተሳሰብ በቃሉ ምልልስ ሲያስተጋባ ሰምቻለሁ።

«ካልደበደበኝ፣ ካልቧጠጠኝ፣ ዝም ብሎ አምሽቶ ከገባ ባንቀው ይሻለኛል» እያለ ሴቶች አወርተዋል። ሌላው ቀርቶ አንጋፋአው የሃበሻው ንጉሥ ጥላሁን ገሠሠ «ካላነጫነጨ፣ ካላበሳጨ፣ ምን ፍቅር ይባላል?» የሚል ግጥም እንካ ተብሎ ተሰጥቶት በውብ ድምፁ ዘፍኗል። ነገር ቢበዛ በሆድ ኣያጫንም» አይጫንም ብዙ ብዙ ማለት ይቻላል።

እንደ አንጋፋው ጳውሎስ ኞኞ የድምፅ ጋዘጣ አባባል ግን አንድ ጥያቄ አለኝ። ፍቅር ምንድን ነው? እንደ ክፍለ የሱስ አበበ፣ የጥላሁን ገሠሠ ገጣሚ አባባል ፍቅር ማለት ፀብ ነው። ክፍለ የሱስ ይሄንን ሲለኝ እንደ ቀልድ አየው ነበር። አሁን ሳስበው ፍቅር እውነትም ፀብ ነው። ምክንያቱም ጥሩ እንገር ቢሆንም ቅናት የሚሉት ሠይጣን የማጋልበው ፈረስም አብርቶ አለ። በተራ አንጎሌ ይቺን ዓለም ሳያት........ነገ መሞታችን ሳይቀር፣ ለምን አፈር ለሚበላው ሥጋ ደጉን ማሰብ ትተን ክፉውን እንፈልጋለን? እያልኩ በየዋህነት አስባለሁ።

ደሞ አንዳዴ......ለምንድን ነው ጽልመታዊ (Dark Side of Life) ይሉታል አንዳንዶቹ የሆነ የፍቅር ገጽታ ብቻ በሙዚቃው፣ በቲያትሩ በፊልሙ የሚታየን? ለምሳሌ «ቀጠሮሽ እየጠበቅኩ፣ ያች ቀን ትዝ ትለኛለች መቼ ነው ፍቅራችንን አቧጡፈን ደስ የሚለን? ምንጊዜም የኔ ነሽ......» የሚል ዓይነት ዘፈን ሳንሰማ ልንሞት ነው እንዴ? ወይስ.......«ባቄላ ቆርጥመን እንፋቀርና መለያየታችን በእንባ መከተብ አለበት፣ ልብ አርጊ እንዳይቆጭሽ፣ ኋላ እንዳይቆጭሽ አሳይሻለሁ.....» የሚል ከድሮው ዘፈናችን የባሰ ተስፋ አስቆራጭ ነገር......ባህላችን ሊሆን ነው? ሕብረተሰባችንን ለቅናት እንደሚጋብዝ ትንሽ እንኳን ሊሰማን አይችልም።

እኔስ ቴዲ አፍሮ ይምጣልኝ። «ሽመን ደፈር» ን ደጋግሜ ሰምቼዋለሁ። ፍቅር የፈጣሪ መሆንዋን፣ ልዩነት እንደሌለበት አንድ ብንሆን እንዴት እንደሚያምርብን........በጥሩ ዜማና ግጥም አርክቶኛል ማለት እችላለሁ። ሃይማኖቶች በሽመንደፈር ጣልቃ ቢገቡ ቅናቱ የእነሱ እንጂ የእሱ አይደለም። በእኔ እምነት......ለክፉ ቅናት ቦታ ያልሰጠ፣ የዘመኔ ዘፋኝ እሱ ብቻ ነው።

ለማንኛቸውም.....ይህቺ ዓለም እግዜሩም ፈጥሯት፣ ሠይጣን በክፋነቱ ላጠናብራት ቢል፣ ለተንኰሉ ተንሸዋረን ባንጠብቀው ይሻላል.......በማለት ጽሑፌን እደመድማለሁ።

# ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ

## (ሕዝባዊ ስንኝ)

«ይምጡ በዝና አዲስ አበባ» የተባለች አንድ የቆየች መጽሐፍ አለች። ስለ አዲስ አበባ ከተማ ጠቃሚ ኢንፎርሜሽን የያዘች ነች። «ይምጡ በዝና» ምን የመሳሰሉ ፎቶ ግራፎች አሏት። ብትፈልጓት ግን አታገኙዋትም። ብርቅዬ ናት። የዛሬ አርባ አምስት ዓመት ግድም ከመፍረሱ በፊት የድሮ ፒያሳ፣ ኪንግ ጆርጅ ባር፣ ሳባ በረንዳ፣ ቴክሳስ ሻይ ቤት፣ ሲኒማ አድዋ ሁሉ በዛች መጽሐፍ ይታይ ነበር። ከላይ ከወደ ሴንትራል ቡና ቤት (አሮስቷቸው ይጣፍጥ ነበር) ስትወርዱ ልብስ ሠፊዎች፣ ፀጉር አስተካካዮች፣ አልፎ አልፎ ትናንሽ ሱቆች.....ታያላችሁ። ግን ቀኙን ከዞራችሁ ዛሬም የማልረሳው «ዞብል ቡና ቤት» የሚባል ረጋ፣ ደርበብ የሚሉ ሰዎች የሚያዘወትሩት ቡና ቤት ነበር። ከጊዮርጊስ ቁልቁለቱን ይዛችሁ ፊት ለፊቱን ከወረዳችሁ ቀን ቀኙን ቀጭን አስፋልት ስታዩ........ጎሚስታዎች ሁለት ወይም ሦስት ሱቆች እና ሱቅ በደረቴዎች ከረሜላ፣ ማስቲካ እያሉ ለመሸጥ ሲዘዋወሩ ካጋጠማችሁ በኋላ.......በቀጥታ ግራውን ትታጠፉና «ክብረ - መንግሥት) የሚባል ሆቴል ትገባላችሁ። እዚያ የሃምሣ ሳንቲም ፓስታል ፋርኖ፣ ወይም ቀይ ምንቸት አብሽ ከነእንቁላሉ በልታችሁ በሃምሳ ሳንቲማችሁ ሦስት ፊልማችሁን ታያላችሁ።

ትዝታዬ ይኼ ብቻ አይደለም። የከተማዋን ብቸኛ አገልጋይ ጋሪ ተከራይቶ ነድቷል የሚሉኝ ዘፋኙ አለማየሁ እሸቴ እኔ ሞጆ ከምትባል የገጠር ቦታ መጥቼ ቴክሳስ ሻይ ቤት ስገባ ዝም ብሎ በስሜት ብቻ ገና ፖሊስ ኦኬስትራ ሳይቀጠር እጁን እንደ ታምቡር መቺ ጠረጴዛው ላይ እያጫወተ ሲያንጐራጉር አየው እንደ ነበር አስታውሳለሁ። አለማየሁ እሸቴን ቆንጆ ፀጉሩን ማየትና ኤልቪስ ፕሪስሊን የመሰለ አካሄድ። አስተያየትና አቋቋሙን በተለይም የዌስተርን አክተሮችን ዓይነት አለባበስ ስናይ የወጣትነት ደስታ ይሰማን ነበር ፡

ይሁን እንጂ «ይሄንን ሁሉ ለምን ዘበዘብክ?» የምትሉኝ የዘመኑ ወጣቶች እንደምትኖሩ ሰለማውቅ «ወደ አዲስ አበባ» ፅሁፌ ልመለስ ነው። ዘፋኙ ምኒልክ ወስናቸው ዱሮ እንዳለው «ትዝታ አያረጅም። ትዝታ ይልቁንስ እየታደሰ ይሄዳል። የሙዚቃን የባህልን ሂደትም ሆነ ወጣ ገባ ጉዞ ማንም ከቶ ሊያቆመው አይችልም። እና.......ለዚህም ነው.....አሁን አዲሳባን እንዳሰኘኝ ልቃኛት የምፈልገው።

በሥነ - ጽሑፍ አምባ ካየሁትና ካጠራቀምኩት አንድ ሁለቱን ባወራላችሁ ደህና ይመስለኛል። ከ1948 የታተመው የደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሃዋርያት «አርአያ» የተሰኘው ረጅም ልብ - ወለድ ላይ አዲስ አበባ ተገልጻለች። ከፈረንሣይ አገር እርሻ ትምህርት ተምሮ የመጣው ዋናው ገፀ - ባህርይ አርአያ ከድሬዳዋ አንስቶ ከተማችንን እንዴት እነዳስተዋላት የምናውቅ ጥቂቶች ሳንሆን አንቀርም ብዬ አስባለሁ። ከዚያ ልብ - ወለድ አዲስ አበባ መጠነኛ ባህር ዛፎች፣ ጎጆ ቤቶች፣ ጭር ያሉ ሠፈሮች፣ «እንደምን ዋሉ» የሚሉ ቅን ሰዎች......የነበሩባት ከመሆንዋም በላይ ዘመኑ የፈቀደው ጌታና ተከታይ አሽከር፣ በቅሎ.....አልፎ አልፎ

ፈረስ......የሃገር ልብስ......እጀታ ያለው፣ የሌለው........ደሞ በርኖስ፣ በጣም......አልፎ አልፎ......ሌባ ብርቅ የሆነበት.....መንገዱ. ጐራንጉሩ ጠጅ ሳይሆን ማር ራሱ የሚሸትበት...... «ወንድሜ ሙት» ከተባለ ዳኛ ጋ ሁልጊዜም የማይኬድባት......መሆኗ ተገልጿል።

ከዚያ በኋላ.......አዲስ አበባ ጣልያን ገብቶ ሽርሙጥናን፣ ውሽትን፣ መካካድን......አስተምሮ ከሄደ በኋላ «እንደ ወጣች ቀረች» የሚባል ልብ - ወለድ ተጻፈ። እንደዚያ እንደዚያ የአዲስ አበባ ምንነት ይቀጥላል። ፊውዳሉ፣ ንጉሣዊ መሣፍንታዊው፣ ወጣቱ፣ ዩኒቨርሲቲው፣ ታክሲው ቤንዚኑ ሁሉ በዚች ያልታደለ ከተማ ላይ ቀጠለ። በእንጦጦ፣ በሾላ በወጨጫም፣ በፉሪም አካባቢ ያሉ ባህር ዛፎች «ኧረ ተውን» ማለት እስኪቀራቸው ድረስ ተጨፈጨፉ። ምን የቀረ ዛፍ አለ? ዱሮ ገና ልጅ ሆኜ በከሰል ባቡር የዱከምን ዳቦ የዱከምን ዳቦ እየገመጥኩ ስመጣ አያቸው የነበሩት ዛፎች ሁሉ ዛሬ አንዳቸውም የሉም። በሃምሣ ዓመት ትዝታ ሳስታውሰው ነገሩ እንዲህ ቢሆንም.....የዱሮ ርስት ማመልከቻዎች የነበሩት አንዳንድ የደረቁ የዛፍ ዘሮች፣ የቡና ቤት፣ የብስክሌት፣ የናይት ክለብ ወይም ምንትሴ.......ድንበሮች ሆነው አያለሁ። ነገር ነገሩ ልማት ነው። ኢኮኖሚው ግን ባለበት ይሄዳል። ይሄ ሁሉ የጊዜ ሂደት ነው።

ወይ አዲስ አበባ......ቢባል ያስኬዳል ለማለት ነው። ወይ አራዳ ሆይ......የሚለው ሲጨመር ደግሞ ወደ ደራሲ መንግሥቱ ለማ ግጥም ያመጣናል። ደራሲው «ባሻ አሸብር በአሜሪካ» በተሰኘው ድንቅ ግጥማቸው «ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ አገርም እድነ ሰው ይናፍቃል ወይ?» ያላሉ። ግሩም አባባል ነው። በግጥሙ አቀንቃኝ በባሻ አሸብር በላይ የሚንፀባረቀው «ጥቁር አፍሪካዊ አይደለሁም» የሚለው የዋህ ኩራትና «ኢንተርናስዮናል» ትዝብትን የሚጋብዘው ነጭ አምላኪነት በጣም የሚደነቅ የኬንት ሥራ ሆኖ ሳለ፣ «ሃገርም እንደ ሰው ይናፍቃል ወይ?» የሚለውን ሕዝባዊ ስንኝ ግን ለምን ተጠቀሙበት ያሰኛል። ምናልባት እሳቸው ግጥሙን በጻፉበት በ1959 አካባቢ (ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያነቡት የሰማሁት) ያንን ደግ ገጽታ ተላብሳ ይሆናል። ዛሬ ግን አዲስ አበባ የምትናፈቅ ነች ወይ? ጥሏት የሄደ ሁሉ እህል ውሃው ይሁን፣ ጊዜ ያላወደመው ሆያ ሆዬ፣ እትብቱ ወይም እዮሐ አበባዬ እየጠራው ይመለስ እንደሆነ እንጂ ከትርምስምስ ትዕይንትና ከፖለቲካ ጨዋታ በስተቀር ምን የሚስብ ነገር አላት?

እውነት ለመናገር..... አውቃለሁ ባይና አጉል ዘመናይ የሚውረገረግባት፣ ባለጌ ሴቶች ሌቱን ቀን ነው ብለው ያወጁባት፣ ለንግድ ብቻ ያሰፈሰፈ ሕብረተሰብ የሚራወጥበትና ውሽታሞች የነነኑባት መሆንዋ በግልጽ እየታየ የዛሬዋ አዲስ አበባ እንዴት ልትናፈቅ ትችላለች?

ግን አዲሳባ አትናፍቂም ቢሏትም አታፍርም። ወደድንም ጠላንም ልሳባችሁ፣ ላታላችሁ፣ ላጥምዳችሁ፣ ማለቷ አይቀርም። ዱሮ ልጆች ሆነን እንደምንጫወትባቸው የሚያማምሩ ብዮች ቀለማቸው ባማረ መኪኖቿ ልትሸውደን ትሞክራለች። እኛ ግን ውስጧን እናውቃለን። አርበኞች መንገድ የተገተረው የተርኪስ ባቡርና ቸርቺል ጎዳናን እያቃሰቱ ይወጡ የነበሩት ባሊላ መኪኖችዋ ይመለሱ ባንልም ከተማይቱን ራስዋን «ቢከፍቱት ተልባ ነሽ» ወይ «ውስጡን ለቄስ አትሁኝ» እንላታለን።

አውግቸው ተረፈ የሚባል ፀሐፊ «ወይ አዲስ አበባ....» በሚል በጻፈው ልበ - ወለድ ላይ «አዲስ አበባ ሕንፃዎችዋ ብቻ ሳይሆኑ ቆንጆ ሴቶችም ከምን እንደ ተፈጠሩ ለመገመት ያስቸግራል። እንዲያውም እኛ የማርያምን ስዕል ነው እያልን ገጠር የምንሳለመው ሁሉ የአዲስ አበባ ሴቶ ፎት ግራፍ ሳይሆን አይቀርም» ይላና በመቀጠል ከላይ የጠቀስኩትን ገመናዋን በሚገርም አገላለጽ ያቀርበዋል። «አዲስ አበባ መብራት በሙብራት ሆና፣ ተንቆጥቁጣ ያሸበረቀች ከተማ ናት። ነገር ግን አብዛኞቹ ነዋሪዎቿ እንደኔ ድሆች ከመሆናቸው የተነሣ ያን በየመንገዱ ሲንቦገቦግ የሚያድረውን መብራት ወደ ቤታቸው ስበው ማስገባት

እንኳን አይችሉም» ይላል። ይሄንን ሁሉ ቢነግሩዋት፣ ቢያስረዷት አዲሳባ ደንቆሮ ነች። አታፍርም። ውግቸው ተረፈ ከሚናገራቸው ነገሮች ዋናውን ቦታ የያዘው ብልጠት ነው። ኤዲያ...... ሁሉም ብልጠት ነው......የቀደመ ብልጥ ነው......ቀማኛው፣ ደንቆሮው ደደቡ፣ አስመሳዩ፣ ለማኙ ሁሉ ብልጥ ነው......ኧረ ስንቱ ይጠቀሳል?!........

ለመሆኑ አዲስ አበባ በውስጧ የያዘቻቸውን ልብ ብላችሁ ብታዩ ምን ይገለጽላችኋል? ዓይኑ እያየ ዓይነ ስውር ነኝ የሚል ለማኝ ጨርቅ ጠምጥሜ ቁስ ነኝ ባይ፣ በየዓውደ ዓመቱ ጃንጥላ ዘርግቶ ለታቦት መፅውቱ የሚል ማስረጃ ጽሑፍ ይዞ የሚዞረው፣ ጺሙን ለዚህ ሲል ብቻ የሚያጎፍረው.....ኧረ ስንቱን ይዛለች? ሰው ለምን ለሌላ ሰው ይሰጣል እኮ አልወጣኝም። በፍፁም አልወጣኝም። ለምሳሌ አንዳንዴ.....ሞቅ ያለው ጎልማሳ ሁለት ሡንደሎች ጆሮውቿ ላይ ሰክታ፣ ሡንደሉንም ሲጃራውንም እያጨሰች ጨርቅ ብጤ አንጥፋ «ጆኒ» እስቲ ጣል አርግበት......ታንክ ዩ. ፍሬንድ» እያለች....... ጫቷን የምትቅም ሴት በዶሮ ማነቂያ በኩል ሲያልፍ ብታጋጥመው አንድ ብር ጣል አድርጎላት ሊያልፍ ይችላል። ሰው እኮ ገንዘብ ለምን ይሰጣል አይባልም። ሲሆን ሲሆን የአካል ጉዳት ለደረሰበት መሥራት እችላለሁ እያለ ሥራ ላጣ፣ አእምሮው ለቀወሰበት፣ የሥነ - ልቦና አፍዝ አደንግዝ ላለበት...... መርዳት አባቶች እንደሚሉት ያፀድቃል።

የለጋሽነት ጉዳይ ከተነሣ አንድ ሁለቱን ልጨምር። ከፍቅረኛው ጋር ሰክሮ መኪናው ውስጥ ቁጭ እንዳለ አንደበተ ርቱዕ ለማኝ መስኮቷ ጋ ጠጋ ብሎ «ያምርባችኋል፣ አይለያችሁ፣ ለዘር ያብቃችሁ፣ ኧረ ምቀኛ አይግባባችሁ» የሚል ምርቃት ከሰማ እጁ ያወጣለትን ገንዘብ የሚሰጥ አለ። ሌላው ቀርቶ የልጅ ልጅ ያዩ አንዳንድ አዛውንትም ጠጁን ከልክ በላይ ሲያደርጉ ከለማኞቹ አልፈው ተርፈው ባቋላ አሹቅና ቆሎ ለሚያዞሩት ኮረዶች ምርቃ (ቲፕ) ሲሰጡ ይታያሉ። ይሄ ይሄ የግል ባህርይ ነውና አያሚግትም። ያለው የሌለው ነውና አያሚግትም። ያለው ለሌለው የተሻለው ከሱ ላነሰው ቢሰጥ ምናለበት?

አዲስ እባበባ ታበዛዋለች። ፍፁም ሥነ - ሥርዓት ለሌላቸው ያለ ምንም ምክንያት ሰው ለሚንቁ፣ ለምሣሌ ታክሲ ውስጥ የተቀመጠች ሳንቲም ያልሰጠች ሴት ልጅ አዋርደው ለሚሳደቡ፣ ሴቶች ተማሪዎችን መንገድ ላይ ለሚያንገላቱ ጋጠ - ወጦች......ፊት ትሰጣለች። ለዚህ ለዚህ አለሁልሽ የሚላት ታማኝ ዜጋ የላትም። አዲስ አበባ ራሷ ፈሪ ሆና ዜጎችዋንም ፈሪ ታደርጋለች። ብዙ ጊዜ የሚያጋጥሟችሁ የከፉ ትዕይንት ምስክሮች ራሳቸውን ብቻ የሚጠብቁ፣ ሌላው ደንታ ቢስ የሆኑ ብቻ አይደሉም። አባሪ ተባባሪ ሆነው «ዓይኔን ግንባር ያርገው ጆሮዬ ይደፈን» የሚሉ ናቸው።

መዲናችን የከተማ መዋቅሯ ቅጥ ያጣ ነው። ሴተኛ አዳሪዎች ቤት አጠገብ ትምህርት ቤት ታያላችሁ። በከሰል መስጫና በልብስ አጣቢዎች መካከል ወፍጮ ቤት (ዱቄት) አለ። በጋራዥ ቁስ ትምህርት ቤት፣ ፍርድ ቤት፣ አጥር ጥግ ጉልት፣ በግ ተራ፣ ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት የአውቶብስ መናኸሪያ፣ መስጊድ አጠገብ ጫት መቃሚያ....... ውጥንቅጥ በየሠፈሩ ይታያሉ። መርካቶ ሠማይ ጠቀስ የንግድ ፎቅ ሥር የላስቲክ መጠለያዎች፣ ከነሱ አጠገብ በፀሐይ የጠወለጉ ሙዞችና ዝንቦች አሥፋልቱ ላይ...... ንግድ ባንክ ፊት ለፊት ጆቶኒ የሚጫወቱ ልጆች.....ቦሌ በሚገኝ መኖሪያ ቪላ ጎን ቅልጥ ያለ ናይት ክለብ መመልከት የተለመደ ነው። ከሁሉም ከሁሉም በላይ ዘግናኝ የሚሆንባቸው ፒያሳን መሃል ለመሃል የሚያቋርጡ አህዮች በተፈጥሮ አስተዋዮች ስለሆኑ ቱሪስቶች ፎቶ ሳያነሷቸው ተሽሎክሉከው ያልፋሉ። ቂሎች በጎች ግን በተለመደው አለንጋ እየተገረፉ በአፍሪካ አንድነት ጽ/ቤት ብቻ ሳይሆን በፕሬዝዳንቱም መኖሪያ በራፍ በኩል ይሮጣሉ። አዲሳባ ይሄንን ሁሉ አይታይም።

አዲሳባን ዛሬ ለገንዘብ መብታችሁ ግን የለአትም። ማንም ያሰኘውን እንደፈለገው ይሸጣል። ነጋዴ አልሸጥም ሲል እንኳ ከልካይ የለበትም። ጫፍዋ ትንሽ የተቆረጠ ብር ይዛችሁ ታክሲ አትሳፈሩም። ጥሩ መጽዋች ብትሆኑ እንኳ ሳትወዱ ክፉ መሆንን ከአካባቢያችሁ ብልሹነት እንኳ ሳትወዱ በግድ ክፉ መሆንን ይሉኝታ ቢስና ደንታ ቢስም ታደርጋችኋለች። ያለ አንድ ብር አንቀበልም የሚሉ የመንገድ ላይ እብሪተኖች፣ ለአሥር ሣንቲም አላስኬድ ብለው ሲጨቀጭቋችሁ መኪና ጎማ ሊያስገቧችሁ የሚሞክሩ ሽማግሌ መሰለው ከጎረምሳ ያነሱ ሰዎችን መዲናችን ታስተናግዳለች።

«ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ወይ» እውነትም አራዳ! ገና ከጥንቱ ሥልጣኔ ሥልጣኔ ሲሸታት የወጣለት ሕዝባዊ መፈክርዋ ነው። እሷ ግን አታፍርም። ምሁር ነኝ የሚል ደንቆሮ፣ ሳስታርቅ ብሎ የሚያጣላ፣ ዋሽቶ የማያስገድል፣ አስመሳይ አፍቃሪ፣ ጉቦኛ ባለስልጣን፣ የነጋዴ ዘራፊ፣ የትልቅ ትንሽ፣ የሐኪም አወናባጅ......ሁሉ ተጭቀውባት አዲስ አበባ አታፍርም። ይልቁንስ አራዳ ነን ብላ ከንቱ ኩራት ትኮራለች።

# ራስን መቀበል (Self Acceptance)

ይሄንን ርዕስ የሥነ ልቦና ወይም የሕክምና ሰዎች ሲያዩ በጉጉት ለማንንበብ እንደሚገፋፉ አውቃለሁ። ምክንያቱም እነዚህ ባለሙያዎች ስያካትሪ፣ ሳይኮአናሊስ፣ ቢሄቪየር አናሊስስ....... የሚባሉትንና ሌሎችንም በሚገባ ያውቃሉ። እኔ ግን ምስኪን የሥነ ጽሑፍ ሰው ነኝና ቢስቁብኝም ይሳቁብኝ ቢወርፉኝም ይወርፉኝ ብዬ.....ዓይን አውጥቼ (ድፍረት ነው የሚባለው) ይኼንን ጽሑፍ ጀምሬያለሁ።

ራስ መቀበል (Self Acceptance) የሚባለው ነገር ምንድነው? ምሁራን ሲባሉ ከላይ ከጠቀስኳቸው ጀምሮ የትምህርት የሶስዮሎጂ የፍልስፍና.......መካሪዎች እየሆኑ «እራሳችሁን ሁኑ» ይላሉ። የሰው ልጆች ግን መቼ ራሳችንን እንደምንሆን እኔ ባለሁበት አካባቢ አናውቅም። እንዲያውም.......ሌሎችን መቼ ነው እምንሆነው ብለን ማሰብ ነው የሚቀናን።

ስለዚህ......ምሁራኑ ሲመክሩን ብዙ የደከሙ ቢሆንም፣ ከእኛ የሚሰሙትን ሰምተው ትንሽ እንኳ ቢዝናኑ ይሻላል ብዬ አስባለሁ። እኔ በበኩሌ ራስህን ተቀበል ቢሉኝ ድንክ ከሆንኩ ድንክነቴን፣ ቀውላላ ከሆንኩ ቀውላላነቴን አፍንጫዬ ቀዳዳዎቹ የሚታይበትን ጎማዳ ቢሆን ፉንጋነቴን (ወይም አስቀያሚነቴን)ን አምኜ «ነኝ» ለማለት ዝግጁ እሆናለሁ። ምሣሌውን ረዘም ላርገው......እጅግ ትልቅ ጆሮ፣ ወይም የዚያን ዓይነት ከንፈር....... በረጅም እጆች ላይ አጭር ቁመና፣ በአጭርነት ላይ ረጃጅም እጆች...... ዓይነት የሰውነት ተፈጥሮ ቢኖረኝ እቀበለዋለሁ።

ማንም ምንም ይበለኝ....... ራሴን ነኝ። ሌላ መሆን አልፈልግም፣ ብዬ ራሴን ተቀብዬ እኖራለሁ። ሀብታም መሆን፣ ድሀ መሆን መማር አለመማር ሁሉ....... እዚህ ውስጥ የሚገባ ይመስለኛል። ይሄን ይሄን እያልን ወደ ማኅበራዊ ሕይወት እየገባን ነው። «ራስን መቀበል» (Self Acceptance) የሚል ትልቅ ጉዳይ ከያዝን ወደ ቁም ነገሮች መግባት ያለብን ይመስለኛል።

«ሴቶች ወፈር ደልደል ሲሉ ደስ ይለኛል» የሚል አንድ ጓደኛ አለኝ። በቁንጅና ውድድር የሚታዩትን የውጭ አገር ሞዴሎች አይወዳቸውም። «የቤት መጥረጊያ ሊመስሉ ምንም አልቀራቸውም» ይለኛል።

«ወፍራም ሴቶች ደስ ይሉኛል የምትለውን አነጋገር አንድ ቀን ትለውጠዋለህ» እያልኩት እንደ ቀልድ ስንከራከር ብዙ ጊዜዎች አሳልፈናል።

እንደ ዘበት ያነሳነው ነገር አበቱ ስንገባ ዘገነነው። ዘሪሁን እሸቱ በዓይኑ የሚያየውን ማመን አልቻለም። «በእኔ ዲሽ ላይ ነው ወይስ በሌላ?» ማለት ሁሉ ጀመረ።

ታይራ ሾው ለእኔ አስገራሚ ነገር አሳየኝ። 250 ኪሎ ግራም ግድም ክብደት ያላት የ31 ዓመት ሴት ናት። የስምንት ዓመት ልጅ አለቻት። ለምን ያንን ያህል እንደወፈረች የራስዋን ምክንያት ተናግራለች። የማይረሳኝ ነገር ግን ሰዎች ተሰብስበው እንዲያዩዋት ስለማትፈልግ.......እቤትዋ ድረስ እየሄዱ በካሜራ ያናገርዋት መሆኑ ነው። እንግዲህ ይሄንን ቅጥ ያጣ ውፍረት ብለን እንለፈው። ተፈጥሮ?......ወይም?.......እንዳላችሁ በሉት።

ጓደኛዬ ቤት ቁች እንዳልኩ ሌላ ቤት ከለንደን መጥታ ታይራ ሾው ላይ ቀረበች። ይቺ ሴት መልኬ አያምርም ብላ የምታስብ ናት። «አስቀያሚ ነኝ፣ ሰዎች ሁሉ ሲያዩኝ ይስቁብኛል» ትላለች። ታይራ ወደ መድረክ እንድትወጣና እንድትታይ ብትገፋፋት እንቢ ስላለች ከመድረክ ጀርባ ሄዳ አነጋገረች። እኔና ዘሪሁን ስናያት አስቀያሚ መስላም አልታየችንም። አፍንቻዋ ጎረድ ያለ ግንባራዋ ወጣ ያለ ከመሆንዋ በስተቀር በባህላችን ፉንጋ የምንላት ሴት ናት። ብቻ እንደ ምንም እየፈረች ወደ መድረኩ ቀርባ፣ በመስተዋት ሁሉ ሌላ ነገር እንደሚታያት ገልጻ ምንጊዜም አስቀያሚ ነኝ ብላ እንደ ምታምን ተናግራ ቀና ብላ እንኳ እዚያ የነበሩትን ሁሉ ሳታይ ወጣች።

በታይራ ሾው የነበረው ሳይኮሎጂስት የሰጠውን አስተያየት አዳምጠን እኔና ጓደኛዬ ተያየን። ትልቋን ወፍራም ሴት ካየብት ደቂቃ ጀምሮ ዓይኑን ማመን አቅቶታል። «ወፍራም ስል እኮ የእሷን ዓይነት ማለቴ አልነበረም» አለኝ በሐሳብ ተውጦ። «እነዚህ ሁለት ሴቶች ራሳቸውን ይቀበሉ ይሆን?» አልኩት እኔም።

ራስን መቀበል የሚለው ጉዳይ ትልቅ ቁም ነገር መሆኑ ስለታሰበኝ ወደ ሐኪም ጓደኞቼ ሄጄ አንዳንድ የሐሣብ ልውውጥ አደረግን። የእኔ ጥያቄ ቀለል ያለ ዓይነት ነበር። በታይራ ሾው ያየሁትን ከነገርኳችሁ በኋላ «ሰው ራሱን እምሆን ካቃተው ምን መሆን ይቻልላ? አድኒት ሲት መልከ ጥፉ ብትሆንስ? አንድ ወንድ ያላሰበውን ነገር እንዲህ ነኝ ቢልስ?» ብዬ ለውይይት ጋበዝኳቸው። በጋዜጠኝነቴ ምሳሌ መቀለብለብዋን እያሰብኩ ወጥሬ ያዝኳቸው።

ወዳጆቼ ስለሆኑ ብዙ ነገር አጫወቱኝ። በሕክምና - ቃላት በእንግሊዝኛ ቢያጣድፉኝም የሰማሁትን ግን እንደ ሚከተለው ልንገራችሁ። ሳይካያትሪ በሰው ልጆች ባህሪያት ላይ ያለው ግንዛቤ ቀላል አይደለም...... ብሬይን ዲስኦርደር ፐርሰናልቲ ዲስኦርደር........ ሌላም ሌላም ብዙ ነገር አሉኝ።

እኔ የማነጣጥረው ሰው እንዴት ራሱን ተቀብሎ «ነኝ» ብሎ አይኖርም? የሚል ሆኖ ሳለ...... እነሱ ግን «አንተ እንደምታስበው አይደለም» እያሉ..... በአንዳንድ ትዝታዎች የገጠማቸውን ነገር አጫወቱኝ። ከእነሱ የተማርኩት ነገር ቀላል አይደለም። ለምሳሌ የተማረም ይሁን ወይም ሌላ በአእምሮ የማስተዋል ችግር በድንገት የሚጀምር ተቃራኒ ጾታን የመውደድ ችግር.......ምንም ሳታደርገው አጠገቡም ሳትደርስ፣ ጠላቴ ናት፣ እገድላታለሁ የማለት ችግር........በመሃል በመሃሉ ደሞ......ወፈፌ ነኝ የሚለው..... ኦ. ፒ. ዲ. ገና እንዳስተኙት የመኪና አደጋውን ረስቶ «ደሜን ለአገሬ» የሚለው አጥንቱ እየተንቋቋ በስካር የንዝዞ የመኪና አደጋ በማግስቱ ካልሆነ የማይገባው........የእኔ አንጎል የማይችለውን ሁሉ........ አወራን።

እውነቱን ለመናገር እኔ ያየሁትን የዘገነንኝን ነገር የራሴን የጋዜጠኛ ወሬ ነገር ማሰብ ቀጥያለሁ። ለምን ወፍራሟ «በቃ፣ እንዲህ ነኝ እንዲህ ሆኜ እንደ ማንም እሞታለሁ። ብላ ራሷን አትቀበልም? ያቺን አስቀያሚ

ነኝ ብላ እንደምታምነው ለምን ሌላ አስቀያሚ ፍቅረኛ እስከሚያጋጥማት ድረስ ራስዋን ሆና አትቆይም? የሚል ነበር የማስበው። የሚገርመው ግን ሳይኮሎጂና ሜዲካል ሳይንስ የተባሉት የዘመናችን ጥበቦች የአገሬን እውነታ እንድዘነጋ ያደረጉኝ መሆናቸው ነው። በእኛ አገር ፍቅር፣ ጋብቻ የምንለው ነገር በእርግጥ ከአፍቃሪዎች ወይም ከባለትዳሮች የሚመነጭ ነው? ወይስ ማኅበራዊ ተፅዕኖ ድህነት፣ በደረጃ፣ አለመስተካከል........ አማት ምራት..... ቅብርጥሴ እይሚጫኑት? ይሄን ይሄንን ሳስብ ቆይቼ ራስን መቀበል ሊኖር ቀርቶ ተሳስቻለሁ የሚል ቃል እንኳ ባደግኩበት ኅብረተሰብ እንደማይኖር ራሲው ለራሴ ደመደምኩ።

እኔ እንደማስበው ራስን መቀበል ያኮራል እንጂ አያዋርድም። በራስ መተማመን እስካለ ድረስ፣ የሰው ልጅ ሲባል ሁሉም እንደየራሱ ይኖራል። ዓይነ ሥውር ብሆን በማሰብ ደረጃ ዓይናማውን ከበለጥኩ፣ ከዚያ የሚሻል ሌላ ምን እፈልጋለሁ? አንድ እግሬ አንከስ ቢል በሁለት እግሮቹ ተቆን ከሚራመደው በምን አነሳለሁ? እንዲያውም አካሄዴ ቁንጠኛ ሆኖ የቆንጆ ሴቶችን ዓይን ልስብ እችላለሁ። በዚህ አጋጣሚ አንድ ቀን በሬዲዮ የሰማሁትን ላጫውታችሁ። ዕለቱ የአካል ጉዳተኞች ቀንን የሚያስታውስ ነበረ። አንድ ሰው እንዲህ ብሎ ሲያወራ አዳመጥኩ። «ልጅ ሆኜ ደብረ ዘይት ከጓደኞቼ ጋር አየር ኃይል ፊልም ልናይ ውችው በር ቆመን ሳለ፣ አንዱ ጓደኛዬን «ማነው ፀሐይዋን ለረጅም ጊዜ ትክ ብሎ የሚያይ?» የሚል - ውድድር - አመጣ። ከዚያ ፀሐይዋን ስናይ ቆየን። ከሣምንት በኋላ አንዱ ዓይኔ ታመመ። ሌላውም እንደዚያው ሆነና ዓይነ ሥውር ሆንኩ» ሲል ምን ያህል በትኩረት እንዳዳመጥኩ ትዝ ይለኛል። ሰውዬው ስሙን ባላስታውሰውም፣ የሕግ ምሁር ወይም Lawyer መሆኑን በሬዲዮ ተናገረ። ራሱን የተቀበለ ሰው መሆኑ ገባኝ። እንዲህ ሆኘ እንዲህ ሆንኩ እያለ ተዝናንቶ አወራ እንጂ በዚህ ዓለም ዱሮ እንዲህ ነበርኩ የሚል ጣጣ ውስጥ አልገባም። ትልቅ የሚያደርገውም ይኸው ነው።

መቼም የሰው ልጆች ስንባል ወንድ ሴት እያልን ራሳችንን ሳንከፋፍል ቀርተን የምናውቅ አይመስለኝም ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ ጥቁሩም ይሁን ነጭ የሰለጠነም ያልሰለጠነም ያደገ አገር ብትሉትም ያላደገ...... ይሄ ሐቅ ሁልጊዜም አለ። ለምሳሌ ወንዶች ስንባል እድሜያችንን ለማሳነስ የሴቶችን አስተዳዳሪ ነን እንዳንባል የማናደርገው ነገር እንደ ሌለ ልቦናችን ያውቀዋል። በአጭር አነጋገር የበላይነታችንን ለማሳየት ራሳችንን መቀበል አንችልም ማለት ነው። አታሳፍሩኝም ብዬ ልማፀናችሁ እንጂ..... ፀሐይ ሳያቃጥለን ጠለቅ የምናደርጋት ኮፊያ..... የወጣት መነጽር...... ታኮ ጫማ ሳየንሳ...... አለባበሳችን፣ አካሄዳችን ሽበት በቀለም መደበቃችን ሁሉ እድሜ ለመደበቅ የምናደርገው መሆኑ ግልጽ ነው።

ወደ ሌላው ጉድ ዘወር ስንል ደግሞ ሴቶች እንዴት ራሳቸውን መቀበል አለባቸው ወደ ሚለው እንመጣለን። ይሄንን እኔ ከማወራላችሁ ይልቅ የአንዲት ሴት ታሪኳን አቅርቤላችሁ ራሷ ትንገራችሁ። ጉዳዩ የሴት ዕድሜ የሚመለከት ነው።

ራሳችንን ለመቀበል ከምንም በላይ እድሜ ትልቅ ሚና ይጫወታል። ወጣትነት ተስፋና ትኩስ ኃይል፣ በራስ መተማመንና ድፍረት ያይበታል። ቁንጅና አብቦ ያሽትበታል። የፍቅር አዝመራም ይሰበሰብበታል። ከዚያ ቀጥሎ የሚመጣው ጊዜ በቤተሰብና በማኅበረሰብ ብሎ በአገር ኃላፊነት ላይ እያነጣጠረ ይሄድና ሽምግልና ወቅቱን ጠብቆ ይከተላል። ሽምግልና በአንጋፋነት ያስከብራል። አስታራቂ መካሪ፣ ታጋሽና አመዛዛኝ...... ይኮንበታል። ከዚያ ወዲያ ያለውን አስቀያሚ የሞት ዋዜማ አለማንሳቱ ይሻላል።

ወንዝ ከተራራ ምንጭ ሆኖ እንደሚነሳ...... እያደገ ትልቅ ጅረት እየሆነ ብዙ ውጣ ውረዶችን ሄዶ ሄዶ ከባርህ እንደሚገባ..... የሰው ልጅ አካላዊ ዕድገትም እንደዚያ ነው። በተለይ ወጣትነት እንደ ጉም እየቦነነ ቀስ

በቀስ ሲጠፋና ሽምግልና (ለወንድም ለሴትም የሚውል ቃል ነው) እንደ ደራሽ ውሃ ከች ሲል ስብዕና ፈተና ላይ ወደቀ ማለት ነው።

«ልጅ መውለድ ቀላል ነገር ባይሆንም በውጤቱ ትልቅ ስጦታ ነው። ዕድሜ ከጎልማሳነት በላይ እየገፋ ከሄደ ግን እንደ ልጅ መውለድ ደታ አይሰጥም - እንዲያውም ያስጠላል» ትላለች ኖራ ኤፍረን፣ ታዋቂዋ ደራሲ። ኤፍረን ስልሳ አምስት ዓመቷ ነው። ያለ አንዳች ጥርጥር ግን 10 ዓመት የምታንስ ትመስላለች። ይሁን እንጂ የሽምግልና ምልክቶችን እያየሁ ነው ትላለች። ከአነጋገሯ ሁሉ የሚገርመው «ልብስ ልገዛ መግባት ያለብኝና የሌለብኝን ስቶር በሚገባ አውቃለሁ። በድንገት ግን ደስ ያለኝ ቡቲክ ገብቼ ልገዛ ብልም ገዝቼ የምወጣው ጥቁር ሙታንታ ነው» ማለቷ ነው። አታውቋቱም እንጂ ኖራ ኤፍረን የወግ (Informal essay) ጸሐፊም ናት። እና በዚህ አባባልዋ «እንደ ወጥቶቹ የሙታንታ ከለር መምረጪያ ዘመኔ አልፏል» ብላ እውነቱን ልትነግራችሁ ፈልጋ ነው። ሌላ የምታስገርማችሁን አንድ ነገር አስንቼላችሁ ወደሷ ማንነት ልለፍ። ኖራ «የዛሬ ሦስት ዓመት በኮምፒውተር ትናንሽ አድርጌ የጻፍኩት ዛሬ ለማንበብ እያስቸገረኝ ነው» ትላችኋለች። ልታዝናናችሁ ፈልጋ ነው እንጂ....... እሷስ የእድሜን ደራሽ ውሃ አሳምራ የምታውቅና አትጨነቁበት ብላ ልትመክራችሁ የተነሣች...... ኪነ ጥበብ የተጠናወታት እውነተኛዋ ሴት ናት።

ከአንድ ዓመት ተኩል በፊት ነውስ ዊክ መጽሔት ላይ እንዳነበኩት ኖራ ኤፍረን ከአሥር የማያንሱ ድርሰቶችዋ በፊልም ታይተውላታል። ኖቨል ወይም ረጅብ ልብ ወለድ (Heart burn) እና (Imaginary friends) የሚል ተውኔት ጽፋለች። ኖራ ኤፍረን በጣም የምትታወቀው «Crazy Salad» እና «Walflower at the orgy» በተሰኙት የወግ ስብስብ ጽሑፎችዋ ነው።

አሁን ለጀመርነው የራስ መቀበል ርዕስ በጣም ቅርበት ወዳለው ጉዳይ ጠለቅ ብለን ስለገባን እንዳትሰለቹ ላስታውሳችሁ። እስካሁን ድረስ ስለ ኖራ የተባለው ሁሉ ቀላልና ተራ ተደርጎ መታየት ባይኖርበትም፣ ይሄኛው የዕድሜን ጉዞ እያዝናና የሚያመላክት ነው። በመጨረሻ ያሳተመችው «አንገቴን እንዴት እንደማልወደው፣ እና ሴት ስለ መሆን አንዳንድ ሐሣቦች» ብላ የጻፈችው የወግ መጽሐፍ በጣም ተወዶላታል።

የኖራ ኤፍረን የወግ መጽሐፍ ስለ አሮጊትነት እያማረረ የሚናገር ይሁን እንጂ «ተፈጥሮን ምንም ማድረግ አይቻልምና እንቀበለው» የሚል አስተሳሰብ በአርት ሂደት የተላበሰ ነው። በፎቶ ግራፍዋ ስታይዋት አንገትዋን በአንዳች የሆነ ጨርቅ የሸፈነችው «የዕድሜን መግፋት አንገት ያጋልጣል» የሚል አስተሳሰብ መሆኑ በግልፅ የምንረዳው ይመስለኛል።

የስልሳ አምስት ዓመት ባለ ዕድሜዋ ኖራ ልታስቃችሁና ለሕይወት ጉዞ እንድታሱ ልታደርጋችሁ ምን እንደምትል እስቲ እንደሚከተለው ላውራላችሁ።

«ባለፉት አሥራ አምስት ዓመታት ሳነብ የኖርኩት አንድ ሰው ሲያረጅ እንዴት የበለጠ ደስተኛና አዋቂ፣ በሳል እየሆነ እንደሚሄድ ነው። ይሄን የሚሉ ሰዎች አብደዋል ወይ? ለመሆኑ ራሳቸውን በመስታወት አይተው ያውቃሉ ወይ? ጀርባዬን በእጄ ልንካ ሲሉ ትከሻቸውን የሚያየውን መከራ አስበው ያውቃሉ እንዴ?! እውነቴን ነው...... እኔ ወደ ሃያ ዓመት ዕድሜ ተመልሼ የኢንተርኔት የፍቅር ቀጠሮ ሲያፍልም አይነካካኝ። ይሁን እንጂ ከአሁኑ ዕድሜሽ ቀነስ አድርገሽ ወደ ወጣትነት ተጠጊ ብትሉኝ እሰየው ብዬ እቀበላችኋለሁ»

የኤፍረን ጨዋታ ራስን ከመቀበል መስመር የሚያወጣን አይደለም። ይልቁንስ ለሴቶች እህቶቿ የምትለው ነገር አላት። «የፕላስቲክ ቀዶ ሕክምና ስፔሻሊስቶች ዘንድ ሄጄ እባካችሁ በሆነ መንገድ ለዋውጡኝና

የምፈልገውን አድርጉኝ ብላቸው.......እምብዛም ሊጠቅሙኝ አይችሉም። ቀዶ ሕክምናውም ቢደረግልኝ ዞሮ ዞሮ፥ በመጨረሻ ላይ ራሴኑ ነው የምሆነው!»

ኤፍረን የተጨማደደውንና የሚያስጠላውን አንገቷን ከወጣት መልክ ጋር አጣምረው እንዲያስማሯትም አትፈልግም። «ይሄንን አድርግውልኝ ያለ ተፈጥሮዬ ወደ ወጣትነት ከሚመልሱኝ አሳዛኝ አንገቴንና ዕድሜ የሰጠኝን መልክ በመስታወቴ እያየሁ........ የሚያምር አበባ የመሰላ ወጣት ላይ ጀርባዬን ሰጥቼ መቀመጥን እመርጣለሁ» ትላለች። ኖራ በርግጥም ጨካኝ አሮጊት ናት። ሆኖም ደራሲ ናትና ሕይወት ላይ መጨከንዋ አያስገርምም።

በመጨረሻም ለወጣቶች ምክር መሰል አስተያየት ስትሰጥ «ውብ አንገታችሁ የእድሜ ጎርፍ ሳይደርስባችሁ ዛሬውኑ የወጣት ቁንጅናችሁን በተገቢ ቦታና ጊዜ ለምትወዱት ወጣት፣ ወይም ለሚመርጧችሁ ሁሉ......በአግባቡ አሳዩ። ደራሽ ውሃው የመጣ እለት ሁሉንም ለእግዚአብሔር ትሰጡታላችሁ» ትላለች።

እውነትም ኖራ ኤፍረን የምትለው ልክ ነው ያሰኛል። የሚወደድ ይወደዳል። የሚጠላም ይጠላል። የሚወደደው ላይመለስ፣ የሚጠላውም የሚወደድ ላይሆን ምን የሐሳብ ውጣ ውረድ የስሜት ድካም እፎይታን የሚከለክል....... ምን ዓይነት ከንቱ ጭንቀት ሊጠናወተን ይገባል?........ኖራ እንዳለችው ብቻ ሳይሆን...... ስብዕናችንም እንደሚያስነገዝበን መፍትሔው ራስን መቀበል ነው።

# ሽሽት

ሽሽት የተፈጥሮ ክሥተት ነው። ሰውም እንሥሣም አውሬም ይሸሻል። በአየር፣ በየብስ፣ በባሕር ያሉ አዕዋፍ ነፍሳት፣ የዓሣ ዘሮች ሁሉ ይሸሻሉ። አንዱ ያባርራል፣ ሌላው ይሸሻል። የዓለማችን ሕግ ነው። ቻርለስ ዳርዊን «በሕይወት ትግል ከበርቴዎች መሀል በጣም የበረታው ውድድሩን አሸንፎ (ሰብሮ) ይወጣል» ያለው ነው። በጠቅላላው መልኩ ሲታይ አንዱ ያባርራል። ሌላው እንዳይሞት ያመልጣል። በኃይለኛና ደማማ መካከል ሕይወት ሚዛኗን እንደ ጠበቀች ይቺ ዓለም ዑደቷን ትቀጥላለች።

የሰው ልጅን በተመለከተ በጦርነትና በወንጀል በአደጋ ጊዜ ሽሽት መኖሩ የታወቀ ነው። ይሄን ይሄንን እንደ መግቢያ ሳድርገው እንጂ እኔስ ልናገር የፈለግኩት ስለ ተለያዩ የሽሽት ሁኔታዎች ነው።

ሁለት ሥንኞችን እንሥላቸውና ወደ ሌላ እንኼዳለን።

1. «ፈርማና ወረቀት ቀሪ ነው ተቀዳጅ

   መተማመን ብቻ ይበቃል ለወዳጅ»

2. «ሥጋም ይበላና ይጣላል አጥንቱ፣ ጠላም ይጠጣና ይፈሣል

   ገፈቱ ዕዳም ይከፈላል እየሠነበቱ።»

3. «ሥጋም ይበላና ይጣላል አጥንቱ፤

   ጠላም ይጠጣና ይፈሣል ገፈቱ፣

ዕዳም ይከፈላ እየሠነበቱ።»

የመጀመሪያው ግጥም የአሰፋ አባተ ነው። ሁለተኛውን ማን እንደገጠመው አላውቅም። ህዝባዊ

ግጥም ግን ሳይሆን አይቀርም። አንድ ሊስተዋል የሚገባው ነገር እነዚህ ግጥሞች የዕዳ ሽሽት ወይም ከአበዳሪ መደበቅ እንደ ዛሬ በማይዘወተርበት ቀደም ባለው ዘመን የተፈጠሩ መሆናቸው ነው። እነሆ - እዳ ምንድነው? መበደርና አበዳሪ ተበዳሪ....... ወደሚለው - ልንመጣ እያኮበኮብን ያለን ይመስለኛል። እዚህ ጨዋታ ላይ ከደረስን ወግ ማለት እንደ ብርሌው ነውና፣ መንግሥትም ይበደራል ከሰው አልፎ መንግሥትም ባለ ዕዳ ይሆናል....... እንዳትሉኝ ከወዲሁ አደራ እላልሁ።

ዱሮ ዱሮ....... «ሒሣብ» የሚል አድን ግጥም ጽፌ ነበር። ዛሬ የት እንደጣልኩት ወይም እንደረሳሁት እንኳን አላስታውስም። ግን ከዩኒቨርሲቲ ልመረቅ - ስል (በ1962) ሶስት አራት ወር በፊት ነበር። የጻፍኩት ዕዳ የሚለው ጽንሰ ሐሣብ ያኔ ተሠርጾብኝ ይሁን......ወይም ሌላ...... እንጃ ብቻ። አንድ አራቱን ስንኝ እንሆ፦

ሰባት ጊዜ ሰባት አራባ ዘጠኝ

አድ አለኝ።

ሶስትና - ሶስት - ዘጠኝ

ምንም የለኝ።

አትሠልቹ እንጂ ግጥሙ ዕዳ ያለበት (ወይም ተበዳሪ) ምን ያህል ይጨነቃል ምን ያህል መሄጃ መንገድ ያጣል.....የሚለውን አሳብ የሚያንፀባርቅ ዓይነት ነበር። ይሄ ግን አሁን ለምንጽፈው ነገር የሚኖረው አስተዋፅዖ በጣም ትንሽ ነው።

ይልቁንስ......፣ ምንም በሉት ምንም አንድ የግል ትዝታዬን ላጫውታችሁ። ነገሩ የሆነ የዛሬ አርባ ግድም ነው። አምቦ ማዕረግ - ሕይወት ትምህርት ቤት አሥራ አደኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ የማውቃቸው ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ። የአዲስ አበባ ልጆች ናቸው። እነሱ ገና ሲኒማ አድዋ ሳይፈርስ ጀምሮ ሲኒማ ኤምፓየር ኢትዮጵያ - ሁሉ ብዙ ፊልሞች አይተው ሠልጥነው አምቦ ሀብታም ዘመዶቻቸው ጋ፣ የመጡ ናቸው። እኔ - ሞጆ ከምትባል የሩቅ አገር የገጠር ከተማ ስለ መጣሁ ያየሁዋቸው ፊልሞች በቁጥር ነበሩ። ይሁን እንጂ አንዷን ያየሁዋት መግለጽ ብቻ ሳይሆን የማውራት የማሣቅና የማዝናናት ዓይነት ባሕርይ ስለ ነበረኝ ታላላቆቼም ቢሆኑ ጓደኛቸው መሆን ቻልኩ። አንድ ቀን ታናሽዬው አርባ ብር አስቀምጥልኝ አለና ሠጠኝ። እኔ ግን ያንን ብር አጠፋሁት። ጠየቀኝ። አጥፍቼዋለሁ አልኩት። ግዴለም፣ ሌላ ጊዜ ትመልስልኛለህ አለኝ። ከዚያ በኋላ አሥራ ሁለተኛ ክፍል ስንጨርስ ተለያየን። ከጥቂት ዓመታት በኋላ፣ ሐረር ጦር አካዳሚ ገብቶ መቶ አለቃ መሆኑን ሠማሁ። እኔም እድሌ እንደመራልኝ የሕይወት ጉዞ ቀጠልኩ።

ከሀያ አምስት ዓመታት በላይ ሳንተያይ ቆይተን...... አሥመራ ዩኒቨርሲቲ የሥነ - ጽሑፍ መምህር ሆኜ ሄድኩ (1980)። ዱሮ የማውቃት አሥመራ ተለውጣ ጠበቀችኝ። ከተማዋ ወታደር በወታደር ሆናለች። አካባቢው ሁሉ ያስፈራል። ደሞ በዚያን ጊዜ አድን የደርግ ጂፕ ኃይለኛ መብራቱን ኮምቢሽታቶ ላይ ካበራ ካቴድራሉም፣ ቡና ቤቱም፣ መስጊዱም ጭር እርጭ ይል ነበር። ሙስታሹን ጠምዘዝ እያደረገ አመዳም ፊቱን ብልጭ አድርጐ «ዝሑል ቢራ» የሚል መኪናውን ያለ ፍሬን አቁሞ የትም ቦታ የሚገባ ተራ የምትሉት ወታደር «እስቲ እታን አጪሱ» የሚያሠኝ ዓይነት ነበር። ወሬዬ ግን ሳይበዛ አይቀርም። ታገሱኝ።

አሥመራ አንድ ሣምንት ያህል እንደቆየሁ አንድ የሚገርም ሁኔታ አጋጠመኝ። ፀጉሬን ልስተካከል በርጋታ እሄዳለሁ ዝም ብዬ እየሄድኩ ሣለሁ በፀሥር ወይም - ሀያ ሜትር ርቀት ጥቁር የጸሐይ መነፅር ያደርገ፣ ዋዝ መኪና ውስጥ የተቀመጠ ሰውዬ በድንገት «እጅ ወደ ላይ» አለኝ። ምን አቅብጦኝ ነው እዚህ አገር የመጣሁት? የሚል ቅጽበታዊ ሐሣብ ጭው እያለብኝ ቆምኩ። እጄን ወደ ላይ አድርጌ ሰውየውን ሳይ ሚሊቴሪ ልብሱን እንደ ለበሰ ክላሹን ጭኑ ላይ አስቀምጦ ወደኒ ደግኗል። ጀርባዬ ላይ የበረዶ ውሃ የሚወርድ መሠለኝ። ግራ ቀኙን ማየት ስጀምር (ጐዳና እቴጌ መነን በሚባለው መንገድ) ሰዎች ሁሉ አፍጠው ከየበሩ የመስኮቱ ትክ እያሉ ያዩኛል። እኔም በቃ አልቀልኛል ብዬ እንደ - ዘመናችን የቀይ ሽብር ሠለባዎች እንጄን ለአካባቢው እንደማውለበለብ እየቃጣኝ ልቀርበው እያሰብኩ እያለሁ «ስማ አንተ ገንዘቤን አታመጣም?» አለኝ በድንገት። ምን ማለቱ እንደሆነ አልገባኝም ከት ብሎ ሢሥቅና መነጽሩን ሲያወልቅ ግን አወቅኩት። የአምቦው ጓደኛዬ ነበር። ኰሎኔል ሆኗል፣ ባለሥልጣንም። ለካ እሱም ወደ ፀጉር ቤት ነበር አካሄዱ። ቁጭ ብለን ጐን ለጐን ፀጉራችንን ተቆረጥን እላችኋለሁ። የጓደኝነታችንን ነገር ለናንተ ግምት እተዋለሁ።

በእውነቱ የግል ትዝታዬን ያወራሁላችሁ የራሴን አስቤ ነውና ይቅር ትሉኛላችሁ። ደሞ በአንድ በኩል በዚያን ዘንድ ከዕዳ ወይም ከብድር የሚሸሹ ጥቂቶች ነበሩ። አሁን ታዲያ...... ትልቅም በሉት..... ደስ እንዳላችሁ..... ዕዳ ውስጥ የማይገባ አልተበደርኩም የሚል ሰው የሚኖር ይመስላችኋል? እኔ እንጃ። በኔ ግምት ሰዎች ሲባሉ አንድ ዓይነት ናቸው። የሚለዋውጣቸው ነገር ቢኖር መልበስ፣ መተጣጠብ ፊት ማሳመር የመኮፈስ ወይም ዘመናዊ መሆን ጥሩ ጥሩ የአነጋገር ብልጠት (ቀልጠፍ ቀልጠፍጠፍ የማለት) - እና የመሳሰሉት ዓይነት ነገሮች ናቸው።

«ሸሸት» ብዬ ያልኩት አባባል ወደ ዕድሜም ሊመጣ ነው ማለት ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ገና ሲፈጥረው ከሠጠው የእድሜ መንገድ አፈንግጦ «የለም የኔ በዚያኛው መንገ ነኝ» የሚል ሰው ዕድሜውን ሲቀንስ ሕይወትን ያመለጠ ይምሰለው እንጂ ከእትብቱ ከማንነቱ ሸሸት ይዟል ማለት ነው።

እኔ የአሥራ ሶስት ዓመት ልጅ ሆኜ አንድ አክስት ነበረችኝ። ዛሬ በሕይወት የለችም። የሌለባት በሽታ የለም። ደም ማነስ፣ ጨጓራ፣ ኩላሊት፣ ፊኛ (የሐሞት ከረጢት ያኔ አይታወቅም መሠለኝ!) ደሞ ሌላ..... የሚያስመልስ እንቅልፍ የሚነሳ ተቆጡ ተወራጩ..... የሚል ዓይንት ብዙ በሽታ ያማታል። እሷ ግን በይ ሲላት፣ የጥንት አገር ልብሷን አምጡ ብላ፣ ነጭ ሻሿን ከጆሮ ግንዷ ጀምራ ግጥም አድርጋ ታሥርና አላፊ አግዳሚውን ለማየት የሚመቻት ቦታ መርጣ ቁች ትላለች። እኔ ደሞ «አባዬ! አሞሽ የለም እንዴ?!» ብዬ ገና የልጅነት ቋንቋዬን ስጀምር በግልምጫ ታቋርጠኝና «ዝም በል ብዬሃለሁ። አንተ እይት ታቃለህ? ለማን ይድላው ብዬ እኮ ነው!! እኔን ታማለች የሚሉኝ? እንደ ዱሮው ነኝ እኔ አክስትህ!» ትለኝ ነበር። ምናልባት ይሄ ዓይነቱ ነገር ሸሸት ከሞት? ወይስ ሸሸት ከበሽታ?

ትልቁን የሸሸት ሚና የሚጫወተው በማሕበራዊ ግንኙነት ውስጥ የሚካሄደው ባለ ዕዳ የመሆን ነገር ነው። ባለ ዕዳ የሆነ ሰው ጭንቀት አይለየውም። ፖሊስ ጣቢያ የማያውቀው የኑሮ እስረኛ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም «ተበዳሪ የአበዳሪ ባርያ ነው» ይላል። ልቡ የፈቀደው ቦታ መሄድ አይችልም። ቢሄድም ከለላ ያስፈልገዋል። ግብዛ ቦታ፣ ሠርግ፣ ላይ ከአበዳሪ ግልምጫና ተረብ የሚያድነው አንድ ሁነኛ ሰው ሊኖረው ይገባል። በእግር ኳስ በረኛ እንደሚያስፈልገው ሁሉ ባለ ዕዳ የሆነ ሰውም የገንዘብ ጥያቄ እንዳይመጣብት ተከላካይ ባልደረባ ከአጠገቡ መለየት የለበትም። ተበዳሪ ምንጊዜም ቢሆን ከፍሎ እስኪገላገል ድረስ ነገሩ እንዲነሣበት ስለማይፈልግ የተለያዩ ዘዴዎችን ሲቀይስ ይኖራል። በዕዳ ምክንያት የሚፈራውን ቦታ ተደብቆ ማለፍ ሰውዬውን እንዳላየ መሆን የተለያዩ፣ ምክንያቶችን መፍጠር አማላጅ መላክ፣ ችግር በገሀድ መንገርና መማፀን ሌላም ሌላም።

ሽሽትን በነዚህ ብቻ ልንገድበው አንችልም። ከራስ መሸሽ ከመጥፎ ጓደኛ መሸ፣ ከአሽሚጣጭና ስም አጥፊ መሸሽ..... አለ። ምቀኛና ሸረኛ ተንኰለኛን ያዝልኝ የምለው ያለ ምክንያት አይደለም። ቢቸግረን ሃይማንትን ተጠልለን ከክፋት ለመሸሽ ጥረት ማድረጋችን ነው። ዝርዝር ውስጥ ለመግባት አንችልም እንጂ የበሽታን ያክልም ባይሆን ከፍቅር የምንሸሽበት ጊዜ አለ። ከኃላፊነት የምሸሽበትም ጊዜ አለ።

እንደ ነገረኛ ጐረቤት ግን አገር ለቃችሁ ጥፉ የሚያሰኝ ሁኔታ የለም። ሰውዬው ባለ ትዳርና የስድስት ልጅጆች አባት ነው። የአየር በአየር ዓይነት ሥራ ነው ያለው። ሲመቸው ይመቸዋል። ሲያጣም በሚስቱ ብርታት ከወዲያው ወዲህ እያለ ኑሮው እንደ ነገሩ እያገላበጠ ያስተናግዳል። መጠጥ ይወዳል። አንዳንዴ ቤታቸው ሞላ ሲል ሚስቱ ለልጆቹ የተሠራውን ሽሮ በትልቅ ጭልፋ እንጀራው ላይ ፈሰስ አድርጋ ትሰጣቸውና ለሱ ብቻ በቅቤ የተንተከተከች ሥጋ ወት በእንጀራ ሽፍንፍን አድርጋ ታቀርብለታለች። ከልጆቹ አነስተኛው «ከአባዬ ወጥ» ብሎ ቁንጮውን እያሻሸ አቤቱታ ሊያቀርብ ሲል «ና!» ይልና እያጎረሰው ይበላል።

ሞቅ ብሎት ቺስታ ሆኖ አምሽቶ ሲመጣ ደሞ ጎመኑና ሽሮውን እያማረረ ከሚስቱ ጋር የነታረካል። በል ሲለውም ይደበድባታል። በግራም በቀኝም ያሉ ጐረቤቶች ሲሰሙ «አቤት አቤት! ደለዛት! ጠለዛት ድምፅዋን እክፍ አድርታ አትጮህም?» ይላሉ። ወዲያው ደሞ ልጆቹ ወደ ተኙበት ይሄዳል። ልጆቹ ወደ ታች ሲሏት ፊት ባዶ የምታደርግና ወደ ላይ ሲሏት እግር እርቃን የምታስቀረው አሮጌ ብርድ ልብሳቸው ውስት ሲገላበጡ ሲያይ «እዩ የናንተ ሕይወት!» ይልና እንባ - ቀረሽ ፀፀቱን ይፀፀታል። ሚስትየው ዘመድ ጎረቤት ሁሉ እያፅናኑ ሲመክሯት «ኧረ ተውኝ እባካችሁ! እህል ውሃ ለዚህ ሲዳርገኝ ምን አድርጊ ትሉኛላችሁ?» ከማለት በቀር ሌላ ቃል አይወጣትም።

አንድ ቀን..... አባ ወራው ያለ ወትሮው ስራ አልቀና ብሎት ብስጭትጭት እያለ እቤት ይመጣል። ማታ ማታ ሰክሮ ወደ ቤቱ ሲሄድ «ዘራፍ» እያለ ባሕር ዛፉን ሁሉ ጠላት እየመሰለው በሐሳቡ ሽጉጥ እየመዘዘ «ዞር በሉ ውርድ ከራሴ ነው» በሚል ድንፋታ ሲያቅራራ የነበረው ሰውዬ ዛሬ አፉ ትስርስር ብሏል። ደብሮታል። ገና እንደ ገባ ብዙ ልብስ ተሰጥቶ አየ። ዝናቡ ደሞ ለተንኮሉ ወዲያው ማካፋቱ ጀመረ። ሲጠጣ የለመደው ቁጣው ልውጣ አልውጣ ማለት ሲጀምረው ወደ በኢት ገባ። ትንሹ ልጅ ባትሪ ድንጋይ እየቀጠቀጠ «በእንባ እየታጠብኩ» የሚባለውን ዘፈን ይዘፍናል።

«እናትህ የት አለች» ብሎ ጠየቀው። «ገበያ ሄዳለች» አለና ዘፈኑን ቀጠለ። አባ ወራው ወደ ሁለተኛው ክፍል ሲገባ ሶስቱ ልጆቹ የሉም። ሌላው አድን ኳስ እያነጠረ ጣራው ላይ ይለጋል። «የቀበሌ ቤት ልታፈርስ ነው?» አለና በጥፊ መታው። ግራ ቀኝ ያሉት ጎረቤቶች አያዳመጡ ነው። አባ ወራው ወደ ማዕድ በኢት ገባ ሲል እደ ሠራተኛ የምታገለግለው የአሥራ ሁለት ዓመቷ የእህቱ ልጅ ታንቀላፋለች። «አንቺ ደግሞ በቀን ታንቀላፊያለሽ?» ብሎ በርግጫ ሲላት ተነሳች። የዝናቡ ካፊያ ጨምሯል። «ኑ ልብሶቹን እናስገባ» አለና ሶስቱም ሲወጡ በጎረቤትነት በስተግራው ያልቱ ልጅ እግር የቤት ሠራተኞች በቆርቆሮ ክፍተት አጮልቀው እያዩት ድምፃቸውን አጥፍተው ይንከተከቱ ጀመር። «አንዴ ሸማኔ ጋ ትላለች...... አንዴ ወፍጮ ቤት..... መኪና ሰፊ........ በሷ ቤት የማናውቃት መስሏት።» ይላሉ ስለ ሚስቱ እያነሱ በማሾፍና በመንበላጠጥ «ለመሆኑ የት ሄዳ ነው?» ይላል እሱ።

ከአባ ወራው መኖሪያ ቤት በስተቀኝ ያሉት ጎረቤቶች ጠና ያሉ ዓይነቶች ናቸው። ከዓርባ ዓእምት አለፍ ያሉ ሲሆኑ፣ አንደኛዋ ባልዋ ሞቶ ልጇን ታሳድጋለች። ሌላዋ ከባልዋ ተፋትታ ልጅዋን እሱ ያሳድጋል። የሩቅ ወሬ የሠፈር ወሬ የአገር አልባልታ....... ሁሉ የሚወዱ ናቸው። አሁን አባ ወራው ሲደነፉ ሲንጎራደድ የሚስትየዋንም አለመኖር አስበው ድብቅ ደስታ ተሠምቷቸዋል። ሰለዚህ ባረጀ ቆርቆሮ ከለላ ስንጥር

መመልከቻ ላይ ዓይናቸውን ደቅነው ሁኔታውን እያጠኑ ይከታተላሉ። «ልብሱን እኮ ካሰጣችው ቆይታለች?» ትላለች አንደኛዋ። ሌላዋ ቀጥላ «ያጠበችው መቼ ነው?....... እሱ ሌሊት ሰክሮ እንደተኛ ነው እኮ! አሀሀሀ!» ትላለች። «ውይ ዛሬ ቀን...... ጉዷ ፈላ» ይላሉ እየተቀባበሉ። ሰውየው በንዴት ይንጎራደዳል። «ገና ጠዋት የወጣች....... ልብሱን ለዝናብ አስጥታ...... በሷ የተነሳ በሽሽተኛ ሆንኩ....... ሽበት ወረረኝ....... ቆይ ብቻ!» ይላል። አንደኛዋ ሴትዮ በዋናው በር ዞራ ትመጣና «ምነው! አልመጣችም እንዴ?» ትላለች «ኧረ ምጣት ይምጣባት!» ብሎ ገና ሲጀምር «የተሰጣው ብቅል እንኳ ገና ወጣ እንዳለች ነው እኛ ያስገባነው......» ትላለች።

ከኋላ ሌላዋ ጓደኛ ጎረቤት ከተል ትልቅና «እንደው ምን ሆና ይሆን? እስቲ አንተ አትቆጣ። ዋናው ነገር ደኅና ትሁን......ገና ጠዋት የወጣች?! ብላ መለስ ትላለች። ሁለቱም ቤታቸው ይገናኙና» «ኧረ እንዲያው ፈረደባት...... ዛሬ መቼም አያስተርፋትም! ገብርኤል ይሁናት...... ደሞ እሷስ ብትሆን ይሄ ዙረት ምናለበት ቢቀርባት?» ሲሉ..... እሱ «ዛሬ ይለይልናል» እያለ ሲዝት...... ደቂቆች ያልፋሉ። ሚስቲትቱ ሰባራ ጃንጥላዋን ይዛ ሌላ ሶስት በፌስታል የተቋጠረ ነገር በእጇቿ ይዛ ሁለት አንጠልጥላ በፀሀይ ንዳድ ፊቷ ከሰል መስሎ ጠውለግ ድክም እንዳለች ስትመጣ ባልዋ ከሩቅ ያያታል። «ያችው መጣችልሽ....... እሷ ናት ብለሽ ነው? ወይስ ዓይኔ ነው...... ኧረ እምጣች ያችውልሽ» አሁንም የጎረቤት የቃላት እሩብታ!

ከዚያማ አባ ወራው ቀረብ ስትል ወጣ ማእልት ፌስታሎቹን ቀበል ጃንጥላውን ከጇ ቀበል አድርጎ እቅፍ እሱና በአንድ እጁ ድግፍ «ኑ ውጡና ግዟት እናንተ አመዳሞች» ማለት ልጆቹን። እሷን ደሞ...... «ምነው እምይ በዚህ ፀሐይ ብቻሽን....... አንዱን ፈልፈላ ልጅ እንኳ አስከትለሽ አትሄጂም? ጃንጥላ ግዛልኝ ብትይኝ...... አፍሽ እንዲህ ደርቆ...... ጎበጥ በልሽ የኔ እመቤት.....»

ኤድያልኝ ኤያ..... ከዚህማ ሐሜተኛ ጎረቤቶች ኩም እርር ድርቅ ክስል!....... ድብን «ሆሆሆሆይ!...... ምን ያለው ወንዲላ ነው..... ሴት አውል...... የወንድ አልጫ.....ማንን ለማናገር ነው ይሄ ሁሉ?......ማን በማን ቤት ጣልቃ ሊገባ?...... ኧረንሺቱ ቀድሞ ለራሱ ያላወቀ...... አውደልዳይ...... ሰካራም....... የሰው አውደልዳይ ሾካካ! የባል ሾካካ!.....» ነገሩ እዚህ ላይ አበቃ። ለመሆኑ..... ሰው ከነገር ያልሸሸ ከምን ይሸሻል?

# ገንዘብ

«ገንዘብ ገንዘብ ገንዘብ ያለው ያውጣ፣ ይሥራ ያሠራበት፣

ሃገር እንድታድግ ሁሉም እንዲያልፍለት.....»

በታዋቂው የሙዚቃ ሰው በተስፋዬ ለማ ዜማ ተደርሶለት፣ በጥላሁን ገሠሠ የተዘፈነው ይህ ዘፈን ብዙ ነገሮችን ያሳስባል። አንደኛ፣ ገንዘብ ያለው ገንዘቡን ያወጣል ወይ? መሥራ ማሣራት፣ የሚባለውስ ነገር ለምንድነው?..... እነዚህና እነዚህን ይመሳሰሉ ጥያቄዎችን ያስከትላል..... ለማለት ፈልጌ ነው። እንዲያውም እኔ እንደሰማሁት የግጥሙ ደራሲ ታዋቂው ኢትዮጵያዊ ፉትቦ አባት ይድነቃቸው ተሰማ ናቸው ይባላል። ዜማ ደራሲውን አላውቅም። ለማናቸውም ግን ይቅርታ፣ ሰለሞን ተሰማን የሚያህል ሰው ረስቼ ለዚህ ዜማና ግጥም መጨነቁ እኔኑ ራሴን አስገርሞኛል።

ስለ ገንዘብ ለመጻፍ ካሰብኩ ቆይቻለሁ ግን ስለ ገንዘብ መጻፍ ደግሞ ለእኔ በሚገባ ምክንያት ቀላል አይደለም። እቅጩን ለመናገር እኔ ራሴ፤ በልቶ የማደር ችግርም ባይኖርብኝ ደሀ ነኝ። ድህነቴን እንዳልደብቀው ሀብታም ያጋጥመኛል። እነሱን እመስላለሁ ብዬ ለመግደርደር ስሞክር ደግሞ ያው እንደ ራሴ የምጠላው ደሀ ያጋጥመኝና «ማነህ አንተ?» በሚል የማይሰማ ቋንቋ ያሳፍረኛል። መዋረድና ማዋረድ ሌላ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ በማፈርና በመኩራት መሃል ማለትም በደሃና በሃብታም መካከል ሆኖ ይህቺን ዓለም ግራና ቀኝ በትዝብት ብቻ እያዩ ማለፉ አልሆነልኝም። አሁን ግን......... የዓመታቶችን እይታዎች ሰብስቤ........ ድፍረቱን ከዋክብትና ጨረቃ ሰጥተውኝ ስለ ገንዘብ ለመጻፍ ተነሳሳሁ።

ገንዘብ ማለት ምንድን ነው?...... ብዬ ልጀምር። ይሄ ጥያቄ ዘመን ከተቆጠረበት ዓመታት ሁሉ ከተመተሩበት ጊዜ ጀምሮ በፈላስፎች በደራስያን፣ በሃይማኖት ሰዎች እና በተራው ሕዝብ ሲጠየቅና ሲመለስ የቆየ ነው።

ለመነሻ ያህል እስቲ፣ የሚከተሉትን አስተያየቶች እንመልከት፡-

እግዚአብሔር ስለ ገንዘብ ምን አስተሳሰብ እንዳለው ለማወቅ ከፈለጋችሁ ለእነማን እንደ ሚሰጥ ተመልከቱ።

ታላቁ ፍሬድሪክ (የጀርመን ንጉሥ)

«ሃያ ፓውንድ ሳገኝ የአንድ ዓመት ወጪዬ አሥራ ዘጠኝ ፓውንድ ይሆናል። በዚህ ገቢና ወጪዬ ደስተኛ እሆናለሁ። ገብዬ - ሃያ ፓውንድ ሆኖ የዓመቱ ወጪየኢ ከሃያ ፓውንድ ከበለጠ ኑሮዬ የስቃይ ይሆናል»

ቻርለ ዲከንስ (እንግሊዛዊ ደራሲ)

«የገንዘብ ፍቅር የኃጢአት ሁሉ ምንጭ ነው»

መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ኪዳን

«የገንዘብ ቦርሳዬን የሠረቀ ምንም አልሠረቀኝም»

ሼክስፒር (ኦቴሎ)

«የገንዘብ ጥያቄ ሲመጣ የሰው ልጆች ሁሉ ሃይማኖታቸው አንድ ይሆናል»

ቮልቴር (ፈረንሣዊ ፈላስፋ)

«የገንዘብ ጉዳይ የተማረውንና ያልተማረውን የሚለይ ወይም አንዱን ከሌላው የሚነጥል አይደለም፣ ተራው ሌባ ከባቡሩ ቅጥልጥሎች አንዱን ቢሠርቅ ምሁር ሌባ ባብሩን በሙሉ ይሠርርቃል»

ታላቁ ፍሬድሪክ (ጀርመናዊ ፈላስፋ)

እነዚህ አስተያየቶች ገንዘብ እንደ ዓለማችን ገዢ አድርገው ይቆጥሩታል። ለምሣሌ ታልቁ ፍሬድሪክ ሀብታሞች ሰላም የሌላቸው እፎይታ የማያውቁና ደስታ የራቃቸው መሆናቸውን ይነግረናል። የምሁር ሌባ ከተራው ሌባ እንደሚብስም እኛ ዝም ብለን የምናመልከውን ከእውነቱ ጋር ፍንትው አድርጎ አውጥቶታል።

መጽሐፍ ቅዱስና ቅዱስ ቁርዓንም ገንዘብ የኃጢአተኞች ሁሉ መነሻ መሆናቸውን ዱሮ ብለው ጨርሰውታል። ደራሲው ቻርለስ ዲከንስም «ገንዘብ ለሚያስፈልገኝ ወጪዬ የማይሆንልኝ ከሆነ ሥቃይ ይጥልብኛል» ሲል ካልኖርኩበት፣ የጎጆ ደስታዬን ካላገኘሁበት ምኔም አይደለም ማለቱ ነው። እንግሊዛዊው

ባለቅኔ ዊሊያም ሼክስፒር ግን ገንዘብን ትንሽ አድርጎ አይቶታል። እንደዛ አድርጎ ቢያየውም ግን ናቀ ማለት አይደለም። ይሄንን ስንኝ የጻፈው የሰው ልጅ ስም (ወይም የሕሊና ኩራት) ምን ያህል ትልቅ መሆኑን እግረ - መንገዱን ሊያመላክት ብሎ ነው። በተጠቀሱት አነጋገሮች (ወይም ጥቅሶች) ልብ ብለን የምናየው የቮልቴርን ጨካኝ አስተያየት ነው። ሰዎች ሃይማኖት የሚያደርጉት ገንዘባቸውን ነው...... የሚሉ ቃላት አልወጣውም። ለሱ ለኑሮ የደም ሥር የሆነው ገንዘብ ሃይማኖትን እንኳን ሳይቀር በሥሩ ያደረገ ኃይለኛ የዓለማችን ክስተት ነው ማለት ነው። ይሆን ሲገርመን ጆርጅ በርናርድ ሾው በራሱ አስመስሎ «እኔ ሚሊየነር ነኝ ሃይማኖቴም እሱ ነው» ብሏል።

ስለ ገንዘብ የሚያስብ ሰው ማሕበረሰቡንም አብሮ ማሰብ አስለበት። ከትንሣኤ (ፋሲካ) በዓል በኋላ ዳግማይ ትንሣኤ ሌላ በዓል አድርጎ የተረፈውን ሲበላ የኖረው ማሕበረሰቡን ከማን አንሼ ብሎ ቅልቅልን የፈጠው ትውልድ እኩል መታየት ያለበት አይመስለኝም። ጊዜ ጊዜን እየወለደ ይሄዳል እንጂ የገንዘብ ጉዳይ ዱሮም ሆነ ዛሬ በየዘፈኖች ይነሣል። የሀበሻው ንጉሥ የተባለው ጥላሁን ገሠሠ በ1952 ዓ.ም ከዘፈነው ዘፈን ሁለት ስንኝ ልንገራችሁ፡-

«እኔስ መስሎ ነበር የምትወጂኝ፣

ለካ ሀብቴን ኖሯል ገና ገባኝ»

ከዚያ በማከታተል በዘፈናቸው ውስጥ፡-

«እንደልቤ አግኝቼ ገንዘብ ካልሰጠኋት፣

ታባርረኛለች እኔ መች አጣኋት??

«የኔ ፍቅር ምክሬን ስሚኝ እባክሽ

ማጣት እኮ ምንም አይደል አትሸሺኝ።»

ከዚያ በኋላ ሦስት ይሁን አራት ትውልድ ቆይቶ ኤፍሬም ታምሩ

«ብትውልም መልካም ውለታ፣

በሐሳብ ብትንገላታ፣

እርሾ ቢጠፋ ማጀትህ፣

ማን አለ ኩቶ ከደጅህ፣

ኪስህ ነው ወዳጅህ።»

እነዚህ ግጥሞች ሁሉም ገንዘብ ሀብትን፣ ፀጋን...... የሚያንፀባርቁ ብቻ ሳይሆኑ ትልቁን ትንሽ ትንሹን ትልቅ የሚያደርግ ልዩ ምድራዊ ኃይል መኖሩን የሚያስተጋቡ ነበሩ። ከማንም ከምንም በላይ ግን ክፍለ ኢየሱስ አበበ የገጠመው «ከሌለህ የለህም» የሚያክል ስንኝ የለም።

«የሚያደምጥም የለም ወይ የሚረዳህ፣

አያልህ ካልሆነ ከሌለህ የለህም።

ማንም ይልክሃል እንደ ልጅነትህ፣

*ማግኘት ከድቶ ሄዶ ማጣት ሲያጋልጥህ።*

*ውለታህ ወሮታህ የላቸውም ቦታ*

*መች ይሆኑህና ለበቃ ሠላምታ።*

*ትልቁም ትንሹም ቢያዩህ አያውቁህም፣*

*ያንተ ነገር ሞቷል ከሌለህ የለህም።»*

ሰለ ገንዘብ ይሄን ይሄን አነሳሁ እንጂ ስለ ሀብታም እስካሁን ያልኩት ነገር የለም። እኔ እንደማስበው እንደ ሀብታም በዚች ዓለም የሚያስገርም ፍጡር የለም። ሀብታም ይወደዳል፣ ይሞገሳል፣ ዕድሜ ይስጥልኝ ተብሎ ይመረቃል፣ ባስ ሲል ደግሞ አላንተ የለም እየተባለ ይሞካሻል። ቢበጀውም ባይበጀውም የዚህች ዓለም ሐቅ ግን ይሄ ነው።

ሀብታሞች ሲባሉ፣ እንዳመጣጣቸው እንዳነሳሳቸውና እንደ ተፈጥሮ ባህሪያቸው ይለያያሉ ብዬ አስባለሁ። ባጠራቀውም ብር የሚመካ ያለኔ ሰው የለም የሚል፣ ትዕቢተኛን ሰው የሚንቅ..... ሀብታም አለ። የቲፎዞ ዓይነቶ ተቆጥረው አያልቁም። ነገ አፈር እንደሚገባ የሚያውቁትን ምስኪን ባለ ገንዘብ ለምን አቧራ ነካህ እያሉ ያልፈለገውን ዓይነት ፍጡር እያደረጉ ሲያሞካሹትና በትንሽ አንጎላቸው ሲሸነግሉት፣ ቲፎዞዎቹ የራሳቸው ጌታ ወይም በራሳቸው ትናንሽ ሀብታሞች የሆኑ ይመስላቸዋል። በመምሰላቸው ብቻ የሚፈጥሩት የራሳቸው ደስታ ዋነኛው ሀብታም የሕይወት አቅጣጫ እንዳይዝ እንዳይታረም..... እና በጎ በጎውን እንዳያስብ ያደርገዋል።

እወንቱን ለመናገር...... እኔ ራሴ ሀብታም ሰው መጣ ሲሉኝ በሠርጉም፣ በሐዘኑም በድግሱም፣ ስንት ጊዘ ሳላስበው ደጋግሜ ኖር ለማለት ተነሥቻለሁ። ሀብታሞች፣ አሁንም ቢሆን ልዩ መስህብ አላቸው። ደግሞም «ለምን አይኖራቸውም?» ብዬ ብሟገት ተሳስተሃል እንዳትሉኝ። ምነው በልማዳችን አንኳ፣ «ያለው ሰው ማማሩ!» እንል የለም እንዴ?! «ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ» የተባለው ዛሬ አይደለም። አበሾች ስንባል ግን በዚህ ዓይነቱ አነጋገር ላይ «እንደሠራ አይገድል» እንደምንል የታወቀ ነው። ከዚያው ጋር አያይዘን «ዓይኔ ይፍሰስ» ስንልም የክፋት አሽቃባጭነታችን አብሮ የሚገለጽ ይመስለኛል ፡

እጅግ የሚገርማችሁ ነገር...... ቢኖር ሀብታም በሕይወቱ የማያውቀው አንድ ሰው አለ። ዓለምን ሁሉ አውቃለሁ ሁሉ በእጄ ሁሉ በደጄ ነው እያለ...... ይሄንን ሰውዬ አያውቀውም። ሰዎችም አልነገሩትም። ይኖር ይሆን ወይ ብሎ መጽሐፍም አላገላበጠም። ቢያውቀው ኖሮ የፈለገውን ሁሉ ባይሆን እንኳ በመጠኑም ቢሆን የተቻለውን ያደርግለት ነበር። ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ አድባርዋም፣ አማካሪውም ጠንቋዩም፣ መጽሐፍ ገላጩም፣ ቃልቻውም ሚስቱም፣ ልጆቹም ሁሉ አልነገሩትም።

ሀብታሙ የማያውቀው ሰውዬ ማን እንደሆነ ግን እኔ ልንገራችሁ? ያውላችሁ ምንም ሳይኖረው ሁሉ ነገር ባዶ ሆኖ በለበሰው ጭርንቁስ ውስጥ ሀብታሙን ቀርጾ እንደሱ የሚራመድ እንደሱ የሚናገር እንደሱ ሻይ ሲጠጣ ውስኪ የሚያስመስል፣......... ያንን እምነት አዳብሮ ሳይታወቀው በተንሸዋረረ ሥነ - ልቦናዊ ሂደት...... ሀብታም ነኝ ብሎ የሚያስመስል የኔ ብጤው ሙልጭ ያለ ደሃ ነው። ለእንዲህ ዓይነቱ በሽተኛ ብታማትቡለት ሳትፀድቁ አትቀሩም።

የሀብታምን ዓይነቶች ለመተንተን ጊዜና ቦታ አይፈቅድልኝም። ነካ አድርገን ማለፍ ስላለብን ግን ከንቀት፣ ከትዕቢት፣ ከማን አለብኝነት፣ ጋር ስማቸው የማይነሳ እንዳሉ እናውቃለን። ገንዘብ አጥቼ ልጽደቅ ባይሉም፣ ደሀን የሚገፉ አሉ። የደሀን ዓመለ ቢስነት በሚገባ እያወቁ፣ መቼስ ምን ይደረግ፣ ይሁን እያሉ ለመጽደቅ

ሲሉ ብቻ ለጋሥ የሚሆኑም አይጠፉም። አክሱማዊው ፈላስፋ ዘርዓያቆብ «ኩሉ ይሤኒ ለእመ ንሤኒ ንሕነ» (እኛ ጥሩ ከሆንን ሁሉም ጥሩ ይሆናል) የሚለውን አባባል ግን ሀብታምም ሆነ ደሀ በምድራችን ላይ እስካሉ ድረስ ይገነዘባሉ ብዬ አላስብም። ይልቁንስ «ንግብአኬ ሀበ ጥንተ ነገር» የሚለው የንጉሥ ዳዊት ቃል የሁላችንንም ምንነት በአሳዛኝ መልኩ ይደመድመዋል።

ከ30 ዓመት በፊት ነው። የዓረብ ሃገር ሀብታም ይመጣና ሒልተን ያርፋል። በሀገሩ ብርቅ የሆነው ነገር እዚህ ለመቀመጥ አጋጣሚ ይሆንለትና ሴት ይዞ ለማደር ወደ መኝታ ክፍሉ ይገባል። የሆቴሉ ሰዎች «አይፈቀድም» ይሉታል። በምን ምክንያት ብሎ ሲደነፋ በተለመደው ትህትናቸው «ሚስትዎ ካልሆነች ሕጋዊ አይሆንም። ምክንያቱም እዚህ ፎቅ ላይ ለተኙት እንግዶች ሁሉ መጥፎ ምሳሌ ይሆንብናል።« ይሉታል። ዓረቡ ሰውዬ «ፎቁን በሙሉ ለሁለት ወር ተከራይቼዋለሁ» ብሎ ቼኩን ገና መጻፍ ሲጀምር የሆቴሉ ሰዎች በሀብታሙ በራሱ ቋንቋ «እስታሂል ኢትፈደል» ብለው ፎቁ ላይ የነበሩትን ሰዎች ወደ ሌላ ቦታ አዛወሯቸው። እናንተ ስታስቡት..... ገንዘብ ምን የማይሠራው ነገር አለ?

ዱሮ ኒውስዊክ ላይ ያነበብኩት ነው። ሁለት የመካከለኛው ምሥራቅ ሀብታሞች በኢ.ፔ.ክ ስብሰባ ብራስልስ ሄደው ከቆዩ በኋላ ለዕረፍት ወደ ጣልያን አገር ይሄዳሉ። ትልቅ ቁማር መጫወቻ ቦታ (ካዚኖ) ገብተው ከተዝናኑ በኋላ የካዚኖውን ባለቤት ጠርተው እስከ ስንት ሰዓት መጫወት እንችላለን? ይሉታል። ባለቤቱም እስከ ሌሊቱ ስድስት ሰዓት ብቻ መሆኑን ይነግራቸዋል። በዚህ ጊዜ «እንግዲያውስ ቶሎ መሄድ ሊኖርብን ነው። ዘና ብለን ለመጫወት እያንዳንዳችን ስድስት ሚሊዮን ዶላር ይዘን ነበር የመጣነው» ሲሉት የካዚኖው ባለቤት በመደሰት «እናንተስ ደስ ይበላችሁ። ካዚኖው ለ48 ሰዓታት ክፍት ይሆንላችኋል» አላቸው።

ገንዘብ ምን የማያደርገው ወይም የማያስደርገው ነገር አለ?! ከበደ ሚካኤል ታሪክና ምሣሌ ላይ ዱሮ የጻፉት ነገር ነበር። ሰውዬው ጫማ ሊገዛ ገብቶ በዋጋ ክርክር ሳቢያ «ቆዳው ይሸታል» ሲለው ነጋዴው «ሽታው ከቆዳው ሳይሆን ከኔ ነው» ይለዋል። አዬ ገንዘብና ሰው!

# የውበት ጉዳይ

ይህ ጽሑፍ በሞዴልነትና በማስታወቂአይ ሥራ የተሠማሩትን አይመለከትም። ምክንያቱም ሜክ. አፕ. አጠቃቀማቸውና ቅርጻቸውን የሚጠብቁበት ሁኔታ ከአሠሪ ድርጅቶች ዓላማና ፍላጎት ጋር በተያያዘ ነውና በሙያ ጉዳይ ጣልቃ መግባቱ አስፈላጊ አይሆንም።

ውበት ስንል ከወንዶቹም ጥቂቶቹን ከግምት ሳናወጣ አብዛዎቹ ሴት ልጆችን የሚመኙትን፣ የሚፈልጉትና የሚጨነቁለትን ውበት ማለታችን ነው። ማንኛዋም ሴት በተለይ አሥራ ስምንት ወይም ሃያ ዓመት ዕድሜ ላይ ከደረሰች በኋላ ቆንጆ ሆና መታየት ትፈልጋለች። ቁንጅና ስትፈልግ ግን አንዳንዶቻችን እንደምናስበው ሁሌም ወንዶችን ለማጥመድ አይደለም። መቼም ወንዶች እንደሚፈልጉት አምሮ መታየት ከሞላ ጎደል የሴቶች ዓላማ መሆኑ አይጠያየቅም። ይሁን እንጂ ቆንጆ መሆን ወይም ባይሆንም ለመቆንጀት መጣር በራሱ ዓላማም ግብም ይሆናል። ማማር ደስ ይላል። ንፁሕ መሆን ለራስም፣ ለፍቅረኛም ለኅብረተሰም ደስ ይላል።

ከጓደኛ ላለማነስ ዋና ምክንያት ይሆናል። በራስ መተማመንን ያስገኛል። ማማር ጥሩ ነው። «ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል» ይባል የለ?

ውበት ማለት በተፈጥሮ የሌለውን በግድ መፈለግ አይደለም። ያለውን እንዲሻሻል ማድረግ፣ ጐልቶ እንዲወጣና መስህብ እንዲሆን ማድረግ የውበት ማንከባከቢያ ዋናው ዘዴ ነው። አጠር ብላ የተፈጠረች ልርዘም እንደማትል ሁሉ ረጅም የሆነችውም ልጠር አትልም። ቁመታቸውን የሚያስተካክሉበት መንገድ ግን ያችኛዋ በታኮ ጫማ ትጠቀማለች፣ ይቺኛዋ ታኮ ባልሆነ ጫማ ወይም ቁመት ቀነስ በሚያደርግ ዓይነት አለባበስ ትጠቀማለች። የእኛ አገር ሴቶች ይሄን አያውቁትም ማለቴ አይደለም። ብዙዎቹ ሲያደርጉት ግን አላየሁም ማለቴ ነው። ሌላው ቀርቶ ለብርድና ሙቀት፣ ለግብዣ (የቀንና የምሽት) ለሽርሽር፣ የሚሆናቸውን አለባበስ አጣርተው አያውቁም ቢያውቁም ሥራዬ ብለው በተግባር አያውሉትም የሚል ሐሜት አለ። እኔ እዚያ ውስጥ ሁሉ የለሁበትም። ጳውሎስ ኞኞ በአንድ ወቅት «ከትራፊኮች ጋር ልታጣሉኝ ነው ወይ?......» እንዳለው ዓይነት ይሄን ጽሑፍ ገና ስጀምረው ፍርሃት ፍርሃት ብሎኛል። ምክንያቱም አበሻነታችን ቁልጭ ያለ ጤናማ ሐሣብን እንደ አቃቂር (ወይም ስድብ) የመውሰድ አጉል ልማድ ገና ከድሮው የተጠናወተው ነውና። ለምሣሌ ገና ብዙ ሩቅ ሳንሄድ ቦርጫም ሴት ሱሪ መልበስ አያምርባትም....... ወይም እግረ ቀጭን ቀሚስ ባትለብስ ይሻላል....... ቢባል እወንት አይደለም? አንድ ሴት ሞላ ያለ ጡት ሳይኖራት ደረቷን ገልታ ብትሄድ ምን ይጠቅማታል? ምናልባት ለሙቀት ብላ ከሆነ በጣም ልክ ናት። በብርዳማ ምሽት እንደዚያ ብታደርግስ? ከአንዲት ሀያ ዓመት ውስጥ ያለች ሴት ልጅ ነገን ሳታስብ በጣም በምትሳሳለት ፀጉርዋ ላይ ፋሽን እንው ብላ በማሰብ ደጋግማ በሞቃቱ አየር ኮፊያ ግንባርዋ ድረስ ብትደፋ ያ ውበት ጊዜያዊ ነው ወይስ ሌላ?

እንግዲህ ፍርሃቱ እየለቀቀኝ መጣ መሰለኝ። ብዙ ብዙ ብናገርም ያመንኩበትን ነገር ወደ ኋላ እያደረግኩ ማፈገፈግ የአልብኝም። እውነት ለመናገር ተወልጄ ባደግኩባት አገር በአለባበሳቸው ብቻ እናትና ልጅን መለየት ያቃተኝ ጊዜ አለ። አንዳንድ ነገሮች ቀድመው ይታያሉ። ጠጋ ሲሉ ደግሞ ሌላ ስዕል ይመጣል። በዚህ ሁኔታ ፊታቸው ላይ የተለያዩ መስመሮች ያሉባቸው መሆኑን ጠጋ ስል ያየሁባቸው ታይት የለበሱ 60 ዓመት የሚሆናቸው እናት እስካሁን አይረሱኝም። ገና በአሥራ ስድስት ወይም አሥራ ሰባት ዓመት ዕድሜዋ ጡቷን ፍጥጥ አድርጋ ሠርግ ቤት ስትመጣ.......እናት እጃቸውን አንገትዋ ላይ ጣል አድርገው አይዞሽ በሚል አስተያእይት ቦርጫቸውን በአንድ እጃቸው ነካ ነካ እያደረጉ እንደ እኩያ ወደ አዳራሹ የገቡበት ሁኔታ በወቅቱ እንደ መዘግነን አድርጎኝ ነበር። የእናትና ልጅ ፍቅር ያስገደዳቸው መሆኑ ቢገባኝም ታዝቤያለሁ።

የውበት ጉዳይ ሲነሳ..... አጋጣሚ ሆኖ የአለባበስን አኳኋን አነሳሁ እንጂ ሌላ ሌላውን መቼ ነካሁት?......። የሊፕስቲክ አጠቃቀም፣ ቆንጆ ከንፈር ያልፈጠረብን እስኪያስመስለን ድረስ..... የሚቀባባው ኮስሞስቲክ ዓይነትና ብዛት ሽቶ አምራቾቹን እስኪያስበረግግ ድረስ...... ዓይን መቀንደቡንና ሽፋሽፍትን መላጨቱ ሁሉ፣ የውበት አስቀያሚዋ የሌላ አገር ጣኦት አሻንጉሊት ስታደርገን....... እስቲ መለስ ብለን ራሳችንን እንቃኝ ለማለት ነው። ዘመናዊነት በየትኛውም የዓለም ጎራ አለ። እንዲያውም ዘመናዊነትን መዋጋትም ሆነ ማስወገድ አይቻልም። ይሄ ሐቅ ዱሮም የተባለ ዛሬም የሚባል ምንጊዜም የኖረን የሚኖር ነው። ነገር ግን ምንም ምን ብትሉ ኅብረተሰብ የሚያምንበት ይሄ ነው የምንለው የሚያከባበረንና ራሳችንን ለራሳችን አሳውቆ ለሌላው ዓለም የሚያስተዋውቀውን........ኢትዮጵያዊነት የሚል ቋንቋ አለን።

አቤት! ይሄ ውበት የሚባ ጣጣ! ስንት ወሬ ውስት ሊያሰባኝ ነው?! አሁን ደሞ ምን ትዝ አለኝ መሰላችሁ? ውበትና ውፍረት ወብትና ቅጥነት። መቼም እዚህ ነጥብ ላይ...... ብዙ ውይይት (እንዲያውም ክርክር) ሊመጣ እንደሚችል ከወዲሁ እገምታለሁ። ተደማምጠን ካበቃን በኋላ ግን የምንስማማበት እንጂ

የምንጣላበት አይሆንም። ባህል የሚለውን ፅንስ - ሐሳብ ጠለቅ አድርገን ካሰብን በኛና በፈረንጆቹ መሃል ልዩነት መኖሩንም መገንዘብ አለብን። በእኛ አስተሳሰብ ወፈረች ማለት እኮ ተመቻት ማለት ነው። ቅርጿዋ ለአበሻ ስሜት ምቹ ነው ማለት ነው። በፈረንጆቹ ወፍራም (fat) የቅርጽ ውበት የላትም የሚል አስተሳሰብ ይኑረው እንጂ ደልዳላ (plump) የሆኑት ከወበት መድረኩ ያስወጧቸዋል ማለት አይደለም። በአበሾቹ ባህል ሞላ ያለች ደልዳላ (ወይም ሞንዳላ) ሴት እንደምትወደድ ምንም አያጠያይቅም። (plump) ፈረንጆቹ ብለው ገና ድሮ ቃል ሲፈጥሩ እኛ የምንወደውና የሚስማማን የወበት ቅርፅ በነሱም ይወደዳል ለነሱም ይስማማል ማለት ነው። አሁን ችግሩ ያለው ወፍራም (fat) የሚባሉትን ሴቶች ቅርፅ እመቀበሉ ላይ ነው ይሄንን አስተሳሰብ ሁላችንም እንጋራለን።

ውፍረት ለእኔ እንደሚገባኝ በተፈጥሮም በአመጋገብም በሥራ ጠባይም የሚመጣ ነው። በሕክምናው ዓም ብዙ በሽታዎችን ያመጣል መባሉን እናውቃለን። መወፈር ለእንቅስቃሴ እንደማይመች በተለያዩ ሁኔታዎች (ለምሳሌ በሥራ፣ በስነ - ልቦናዊ ማኅበራዊ....) ችግር እንደሚያስከትልም ግልጽ ነው። ከውበት አኳያስ እንዴት ይታያል? ወደሚለው ብንመጣ የብዙ ሴቶች አንገብጋቢ ችግር ሆኖ እናገኘዋለህ። በእውነቱ፣ የውፍረትን መፍትሔ እኛ ጠቁመን የምዘልቀው አይደለም። የውፍረትን መፍትሔ እኛ ጠቁመን የምንዘልቀው አይደለም። ውፍረት (እንደ ደረጃው የሚለያይ ቢሆንም) እየበዛ ከሄደ ሲበዛ መቀነስም ካልተቻለ፣ ጤናማ አለመሆኑን እናምናለን። በተቻለ መጠን ከተፈጥሮአችን ጋር እየታገልን ራሳችንን ማሻሻል እንጂ ማማረሩ ጠቃሚ አይመስለኝም።

የውበትን ጉዳይና ውፍረትን በዚህ ከቋጨን....... ውበትና ቅጥነት ወደ ሚለው እንመጣለን። ኒውስዊክ የተሰኘው መጽሔት ስለ ፋሽን በማያወራበት ገጹ በስፔይን ዋና ከተማ ማድሪድ ሞዴሊስቶች እየተግተለተሉ ሲገቡ አዲስ ደንብ ማውጣታቸውን የፋሽን ሾው አፈ - ጉባዔ የሆነችው ቤሊንዳ ለ - ስኮምብ «ከተወሰነ ክብደት በታች የሆኑትን ሴቶች ድርጅታችን ይቀበልም» በማለት የፋሽኑን ዓለም ያስገረመ ንግግር አድርጋ ነበር። በዚህም አሳብ የተደናገጡ መኖራቸው ባያጠያይቅም ጉዳይ የብዙ ፈረንንጆችን አስተያየት መጋበዝ አልቀረም። አፈ - ጉባዔዋ አላግባብ መቅጠንን በማውዛቷ ተስማምተውበታል።

ከብዙ አስተያየቶች አንድ ሁለቱን ብጠቅስላቸው.......

«ሴቶች ቀጭን ካልሆንን ብለው የሚያዩት መከራ አይገባኝም። ሞዴሎች ሲባሉ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ስቃይ ተርፈው የመጡ፣ አሳዛኝና ዘግናኝ ፍጡራን ለምን ይሆናሉ? የፋሽን ኢንዱስትሪ ቅጥነት ተገቢ ነው በሚል ስብከቱ ጣዕረ - ሞት የመሰሉ ሴቶችን ለዚያ እንዲበቁ መገፋፋቱ እጅግ ያሳዝናል.......»

«የማድሪድ ውሳኔ ትክክል ነው። ሴቶች በጣም እንዲቀጥኑ ማድረግ ምን ይባላል? ሞዴሎቹ ቢጠየቁ መልሳቸው አሻቅቦ የሚወጣው ወደ ዲዛይነሮቹና የፋሽን ማጋዚን ፎቶ አንሺዎች ነው። የፋሽን ኢንዱስትሪው ጠማማ አስተሳሰብና ዓላማ ካሁኑ ማቃናት አለብን ሴት ልጅ ለመቅጠን ተርባ መሞት አለባት ወይ?.......»

«ከሴቶች የሥነ - ልቦና ፕሮፌሽናሎች (Psychologist) አንዷ ነኝ። እጅግ የሚያሳዝኑና የሚያስደነግጡ የሴት ልጆችን ችግር እያየሁ ከዕለት ወደ ዕለት ትዝብቱ ሊለቀኝ አልቻለም። ጤነኛና ቆንጆ የሆኑ ሴቶች ወደ ቢሮዬ (ክሊኒክ) በየዕለቱ ይመጣሉ። ቆንጆ ሰውነታቸውን ይጠሉታል። ባላችሁበት ሁኔታ ውበታቸውሁ ይበቃችኋል ስላቸው በጣም መቅጠን ስለሚፈልጉ ብቻ ምግብ ትቼአለሁ ይሉኛል። እንዲህ ያሉት ሴቶች ሰዎች ሳያውቁባቸው በጥንቃቄ እየተራቡ መሆናቸውን ሳስብ ለውበት ሲሉ ሞትን የመረጡ ይመስለኛል። ቁጥራቸው በየጊዜው እየጨመረ መምጣቱን ሳስበው...... የሰሞኑን የማድሪድ ፋሽን ሾው ውሳኔ በጣም መደገፍ ብቻ ሳይሆን ኧብረታታለሁ። አደጋ ላይ የሚጥል የቅጥነት ሩጫ የት ያደርሳል?......»

እንግዲህ መቅጠን፣ በጣም መቅጠን (የመራብን ጣጣ ትተን) ለውበት አስፈላጊ ነው ወይ? ወደ ሚለው ልንመጣ ነው። የፋሽን መሥራቾችና አራማጆቹ ፈረንጆች ቅጥነትን አስመልክቶ ያሉትንና እያመነቡት የመጡትን ከላይ መጥቀሳችን ታዲያ እኛን እንዴት ሊያስቆታ ይችላል ብለን በመገመትም ነውና፣ እዚህ ላይ መነጋገራችን ሌሎች ውይይቶችን ከማስከተል በቀር ሌላ ውዝግብ አያስከትልም ብዬ አምናለሁ።

ቅርፅ የሚባለው ነገር እንኳን በሰው በድንጋይም ላይ አለ። ለምን እንደሆነ ባላውቅም...... ቅርፅ ባይኖር ኖሮ፣ ይቺ ዓለም ሠልችታን የዕድሜያችን ሂደት በሙብላትና መጠጣት ወዘተ......ይወስን ነበር እላለሁ። የቂል አስተሳሰብ ይምሰል እንጂ እኔ ሳስበው..... ዛፎች ሁሉ ወደ ጎን ቢያድጉ..... ወፎች እማይበሩ ሆነው እንደኛ ቆመው ቢሄዱ..... ምን ይባላል? ሰው ድቡልቡል ሆኖ ቢፈጠርስ? የሴቶችን ውበት የሚዳስስ ጣት ባይኖረንስ? የሚዳስሰው አካላቸውን ቦታ ቦታ ባይኖረው? የላዩ እታች፣ የታቹ፣ እላይ ሆኖ የተመሳቀለ ሁኔታ ቢፈጠርስ?......እነዚህ አባባሎች ቅርጽ የትም ይሁን መቼም በአርቲስቱ እይታም ሆነ በመሐይሙ ገጠመኝ (ልማድ) በተፈጥሮአችን መኖሩን በግልጽ ያሳያሉ።

ስለዚህ የሴት ውበት ጉዳይ የሚጀምረውም ሆነ የሚያጠነጥነው ቅርጽ ላይ እንጂ አለ አግባብ መቅጠን ላይ አይደለም። እይፋሽን ሾው ተሳታፊ የሆኑ ሴቶች፣ ሞዴሊስቶች የማስታወቂያም የሕዝብ ግንኙነትም፣ የኦፊስ ሴክሬቴሪዎች ሁሉ..... ቅርጽ መጠበቅ እና ቆንጆ መሆን እንዳለባቸው ይገባናል። ቆንጆ የመሆን ፍላጎታቸው ግን ኢትዮጵያዊነት የተላበሰ ቢሆን ጥሩ ነው። ከአበሻ ወይም ከመላው ሕብረተሰብ የሚፈልገው ቅርጽ መካከለኛ ውፍረት ወይም ደልዳላነት (plump) መሆን ከሆነ ካልቀጠንኩ ሞቼ እገኛለሁ ማለትን ምን አመጣው? አልፎ ተርፎ እራት አልበላም፣ ሙብላት ያስጠላኛል እያሉ ከመሬት ተነሥቶ መመንመን ምን ይባላል? እኔ ሳስበው አርባ ዓመት ላይ ሲደርሱ በዚህ አስተሳሰብ ራሳቸውን አንፀውና ተሸሞንሙነው የኖሩ ሴቶቻችን የጤና መታወክ ብቻ ሳይሆን ያ የሚፈሩት እርጅና ያለ ዕድሜያቸው ጠልፎ ሊጥላቸው ይችላል። ያም እንኳን ባይሆን በውስጣቸው የሌለው ኤች. አይ. ቪ. ሰበብ ተደርጎባቸው፣ ያለ ስማቸው ስም ተሰጥቷቸው የቁም ሥቃይ ሲሰቃዩ ይቻላሉ።

እዚህ ላይ እንግሊዛዊው ባለቅኔ (ገጣሚ) ኦስካር ዋይልድ ትዝ አለኝ። አባባሉን ከምነግራችሁ በፊት ይቅር በሉኝ። ከዛሬ መቶ ምናምን ዓመት በፊት የነበረ ሰው ነው። እና..... እንደዚያ ዘመን ጓደኖቹ ሁሉ ሴቶችን መጠራጠር መጥላትና መናቅ፣ ተንኮለኞችና ሟርተኞች ናቸው ብሎ ማሰብ ደስ ይለው ነበር። እና ምን አለ መሰላችሁ? «ሴት ልጅን ቆንጆ ነሽ ካላችኋት ሰይጣን ያንን ያላችሁንት አንድ ሺ ጊዜ ያስተጋባላታል» ይሄ እንግዲህ ውበትን በጣም እንደሚፈልጉ ያሳያል። እንደ ማርጋሬት ታቸር አባባል ደግሞ «ዓላማውን በተግባር እንድትተረጉምለት እግዚአብሔር ለወንድ ሴትን ፈጠረለት»። ይሄን አስተሳሰብ እነ ጎልዳሜየር፣ እነ ኦልብራይት ከመጋራታቸው በፊት ብዙ ሴት ደራስያን ገና ዱሮ ብለውታል። ብርቱነታቸው፣ ዓላማ ወደ ኋላ እንዳይል ጭካኔም ሆነ ደግነት (ሁለቱም ያሉ ናቸውና) በአግባቡ እንዲከወን......የዓለማችን አስፈላጊነትና ተፈላጊ ድብቅ ሻማዎቻችን ናቸው።

ጀምስ ሰርበር የተባለ አሜሪካዊ ጋዜጠኛ ብዙ ልምዶችን በኒዮርክ ታይምስ ላይ ሲአካብት ቆይቶ ጥሩ ወግ (essay) ፀሐፊ ለመሆን በቃ። ከሱ ወጎች አንዱና እጅጉን ያስገረመኝ በአርዕስቱ «ለጥሩ ጋብቻ ያሉኝ የግሌ አሥር ደንቦች» (My ten rules about marriage) የሚለው ነው። ባለ ትዳርና የልጆች አባት የነበረው ሰርበር የራሱን ያደገበትን የአሜሪካ ሕብረተሰብ ጥሩ አድርጎ ተችቷል። ደንቦቹን ዛሬ አላስታውሳቸውም። የማስታውስ፣ እንኳን ቢሆን ሴቶቻችንን ስለሚያስቆታ አንዱንም አልናገረውም።

ይልቁንስ የሚገርማችሁ (ኡኡቴ - ደሞ - ይሠኛል)። ሰርበርን ተከትዬ የራሴን አምስት ደንቦች አላወጣሁ መሰላችሁ ቂ.....ቂ.......ቂ......

1ኛ/ <u>ራስሽን ሁኚ፡-</u> ማኔጅመንቱም ኤጅኬሽኑም፣ ሶሻል ወርኩም፣ ሩራሉም፣ ኧርባኑም ሳይንስ ራሳችሁ ሁኑ ይላል። ሥነ ልቦናማ ዋናው ነው። ስለዚህ ሌላውን አልሆንም ማለት ምን ያቅታል? ሳያዛልቅ ያችኛዋን መምሰል ምን ይጠቅማል? አንቺ ለአንቺነትሽ አንቺ ነሽ። እሷ ለእሷነቷ እሷ ነች። ስለዚህ ቀጭን ከሆንሽ ቀጭ ነሽ። ወፍራምም ከሆንሽ ወፍራም ነሽ። ጠረጴዛው ተዘርግቶ ሲለካ መሃሉ ላይ ቦታ ካገኘሽ ጥሩ ነው። አለዚያ ራስሽን ብትሆኚ ተቀብለሻልና ከድሉ ሦስት አራተኛውን በእጅሽሽ አስገብተሻል። ቀሪው ጊዜውን ጠብቆ ይመጣል።

2ኛ/ <u>ዋናውን የውበት መስህብሽን ፈልጊው፡-</u> ቸል ስላልሽ ነው እንጂ መስህብ አለ። «ሰላም ቀንዲ አይከብዳትም» እንደሚባለው በደንብ አበክረሽ አላሰብሽውም እንጂ በውስጥሽ አለ። በዚህች ዓለም ላይ እንደ ወንዱ ሁሉ ሌሎቹን እያዩ ራሳቸውን የሚረሱ ቀናተኛ ሴቶች አሉ። ልብ ብለሽ አላስተዋልሽም እንጂ ራስሽን ማንም ፍጡር ሳይሰማሽ ብትፈትሺ ያች ካላት መስህብ የማያንስ ወይም የበለተ አንቺ ዘንድ አለ። ይሄንን በአጭሩ ላብራራልሽ። ሰዎች የማዩትን የውጭ አካልሽን እርሺና ስለ ሴት ልጅ መስሕባዊ ጥበብ አስቢ። ያ ውበት መመኪያሽ መሆኑን ካሰብሽና ካወቅሽ እና በተግባር ልጠቀም ካልሽ ይቺ ጉረኛ ዓለም ከቶም አጠገብሽ አትደርስም።

3ኛ/ <u>አካላዊ ውበትን ውስጣዊ ውበት እንደሚተካውና ባይበልጥም እንደሚስተካከል እወቂ፡-</u> እንግሊዞች «ቆንጆ ማለት ቁንጅና የሚጠይቀውን የሚያደርግ ነው» የሚል ምሣሌያዊ አነጋገር አላቸው። (Handsome is as handsome does) በዚህ አባባል ውበት አካላዊም ውስጣዊም መሆኑን እንገነዘባለን። ውበት አፍራሽ ነገሮች አሉት። ጥሩ ቅርጽን መጥፎ አቋቋም ያባለሽዋል። ብሩህ የሆነ የፊት ፀዳልና ፈገግታ በማያስፈልግ ጩኸትና ተነታራኪ ድምፅ ይደበዝዛል። ቆንጆ መልክ የሚፈነጥቀውን ብርሃን ሾካካነትና የሞጥሟጣነት ባህርይ መንገድ ያስቀረዋል። ስለዚህ ውበትሽ ከመልካም አንደበት፣ ከጥሩ እንግዳ አቀባበል፣ እርጋታና ደርባባነት የሚመነጭ መሆኑን እመኚበት ውስጣዊ ውበትሽን ከአዕምሮሽ ጋር ከተጠምቀምሽበት አካላዊ መስህብሽም እየጎላ ይሄዳል።

4ኛ/ <u>ትምህርትና ንባብ ማሕበራዊ መግባባት በአካልሽ ዙሪያ የምትፈልጊውን ውበት ሙሉ ለሙሉ ባይተካውም የተሟላ ያደርገዋል፡-</u> ትምህርት ከንባብና ከማሕበራዊ ግንኙነት የሚቀምስና አዕምሮ የሚያዳብር የዕድሜ ልክ ሂደት ነው። በራስ መተማመንን ይፈጥራል። አካልሽ በዳበረ አዕምሮሽ ከታዘዘ ፉንጋነትሽም ሆነ የተዛባ ቅርጽሽ የራሱን መስህብ ይፈጥራል።

5ኛ/ <u>አርቲፊሻል (ቅብ ተፈጥሮ) በምንም ዓይነት አይጠቅምሽም፡-</u> ለጊዜው ሊያረካሽ ቢችልም አያዛልቅሽም። ዘመናዊ በተባሉ መንገዶችና ካፌዎች...... ልክ እቤታቸው መስታወታቸውን እያዩ የማማር ልምምዳቸውን እንደሚያደርጉት ዓይነት፣ አረማመዳቸው አኳኋናቸው ሁሉ ያንኑ የቤቱን የሚመስላቸው ቆንጆ ሴቶች አይቻለሁ። አመለካከታቸው የአካል እንቅስቃሴአቸው አካሄዳቸው..... ሕይወት የሌለው የሥዕል ዓይነት ይሆናል። አንድ ቆንጆ ልጅ በአጠገብዋ ባሉት ሱቆች (ወይም ቡቲክ ምናምን) ለናሙና ኮት፣ ሱሪ አድርገው የተገተሩትን ግዑዛን መምሰል አለባት እንዴ?! ግራ ቀኝ የማይታይ ሴት እኮ ግዑዝ ናት። ፍጥጥ አድርጋ በአርቲፊሻል እይታ የምታተኩርበት ሰማይ እንኳ ቆንጆ ነሽ አይላትም። አካሄድሽና አስተያየትሽ የተጠናም ዓይነት ቢሆን እንኳ ተፈጥሮሽን ሊደብቀው አይገባም። ሥዕል አትምሰዪ የሚለው

ማጠቃለያ ምክሬ ንቅናቄሽ፣ የዓይኖችሽ ትክታና ጠቃላላ ገፅታሽ ፈገግታ ጨምሮ ተፈጥሮአዎ ማንነሽት የሚያንፀባርቅ ይሁን......የሚለውን ይመለከታል። ውበት ኖረሽም አልኖረሽም ሰው ነሽና!

# አንድ ቀን እንደ ለማኝ

ልመና ሥራ ነው። ልመና ግዴታም ነው። ከላይ ከታዘዘ ዕጣ ፋንታም ነው። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ዕጣ ፋንታ ሆኖብኝ አያውቅም። እጅ እግሬ ደህና ነው። እንዲያውም ሰውነቴን አውቄ ለፈስፈ አንዳንዴም እንክስ ኮሰስ እያደረግኩት ነው እንጂ በፊዚካል ረገድ ጥሩ አቋም አለኝ። ለመናን እንደ ሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ሥራና ግዴታም ያደረግኩት ያለ ምክንያት አይደለም። ከግዴታው ብጀምርላችሁ..... ሰው ካጣ ከነጣ ምን የማያደርገው ነገር አለ?! ያልሞከርኩት የሥራ ዓይነት የለም። ከዕለት ጉርስ ያልፍኩበት ወቅት አላጋጠመኝም። ዶኬዬን በልቼ የስሙኒ ጠጄን ከአካል ጉዳተኖች ጋር አራት አምስቷን ጠጥቼ በረንዳ አድራለሁ። ሥራ ስለዋውጥ ከርሜ አንድ ቀን በድንገት ታመምኩ። ተንሥቼ መሥራት አልቻልኩም። በተኛሁበት የሚያውቁኝ ሣንቲም እየወረወሩልኝ ያገኘሁትን እየቀማመስኩ አንድ ወር ያህል ቆየሁ። ከዚያ አገግሜ ሥራ ፍለጋ ብዞር ከየት ይምጣ?! ልመና ግዴታ ሆነ። ግዴታ ደግሞ ያለ ሥራ ስለማይሆን ልመናን ሙያ አደረግኩት።

መጀመሪያ ጓደኖቼ እርጥባን ብለው ሃያ ብር ያህል አሰባሰበው ሰጡኝ። እሱን ይገቼ መርካቶ ጭድ ተራ ሄጄ ለማኞች ለነጋዴዎች የሚሸጡትን ቡቶቶና በነጭ ክር የተተበተበ ማላበሻ ሁለት ዓይነት ካልሲና የተጣመመ፣ አፍንጫው ወደ ላይ ያሞጠሞጠ አሮጌ ጫማ ገዛሁ። ከሃያ ብር አሥራ ሁለቱንም አልጨረስኩ። ያን ያንን እዛው ለባብሼ ከጭድ ተራ ወታ ስል ደንበኛ ለማን መሆኔን ለማረጋገጥ መስታዋወት ማየት አላስፈለገኝም። የዚያን ዕለት ሥራዬን ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ጀመርኩ። የተቻለኝን ያህል በድሪቶዋ ላይ ጣል ባደረግኳት ውትፍትፍ ጨርቅ ፊቴን በከፊል ሸፋፍኜ ዳግማዊ ምኒልክ ሐውልት ፊት ለፊት ባለው በር እግሪነ ሸፈፍ አንከስ አድርጌ ገና እንደደረስኩ ለማኝ ሁሉ ዓይኑን አፈጠጠብኝ። እድነ መደንገጥ ብሎ ባገኘሁት ክፍት ቦታ ቁጭ ስል፡-

«ወንድም ይሄ ቦታ ያንተ አይደለም» አለኝ አንድ ሁለት እግር የሌለው ለማኝ።

«ቤተክሲያን አይደለም እንዴ?» አልኩት።

«ያንተ አይደለም አልኩህ ያንተ አይደለም» አፈጠጠብኝ።

«እሺ.......የማነው?»

«የማንን ቦታ ምነው የሚጠይቀው አባክህ?» አለ ከሱ አጠገብ ያለው ዓይነ ሥውር። ይህን እንዳለ «ስለ ጊዮርጊስ» እያለ በጣልቃ መለመን ጀመረ።

ነገሩ አናደደኝ። በገዛ አገሬ ባይተዋር ያደርጉኛል እንዴ?!

«ግብር ከፍላችሁበታል እንዴ?» አልኩ በቁጣ።

የመጀመሪያ ለማኝ ዱላውን አነሣ። «ኸረ ቆዩ እኔ አስታግስላችኋለሁ» አለና ወጠምሻ ለማኝ ተነስቶ ከወዲያኛው ረድፍ ቡጢ ጨብጦ ወደኔ ራመድ ማለት ጀመረ። ጡንቸኛ ጎረምሳ ነው። በብርድ ልብስ ተጀቡኗል። አጭር ቁምጣውን የሞላው ጥቁር ጭኑ እዚያ በተሰበሰቡበት ለማኞች ላይ ሁሉ የሚያፌዝ ይመስላል። በጥፊ ቢማታ መዳፉ የማንንም ፊት ሙሉ በሙሉ ሊሸፍን ይችላል። እኔ ግን ዛቻውን ከመጤፍም አልቆጠርኩት። ለመከላከ ስዘጋጅ፡-

«ኸረ ተው...... እግዚአብሔር ደጃፍ ደግ አይደለም......» አሉ አንዲት መነኮሲት።

«አስታርቋቸው» የሚለውና «ይለይላቸው» የሚለው ወገን ሲጯጯሁ፡-

«ና ወዲህ.......» አሉኝ ፊት ለፊቴ የተቀመጡት ሽበቶ ለማኝ። በጣም ጎስቋላ ናቸው። ዕድሜ ጎድቷቸዋል። ጥርሳቸው ወላልቋል። ግርማ ሞገሳቸው ግን በግልፅ ይታያል።

ወደ ሽበቶው ሄጄ ጎናቸው ቁጭ ስል ጠብደሉ ለማኝ እንደ ማፈር አለና ተመለሰ። ሌሎቹም የሆነ ነገር እያልጎመጎሙ ትክ ብለው ያዩኝ ጀመር።

«ዓለም እኮ የሁሉም አይደለችም...... የኔ ልጅ.....» ገና ከማለታቸው።

«ታዲያ ለልመና ቦታ ይከለከላል?» አልኳቸው ሲቃ እየተናነቀኝ። የታፈነው ንዴቱ ልውጣ ልውጣ ማለቱን ቀጥሏል። እንዴት ተወልጄ ባደግኩበት አዲሳባ!።

«አየህ.... ጥጋብ የተጀመረው በኛ ነው...... ለዚህ ነው የማያልፍልን..... ለዚህ ነው ባለ ፀጎች የሚስቁብን...... ወጣቶች የሚፀየፉን። በፀባይ ለመኖር ነው መጣር ያለብህ.....» አሉኝ።

«እሺ....... አባቴ» አልኳቸው።

«ደሞ....... በሚስጢር ያዘውና.....» ማለት ሲጀምሩ።

«ደሞ ምን?» አልኩ ቸኩዬ። ምን ምሥጢር ይኖራቸው ይሆን?...... አልኩ በሆዴ።

«እኛም ጋ የእሥር ቤት የሻማ ዓይነት ደንብ ስላለ...... ሀያ ሰላሣ ብር ያህል መተዋወቂያ መስጠት አለብህ። አሁን ካላህ አሁን ትሰጣለህ.......ከሌለህ ሦትስ አራት ቀን ሠርተህ ትሰጣለህ...... አይዞህ አትጨነቅ....... እኔ እነግራቸዋለሁ......» ሽበቶው በሹክሹክታ ነገሩኝ።

«እሺ....... አባቴ ኸረ ከቃላችሁ አልወጣም...... ግን እንደው ለማወቅ...... ክፍያው ምን የሚሉት ነው?»

«አይ..... እስካሁን እንኳን ስም አላወጣንለትም። ግን ለጊዜው የጊዮርጊስ ግብር ልትለው ትችላለ። ምን መሠለህ አንድ ሃያ ብር ያህሉ ጌጃ ሠፈር ተሰብስበን የሰንበት ጠላ የምንጠጣበት ነው። የቀረውን ሠላሣ ብር አዲስ ለማኞች ሲመጡ የሚሰጡትን ለጠላ እየቆረጥን አንድ ላይ አጠረቃቅመን ለዓመቱ ሚያዝያ ጊዮርጊስ ጧፍ፣ ዕጣንና ሌላም ሌላም ገዝተን ለቤተ ክርስቲያኑ ገፀ - በረከት እናቀርባለን።»

«ጥሩ ነው በእውነቱ...... ለማነው ገንዘቡን የምሰጠው?» ስል ጠየኳቸው።

«ሰብሳቢያችን ቅድም ሊጣላህ የነበረው ጎረምሳ ነው። ገንዘብ ተቀባዩ እኔ ነኝ» አሉኝ።

የሽበቶውን ምክር ሰምቼ እሳቸው አጠገብ እንደ ተቀመጥኩ ሥራውን መለማመዴን ተያያዝኩት። ይገርማችኋል..... የልመና ሥራ ምን አይናፋር ቢሆኑ ቶሎ ይለመዳል። አዲስ ጀማሪ ከሆኑ ነባሮቹን አርአያ እያደረጉ መሄድ ነው። የሰማነውን ግጥም ለማጥናት ብዙ ጊዜ አይፈጅብንም። የሙያው ጠባይ ራሱ

እንድተጋበት ይጎተጉተናል። ስለ ግጥሞቻችን በሚቀጥለው በሠፊው አወጋችኋለሁ። ከዚህስ ይልቅ በጣም የሚገርመው ሰውነታችን እንዴት መለመን ስንጀመር እንደ ሚለወጥ ልነግራችሁ አልችልም። የማንም ለማኝ ሴት የሚያማልል ትላልቅ ዓይን ሥራውን ሲለማመድ ከመሬት ተነስቶ ትናንሽ መሆና ሞጭሞጭ ማለት ይጀምራል። ለወትሮ የሚንቀዠቀዠው ምራቅ ከንፈርና ከምላስ ጋር ጠበኛ ይሆናል። ለዘመድ አዝማድ በግድ ይመነጭ የነበረው እንባ በልመና ሥራ ላይ ካልወረድኩ እያለ ደህነኛውን የእግዚአብሔር ዓይን ካላስጨነቅኩ ማለቱ አይቀርም። ጉልበት በራሱ ሥልጣን በረክረክ ይላል። የለማኝ መዳፎች ከሣንቲም ጋር ትውውቃቸው እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ የሚንቃጭል ማንኛውም ዓይነት ድምፅ የትም ሆነ መቼም ዘወር ያስብላቸዋል። እኛ በበኩላችን ይሄን ይሄንን «ንቃት» እንለዋለን። የሴተኛ አዳሪ መንጋዎች በር ላይ ቆመው ጨለማ የሚጋፉ በጭፈራ ነፍሳቸውን በሃያ አራት ሰዓት አንዴ የሚያቁ፣ ቦሌንና ሌላ ሌላውን በሌሊት እርቃናቸውን የሚዞሩ..... ዝሙት አዳሪዎች «ንቃት» አለን ካሉ እኛ እንዴት አይኖረንም? በነሱ በኩል «ፍንዳታዎች» ቢኖሩም እኛም የራሳችን ስላለን በማኅበራዊ ሕይወት አንተናነሰም!

በዕለቱ የሥራ ክፍፍል ስለምናደርግ በየተሰማራንበት ያየነውን በግልጽና በቅንነት ስለምንነጋገር ወደ ፈለግነው ቦታ በጧት አዝግመን እንደርሳለን። መቼም ደስ ያለው ሰው ሌላውን ቢያስደስት ደስ ይለዋል። በፌስታላችን የማናውቀው የምግብ ዓይነት የለም። የሠርጉ ወይም የግብዣው ቢፌ ባይትረፈረፍም ተመጣጥኖ ወደ ፌስታላችን ይገባል። ዶሮ ወጥ፣ ቀይና አልጫ፣ ምንቸት አብሹ፣ ጥብሱ፣ ክትፎው......ወጉን በሥነ ሥርዓት ባይጠብቅም ከተነካካ እንጀራና ዳቦ ቆጮ ጋር በተራችን ይሰጠናል። ብዙ ጊዜ የምንይዘው ፌስታል ትልቅ ነው። ታዲያ ያንን አሳድረነው በማግስቱ አንዱ አጥር ጥግ ጠጋ ብለን ስንከፍተው በተለይ የአልጫው ፍትፍቱ ቅባቱ ጨረቃ መስሎ ሲታይ፣ ደስ ከሚል የሚያውድ ሽታው ጋር መንገደኛውን ወደኛ ዞር ብሎ በጉጉት ምራቁን እየዋጠ እንዲያልፍ ያደርገዋል።

ቀኑን ሙሉ ለምኜ በኪሶቼ ያጨቅኳቸውን ዝርዝር ሣንቲሞች ወደ ብር የሚለውጥልን አርበኞች መንገድ ሱቅ ያለው ዘበርጋ የሚባል ቀልደኛ ሰው አለ።

«እናንተ እኮ ባላንስ ምግብ ነው የምትበሉት» ይለኛል ፌስታሌን ትክ ብሎ እያየ።

«ምንድ ነው ባላንስ?» እጠይቀዋለሁ።

«እሱንም አታውቅም ለማኝ ሆነህ.....» ዘበርጋ ምን እንደሚያወራ ብዙ ጊዜ አይገባኝም። አማርኛው ወልጋዳ ነው። የሪሱ የተለየ አስቂኝ አነጋገር አለው።

ነገሩ ግራ እንዳጋባኝ ሲያውቅ «የተመጣጠነ ምግብ ማለት ነዋ! ምነው ትምህርት በሬዲዮን አታዳምጥም?» ይላል። ዘበርጋ ምንም ትምህርት ሳይኖረው በኛ በኛ ላይ የበላይ ለመሆን ይሞክራል። እኛ አንበሸቅለትም እንጂ ሊያሾፍብን የማያደርገው ጥረት የለም። እኔ በተለይ ሳላስበው መንገድ እሰጠዋለሁ።

«ሥራ እንዴት ነው?» እለዋለሁ ሳይቸግረኝ።

«ቀጥ ብሏል....... ምን ሥራ አለ........ ንግድ ዱሮ ቀረ......» ይላል

«እግዚአብሔር ያውቃል....... ይኸው እኛስ የሰው እጅ እያየን እንኖር የለም?» እለዋለሁ።

«ኸረ - ኸረ - ኸረ...... የናንተ ሥራ እኮ ከኛ ባሥር እጥፍ ይሻላል.....»

«እንዴት?»

«ምን እንዴት ያስብልሃል?...... ናሙናውን ከፈለግክ ይኼው በቀን የምትመነዝረው አታይም?»

«ተገኘም አልተገኘም...... ያው ከዚህ መከረኛ ሆዳችን አያልፍም።

«ተባለ እንዴ!...... መከረኛ ሆድ!...... እኛ ዘይት የሌለው ዶኬ እየበላን ሰርተን ባለቤቱ እናስረክባለን። እናንተ የድግስ ኬክ እንኳን አይቀራችሁም። ደሞ አሁን አንተ የምታገኘው ወር ሲደርስ ስድስት መቶ ብር አይመጣም አልክ?»

ታዲያ አልናገረውም እንጂ...... አንዳንዴ ሳስበው በኛም ሕይወት ይቀናብን ይሆናል እንዴ? ለምሳሌ ሦስት ሆነን ሰባራ ባቡር አካባቢ አንድ ትንሽ ማድ በኢት ስልሳ ብር ተከራይተን ነው የምንኖረው። ሰሌኖችንና ተደራርቦ የተሰፋውን ድሪቶአችን ለኛ ሁሉን ነገር ማለት ነው። ከጓደኞቼ አንደኛው አይነሥውር ሲሆን ሌላው አንድ እግሩ የተቆረጠ ነው። ይህነኛው እኔ ስለሆንኩ ሁለቱንም እየጎተትኩ ተያይዘን እቤታችን እንገባለን።

የሠፈሩ ዱርዬዎች ብዙ ጊዜ ገንዘብ ሊሰርቁን ሞክረው የተሳካላቸው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። እንዳልኳችሁ በዚህ ኑሮአችንም ይቀናብናል። የአከራያችን ገረድ አልፎ አልፎ ቡና ታፈላልናለች። ቤታችንንም አቧራ በአቧራ አርጋ ትጠርግልናለች። ታዲያ የሚገርመኝ «ከኛ ኑሮስ የናንተ ልመና ይሻላል» ትለናለች። አንድ ዓይነ ሥውር ጎረቤታችን ዕድሜያቸው ሰባ ሳያልፍ አይቀርም። «ጧሪ ቀባሪም የለኝ...... እንደናንተ ልመና ለምጄ ቢሆን ኖሮ......» ይሉና። ለካ ለማኝም አንዳንዴ እንደ ሰው ይታያል?

በውነቱ ይሄንን ስል ራሳችንን ዝቅ አድርገን እናያለን ማለቴ አይደለም። እንደ ማንም ሰው እንቃለዳለን፣ እንተጋገዛለን፣ ቆንጆ መልክና ገላ እናውቃለን፣ እናፈቅራለን፣ እንጠላለን፣ እንቀናለን፣

«የሴቶች ቁንጅና በምን ታውቃለህ?» ይለኛል ቃኛቸው የተባለው ጓደኛዬ። የዓይኑን ብርሃን ያጣ ነው። የምትመራው የዓሥራ አንድ ዓመት ቆንጆ ልጅ አለችው።

«ያው እንግዲህ እንደምታውቀው......» ብዬ ልነግረው ሳቅማማ.....

«እሺ...... እኛ ሰለማናይ አናውቃቸውም?......»

«እንደሱ አልወጣኝም........»

«አዎ እውነትክን ነው........ አባቴ ቃኛቸው አለኝ እንጂ ውበት በዓይኔ የምቃኝበት የዓይን ብርሃን የለንም። የልጄን ቁንጅና እንኳን ሰው ይነግረኛል እንጂ አላያትም.....» ይላል ሆድ እየባሰው።

እኔ ግን እንደምንም ሞራል ልሆነው እሞክራለሁ።

«አይ....... እንደዚህ አታስብ..... ከማን ታንሳለህ አንተ?» ስለው

«እሱማ ምን እንሳለሁ?...... አየህ...... ለማኞች ስንባል እናንተ በዓይን

እናውቃለን የምትሉትን የመልክ ውበት እኛ በጃችን በመዳበስ እናንተ ይበልጥ እናውቃለን» የሚል መልስ ይሰጠኛል።

«እሱን እንኳን ተወው..... እንዴት መልክ በጅ ዳሰሳ ይለያል? አሁን እናንተ ቆንጆ ከንፈርና ጥርስ፣ በተለይም ቆንጆ ዓይን ታውቃላችሁ?» እለዋለሁ። አባባሌ የየዋህነት መሆኑን እሱም ያውቀዋል። እናም አፍ የሚያስይዝ ድንቅ አስተአያየቱን ያስደምጠኛል። መልሱ እኔኑ መልሶ ያሳፍረኛል።

«ስማ...... የናንተ ዓይን ጥሩ ቅርስ አይደለም። ትልቅ ቂት ካየ አብሮ ይነጉዳል። አንድ የቆመ ጡት ዓይናችሁን ያሰክረዋል። የኛ እጅ ግን ከዓይን ይበልጣል። የሴቶችን ቅርጽ እንደ ሰዓሊ በመነካካት እናውቃለን። እንዲያውም የቅርጽ ውድድር ቢኖር ዳኞች እንሆን ነበር።» ደላል ቃኛቸው።

የፍቅሩን አነሣሁላችሁ እንጂ በመሀላችን መቀያየምም ጠብም አንዳንዴ ይከሰታል። በፍቅረኛ መቀናናትም አለ። ልመና ላይ ግን እንደ ሊስትሮዎች ግድየለም መባባል አናውቅም። በተለይ ታክሲ ላይ እንረባረባለን። ምን ጥሩ ጓደኞች ብንሆን የምንከባበረው ከልመና መልስ ወይ ምሳ ስንበላ ወይ በመኝታችን ሰዓት ነው። በቤተ ክርስቲያን ስንውል ጥሩ ጠባይ እናሳያለን። ባዕድ ሲመጣብን እኛን አለመስል ካለ አድመን አበሳጭተን እንዲገለል እናደርጋለን እንጂ በእንዲህ ዓይነቱ ቦታ ያደግንበት ይሉኝታችን ጣልቃ አይገባም።

አንድ ቀን የሆነውን ልንገራችሁ። አንዲት ለማኝ ልጅዋን እንዳዘለች መጥታ አለምዘውድ አጠገብ ቁች አለች። አለምዘውድ የአካል ጉዳተኛ ነው። ልጅ ሆኖ ቦምብ ሲቀጠቅጥ ሁለት እጆቹን አጥቷል። ታዲያ ከሁላችንም ነጭናጫና ነገረኛ ነው። ጥሩ ጠባይ ካላሳዩት በእግሩም ተራግጦ ልደበድብ ይላል። እድናልኳችሁ ግን ለጥሩ ሰው ምንጊዜም ልቡን ክፍት የሚያደርግ ርኅሩህ ሰው ነው። ሴትዮዋ ገና መጥታ ጎኑ እንደተቀመጠች፡-

«ማን ትበያለሽ?...... ከየት አካባቢ ነው የመጣሽው» ሲል ጠየቃት

«ማንስ ብባል ባልባል። ከየት ልምጣ አልምጣ....... እንዳተው ለማኝ ነኛ! አለችው በድፍረት።

«ምን አልኩሽና እንዲህ ትመልሺልኛለሽ» አላት እሱም። የስድብ ዓይነት ይለዋወጡ ጀመር። ባንገላግላቸው በጣም ይካረሩ ነበር።

ሦስት ቀናት ብናያት ብናያት ሴትዮዋ ምንም ለውጥ አላመጣችም። በኋላ እንደውም አሥራት የተባለው አካል ጉዳተኛ ጓደኛችን «ታሪኳን ሰምተናል፣ ቡዳ ናት» ብሎ አስወራባትና ዕድራችን ይሄንኑ ነግሯት ሄደች። ከዚያ ወዲህ አይተናትም አናውቅም። ስትሄድ የተናገረችው ነገር አጥንት የሚሰብር ነው። «ቡዳ አላችሁኝ? ቡዳ አላችሁኝ? ምነው እባካችሁ? ብበላ ብበላ ሰው አጥቼ እናንተን እበላለሁ? ቅዱስ ጊዮርጊስ ይፋረደኝ......» ብላ የተራገመችው እርግማን ምንጊዜም አይረሳኝም።

እስቲ አሁን ደግሞ በቃላችን ፈጥረን ከምንለምንባቸው ጣዕም ያላቸው ግጥሞች ምርጦች ምርጦቹን ላቅርብላችሁ። ልለያችሁ። ለጊዜው ሦስቱን ልንገራችሁ። ምሥጢር ባወጣም ዕድራችን ይቅር እንደሚለኝ ተሥፋ አደርጋለሁ። ድመት ዓይኔን ያጠፋችው። በአንድ ዓይኔ ግን እንደማንም እያለሁ። ያነጣጠርኩት ጥይት ዓላማውን አይስትም ነበር። ማንም ሰው ሲጠራኝ ዘወር እላለሁ። ቅጽል ስሜ ተዋህዶኛል። አልፎ ተፍሮ ስሜን በጣም ከመልመዴ የተነሣ አስደንጋጭ ነገር ድንገት ከሰማሁ «ቶኪቻው ሸዋ» ማለት ይቀናኛል።

የዘበኝነት ሥራ የጀመርኩት ዶክተር ይሥሐቅ በሚባል ሀኪም መኖሪያ ቤት ነው። ጥያቄው የፖሊስ ምርመራ ምስጋን ይንሣው።

«ትዳር አለዎት? ልጆችስ?»

«አዎ.... አራት ልጆች....»

«በፊት የት ይሠሩ ነበር?»

«ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት»

«ምን ክፍል?»

«ኬሚካል ክፍል?»

«እዛ ሲሰሩ ነው አይንዎን......» ገና ከማለቱ «ኸረ ድመት ነች ያጠፋችኝ» አልኩና አቋረጥኩት «ታዲያ እንዴት ነው የማየት ችሎታዎ?»

«እያለሁ እንደማንም። አያስቡ።»

«ማለቴ በቂ ኃይል አለው ወይ ደህነኛው?»

«አዎ፣ በቂ ኃይል አለው። መቸም ሳይ ኖሬያለሁ...... ይኸው አሁንም እያየሁዎት ነው እርስዎን.....»

«በጨለማስ እንዴት ነው?» አለኝ

«በጨለማማ በጣም ያያል» አልኩ

«እንዴት?»

«ጨለማውን ለመቋቋም ጉልበት ይጨምራል»

ሰማንያ ብር ደመወዝ ቀለብ ከቤት በሚል ተስማማንና በማግሥቱ ተቀጠርኩ። ሰውየውን ጥሩ ሆኖ አገኘሁት። ሚስቱ ግን መጥፎ ሰው ናት። በሆነ ባልሆነው ትቆጣለች፣ ትሳደባለች። የመኪናው በር ቶሎ ካልተከፈተላት እሪ ነው። ሽሚዙ ትንሽ ቆሸሸ ካለ መራገም ነው። እናትየው ይብሳሉ። አንድ ቀን የአንገቱን ሀብል ሰርቀሃልና አምጣ ብለው ወጥረው ያዙኝ።

«ኸረ እባክዎን....... ወርቅ የሚባል ነገር ባይኔም አላየሁ» ቀሰረው።

«ኸረ ይቺኑ የቀረችውን ይድፈንብኝ አላየሁም» በኔ ቤት መማሌ ነበር።

«የት ይቀራል መደፈኗ! ያኛውንም ያጣኸው በሌብነት ነው» አልለቅ አሉኝ። በኋላ ዶክተር ይሥሐቅ ደረሰና ገላገለኝ።

«ቀስ ብለን እናጣራለን..... አሁን አይናደዱ..... ይተውአቸው» አሏቸው።

እውነትም በፖሊስ ምርመራ ስንመላለስ ከርመን ገረድየዋ መስረቋን አመነች። አሮጊቷ ይቅርታ እንኳን አልጠየቁኝም። አመት እንደሰራሁ ለቅቄ ወጣሁ።

ከዚያ አንድ እህል ነጋዴ ቤት ተቀጠርኩ። እሱ የሚሰራው አማኑኤል ሠፈር እህል በረንዳ ነው። በሰፊው ግቢው መለስተኛ መጋዘንም አለው። እህል በጆንያ ታጭቆበታል። ቤቱ ትልቅ ነው። ቤቱን ብቻ ሳይሆን መጋዘኑንም እንድጠብቅ ነው ውላችን። ምን የሚያህል ዱላዬን ይዤ ፍጥጥ እንዳልኩ ነበር የማድረው። ሲነጋጋልኝ እስከ ሶስት ሰዓት እተኛና ወደ ቤቴ እሄዳለሁ። ማታ የተለመደው ሥራ ይቀጥላል። የአቶ ድንቁ ባለቤት ደግ ናት። በርከት አድርጋ እራት ትሰጠኛለች።

ከእኛ የሚቀጥለው ግቢ የሃጂ ነስረዲን መኖሪያ ነው። የታወቁ ከበርቴ ናቸው። ሦስት አራት ፋብሪካ አላቸው። ግቢ ሲገቡ በሁለት መኪኖች ታጅበው ነው። አርብ አርብ ትልቅ ግብዣ ይደግሳሉ። ድሆች በራፋቸው ይሰበሰቡና መፀውቱበታል። ዓርብ (በነሱ አጠራር ጁምአ) ምሳ በተባለ በኋላ የሁለት መቶ ብር ጫት ይቃማል። ዘበኛቸው ሙስሊም ነው። የሚደረገው ሁሉ ያጫውተኛል። ከሐጂ ነስረዲን ቤት የመንዙማ ዜማ ሁሌም ይሠማል። ዘበኛው ከማል ራሱ ጥሩ አንጎራጓሪ ነው። ጫት እንደ ልብ ይሰጠዋል። ቡናውን

ሻዩን ብርድ ልብሱን ተሸፋፍኖ እየላፈ ሞቅታ ወይም ምርቃት ላይ ሲደርስ እሱም በሚያምር ድምፁ ያንቆረቁረዋል።

«እባክህ ጌትዬ ኧረ ዕድሌን ባርከው፣

ተገጥቧል ጀርባዬ ዘወትር የማከው።

ኃላፊው አንተ ነህ ለሠራኸው ዕቃ

ችግርም ልክ አለው ትዕግሥታችን ይብቃ

እኛም ልንሠጥ እንጂ መቼ ልንተኛበት

ማጣት በገንዘብ ላይ በሩን ባይዘጋበት።» የማከል ግጥሞች መሬት ጠብ አይሉም።

የአቶ ድንቁ ቤት ሥራ ተሥማምቶኝ ነበር። ዳሩ ምን ያደርጋል። አንድ ሌሊት ተዘናግቼ እንቅልፍ ጣለኝና ሌቦች በአጥር ዘለው ገብተው የመጋዘኑን በር ሰብረው ብዙ ገንዘብ ዘርፈው ሄዱ። እኔም ለምርመራው ፖሊስ ጣቢያ ሁለት ወር ታስሬ ከረምኩ። ምናልባት እንዴት እንደዚህ ሊሆን ቻለ ብላችሁ ልትገረሙ ትችሉ ይሆናል። እንዴት የመጋዘኑ እህል አልተወሰደም ትሉም ይሆናል። ነገሩ እንዲህ ነው። የነጋዴ ነገር ሆነና ለካ አቶ ድንቁ በአሮጌ ቁም ሣጥን በፌሥታል አስሮ ብር አቀምጦ ኖሯል። እንደሰማሁት ሃምሳ ሺ ብር ነበር አሉ። እዚያ ያስቀመጠው ደግሞ አይጠርጥርም ብሎ አስቦ ነበር። እኔ ከደሙ ንፁሕ ስለነበርኩ በነፃ ተለቀቅኩ። በኋላ ቆይቼ እንደ ሰማሁት ውስጥ ዓዋቂ የሴትዮዋ ዘመድ ነበር አሉ ሌቦቹን የመራቸው። ያንን ካወቅኩ በኋላ ወሬውን ጠይቆም አላውቅም። ሥራ መፈለጊያ የአንድ ወር ደሞዝ እንኳ ሳይሰጠኝ እንደወጣሁ ቀረሁ።

ሁለት ወር ፈትቼ ቆየሁ። እታፈራሁ እንጀራ እየሸጠች እኔም ልጆቹንም ቻለችን። ወይኔ ቶክቻው እያልኩ በትዕግሥት የዕድሌን አቅጣጫ ስጠባበቅ መርካቶ የአንድ ቡና ቤት ዘበኛ ሆኜ ተቀጠርኩ። ለጀመሪያ ጊዜ ዩኒፎርም ለበስኩ። ሥራዬ በር መክፈትና መዝጋት ነው። ከአንድ ጓደኛዬ ጋር እየተጋገዝን እንሰራለን። ሥራው ግን አድካሚ ነው። እስከ ሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ጠጪ አያቋርጥም። ረብሻ በየጊዜው ይነሣል። እንደ ትንሽ ልጅ መላከም። ምግብን ጨምሮ ደሞዙ ስልሳ ብር ነው። ቢሆንም ለጉርሻ እያሉ ደንበኞች ሰለሚሰጡኝ ከበፊቱ በጣም የተሻለ ገቢ አለኝ። አሁን በቅርቡ አንድ ሀብታም ነጋዴ ተዋውቄያለሁ። ማርቸዲሳቸውን ስለምጠብቅ ብቻ በመጡ ቁጥር አስር አስር ብር ይሠጡኛል።

# አንድ ቀን እንደ ሰዓሊ

የሰዓሊነት ተሰጥዎ ያደረብኝ ገና የስምንት ዓመት ልጅ ሳለሁ ነበር። አባቴ ቄስ ነበሩ። ቅድስት ማሪያም ኢየሱስ ክርስቶስን አቅፋ የሳሉትን ስዕል ደጋግሜ እመለከት እንደ ነበረ ትዝ ይለኛል። አንድ ቀን እንደ ቀልድ እርሳስ ቀረጽኩና የእርሳቸውን ሥዕል በመጣ አስመስዬ ሳልኩና አሳየኋቸው። በርታ ቀጥልበት አሉኝ። እናቴ ነበእር የምትቃወመው። «እርስዎ ሞነጫጨ ምን ተጠቀሙ......» ትላቸዋለች። «ይሄን ስዕልህን ተውና ጥናትህን አጥና። እሱ ነው የሚያዋጣህ» እያለ የሚገርፈኝ አስተማሪም እንደ ነበር አስታውሳለሁ። እኔ ግን

ምንም ተስፋ ሳልቆርጥ እየተደበቅኩ መሳሌን ቀጠልኩበት። ሥነ - ጥበብ ትምህርት ቤትም ገብቼ ተመረቅኩና ቲያትር ቤቶች ስድስት ዓመት ሠራሁ። አሁን በግሌ እሠራለሁ።

የስዕል ጥበብ ልዩ ፍቅር ያሳድራል። እንዴ ከተቆራኙት ለመላቀቅ ያስቸግራል። በየቀኑ አዳዲስ ሐሳብ ይመጣልኛል። ታዲያ የመታልኝን ሁሉ ለመሥራት ጊዜ ያጥረኛል። ከእውነታው ጋር የሚሄዱ ስዕሎችን መሳል እወዳለሁ። በተለይ ለስዕል የሚመቹ ሰዎች ሲያጋጥሙኝ የሚሰማኝን ደስታ ልነግራችሁ አልችልም።

አንዳንዶቹን ብገልጽላችሁ ደስ ይለኛል። አንድ ጓደኛ አለኝ። ዕድሜው ወደ ሃምሳው ይጠጋል። ራሰ በራ ነው። ፀጉሩ ሽበት ጣል ጣል ብሎበታል። በቀይ ፊቱ ላይ ከላይ እስከ ታች ችምችም ብሎ የተንዠረገገው ፂሙ ሙሉ በሙሉ ሽበት ነው። ሰልከክ ካለው አንጫው ግራና ቀኝ ጢቅ ብሎ የሚፈጥርለት ገጽታ በእጅጉ ዓይን ይስባል። ያለ ምንም ማጋነን ግርማ ሞገስ ሰጥቶታል። አነስ ያሉት ዓይኖቹ ጥራት አላቸው። ትናንሽ ጥርሶቹ ሳቅ በሚልበት ጊዜ ወደ ሃምሳው የተጠጋውን ዕድሜውን ዝቅ ያደርገዋል። በሐሳቤ ደጋግሜ እያስተዋልኩ ሳልኩት። ስዕሉን «ጺሞ» ብዬ ሰይሜው ስቱዲዮ ሰቅዬዋለሁ።

አንድ እግረ ቆራጣ ሰውዬ ሠፌ ኬሻ ባርኔጣ እንዳጠለቀ አስፋልት ዳር ሱቅ ተደግፎ ነጠላ ይቋጫል። አጠገቡ ውሻ ተኝቷል። ነጠላውን ሲቋጭ አስተያየቱን ልብ ካላችሁት ወዲያ ወዲህ ውር ውር የሚሉትን መንገደኞች ያማትራል። ወደ ግራም ወደ ቀኝም እንዲመለከት ለማድረግ ሁለት ወራት ፈጅቶብታል። ዓይኖቹን በሁለት አቅጣጫዎች እንዲመለከት ለማድረግ ሁለት ወራት ፈጅቶብታል።

በመሠረቱ ነጠላ የሚቋጭ ከቄራ መኪና ሥጋ የሚሸከም፣ ሸንኮራ አገዳ ትከሻው ላይ የያዘ፣ እጆቹን ራሱ ላይ አድርጎ መሬት መሬት የሚያይ ሊስትሮ..... እነዚህን የመሳሰሉ ሰዎች ዓይኔን ለትኩረት ይስቡታል። ልብስ የምታሰጣ ልጅ እግር ሴት ወይም ኮረዳ አይቼ አልጠግብም። ማጋነኔ አይምሰላችሁ። ልብሱን ለማስጣት ወደ ሽቦው ስትንጠራራ የለበሰችው ሹራብ ወደ ላይ ሲሳብ ሸንጧ ምን ዓይነት የሐረግ ቅርጽ እንደሚፈጥርና ባቷ እንዴት ገለጥ ወጣ እንደሚል አስቡ።

በርግጥ ለሰዓሊ ደስ ይሚሉ ሰዎች አሉ። ጌሾ ወይም ብቅል የሚወቅጡ ጡንቻማ ሰዎች ለብሩሽ ይመቻሉ። ሙቀጫውን በሁለት እጆቹ እንቅ አድርጎ ይዞ ዓይኖቹን ጨፈን ያደረገ ወጣትም በጠዋት ፀሐይ አይታ «ለጌሾው ወቀጣ፣ ምንም ሰው አልመጣም» ትኩሱን ጉበት ሥጋው እንደ ተበለተ እዛው ቁጭ ብለው የሚበሉ የቅርጫ ማኅበርተኞች መሳል እየፈለግኩ እስካሁን አልተሳካልኝም።

ለምን እንደሆነ አላውቅም። ምናልባትም እኔ አድን ስል ሁለት ስል ልጆች ተወልደው በእህል ውሃ ጋብቻ ትዳር ስለመሠረትኩ ይሆናል። ወይም «ሙሽራዬ» የሚለው ዜማ እያነሆለለኝ። ምክንያቱ በርግጥ አላውቅም። ሙሽሮች መሳል እወዳለሁ። እንዲያው ገና የጥሪው ወረቀት ሲደርሰኝ «ሠርግ» ስለሚባለው ታላቅ የሕይወት ምዕራፍ ማሰብ እጀምራለሁ። ሙሽራና ሙሽሪት ላይ የሚታየውን ደስታ፣ የሚዜዎቹን ፀጉር አሠራርና አለባበስ በብሩሽ ለመቅረጽ እቸኩላለሁ። የአንዳንዶቹ ሠርገኞች ፊት፣ የቅጽበቱ ዓይናፋርነትና ፍንክንክታ ከወትሮው የተለየ ስለሚሆን ለስዕል ያመቻል። አለባበሳቸው ብቻ ለኪነ ጥበብ ራሱን የቻለ ይዘት ኧልው።

የሥዕል ጥበበ ውበት ነው። ፀፅትን ከሳልከው ውበት ያፈልቃል። ናፍቆትና ሐሣብ ዓይን ውስጥ የራሱን ፏፏቴ ሲፈጥር ታየዋለህ። ንዴት በሽፋሽፍትና በዓይኖች ቆብ እየተጨማደደ ምናባዊ ፍርሃት ይለቅብሃል። ዕድሜ መስመሮቹን ቆዳ ላይ ሲዘረጋ፣ ብሶት የሕይወት ማድያቱን በተጨማደደ ፊት ላይ ሴልቀልቅ፣ ደስታ በፈገግታ ብርሃን ሲገለጽ፣ ሩቅ በሚያዩ ዓይኖች ተስፋ ሴከሰት..... በስዕል ውስት ውበት ገኖ ይታያል።

«ትመጫለሽ ብዬ ሳይ ማዶ ሳይ ማዶ፣

የልጅነት ዓይኔ ሟሟ እንደ በረዶ»

ውበትን በሥዕል መግለጽ መቻሌ ልዩ ደስታ ይመስለኛል። የዓይን ጥበትና ስፋት፣ በርቀት የሚፈጥረው መስመር፣ የሚያፈልቀው ብርሃን...... ፍቅርን ያስተጋባል። አንዳንዴ ደሞ ለውጥ ሳደርገው የትዝታ እንጉርጉሮውን ያንቆረቁርልኛል። ሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት መምህሬ የነበረው ሰዓሊና ገጣሚ ገብረ ክርስቶስ ሲገባ ያንን ስዕል ያይና አራት አምስት ጊዜ የተለያዩ ዓይኖቹ እየሳለ ምን እንደሚያስመለክቱ ሲገልጽልን እንገረማለን። «ዓይን የራሱ ምትሐት አለው» የሚል አባባል ነበረው።

ሠዓሊ ውበት አድናቂ ነው ተፈጥሮን አይቶ አይጠግብም። አበባው፣ ድንጋዩ፣ ተራራው፣ ሰማዩ ሁሉ የእይታው ማረፊያ ነው። በተለይ የሰውነት ቅርጽ ለብሩሹ ይስማማዋል። እኔ ለምሳሌ ቁርጭምጭሚት ሳይቀር የሚያምርባቸውን ሴቶች ለይቼ አውቃለሁ። ቆንጆ እግር ይማርከኛል። ውብ ተረከዝ ከተስተካከሉ ጣቶች ጋር የሴትን እግር ሲያሳምር ማየት ምንኛ ደስ ይላል መሰላችሁ፣ ብዙዎቻችሁ የምታውቁት ሠዓሊያን ስንባል የጡት ዓይነት በመሣል መለማመዳችንን ብቻ ነው። እኛ ግን የአጥንት ቅርጽ ሁሉ አይቀረንም። የደረት ስፋት የክንድ ርዝማኔ፣ የዳሌ ቅርጽ ሁሉ የሚወስነው በአጥንቶቻችን አፈጣጥ ነው።

አሁን በቅርቡ አንድ ወዳጄ ምርጥ የሚባሉት የቆንጆ ዘሮች የት አገር ይገኛል ሲል ይጠይቀኛል። ላቲን አሜሪካ። ምሥራቅ አውሮፓ፣ ሊባኖስ፣ ሞሮኮ፣ ቱኒዚያ...... ብዬ መለስኩለት። እሱ ግን ኢትዮጵያ ነች ብሎ ተከራከረና አሳመነኝ። እውነትም የዓለምን ቆነጃጅት የውበት ዓይነት የያዘች ኢትዮጵያ ነች። ከጥቁር ጥቁር ከጠይም ጠይም ከቀይ ዳማ የቀይ ዳማ ከቀይ ቀይ...... የዓለም ዝርያ ቢባል በሃገራችን ይታያል። የጃፓን፣ የአረብ የፈረንጅ፣ የፊሊፒንስ፣ የላቲን የቤኒን......መልክ አይታችሁ አታውቁም? ምን ያደርጋል....... ድህነቱ አስቸገን! ሌላው ቀርቶ ለዓለም ቁንጅና ውድድር አንድ ሴት እንኳን ፓናማ ከተማ ለመላክ አቅም ማጣታችን ያሣዝናል።

የውበት ነገር ሲነሣ በሠዓሊነቴ ያለኝን ከፍተኛ ስሜትና ደስታ ሳስበው አይናውጣነቴ ለራሴው ያስገርመኛል። የዛሬ ዓመት ግድም ታክሲ ውስጥ የአንዲት ወጣት እግር በነጠላ ጫማ እንዴት እንደሚያምር አይቼ «እባክህ በጄ አንዴ ልዳሰውና አቤት ስገባ ልሣለው» እስከ ማለት ደርሻለሁ። ሣቋ ቢመጣባትም ፈቀደችልኝ። አንዲት አሮጊት ሴትዮ ብቻ ነበሩ በጄ ነካ ነካ ሳደርገው ያዩኝ። ልጅቷ ላላፈረችው እሳቸው አፈሩላትና «መጥኔ» አሉ። ድሮስ የድሮ ሰዎች የራሳቸው ቁንጅና እንኳን የት ይገባቸዋል?! በበኩሌ ግን ውብ ሴት ሳልስል ያሣለፍኩት - ሣምንት የለም።

ካርቱን መሣል ሌላው ተሰጥምዬ ነው። አንድ ካርቱን የአስር ገጽ ያህል መልዕክት አለው። እያዝናና ያስተምራል። እያስገነዘበ ያስቃል። ይዘቱ ደሞ የትም ይገኛል። አድን ቀን አውቶብስ ውስጥ ሁለት ጓደኞሞች የተናገሩትን ሰምቼ የእኔንም ፈጠራ ጨምሬ እንዴት ካሩትን እንዳደረግኩት ልንገራችሁ!-

1. ዲቪ ደረሰው እኔ? (በመገረም)
2. ቀላል ደረሰው ትላለህ (እየሣቀ)
3. ታንሴሽን ለኛ አትሆነንም (በመተከዝ)
4. አርፈህ ሎተሪን አትቆርጥም? (እያሾፈች)

ውይይት ታክሲ ዘመናዊ ማርቼዲዝ ገጭቶ አጋመኝ። የታክሲውን ሾፌር ድንጋጤ በሃሳቤ አይቼው

እንደሚከተለው ሣልኩት።

1. ታክሲዎች ስትባሉ ትንቀዠቀዣላችሁ (ወገቡን ይዞ በኩራት)
2. ለርሴ ሰላሳ የትራፊክ ቅጣት አለብኝ....... በምኔ ላሰራው ነው (ጭንቅላቱን ይዞ)

ካርቱን ሥዕል በሐሣብም ይፈልቃል። ዘመኑን፣ ወቅቱን ኅብረተሰቡን ተከትሎ በፈጠራ ይቀመጣል። ለምሣሌ የዘመናችንን ፍቅር በሂስ መልኩ ለማየት የሚከተለውን ካርቱን ስያለሁ። የስዕሉን ሁኔታ ለምናባችሁ ትቼዋለሁ። አስቂኝ እንደሚሆን ያለ ጥርጥር ትገምታላችሁ። አጭር ቀሚስ የተጋለጠ ደረት፣ ያፈጠጠ ጡት ሊፕስቲክ፣ የተላጨ ሽፋሽፍት ወዘተ.....

አንድ ሽማግሌ በትር ተደግፈው ሦስቱን ሴቶች «ምን ዓይነት ወንድ ደስ ይላችኋል?» ብለው ይጠይቋቸዋል።

መልሳቸው:-

1. ገንዘብ ያለው
2. ሀብትና መኪና ያለው
3. ሴት የሚወድ

የሴቶች ማንነት ፍላጎትና ጠባይ ከሥዕሉ ትረዳላችሁ። በዚህ ዓይነት ወቅታዊ የሆኑ ሁለት ካርቱኖቼን አቅርቤላችኋለሁ ለዛሬ እሰናበታችኋለሁ።

የኤች. አይ.ቪ./ኤድስ ማስጠንቀቂያ በቴሌቪዥን እየተሰጠ ነው። ሰዎቹ ወንዶች ናቸው።

1. ኮንዶም እኮ ሁልጊዜ መጠቀም
2. ጥሩ ምግብ በገፍ መብላት ዕድሜ ያራዝማል
3. ክትባቱ ተገኝቷል ይባላል
4. ራሳችሁን ባታታልሉ ይሻላችኋል!

ሌላው ደግሞ ይኸውላችሁ። ቦታው ሴቶች ራቁት የሚደንሱበት ነው። «ማጨስ ክልክል ነው» የሚለው ተሠርዞ «ማጨስ ይፈቀዳል» የሚለው ተተክቷል። በሌላው ግድግዳ «Varety is spice of life William Shakespeare» የሚል ተጽፎ ይታያል።

<u>የመጀመሪያው ጥንድ:-</u>

1. በለውጥ ታምኛለሽ እርግጠኛ ነኝ!
2. አይደል?!

<u>ሁለተኛው ጥንድ:-</u>

1. በረድሽ እንዴ......
2. እንደውም..... እጅህ ያሞቀኛል

<u>ሦስተኛው ጥንድ:-</u>

1. የገጠር ልጅ ትመስላለች...... እንዴት እዚህ መጣች (በሃሳቡ)
2. እግዚአብሔር ይይልህ....... ደላላ ነፍስህ አይማርም (በሃሳቧ)

# አንድ ቀን እንደ ቢሮ አለቃ

የመንግሥት ሥራ ከጀመርኩ ሃያ ዓመት ያልፈኛል። ከታች አንሥቶ እስከ ላይ ድረስ የመሥሪያ ቤቱን ውጣ ውረድ ቢሮክራሲውን ሁሉ በሚገባ አውቀዋለሁ። በተለያዩ አለቆች ጭቆና ሹመት ሳላገኝ ለረጅም ጊዜያት ኖሬያለሁ። የሰው ወሬ እንደሚሰማኝ ቢሪክራት ያሚያስጠላ ሰው ይኖራል ብዬ አላምንም። ከአሥር ዓመታት በፊት እንዲህ ያሉ አለቃ ነበሩ «ምን እየሠራ ነው?» የሚል ጥያቄ ጠይቀው አያውቁም። «የሚመካበት ሰው አለው? ገዘብ አለው?.......» ማለት ይወዳሉ። ከመሬት ተነስተው ነገር ያሽታሉ። ከሦስት ዓመት በኋላ ባይቀየሩ ብዙ የውድቀት ጉድጓድ ይምስሉኝ እንደ ነበር እርግጠኛ ነኝ።

ሌላው ከሳቸው በኋላ የመጡት አለቃ ሴት እጅግ በጣም ይወዳሉ። ቀሚስ ያጠለቀች ሁሉ ታፍነከንካቸዋለች። ቆንጆ ማየት እንደ አልኮል ያሰክራቸዋል። ታዲያ ከመሥሪያ ቤታችን ሴት ባልደረቦች ጋር ቅርበት የሚፈጥር ሠራተኛ ይጠመዳል። ለተግሣፅና ቅጣት መንገድ ይፈለግለታል። በዚህ ሁኔታ እኔ በተፈጥሮዬ ጨዋታኛ ስለሆንኩ ሴቶቹ ያቀርቡኛል። አቀራረቢ ሁሉ ወንድማዊ መሆኑን የግቢው ሰዎች ቢያውቁም አለቅችን ግን በነብር ዓይን ያዩኝ ነበር። «ዋልጌ ነው...... ሥራ አይወድም...... አድማ ከማስነሳት አይመለስም........ ወሬኛ ነው......» ያላሉኝ ነገር የለም። በሰበብ አስባቡ ሦስት አራት ጊዜ ከደሞዜ ቀጥተውኛል።

በሦስተኛ ተራ ቁጥ የማነሳቸው ደግሞ ጥሩ ዲስፕሊን ያላችው የቢሮ ዝሙት የሚያወግዙና ሥራ የሚወዱ ናቸው። ታዲያ ምን ያደርጋል፣ በአጠቃላይ ሰው የሚባል ፍጡር አይወዱም። ማንንም ይንቃሉ። ከኔ በላይ ያወቀ ለአሣር ነው ባይ ናቸው። አስተሳሰባቸው ሁሉ የዱሮ ነው። በዱሮ ነገሮችም ሁሌም ይመካሉ። «ዛሬ ምን ሰው አለ....... ዛሬ ምን ዕውቀት አለ...... ሁሉ ነገር ለብ ለብ ነው.....» ይላሉ። ሥራ ላይ ያላቸው ጠንቃቃነት አይጣል ነው እናም የቁንጫ መላላጫ ማውጣት ደስታ ይሰጣቸዋል። ፀሐፊዎች አራት ነጥብ ከረሱ ቢሮው ይታመሳል። «ኧረ ምን ትውልድ ላይ ጣለን ጌታዬ?! ብለው ከተናደዱ መመለሻም የላቸው። ከጠባያቸው ሁሉ እጅግ የሚከፋው ሠራተኞችን በሥነ ልቦናዊ ጅራፍ የመጉዳታቸው ሁኔታ ነው። ተስፋ ማስቆረጥ ያረካቸዋል። በተለይ እኔን «እየው.....ሠርተህ.........የት እንዳለህ ተመልከት አንድ እርምጃ አልተንፏቀቅክ......እገሌ ያለሁበትን ቦታ ተመልከት....... አንተ ተንልተህ እሱ ሎህ ሄዷል......» ይሉኝ ነበር። አዬ የዚችን ዓለም ጥለው ሄዱ።

ከዚያ በኋላ ነው በዓመቱ ሹመት ያገኘሁት። የትልቅ ቢሮ ኃላፊ ከሆንኩ ስድስተኛ ዓመቴን ይዣለሁ። የተሾምኩ ዕለት የነበረውን ግብዣና ደስታ ልነግራችሁ አልችልም። ወዳጅ ዘመዶቹ በነፍስ ወከፍ ጠርሙስ ውስኪ ወይም ደርዘን ቢራ ይዘው መጥተው ሌሊቱን እንደ ቀን ስንንበሻበሽበት አደርን።

አዲሱን ስራ እንደጀመርኩ ሰሞን ድሮ የማውቅቸውና የቅርብ የሚሆኑኝ ሰዎች እንደ አዲሱ ሰው ሳያዩኝ በጣሙን የተገረምኩ መሆኔን አስታውሳለሁ። ለካ ሥልጣን ራሱን የቻለ ቤተ ክርስቲያን  ነው! አናንዱ እንደ ደራሽ ውሃ የሚያስነደነግጥ ክብር ይሠጠኝ ጀመር። የነሱ ግን የተለየ ሆነብኝ። መጋረጃው ይለወጥ......ወንበሩ አርጅቷል.......የመሰብሰቢያው ጠረጴዛ (ኮንፍረንስ ቴብል) ሌላ ቀለም ይቀባ...... የሚሉ ሰዎች ተፈጠሩ። «ታግሥህ ይኸው ተሳካ...... የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣዋል፣ እውነት ትመነምናለች እንጂ አትሞትም........እግዚአብሔር የቅርብ የሩቁን ያያል.......እንዲያውም ይሄ ሲያንስህ ነው......እግዚአብሔር የቅርብ የሩቁን ያያል..... እንዲያውም ይሄ ሲያንስ ነው.......» የሚሉ ሰዎች በዙብኝ።

በእውነቱ የሹመትን ነገር በዚያን ሰሞን ነው የታዘብኩት። ለምሳሌ አንዳንዶቹ በምክር ሰጭነት ሽፋን ቢርዬ ሹክክ ብለው ገብተው የሚናገሩት ንግግር ከማስገረም አልፎ ያስቃል።

«ሹመት ያዳብር ጌታዬ.....» ይለኛል አድኑ፣ ለጥ ብሎ እጅ ይነሣል።

«አመሰግናለሁ......» እላለሁ እኔ

«ሁላችንም እጅግ ደስ ብሎናል.....»

«በተለይ የእኔማ ደስታ...... ታውቀኝ የለ......»

«እንዴታ...... ገና የግቢው አጥር በብሎኬት ሳይታጠር....»

«እሺ....... ታዲያስ...... ይሄ የግብዣው ጋጋታ...... መጠጡ እስካሁን ስሜቱን አለቀቀኝም እባክህ»....... አርዕስት ለመለወጥ ቀዳዳ እፈልጋለሁ።

«ምን ይጠየቃል.....ተብላ ተጠጣ..... ደሞ ላንተ ደስታ ይሄ ይብዛ?» ይላል።

እንዲህ ዓይነቱ አድናቂ ቀጠል አድርጎ ወደ ምክር ይገባና ወደ ሌላው ይሸጋገራል፦

«እንግዲህ ጠንቀቅ ነው!......» ይጀምራል፣ ድምፁን ዝቅ አድርጎ።

«እንዴት ማለት?» እጠይቃለሁ፣ ወረቀቶች እያገላበጥኩ።

«አይ...... ለሥራውማ ማን ብሎህ......» ይልና ወረቀቶቹ ላይ ዓይኖቹን ያንከባልላል።

«እንግዲህ የተቻለኝን እጥራለሁ እጥራለሁ» የግድ የሚለውን መስማት አለብኝ።

«ቤቱ የምታውቀው ነው..... አዲስ ነገር እኮ የለም.....ብቻ እንደው.....»

«ብቻ ምን?»

«ሰዎች አታቅርብ..... የሚያደርጉት አይታወቅም.....»

«እሺ.......»

«በተለይ ያ የክፍል አለቃ መሠሪ ነው.....» ወደ ዋናው ነጥብ ይመጣል።

«እኔ እንኳን የተለየ ነገር አላየሁበትም....» እለዋለሁ።

«የዋህ ስለሆንክ ነው.... አይምሰልህ.... ዋዛ ሰው አይደለህም......ወሬኛ ነው..... ምሥጢር እንዳትነግረው...... ያንተን ቦታ ይፈልገዋል......እገሌን ከሹመት ያስወረደ እሱ አይደለም እንዴ?...... ደሞ ጠንቋይ ቤት ይመላለሳል...... ዋናው ሥራ አስኪያጅም እየያዛቸው ይሄዳል!».....

የተሾምኩ ሰሞን ቢሮዬ የማይገባ ሰው አልነበረም። አንዱ በጧት መጣና «ይቺ መኮስተሪያ አትሆንም» አለና ደህናው አሽትሬ ወስዶ የራሱን አመጣልኝ። የሂሳብ ክፍል ኃላፊዋ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ቴሌቪዥኑን ቆንጆ ጥልፍ ያለበት ጨርቅ አለበሰችው። «መታሰቢያ ትሁንልኝ» አለችኝ። እኔም የግድ ማመስገን ነበረብኝ። ምሳ የሚጋብዙኝ ነበሩ። ሁለት በጣም የምቀርባቸው ጓደኞቼ ድሮ ድራፍት እምንጠጣበት ቦታ ሊገብዙኝ አልፈለጉም። ከኢትዮጵያ ሆቴልና ከግዮን ሆቴል አስመረጡኝ። እኔ ግን ስላልተመቸኝ ልገኝ አልቻልኩም።

እስከዛሬ በጣም የሚያስገርመኝ የልጅነት ጓደኛዬ የመዝገብ ቤቱ ኃላፊ ቢሮ መጥቶ ረጋ ብሎ ያነጋገረኝ ጉዳይ ነው። ገና እንደገባ የተለመደውን «እንኳን ደስ አለህ......» እንደ ሌሎቹ ስንዝሮ ንግግሩን ቀጠለ።

«ይቺ ዓለም የራሷ ብልሃት እንዳላት ታውቃለህ.......» አለኝ ዓይኑን ዓይኔ ላይ ተክሎ

«ምን ዓይነት ብልሃት?» ጠየቅኩት።

«ወቸ ጉድ!...... አሁን እውነት አጣኸውና ነው?»

«በእውነት አልገባኝም»

«እኔ እኮ የምሥጢር ጓደኛህ ነኝ...... አይደለም እንዴ?» እንደ መቆጣት ከጀለው።

«እኮ ንገረኝ..... ወደ ነጥቡ ግባልኝ...... ገና ብዙ ሥራ ይጠብቀኛል....»

«አልፈራህም ማለቴ ነው..... ገባህ?»

«እሺ ገባኝ.....»

«እና ግራ ቀኙን ማየትና ማጤን ያስፈልጋል......»

«እኮ ምኑን?»

«ሰው እንደሚሆነው መሆን ነው.... ማለቴ ነው.....»

«እንዴት» አልኩት «ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል» ወደ ሚለው..... ማምራቱን በአነጋገሩ ብቻ ሳይሆን በአኳኋኑም አውቄበታለሁ። እሱማ የት ይቀራል....... ባይሆን መመጠንም ተገቢ ነው እንጂ...... አልኩት በልቤ።

«ራስን መጥቀም አይከፋም» ፍርጥ አድርጎ ነገረኝ። ከአብሮ አደግህ አትሰደድ ብሎ የለ መጽሐፉ። እኔ ግን መግደርደር ፈለግሁ። ምንም መልስ አልሰጠሁትም። እንዲህ ዓይነቱ ነገር ለሚስትህም ቢሆን አይነገርም። ከአፍ ከወጣ አፋፍ ተብሎ የለ! እውነቴን ነው...... በዚህ ዓለም ላይ በተለይ ባሁኑ ዘመን ማን ይታመናል......። አብሮ አደጌ ቀጠለ፦

«ለምሳሌ ለልጆችህ ጎጆ እንድትቀልስ.......» አለኝ

«እሱማ እንደምንም አለ...... ጨረቃ አቅርበህ.....»

«እስቲ አስብበታለሁ....»

«ያልታጨደው ሣር ራሱ በኮንትራት ቢሸጥ.....»

እንደ መፍራት አልኩ። ምንም መልስ አልሰጠሁትም። እሱ ግን ቀጠለ። ስንት ትርፍ ቆርቆሮ፣ ቀለም፣ አጠና፣ የወላለቀ ጠረጴዛና ወንበር መጋዘን እንዳለ ሁሉ አወራልኝ። ሳስበው ዘገነነኝ። ጎጆ መቀለስ ደሞ አማረኝ። ከራሴ ጋር መታገል አለብኝ።

ያኔ አንድ ሐሳብ ብልጭ አለልኝ። ዕቃውን ሁሉ በመኪና አስጭኜ ሸጥኩና ለዋናው ሥራ አስኪያጅ ሠላሳ ኢንች ከለር ቴሌቪዥን በሥጦታ መልክ ሠጠኋቸው።

«ገና ከመሾምህ ምን አሳሰበኝ የኔ ልጅ.....» አሉኝ።

«አንቴ ዱባይ ይነግዳል..... ሁለት ሲልክልኝ አንዱን ለርስዎ አስቤ ነው..... ዕቃው እዚህ አገር አይገኝም ብዬ ነው እንጂ ትልቅ ሥጦታ ሆኖ እኮ አይደለም፣ ጌታዬ......» አልኳቸው።

«ኧረ መልካም አስበሃል..... እሱን ለኔ አድርገው የእኔና በቅርቡ ጎጆ ለወጣው ልጅጄ እሸልመዋለሁ» አሉኝ።

ተግባባን። መግባባታችንን ቀጠልንበት። ቅዳሜ ዘወትር ምሽቱን ከከተማ ወጣ እያልን እንጠጣለን። ቀስ እያልኩ ወደ ሣር ሽያጭ ገባሁ። ብዙም ባይጠቅመኝ ለዓውደ ዓመት ወጭውን ቻለልኝ። ለራሴም ለአለቃዬም የአምስት መቶ የአምስት መቶ ብር ሙክት ገዛሁበት። ከሁሉም የጠቀመን የመኪኖቹ ጨረታ ነበር። ከዚያ በተገኘው ገንዘብ ከሁሉም የጠቀመን የመኪኖቹ ጨረታ ነበር። ከዚያ በተገኘው ገንዘብ በአርባ ሺ ብር ቆንጆ ዲ ኤክስ ገዝቼ ለሚስቴ ሰጠሁ። የዲ ኤክስ መሪ ገና እንደ ጨበጠች አሮጌ ተደስተው የመንግሥት አራት ቁጥር ፓጃሮ አዘዙልኝ። እሳቸውም በዱሮ ቪላ መኖሪያ ቤታቸው ላይ ለእንግዳ ማረፊያ የሚሆን ሁለት መኝታ ቤትና አንድ ሠፊ ሣሎን ቀጠለብን።

የቢሮ አለቃ መሆን ብዙ ዕድል አለ። ለበታች ሠራተኛ የሚመጣውን የውጭ የሥራ ጉብኝት ለኛ እናደርገዋለን። ጠያቂ የለብንም። አለቃዬ አውሮፓ ብዙ ጊዜ ሄደዋል። እኔ ለንደን ለሥራ አስምት ቀን ሄጃለሁ። አራት እድል አፍሪካ ከተሞች ደርሶኛል። የውጭ ምንዛሪም የሚናቅ አይደለም። ቢያንስ ለሚስቶቻችንና ለልጆቻችን ልብስና ጫማ መግዣ ይሆነናል። ቃሉ ጉቦ ቢሆንም እኔ በበኩሌ የማየው የብዙ ዓመት የጭቆናዬ ማካካሻ አድርጌ ነው። ኦዲተር የለም ወይ የሚል ጥያቄ አንዳንዶቻችሁ ታነሱ ይሆናል። የሞኝ ጥያቄ ነው። በልቶ ማብላት ካለ ምን ችግር አለ።

ገንዘብ ገንዘብን ይወልዳል ይሉ ነበር አያቴ። እሳቸው እንኳን የኖሩት ጋሻ መሬትን በሚወልድበት ዘመን ነው። ግን እውነታቸውን ነው። መጽሐፍ ቅዱስስ «ላለው ይጨምርለታል» ብሎ የለ! ሹመት ፈላጊ ሁሉ ገፀ በረከት ያዥጎደጉድልኛል። ለሥራ የመጡ ጨረታዎች ባዶ እጃቸውን አይጎበኙም። ማተሚያ ቤቶች፣ ስቴሽነሪዎች፣ ነዳጅ አቅራቢዎች፣ የመኪና ዕቃ መለዋወጫዎች....... አብልቶ መብላት በምልክት የሚገባቸው ናቸው። እውነትም ሲሾም ያልበላ!......

ሹመት በገንዘብ ብቻ አይወሰንም ቆንጆና እሸት አይታለፍም የሚለው አባባል እውን የሚሆነው የቢሮ አለቃ ሲኮን ነው። በውበት ዓለም ታሽጎ፣ የተቀመጠው ውድ ጥቅማ ጥቅም ሁሉ ሳይለፉ ሳይደክሙ. ሳይወጡ ሳይወርዱ ራሱ በር አንኳኩቶ ይመጣል ፡

ገና የተሾምኩ ሰሞን ለእንዲህ ዓይነቱ ዓለማዊ ወይም የቁንጅና ጉቦ የተዘጋጁ እንደ ነበሩ ገምቼ ነበር። «መጋረጃ ይለውጥልዎት፣ ቀለሙ እንዲህ ቢሆንልዎት፣ ይሄ ፍሊት ጠረኑ ስለማይለቅ ሌላ ቢሆንልዎት.......» ከሚለው ዓይነት አባባል ብዙ ነገር ጠርጥሬያለሁ። አንድ ቀን አንዲት ቆንጆ ቢሮዬ መጣችና....

«እንኳን ደስ አለዎት ሳልል ቆየሁ» አለችኝ።

«ምንም...... አይደል....... አይዞሽ» አልኳት

«ዕረፍት ላይ ስለ ነበርኩ.....»

«አይ ሲ»

«ድሮ አላውቅዎትም....... በቅርቡ ነው የተቀጠርኩት.....»

በጣም ታምራለች። ቅርጿ በጣም ያማልላል። የለበሰችው ቀይ ሱሪ ገና ስትፈጠር አብሯት የተሠራ ይመስላል። ፀጉርዋን ዘመን አመጣሽ በሆነ ቅባት አዘናፍላዋለች። ስትሥቅ ልብ ስንጥቅ ታደርጋለች። ጠይምነቷ ውበቷን አድምቆታል። በተለይ ልቤ አመታቱን ጨመረ።

«እኔም ያየሁሽ አይመስለኝም.....» አልኳት።

«ብዙ ሠራተኖች የርስዎን መምጣት ሲያደንቁ እሠማለሁ» አለች በሚማርክ አስተያየት በረጅሙ ተንፍሳ።

«አንቺ ደስ አላለሽም ማለት ነው?»

«ኧረ!...... በምንም ተአምር!»

«ስቀልድ ነው....... ቆንጆ ልጅ ቀልድ አትጠላም ብዬ ነው......»

«አይደል.......»

«እውነቴን ነው...... ታምሪያለሽ...... ካላመንሽ መስተዋት እይ......» አልኳት።

«አይደል.....» ከመሬት ተእንሥቶ ፍንክንክ ብላ ሣቀች።

«እሺ...... ልሂድ.....»

«አትጥፊ......»

ከልጅቷ ጋር ተወዳጀን።፡ በዓመቱ ደሞዝ ጨመርኩላት። ቅናት ያስቸግረኛል ብዬ ነው እንጂ የፊልፍ ሥራም እንደ ልብ አዝላት ነበር። የቁንጅናው ጉቦ በሷ ብቻ አላበቃም። ባሠፍረው ወረቀቱ አይበቃምና ትረካዬን አቁሜ ልሠናበታችሁ። በመጨረሻ እንድታውቁ እምፈልገው እውነትና ንጋት መምጣቱ አይቀርምና ይሄንን የጻፍኩላችሁ ማረሚያ ቤት ከታሰርኩባት ክፍል ተከዤ እንደ ተቀመጥኩ መሆኑን ነው።

# አንድ ቀን እንደ ሀብታም

የመጀመሪያ ጥያቄያችሁ «ዱሮ ምን ነበርክ?» እንደሚሆን አልጠራጠርም «ገንዘብ ነበረህ ወይ? ኑሮህ እንዴት ነበር?» ማለታችሁ አይቀርም። ከዚያ ቀጥላችሁ «እንዴት ነው ሀብታም የሆንከው?» ልትሉ ነው። እኔ ግን እነዚህን ብቻ ሳይሆን ስለ ብዙ ነገር እያነሳሁ አጫውታችኋለሁ። ዋናው የምለምናችሁ ግን የምናገረው የግፍ አድርጋችሁ እንዳትወስዱብኝ ነው። ወደ ንቀትም አትውሰዱብኝ። እኔ ሰው ንቄ አላውቅም። ማጣት ብቻ ሳይሆን ገንዘብም የሚያመጣሁን ጣጣ በግልጽ ቋንቋ ሳልደብቅ ወይም ይሉኝታ ሳይዘኝ ከመናገር በስተቀር ምንም ክፉ ዓላማ የለኝም። «በደረስክበት ሰው የምታሳጣ፣ ሌላስ አልልህም ማጣት አንተም እጣ» ብሎ ክፍለየሱስ አበበ ዱሮ የገጠመውን አስታውሳለሁ። «ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ» ከተባለ ቆይቷል። ማጣት ምን ያህል መጥፎ እንደሆነ በነዚህ አነጋገሮች ውስጥ ይስተጋባል ገንዘብ በአግባብ ካልያዙት ወዴት እንደሚመራ ማወቅ አያስቸግርም።

ሙልጭ ያልኩ መናጢ ድሀ ነበርኩ የምልሰው የምቀምሰው አንኳን አልነበረኝም። እናቴ ከሞተች በኋላ አክሥቴን ተጠግቼ ነበር የምኖረው። በኋላ በኮንትሮባድን ንግድ መጠነኛ ገንዘብ አገኘሁ። ያንን አራጣ

እያበደርኩ አገላበጥኩ። ዛሬ..... ይመስገነው በቂ ሀብት አለኝ። አሪፍ መኖሪያ ቤት ቆንጆ መኪና፣ አንድ አውቶብስ አለኝ። ሀብታም ስለ ጥሬ ገንዘብ ስለማያወራ ያለንኝ ካፒታል መጠን አልነግራችሁም።

ኮልፌ ከሚስቴና ከሕፃን ልጄ ጋር እኖራለሁ። የአቶ ዝናቡ ቤት የት ነው ካላችሁ ማንም ያሳያችኋል። ቤቴ በግንብ የታጠረ ነው። ዙሪያዬን ቃኘት ሳደርግ የማያቸው ደሳሳ ቤቶች ያሣዝኑኛል። ሆኖም ሲቸግራቸው እደርስላቸዋለሁ። አንዳንዶቹ «ጋሽ ዝናቡ፣ ከእግዚአብሔር ያገኙታል። የሚቀርቡኝ እርስዎ ነዎት» ይሉኛል። አሁን በቀደም ሁለት ደሀ እህትማማቾች እናታቸው ሞታ ለከፈንም ለሣጥንም ስላጡ የሠፈሬ ልጆች አሮጌ ጨርቅ ብጤ አንጥፈው መንገዳቸውን ሣንቲም ጣላ አደረጉላቸው እያሉ ሲያስተባብሩ እኔ ለምሳ እቤት እየገባሁ ነበር። ቢ. ኤም. ደብልዩ መኪናዬን አቆምኩና ወረድኩ።

እትዬ አስካለ ሮጣ መጣችና «ይኸውልህ ጋሽ ዝናቡ..... የኛ መጨረሻ እንዲህ ነው!» አለችኝ እየጮኸች። የእሷ ነገር እየገረመኝ ነው። በዕድሜ የስንት ታላቄ ናት። ነገር ግን ሁሌም ጋሼ ነው የምትለኝ። ልጅ ሆኜ የስንት ታላቄ ናት። ያኔ ሳጂን ባልዋ አልሞቱም። ደህና ኑሮ ነበራት። ታዲያ እትዬ አስካለ እኛ ድሆች ስለ ነበርን በዓውደ ዓመት በግ አርዳ ትጋብዘናለች። ለፋሲካና ለእንቁጣጣሽ ዶሮ ትገዛልናለች። በኋላ የስዋ ኑሮ ሲያሽቆለቁል እኔ ሀብት አገኘሁ። ዛሬ በደንብ ልረዳት በቅቻለሁ። ልጆችዋን አስተምርላታለሁ። የጠየቀችኝን አደርግላታለሁ።

«ይኸውልህ...... የኛ ነገር እስከዚሁ ነው። ሰው መቅበር ያቃተበት ክፉ ዘመን......» ስትለኝ፣ ውሠጂኝ ብያት ለቅሶው ቤት ሄድኩ። ቤትዋ ትንሽ ክፍል ናት። ከመጋረጃ ጀርባ አስክሬኑ ተቀምጧል። እህትማማቾቹ ሣጥን ላይ ቁጭ ብለው ያለቅሳሉ። ከሦስት ሴቶችና ከአንድ ሽማግሌ በስተቀር ሌላ ማንም የለም። ከእድር ተለምኖ የመጣው አራት አምስት አግዳሚ ባዶውን በራፉ አጠገብ ዝናብ ያካፋበታል። እንባዬ ሊመጣ ምንም አልቀረውም። ከልቤ አዘንኩ። ቤቱ ቀፈፈኝ የምታመም መሠለኝ። አንድ ሺ ብር ወርውሬላቸው ወጣሁ።

ከሠፈሬ ወይም ከዘመዶቼ ውጪ ሲሆን ግን ገንዘቤ ያሳሳኛል። «ደክሜ ነው ያመጣሁት» የሚል ሐሳብ ይመጣብኛል። ለዘመድም ሆነ ጓደኛ ካልባሰ በስተቀር እንጀኔን አልዘረጋም። ያላሳደጉኝ ሁሉ «አሳድጌ አሳድጌ» ቢሉኝምም ሰዎች ከስንፍና እስካላስወገዱ ድረስ አንጀቴ አይላወስም። ገንዘብ ያልሠጠኋቸው ሁሉ፣ በስንፍና ሌባ ሆነ ያገኘኋቸው ዘመድ ተብዬዎች ሁሉ «እንደ ስሙ ገንዘብ ስለዘነበለት ጠልቶኛል» እኔ ለራሴ ካልመሠለኝ ጉዳዬ አይደለም። በሥራው ታማኝና ትጉህ ከሆነ ማንም ባእድ ከዘመድ ይበልጥብኛል። ኖሞኒ ኖ ፈኒ - ነው ዋናው ነገር።

የዱሮ ጓደኞቼን በኑሮ ከበለጥኳቸው ቆይቻለሁ። አንዳንዶቹ አልቀናቸውም። ታደሰ ልብስ ሠፊ ነው። ዱሮም ከእጅ ወደ አፍ ነበር የሚኖረው። አሁን ደሞ ሳልቫጅ መአበት። ኪሮስ አውቶብስ ተራ አይታጣም። ደላላ ነው። ገረመው ውይይት ላይ ተቀጥሮ ሹፌር ሆኗል። ዓለማየሁ ብቻ ነበር ከነሱ ሁሉ ታታሪ። መጀመሪያ መስተዋት ሥራ ውስጥ ገብቶ ተጨማሪ ብርቱካን ቤትም ከፍቶ ነበር። ለነገሩ ደህና ገርቶለት ነበር። ከዛ በኋላ ምን እንደነካው አላውቅም። ሴት አብዝቶ መውደድ አከሰረው ይባላል። ገረመው በንግዱ ወረድ ሲል አይዞህ ብሎ ሞራል የጋረደለት ዓለማዬሁ ራሱ ተጋረደበት ይሉኛል። ዕድል የሚባለው ነገር ላካ ይሄንን ይመስላል ማለት ነው? ኧረ እንኳን የመርካቶው ቅዱስ ራጉዔል እነሱን አላረገኝ! የዱሮ ነገር ዱሮ አልፏል። ሀብት ይኑረኝ አይኑረኝ...... ለምን ላላፈ ታሪክ እጨነቃለሁ?!

የወትሮ ሥራዬን ጠዋት አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ እጀምራለሁ። የሥራ ጓደኞቼን ተሯሩቼ እጨርሳለሁ። ምሳ ስበላ እንኳን ሰዓቴን አላውቀውም። ወይ ስምንት ወይ ዘጠኝ ሰዓት ሊሆን ይችላል። ብር ካለ ምን

ለመብላት የሚያስብ መሠላችሁ? ምሳው ቁርሱ እራቱ ራሱ ራሱን እየገፋ...... የኢጋፋሪው ዓይነት ፕሮግራም እያደረገልኝ ቁጭ ባልኩበት እፊቴ ይመጣልኛል። ስለ ጤንነት ግን አደራችሁን እንድታነሡብኝ።

የቀኑን ሥራዬን ከፈጸጸምኩ በኋላ...... መሽት ሲል..... ተራ ሰዎች የማያውቁት ቤት እገባና ከነጋዴ ጓደኖቼ ጋር ውስኪ እጠጣለሁ። እዚያ የምንገናኘው ጨዋ ቤት፣ ሴት አስተናጋጅ የሌለበት የጓደኞችን ግሮሰሪ መሆኑን አውቀን ነው። መኪኖቻችንን እንኳ የሚያውቅ ሰው እምብዛም የለም። «ሬ - ላ - ክ - ስ እናመጣለን። አንዱ ተነሥቶ በከተማው የደረሰውን ጉድ ያወራል። አንዱ ስለ ከአሜሪካ የጸፈለትን ይጨምራል። ውሸትክን ነው አይደለም እየተባባልን ስንነጫነጭና እበልጥሃለሁ - አትበልጠኝም - በሚል ዕውቀታችን ስንከራከር ደስ ይለናል።

በእንዲህ ዓይነቱ የሳውቅዮሽ ክርክር ውስኪ እንዴት እየተጠጣ የሚሄድ መሠላችሁ? ጫት የሚቅሙ ሰዎች ከኛ በላይ አመረቅኑም። በቃ ጠርሙስ ይወርዳል - ይጠጣል። ሌላ ይወርዳል - ይጠጣል - ሌላ - ሌላ - እያለ ሲቀጥል ጨዋታው ይደራል። መሣቅ ነው.....መፍነክነክ። እውነተኛ ሣቃችንና የራስ ትችታችን የተደበቅንበት የአዱኛ ዋሻ በርቅሶ የሚወጣው በዚያን ሰዓት ይመስለኛል።

ቆዩኝ አንድ ጊዜ - በቀልድ የሚያፍነከንከንን ተረባችንን ነካ ነካ አድርጌ ላውራላችሁ። ማታ ማታ ደምሴ ግሮሰሪ ያለ ቀልድ ቢጻፍ መጽሐፍ ይወጣዋል።

«አይ ከሊፋ - ፑሽ አፕ እኮ አከሣህ። ስሊም ለመሆን ፈልገህ ነው?» ይላል ተሻለ። የሁለት ሆቴል ቤትና የአምስት ሱፐር ማርኬት ባለቤት ነው።

ከሁላችንም በፕሮግራም የሚኖረው ከሊፋ «ጡንቻዬንስ ለምን ረሳሀው?» ይለዋል፣ ኮራ ብሎ። «አንተስ ተደብቀህ ስፐሪንግ ትስብ የለ» ይተርበዋል እሱም በተራው።

የቅርብ ጊዜ ባለ ፀጋ የሆነው ግደይ ቀበል አድርጎ፣ «ቀንቶ ነው፣ ለምድን ነው ዝም የማትለው? ስፕሪንግ ቢስብ ዓይኑ ቢመታ አንተ ኃላፊ ነው?» ይላል።

«ታኮ ጫማ የማያደርገውን ትታችሁ ስለ ጤነኞቹ ታወራላችሁ» ጣልቃ ይገባል ደቻሳ፣ ወደ ተሰማ እየተመለከተ።

ተሰማ ተረብ በተረብ መመለስ አይችልም። ሲቀልዱበት ምንም አይመስለውም። በቁም እንገር ነው መልስ የሚሰጠው «ታኮ ጫማ የማደርገው እኮ አጭር ስለሆንኩ ነው። ለማማር ወይም ለማጌጥ አይደለም። ምን ያስገርማል?» ይላል ረጋ ብሎ።

እኔን ደግሞ የሴት አድናቂ በመሆኔ ይተርቡኛል።

«ሴት እንደመውደድህ እንዴት እንዳልከሰርክ ይገርመኛል»

# ጥላሁን ገሠሠ እኔ እንደማውቀው

አርቲስቱ ትሁት ነው። በቅርብ ለማያውቁት ኩራተኛ ሊመስል ይችላል። ጳውሎስ ኞኞ በአንድ ወቅት (1958 ይመስለኛል) «ጥላሁን ገሠሠን ትዕቢተኛና ኩራተኛ አድርጌ እያየሁት እጠላው ነበር። አንድ ቀን

መድረክ ላይ ካየሁት በኋላ ግን ድምፁና እንቅስቃሴው ብቻ ሳይሆን ትሕትናው ሰው አክባሪነቱ፣ ማርኮኝ አድናቂው ሆንኩ» ብሏል። ገጣሚና ደራሲ ሻምበል አፈወርቅ ዮሐንስም «ይህ አርቲስት እጅግ ብርቅዬ ነው። ገና ወደ ፊት ብዙ ተአምር የሚፈጥር ነውና ካሁኑ እንደ ቅርስ በቴሌቪዥን መቅረጫ እያስቀረጽን ለትውልዶች እንድናስተላልፍ ጥሪ አቀርባለሁ» ያለው ከ40 ዓመታት በፊት ነበር።

ዛሬ ሁለቱም አንጋፋ የሥነ ጽሑፍና የጋዜጣ ባለሙያዎች የነበሩት ዕውቅ ሰዎች በሞት አንቀላፍተዋል። አርቲስቱ ግን አስተያየታቸውንና ምኞታቸውን አሟልቶ ከድንገተኛ አደጋና ከሐምም ስቃይ ግብግብ ገጥሞ፣ ሞራሉን ጠብቆ አድናቆቱ ከፍ እያለ ሄዷል እንዲሁም በዚህ አጋጣሚ «የጠላሽ ይጠላ» የሚለው (master piece) ዘፈኑ የሻምበል አፈወርቅ ግጥም ነው። «ሊሞቱ ሰሞን ኢትዮጵያን አስቤ ነውና የጻፍኩት አንተ ተጫወተው አሉኝ» ሲል አጫውቶኛል። «በየት ነው መንገዱ» የሚለውም ግጥም የሳቸው ነው።

የአርቲስት ጥላሁን ገሠሠ የሕይወት ታሪክ 60ኛ የልደት በዓሉ በተከበረበት ቀን በ1992 ዓ.ም ያቀረቡት ጊዜ ምንጊዜም የምረሳው አይደለም። እኔና «ከሌለህ የለህም፣ እኔ አላማረኝም የአሥራ ሦስት ወር ፀጋን» የገጠመለት ክፍለ ኢየሱስ አበበ እስከዛሬ ድረስ ከአርቲስቱ ጋር ስንተዋወቅ ስልሣ ዓመታት ተቆጥረዋል።

ከጥቂቶች ጓደኞሞችና አንዳንድ ሰዎች በስተቀር ስለሱ ብዙም የማይታወቅ ሀቅ ነው። በጓደኝነት ቁጭ ብለን ስንጫወት ስንስቅም ሆነ ስናዝን ዝም ብሎ የራሱን ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ዘፈኖች ያንጉራጉልን ነበር። ጥላሁን ሌሎች ዜማዎችን ለውጦ ለዋውጦ ሲጫወታቸው ምን ያህል እንደ ሚያሳምራቸውና እባክህ ይቀረጽ እንደሚባል የታወቀ ነው። እጅግ የሚገርመው ግን እንዳትቀርጹት እያለ የሚወተውተው ገታራነቱ ነበር። አርቲስቱን በድምፁ ብትወዱትም በገትጋታነቱ ቅር ያሰኛችኋል።

«ድምፅ ማውጣትና አፍ አከፋፈት ያሳየኝና ያስተማረኝ እሱ ነው» ብሎ መሐሙድ አህሙድ ሲናገር ሰምተናል። መሐሙድ ለኔም ሆነ ለብዙ ኢትዮጵያውያን ተወዳጅ የሆነ ዝነኛ ድምፃዊ ነው። ሌሎችም የቆዩና ወጣት የሆኑ የምንወዳቸው አርቶስቶች አሉ። ጥላሁን ገሠሠ የመሐሙድን ጨምሮ ከ«ዘራፊ» ጀምሮ እስከ ዛሬ የተዘፈኑትን አቆንጅቶ ለመጫወት በምንም ዓይነት ሁኔታ ሙብታቸውን ለመንካት አይፈልግም ሞክሮም አያውቅም።

አርቲስቱ ብዙ ጊዜ ዝምታን ይመርጣል ምሥጢር የመጠበቅና ሐሜት የመጥላት ባህርዩን እንደንቅለታለሁ። ብዙ ሰዎች ከዕድሜው አንስቶ እስከ ትዳር አለሙ ድረስ የተለያዩ ስሞች እንደሚሰጡት ቢያውቅም በማንም ላይ ጥላቻ ማሳደር እንደማይወድ እኔም ሁከት በቅርብ የሚያውቁት ይረዱለታል። ግፍና በደል የሚደርስባቸው ወይም የደረሰባቸው ሰዎች ያሳዝኑታል። ለዚህም ይመስለኛል «ዋይ ዋይ ሲሉ» የሚለው ዜማው ላይ እንደታየው እንባው ቅርብ ነው።

ጥላሁን አንዳንዴ ሆድ ሲብሰው አይቻለሁ። ይኸውም አንደኛው ድምስጹን ከመውደዳቸው የተነሳ «ይሄን አንጉራጉልኝ......... ሚዜ ሁንልኝ.........» የሚሉት አፍቃሪዎቹ ሲበዙበት ነው። ለዚህም «ድምፅም እኮ እንደ ሌላው አካላችን ይደከማል - ባይደክምም ይጐዳል......» የሚል ቀልድ የቀላቀለ አባባል አለው። ይሄም ሆኖ ግን ብዙ ብዙ ጊዜ ታከተኝ ሳይል ለሚወዱት ሁሉ ጣዕመ ዜማውን አንቆርቁሯል። ለብዙ ብዙ ጊዜያት በትንሽ ክፍያ ለችግር የዳረጉት አሠሪዎች እንደ ነበሩ ስናስታውስ እንደ ማንም ሰው ገንዘብ ሲያጣ ሆድ ቢብሰው አያስገርምም። የድምፅ ንጉሥና ዝነኛ መሆን ከሰብዓዊነት ጋር የተሟላ መሆን አለበትና!

ስለ ጥላሁን መናገር የምንፈልገው ስለ ዓይናፋርነቱ ነው። ዓይናፋር ስል ፈሪ ወይም ዳተኛ ማለቴ አይደለም። አፍጥጦ በተራ ደፋርነት በአንድ ጉዳይ ላይ የመግፋት ፍላጐቱም ሆነ ልማዱ የለውም። በተቃራኒ ዖታ ያለበትን ርብርቦሽ ሰዎች ሁኔታው ሳይገባቸው በተለያየ ግላዊ ትዝብት ሰውዬውን ሲያወግዙ ስሰማ

ከጓደኝነት ያልመነጨ የራሴ አስተያየት - ይሄንን እንድናገር ያስገድደኛል። አርቲስቱ እኔ እንደማውቀው (ሁሉንም እንደዚያ ማለቴ አይደለም) ሌሎች ደፍረው ይገቡበታል ወይም ይመጡበታል እንጂ እሱ በቅድሚያ በርግዶ ሲገባ አይቼ አላውቅም።

ዝነኛነት ከየትም እንደሚጀምር ማንም ያውቃል። ከልቡ ጓዳ ገብታችሁ ብታዩት ግን ዝና አድናቆታችሁን በውል አዳምጦ መልስ መስጠት የሚቸግረው ሰው ነው። እውነት ለመናገር እኔ አንባቢዎቼን ፈርቼ ነው «ዝና የሚሰለቸው አርቲስት» ብዬ ስለሱ ብናገር ደስ ይለኝ ነበር። የተሠጥዎውን ታላቅነት አንደኛ የሚያይ ስላልሆነ ልቦለድ ብስፍ «ደደቡ አርቲስት» ብለውም ደስ ይለኛል። የዛሬውን ግምት ውስጥ ሳያስገባ ነገ ሌላ መፍጠሩን ብቻ የሚያስብ ነው። ይሄንን ያልኩት፣ እኔ እንደማውቀው ከሆነ፣ ጥላሁን ገሠሠ ስለ ራሱ ስትነግሩት፣ ሊሰማችሁ አይፈልግም። ሰማኋችሁ ቢላችሁም ውሸቱን ነው። ምክያቱም ምንጊዜም የሚያስበው የግል ችግሩንና ተሰጥኦና በረጅም ጊዜ ልምድ ያዘጋጀለትን የኪነ ጥበብ አምላክ ነው። ታዲያ እግዚአብሔር ማንን እንዴት ይፍጠር ትላላችሁ።

ጥላሁን ገሠሠ በ1932 ዓ.ም መስከረም 17 ቀን ከአቶ ገሠሠ ወ/ኪዳንና ከወ/ሮ ጌጤ ጉርሙ በአዲስ አበባ ከተማ ተወለደ። ከዚያ 13 ዓመት እስኪሞላው ድረስ ከሴት አያቱ ከወ/ሮ ነጌዬ አብደላ ጋር በወሊሶ ከተማ አደገ። «አያቴ ከሆያ ሆዬ በስተቀር የሙዚቃ ፍቅሬን አያቁም ነበር» የሚለው ጥላሁን በራስ ጐበና ዳጨው ት/ቤት ተምሯል።

ጥላሁን በልጅነቱ ወደ ሙዚቃ በጣም ያዘነብል ነበር። ሰንደቅ ዓላማው ሲወጣና ሲወርድ መዝሙሩን የሚዘምረው እሱ ነበር። ከጓደኞቹ ጋር ሲጫወት ያንጐራጉራል፣ መንገድ ሲሄድ ያንጐራጉራል። ብቻውን ሆኖ ማዜም እጅግ ደስ ይለው እንደ ነበር እሱም አብሮ አደግ ጓደኞቹም ያስታውሳሉ። ከትምህርት ከአራተኛ ክፍል ያላለፈ ቢሆንም መዝሙር አስተማሪዎቹ ከመቶ መቶ አስር እንደ ሰጡት ያስታውሳል።

ጥላሁን ራስ ጐበና ዳጨው ት/ቤት ሲማር ልዑል መኮንን ኃ/ሥላሴ ለጉብኝት መጥተው ሽለላና መዝሙር አሰምቷቸው «አዲስ አበባ እንድትመጣ» ብለውት ነበር። ሁለት ጊዜ ለመምጣት ሞክሮ አልተሳካለትም። አንድ ጊዜ ቱሉ ቦሎ ደርሶ ሲመለስ አንድ ጊዜም በአንድ ሠርግ ላይ ዘፍኖ ተመልሷል። እኔ አምቦ ሁለተኛ ደረጃ ስማር ከወሊሶ ተመድበው የመጡ ተማሪዎች ስለ አርቲስቱ ሲያወሩ (ጓደኞቸው ነበርና) «ት/ቤታችን ፊት ለፊት አንዲት የግራር ዛፍ ሥር ቁጭ ብሎ ያንጐራጉር ነበር» ብለው ነግረውት ነበር። ጥላሁንም ይህንን ጠይቄው ሲመልስልኝ እውነት መሆኑን ገልጾልኝ ዛፏ ግን ዋርካ ነበረች ብሎኛል።

«ለመጨረሻ ጊዜ ወሊሶን ለቅቄ በመጣሁበት ቀን በጨርቅ የተሳቸውን ማንገቻ ያላት ደብተር መያዣዬን ዛፉ ላይ አንጠልጥያት መጣሁ» ብሎኛል። «አቶ ኢዮኤል ዮሐንስን እንደ አባቴ እቆጥራቸዋለሁ። ምክንያቱም ልዑል መኮንን ሽለላና መዝሙሬን ባሰማኋቸው ጊዜ አዲስ አበባ እንድትመጣ ብለውኝ መምጥት እየፈለግኩ በተለያዩ ምክንያቶች ሳልመጣ ቀርቼ አቶ ኢዮኤል ወሊሶ ቴአትር ሊያሳዩ መጥተው አዲስ አበባ እንድትመጣ ብለው ሀገር ፍቅር ያስገቡኝና ሙያዬን ያስጀመሩኝ በመሆናቸው ነው። ታላቅ ሰው በመሆናቸው እጅግ አከብራቸዋለሁ» ይላል አንጋፋው አርስቲስ።

እዚህ ላይ ጥላሁን ገሠሠ ዝነኛ መሆን የጀመረው መቼና እንዴት ነው? ብለን መጠየቅ ግዴታችን ይሆናል። ጥላሁን ሀገር ፍቅር ማኅበር እያለ ከ«ጥላ ከለላዬ» ጀምሮ በርካታ ዘፈኖችን በመሰንቆና በክራር ታጅቦ ዘፍኗል። ከእነዚህ መካከል «ብርቱካኔ» የሚባለውም አለ። ወደ ክብር ዘበኛ ሙዙቃ ክፍል ከገባ በኋላ ሠራዊቱ በወቅቱ ታይቶ የማይታወቀውን የጦር ትርዒት ሱሉልታ ላይ ሲያሳይ ይቺን ዘፈን (ብርቱካኔ) የ16 ዓመቱ ድምፃዊ በአኮርዲዮን ታጅቦ ሄልሜት አድርጐ ዘፈናት። ዘፈኗ ከሀገር ፍቅር አዘፋፈኑ እጅግ የምትጥም

ነበረች። የዚያኑ ዕለት ተመልካቾቹ ሁሉ ስለ ጥላሁን ድምፅ ማማርና ማራኪነት ሲያወሩ አመሹ። የዝናው ችቦ በዚያች ጀምበር ተቀጣጠለ ማለት ይቻላል።

ጥላሁን ሀገር ፍቅር ማኅበር ሲቀጠር ደሞዙ ሰላሣ ብር ነበር። በኋላ አሥር ብር ተጨምሮለት አርባ ብር ሆነለት። የክብር ዘበኛ ኦርኬስትራ በ1949 መጨረሻ በብር ሰማንያ ወሰደው። የቅርብ ጓደኞቹ እንደ ነገሩኝ በጣም የሚቀርበው ጓደኛው ፍሬው ኃይሉ ነበር። አንድ ሻይ ቤት ደብተር ላይ እየጻፉ «አቡሲታ» የተባለ ምግብ በሃያ ሳንቲም ይበሉ ነበር። (ሻይ ቤቷን እኔም ራሴ ከነባለቤቷ አውቃታለሁ አሁን ሱቅ ሆናለች)

ጥላሁን ብስክሌት መንዳት በጣም ይወዳል። ፍሬው ኃይሉ አሥር ሳንቲም አራት ኪሎ ዞሮ ለመመለስ ይከራያል። ግማሹን መንገድ ይነዳና ለጥላሁን ቀሪውን መንገድ ያስነዳዋል እና የበላውን የ20 ሣንቲም «አቡሲታ» ጥላሁንን ደብተሩ ላይ ያጽፈዋል።

አንደኛው ጓደኛቸው እንደነገረኝ ፓስቴ መብላት በጣም ይወዱ ነበር። እንጭ ሸሚዛቸውን እንደ ለበሱ ፓስቴ ሲበሉ ለሥራ ይፈለጉ ኖሯል። የዚያን ጊዜ የቴአትር ቤቱ ሥራ አስኪያጅ አቶ ኢዮኤል ዮሐንስ ድንገት ይደርሱባቸዋል። እነሱ ሸሚዛቸው ውስጥ ከተው ፍጥጥ። ፓስቴውም ዘይቱ ቀልጦ ሲያሳጣቸው ታየ።

ጥላሁን ብዙ ጊዜ ትርዒት ሲያቀርብ ተመልካቾቹን አይመለከትም። ዓይኖቹን ከመድረክ ወዲያ አሻግሮ ነው የሚመለከተው። ጓደኞቹን የዚህ ምሥጢር ምንድነው? ብዬ ጠይቄያቸው ነበር። አንዲት ቆንጆ ሴት አብሮ እንዲያያት ባለቤቱን ጠብቃ እየተከተለች አጠገቧ በየጊዜው ትቀመጥ ነበር። ጥላሁን አገሩ ገባውና አንዴ ወደ መድረክ፣ አንዴ ከመድረክ ወዲያ፣ ወደ ሰማይ ወደ መሬት ለመመልከት ተገደደ። ይህ እስከ አሁን ልማድ ሆኖበት ቀርቷል ብለውኛል።

አርቲስት ጥላሁን ገሠሠ በሚመለከት የተመለከትኳቸውንና ያደመጥኳቸውን አንዳንድ አስደናቂ ሁኔታዎች በገጠመኝ መልክ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

አንድ ጊዜ ጥላዬ ጨዋቃ የተባለው አርቲስት አንድ ዜማ ደርሶ ጥላሁን አስተያየት እንዲሰጠው ይጠራዋል። እኔና ክፍለ ኢየሱስ ይዞህ ሄደ። ጥላዬ ዜማውን በፒያኖ እየታጀበ አሰማን። «እስቲ ደግመህ ዝፈነው» አለው ጥላሁን። ደገመለት። ጥላሁን ጥቂት ጊዜ ሲያስብ ከቆየ በኋላ «ጥሩ ዜማ ነው። ጥሩ ሠርተኸዋል። ግን እንግዲህ ቢሆንስ?» አለና በሚገርም ቅላጼው ሲያስረቀርቀው ሁላችንም ዘፈን ቀረን። እዚያ በቦታው ላልነበረ ሰው በእውነቱ ለማመን ያስቸግራል። ፍፁም ለውጦታል። «ጋሼ ጥላሁን እባክህ ዜማውን ልሰጥህ አንተ ተጫውተው» አለው።

«ጥላዬ እኔ የማንንም ዜማ ተጫውቼ አላውቅም። ካስፈለገ ፕሮግራም አውጥተን አለማምድሀለሁ» አለው። ጥላዬም «እስቲ አንዴ ድገምልኝ» አለው። እንደ ታዋቂው ጥቁር አሜሪካዊ የትራንፔት ንጉሥ ሉዊዝ አርምስትሮንግ በአንድ ዜማ ተወስኖ የማያውቀው ጥላሁን በድጋሚ አሻሽሎ እዚያው በዚያው ለዋወጠው። «ሺህ ጊዜ ብለማመደው እንደ አንተ ላመጣው ቀርቶ አጠገብህ አልደርስምና እባክህ ሕዝብ ይስማ፣ ፈርሜ ልስጥህ» አለው ጥላዬ። «ጥላሁን ገሠሠ ሰጥቼዋለሁ ብለህ በጋዜጣ አወጣውና ልጫወተው» ብሎ እንደ ቀልድ ሲናገር ሁላችንም ተሳስቀን ተለያየን። ያን ቀን ጥላሁንን ለምትህተኛ ድምጹና ችሎታው ጥላዬ ደግሞ ለዜማ ደራሴንቱና ልበ ቸርነቱ ሁለቱንም አደነቅናቸው። ጥላሁን ያንን ዜማ ረስቶት ይሆናል። አንድ ጥሩ ዜማ እንዳመለጠን ግን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

ጥላሁን እንደ ዛሬ በጣም ውድ መኪኖችን ባልያዘበት ጊዜ በ70ዎቹ መጀመሪያ እየተበላሸች ታበሳጨው በነበረችው ሬኖ መኪናው እኔንና ብዙ ግጥሞች የገጠመለትን ክፍለ ኢየሱስ አበበን ይዞ ከወደ ለገሀር ስንመጣ

ቸርችል ጎዳና ላይ መብራት አቆመን። መኪና ሲነዳ «ጎራው»ን «ገብልዬ»ን «መላመላ»ን ለራሱ ማንጎራጎር ይወድ ነበር። ከእነዚህ አንዱን ይመስለኛል ሲያንጎራጉር አረንጓዴ ሜርሰዲስ መሪ የጨበጠች አንዲት ቆንጆ ልጅ ፍዝዝ ብላ ስታዳምት አየን። ወዲአይው ቀዩ ጠፍቶ አረንጓዴው በራ። መኪኖቹ ጉዞ ሲቀጥሉ ወጣቷ «ጥላሁን እንጉርጉሮህን ቀጥል፣ አትንቀሳቀስ። የትራፊክ እኔ እቀጣለሁ» ስትል ተነስተን ሄድን። ጓደኛዬ «ህ! ያንተ ድምጽ መኪናም ውስጥ ይፈለጋል፣ ቀይ መብራት ላይ እንኳ። አይ እምታደል!» አለ።

ለጥላሁን ሩኅሩህነት አዛኝነትና ሰው ወዳድነት ሁልጊዜ ምሳሌ የማደርጋት ዛሬ በሕይወት የሌልች አንዲት ሴት ነበረች። ይህቺ ሴት አሜሪካ ሀገር ከፍተኛ ባለሥልታን የነበሩ ኢትዮጵያዊ ወስደው የቤት ሠራተኛቸው ያደርጓታል። ዋሽንግተውን ዲሲ አንድ ዓመት ያህል እንደ ተቀመጠች ልጃቸ ይደፍራትና ታረግዛለች። በዚህ ጊዜ ያረገዘችውን እንድታስወጣ ያደርጉና ወደ ኢትዮጵያ ጥቂት ገንዘብ ሰጥተው ይልኳታል። በሁለት ወር ገንዘቡ ሲያልቅ ዘመዷ ቤት ቡና ቤት ትገባለች። ሁሉም ሰው «አሜሪካ» እያለ ይጠራታል። በእውነተኛ ስሟ አትታወቅም ነበር። ጓደኞቼን እየወሰድኳቸው ሲያይዋት ያዝኑላታል። አንድ ቀን ጥላሁንን ወስደነው ታሪኳን እንድታወራለት አደረግን። «ለራሳቸው ክብር አንቺን? ወይ አላስተማሩሽ ወይ አላኖርሽ! ወርውረው ጣሉሽ?» ብሎ እንዳለቀሰ ትዝ ይለኛል። ግጥም ፃፍልኝና ልዝፈነው ብሎ ነበር። ሳይሆን ቀረ እንጂ።

መደነቅን መቼም ማንም የሚጠላ የለም። ጥላሁንን ደግሞ ማንም ሰው እንደሚያደንቀው ግልጽ ነው። አንድ ጊዜ በብሄረ ጽጌ መናፈሻ የነበረው ትዕይንት ለዚህ መልካም ምሳሌ ይሆነኛል። ጥላሁን ለአንድ ጓደኛችን ሚዜ ሆኖ ነበር።

የሙሽራ ዘፈኖች እየዘፈንን ጭብጨባው ሲጧጧፍ የሌላ ሠርግ እድምተኞች የራሳቸውን ቡድኖችና አቀንቃኞች ትተው መጥተው ከእኛ ጋር ተቀላቅለው ያጨበጭቡና እስክስታ ይወርዱ ጀመር። ጥላሁን ዘፈኑን አቋረጠና «ልብ አድርጉ። እኔ ጥዬ መሄዴ ነው። አምጡ ኮቴን! ሠርግና ሞት እኮ አንድ ቀን ነው። ሂዱ ወደ የሙሽሮቻችሁ» ብሎ ተቆጣ፣ ላቡን ከግንባሩ እየጠራረገ። ሰዎቹ ሲመለሱ ሥነ - ሥርዓታችን ቀጠለ።

አርቲስ ጥላሁን ገሠሠ በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ መሳተፍ ብቻ ሳይሆን መረዳጃ ማሕበር በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ አነሳሽ መሆንም ደስታው ነው። አንድ ጊዜ አሥር የምንሆን ሰዎች የመረዳጃ ማህበር መሥርተን በነበረበት ወቅት እኔ የማኅበሩ ፀሐፊ ሆኜ ሕጉን ባረቅም በጠቅላላው ማኅበሩ ይንቀሳቀስ የነበረው በጥላሁን የቃል ሕግ ነበር። እሱ ያለው ይፀድቃል! እሱ ያወገዘው ይሰረዛል። የሚያቀርባቸው ሃሳቦች የምናምንባቸው ቢሆኑም በአብዛኛው የሚገዛን ድምፁ ነበር። ከተጨቃጨቅን ሲያንጐራጉርልን ዝም እንላለን። ስብሰባ አቋርጦ መሄድ የሚፈልግም ካለ እሱ ሲያንጐራጉር ቁጭ ይላል። ሦስት ዓመት ከቆየንበት የማህበሩ ግንኙነታችን ገንዘብ ለማሰባሰብ የጥላሁን ዜማ ትልቅ ሚና ተጫውቷል። በኋላ «አንድ ዘፈን ስትጠይቁ ለማሕበሩ ሁለት ብር አስቀምጡ፣ ድጋሚ ስትጠየቁ አንድ ብር ያስጨምራል» የሚል ደንብ አወጣና የብር ዓይነት ጠረጴዛው ላይ ይከመር ጀመር። የደሞዝ ዘሞን ቢያን ብር 30 የማያወጣ አልነበረም። በአንድ ቀን ብር 70 ያስቀመጠም ከመካከላችን ነበር።

ጥላሁን ብዙ ብር እንድናዋጣ ሆን ብሎ ዘፈኑ ያስጥረዋል። ያኔ ድጋሚ እንጠይቃለን። ካፒታላችን ትንሽ ቢሆንም የመረዳዳት ጅምራችን የሚያበረታታ ነበር። በኋላ ግን በቀይ ሽብር ምክንያት መሰባሰብ አደኛ እየሆነ ስለ መጣ ለጊዜው ተበታተንና የማሕበራችን ነገር አከተመለት።

በመጨረሻም የጥላሁን ዜማ በአንድ ምሽት ያመጣውን ውጤት ልገልፅላችሁ እወዳለሁ። ካዛንቺስ ያለ ጓደኛችን ቤት ሆነን ስናወጋ በድንገት አንድ ሴት ከጎረቤኢት ሮጣ መጥታ ሳሎኑን አቋርጣ መኝታ ቤት ስትገባና በሩን ስትዘጋ ባልዬው ተከትሎ መጣ። ጥላሁን «የጠላሽ ይጠላ» የሚለውን ዘፈን ያንጐራጉር ነበር። በስሜት

ተውጠን እርጭ ብለን አያዳመጥነው ያንቆረቁረዋል። ባልዬው ልክ ተንደርድሮ ሲገባና ገላጋዮች ሲይዙት ሰውዬውን እያየ ጥላሁን ገና በካሴት ያላስቀረፀውን ዜማ ጣራው እስኪሰነጠቅ ይለቀዋል። ሰውዬውም «ጥላሁን አለ እንዴ?» አለና እንደ መደንገጥ ብሎ ፊቱን ወደ እኛ አዞረ። አርቲስቱ ግን ቀጠለ። ሰውዬው ቁጭ አለ። ጥላሁን በዚህ ጊዜ (ሰውዬው ቁጭ ሲል) ዘፈኑን አቋረጠ። በሚያሳዝን አስተያየት መሬት መሬት እያየ «ወይ ቅዱስ ገብርኤል የጥልዬን ድምፅ ልስማበት ወይስ የእሷን ለከፋ» አለ። አንድ ጊዜ ሳቃችንን ለቀቅነው።



# ስለደራሲው በጥቂቱ

መስፍን ሀ/ማርያም የካቲት ፳፫ ቀን ፲፱፴፯ ዓ.ም. በምሥራቅ ሸዋ ሞጆ ከተማ ተወለዱ፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሞጆ ት/ቤት፣ የሁለተኛ ደረጃን በአንቦ ማዕርገ ሕይወት ት/ቤት አጠናቅቀዋል። የከፍተኛ ትምህርታቸውን በአ.አ. ዩኒቨርሲቲ ተከታትለው በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ በቢ.ኤ ዲግሪ ተመርቀዋል፡፡ በተጨማሪም ከብሪቲሽ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ ካናዳ በፈጠራ ድርሰቶች አጻጻፍ ኤም.ኤ. ዲግሪ ኤም.ኤፍ.ኤ ተቀብለዋል፡፡

“የቡና ቤት ሥዕሎችና ሌሎች ወጎች”፣ “ዓውዳመት”፣ “አዜብና ሌሎችም አጫጭር ልቦለዶች”፣ “የሌሊት ድምጾች” የሚሉ ልቦለድ ሥራዎችንና የወግ ጽሑፎችን ለንባብ አብቅተዋል፡፡

**ምንጭ:** የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር ለሚሊኒየም ያሳተመው አጀንዳ።

## <u>የደራሲው ሥራዎች</u>

1. የቡና ቤት ሥዕሎች(ወግ)
2. አዜብና ሌሎች ዐጫጭር ድርሰቶች(ልብወለድ)
3. ዓውደ ዓመት(ወግ)
4. የሌሊት ድምፆች(ወግ)